ስውሩና ያልተነገረው የአይሁዳውያን እና የኢትዮጵያውያን ታሪክ

ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ

Copyright 2010. Fikre Tolossa.

ISBN: 978-1-4583-7701-2

Library of Congress Catalogue-in-Publication Data.

መታሰቢያነቱ

ይህ መጽሀፍ፣ ብርቅዬና ጥንታዊ ታሪካችንን መዝግበው ላቆዩልን ባለውለታዎቻችን፣ ለንጉሥ አክሱማይ ሲራክ፣ ለአጼ ላሊበላ፣ ለአጼ አምደጽዮን፣ ለዘግዱር ዘ ቤተ አንዳ እና ለወዳጄ ለመሪራስ አማን በላይ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ

ማውጫ

መግቢያ 8

የመልከጸዲቅ እና አብርሃም ግኑኝነትና ማንነት፤
መጽሀፈ ያሻር፣ እና ጎርንሽዋ 28

የመልከጸዲቅ ልጅ ጣና ደሴት ላይ ሰፍሮ ኢትዮጵ እንደተባለ በኋላ
ልጆቹ ጠቢባን ነሥታት ለእየሱስ ገዳ ስለማቅረባቸው 61

የእየሱስ ክርስቶስ በግብጽ፣ መርዌ እና ኢትዮጵያ ቆይታ 74

ነብዩ ሙሴ እና ኢትዮጵያዊው አማቹ ሊቀካህናት ዮቶርአብ 80

ልዕለ-ሰብዕ የሆነው አጼ እስያኤልና ንግሥተ-ሳባ 97

ግሥተ-ሳባ እና ቀዳማዊ ምኒልክ 106

የኢትያኤልና የንጉሥ ሰለሞን ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ 120

ንግሥት ዮዲት እና ለኢትዮጵያ የዋለችው ውለታ 136

የዮዲት ባል መራ ተክለሃይማኖትና የዛጉዌ ስርወመንግሥት 149

የዛጉዌ እና ምኒልክ ልጆች ግንኙነት እና እስራኤል 154

ራኬብ፣ ነቢዩ በልዐም፣ ሩት፣ እና የዳዊት እናት ኢትዮጵዊቷ
አዶልያ 163

የቤተ እስራኤል ስልጣን፣ ሌዋውያን እና ክርስትና በኢትዮጵያ ... 176

የአፋር ገናናነት በጥንታዊ አፍሪካ እና እስራኤል 198

የነቢዩ ኤርምያስ እና የኢትዮጵያዊው አቤሜሊክ ወዳጅነት 209

መደምደሚያ 216

አባሪዎች 222

ዋቢ መጻህፍት 234

ለፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ

ቫሌዮ፣ ካሊፎርኒያ

አሜሪካ

ክቡርነትዎ!

ለደብዳቤዎና ‹‹ስውሩና ያልተነገረው የአይሁድ ህዝብና ኢትዮጵያዊያን ታሪክ›› በሚል ርዕስ ላጠናቀሩት ግሩም መጽሐፍ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ስላለፈው ዘመን የእስራኤል ህዝብ ታሪክ በኢትዮጵያዊ እይታ ላከናወኑት ጥናታዊ ስራ አድናቆቴን ልገልፅልዎ እወዳለሁ። በአይሁዳዊያንና ኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያለው ቅርበት እንደጠቆመት ሥረ መሰረቱ በመፅሐፈ ነገስት የሚጠቀሰው የንግስት ሳባ ከንጉስ ሰለሞን ጋር መገናኘት ነው። እንዳሉትም አብዛኞቻችን ኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረው የአይሁድ ህዝብ ታሪክ የምናውቀው ጥቂት ነው። ደብዳቤዎና መጽሐፎ የእስራኤል ሰፊ ህዝብ ያልተገነዘባቸውን አያሌ ዝርዝር ቁምነገሮች የሚገልጥ ነው።

የእስራኤል መንግስት ለሺህ የሚቆጠሩ ቤተ እስራኤላውያን ፍልሰትና አቀባበል በትጋት ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ በእርግጥም የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም። ትስስራችን የባህላችን አንዱ ገፅታ መሆኑ ቀደም ብሎ ታውቋል። ቤተ-እስራኤላውያን በብዛት በአይሮፕላን ያጓጓዘው፣ ዘመቻው በንጉስ ሰለሞን የተሰየመው ከንግስት ሳባ ጋር ያለው ግንኙነት ይፋ ስለሆነ ነው።

ግኙቶችዎ በምሁራንና እንዲሁም በህብረተሰቡ ዘንድ ሰርፀው ግንዛቤ የሚያመነጩ፣ በሁለቱ ህዝቦች መካከል ያለውን ትስስር የሚያጎለብቱ፣ በእስራኤል ውስጥ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞች በጎ አስተሳሰብ የሚጭሩና በኢትዮጵያም ስለ እስራኤል ያላትን አመለካከትም የሚያሻሽሉ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ነኝ።

ለተቀዳጁት ድሎች እንኳን ደስ አለዎት እያልኩ በጥረቶችዎ ሁሉ ስኬታማ እንዲሆኑ እመኛለሁ።

ኤም.ኬ. ዮኤል ኤደልስቲን

የእስራኤል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ

መግቢያ

ይህ ጽሁፍ ከዚህ ቀደም ከኢትዮጵያ ውጪ በየትኛውም ቋንቋ በእዚህ መልኩ ያልተወሳና ያልታተመ ከአይሁድ ህዝብና በአጠቃላይ ከዓለም ህብረተሰብ ተሰውሮ የቆየ ታሪክን አካቷል። ምንም እንኳ የአይሁዳውያንና ኢትዮጵያውያን ታሪኮች የተሳሰሩና ሁለቱ ህዝቦች እነዛኑ ታሪኮች በስፋት የሚጋሩ ቢሆንም፣ ይህን ክስተት አይሁዳውያን አያውቁም፤ ዘመናዊዎቹ ኢትዮጵያውያንም እንዲሁ። እውነታው ግን ሁለቱ ህዝቦች ላለፉት 4000 ዓመታት የታሪካቸው የተወሰኑ ምእራፎች አንድ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በአንድ የአምልኮ ስርዓት መፅናታቸው እና እነዚህን ነገሮች ጠብቀው ማቆየታቸው ነው። የአይሁድ ህዝብ ጠለቅ አድርጎ ቢያጤን ታሪኩ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተዘግቦና ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ተሸርቦ ያገኘዋል። ከዚህም በላይ እስራኤል ውስጥ ደብዛቸው ጠፍቶአል የተባሉትን የአይሁድ ሃይማኖታዊ

ክንውኖችን፣ ስርዓተ አምልኮዎችን፣ ያሸበረቁ ልብሶ-ተክህኖዎችን እና ንዋየ ቅዱሳትን፣ እንዲሁም እግዚአብሄር ራሱ በእጁ ጽፎ አስርቱን ትእዛዛት ያሰፈረባቸውን ሁለት ዕላቶች እና ሌሎችንም ቅዱሳን ቅርሶች ኢትዮጵያ ጠብቃ አቆይታለች።

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ካህናት አፍሪካውያን-ኢትዮጵያውያን ሆነው የክርስትና እምነት በደፈናው ቢከተሉም፣ የአይሁድ ካህናት ትውልዶች መሆናቸውን ይተርካሉ፤ የክርስትና አምልኮታቸውንም ከአይሁድ እምነት ጋር አዋዝተው ይገኛሉ። እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት መሆኑን ለማረጋገጥም ዕላተ-ሙሴና የእስራኤል ካህናት አልባሳት ቅጂዎች፣ እና ቅዱሳት አርናዊ ቁሳቁሶች በቤተመቅደሳቸው ያኖራሉ። የትኛውም (አገር በቀል) የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን እንደታቦትና ጸናጽል፣ ከበሮዎችና ድባቦች የመሳሰሉ ቅዱሳት እቃዎች ከሌሉት ምሉእነት አልነበረውም። አሁንም የለውም። የኢትዮጵያ ቀሳውስት ስለ አብርሃምና ሙሴ ሲያወሱ ‹‹ቀደምት አባቶቻችን›› ይላሉ። የአይሁዳውያንና የኢትዮጵያውያን ግንኙነት በፈላሾች ብቻ እንደተጀመረ የሚገምቱም አሉ። ይህ ከእውነት የራቀ ነው። ፈላሾች በኢትዮጵያ ለመስፈር የመጀመሪያዎቹ አይሁዶች አልነበሩም። የዛሬ 3500 ዐመት ሙሴ በህይወት እያለና ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር የዛሬ 3000 ዐመት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሌሎች

አይሁዳውያን ከእነሱ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ከመኖራቸውም በላይ፣ ፈላሾች ወደ ኢትዮጵያ ከመፍለሳቸው አስቀድሞ ለ500 ዐመታት ያህል የንጉሥ ሰለሞን ዝርያዎች ነን ብለው በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የነገሡ ሰዎች ነበሩ። በዚህ መዕሐፍ ወደፊት እንደምናየው፣ ፈላሾች በእርግጠኝነት የመጨረሻዎቹ እንጂ የመጀመርያዎቹ መጤዎች አልነበሩም።

የአይሁድ ህዝቦች በሌሎች አገሮች ሴማዊ የዘር መድልኦ እና እንግልት ቢደርስባቸውም ኢትዮጵያ ውስጥ ተደላድለው ከመኖራቸውም በላይ፣ በካህንነት የማገልገል እድልም አግኝተዋል። ንጉሥና ንጉሠ ነገሥት ሆነውም ነበር። በእርግጥም የቀድሞዎቹ አይሁዳውያን በሌሎች አገሮች የተነፈጉትን በትረ-መሴና እና በትረ-ዙፋን ኢትዮጵያ ውስጥ ጨብጠው፣ ሃብት አካብተው፣ ግላዊና ሃይማኖታዊ ነፃነት ተቀዳጅተው ለመኖር በቅተዋል።

በተለይ ባለፉት 3000 ዓመታት የኢትዮጵያ ነገሥታት ራሳቸውን የንጉሥ ሰለሞን ዝርያዎችና የሰርወመንግሥቱ ወራሾች አድርገዋል። ከንጉሥ ሰለሞንና ከንግሥተ-ሳባ አብራክ ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጀምሮ በ1966 ዐመተ ምህረት ዙፋናቸውን በህዝባዊ አመፅ እስከለቀቁት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ድረስ የሰለሞንን ስርወመንግሥት በመወከል በኢትዮጵያ 225 ነገሥታት ዙፋኑ ላይ ወጥተዋል። ይህ መዕሃፍ፣ የክርስትና እምነት ወደ

ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ኢትዮጵያን የገዙ ነገሥታትንና ሃኒያትን ታሪክ በመጠኑ ያስቃኘናል።

አብርሃም የህይወት ታሪኩን በጽሁፍ አላሰፈረም። ማንበቡና መፃፍ ችሎም እንኳን ቢሆን፣ ንጉሥ ወይም ካህን ስላልሆነ የህይወት ታሪኩን ለመዘገብ ምክንያት አልነበረውም። ከኖረበት ዘመን 650 ዓመታት በኋላ ሙሴ በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ገድሉን እስካሰፈረለት ጊዜ ድረስ ታሪኩ በራሱ ልጆች ዘንድ በጽሁፍ ተመዝግቦ አልተገኘም። የአብርሃም ወዳጅና የኢትዮጵያውያን ቀደምት አባት የነበረው መልከጸዲቅ ገድል ግን እንዲያ አልሆነም። ወራሾቹ ነገሥታትና ካህናት ስለነበሩ፣ በህይወታቸውና በመንግሥታቸው ዙርያ የሆነውን ሁሉ ዘግበዋል። መልከጸዲቅና አብርሃም ወዳጆች ስለነበሩ ይህን ሀቅ የንጉሥ-ካህኑ የመልከጸዲቅ ልጆች ከትበውታል። ታዲያ ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ካህናት፣ እንዲሁም የመልከጸዲቅ ልጅ ኢትዮጵ፣ ስለ አብርሃም ህይወትና ከእነርሱም ጋር ስለነበረው ትርጓት ቢጽፉ አያስገርምም።

አብርሃም ከመልከጸዲቅ ጋር ቤተሰቡን ጨምሮ ስለነበረው ግንኙነት ክህኑ እና ከንጉሠነገሥቱ ከኢትዮጵ በኩል ቀጥተኛ የዘር ግንድ ከነበረው ከምድያሙ ካህን ከኢትዮጵያዊው አማቱ ከዮቶርአብ፣ ሙሴ ብዙ ታሪክ ቀስሟል። ሆኖም ሙሴ

አርቅቋቸዋል በተባሉት ድርሳናቱ ከአማቹ የተማረውን ሁሉ ነገር በዝርዝር ለማውሳት አለመፈለጉ ቅር ያሰኛል። ስለዚህ በዚህ ሥራ የማቀርበው ታሪክ በተለይ ለአይሁዳውያን፣ በአጠቃላይ ለዓለም ህብረተሰብ አዲስ ቢሆን አያስደንቅም።

ይህን ፅሁፍ ሆነ ብዬ አስቤበት ቅልብጭ አድርጌ ለመግፍ ሞክሬያለሁ። ለዚህም ምክንያቱ ጥድፊያ በበዛበት በዚህ ዘመን፣ አንባቢ ቢሆንለት በአንድ ዙር ተወጥቶት ጊዜውን እንዲቆጥብ ነው። ስለሆነም አውሮፕላን ወይም አውቶቡስ ላይ፣ አለዛም ቆይታን በሚጠይቅ የትኛውም ቦታ ተነባቢ ያደርገዋል። ከዚህም በላይ ምንም እንኳ ዋቢ መረጃዎች በመጠኑ ባስገባና የተወሰኑ መፃህፍት ብጠቅስም ተወዳጅ ትረካ እንዲሆን የምሁራዊ ሀተታ አላበዛሁበትም። በዋቢ መጻህፍት ብዛትም አልጠቀጠቅኩትም ወይም አላንዛዛሁትም። መጽሀፉ ለታሪክ ምሁራን ሳይሆን ለብዙሃኑ አንባብያን እና ግንዛቤ የታቀደ ነው። ለወትሮውም ቢሆን ታሪክ ለህዝብ እንጅ ለባለታሪኮች ለራሳቸው ተበሎ አይጻፍም። ይህም ሲባል ዋቢ መጻህፍት አላቀረብኩም ማለት አይደለም። አያሌ መጻህፍትን በጥልቀት መርምሬ ለእዚህ ታሪክ በቂ ይሆናሉ ያልኳቸውን ያህል በዋቢነት አቅርቤያለሁ። ስለዚህም፣ መጽሃፉን ለመጻፍ ስነሳ የመረመርኳቸው መጻህፍት በዋቢነት የጠቀስኩዋቸው ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። እነሱስ

በርካታ ናቸው። ሆኖም፣ እንደ ዋቢ ያሰፈርኩዋቸው እጅግ አስፈላጊ መስለው የታዩኝን ብቻ ነው። ታዲያ ምንም በርካታ መጻህፍት ብመረምርም፣ ታሪካችን እውስጤ ጠልቆ ስለተዋሃደኝ እንደው ለወጉ የማይቀሩ ማጣቀሻ መጻህፍትን እመለከት ነበር እንጂ እንደወረደ በቀጥታ ነው የከተብኩት።

ይህ መጽሀፍ ሀይማኖታዊ አይደለም። ሀይማኖታዊ ከመሰለ፣ በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ቀዳሚ-ዘሮቻችን ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ስለነበሩ ነው። እነሱ እንደዛ ከነበሩ ደግሞ እውነተኛ ታሪካቸው ከሀይማኖት ጋር መያያዙ አይቀሬ ነው። የእነሱን እውነተኛ ታሪክ የሚጽፍ ሰው ደግሞ ሀይማኖታዊ እንደነበሩ ሸፋፍኖ ሊያልፍ አይችልም። ከሸፋፈነው ማንነታቸውን ደብቀው ማለት ነው። ማንነታቸውን ከደበቀው ደግሞ ታሪካቸው አልተሟላም ማለት ነው። የእነሱ መንፈሳዊነት የማይስማማን በዛሬው ጊዜ የምንኖር ኢአማኒዎች ከአለን ደግሞ እኛ ላለማመን ነጻነት ቢኖረንም፣ በዘመን ወደ ኋላ ተጉዘን የቅድመ-ዘሮቻችንን አምነት ልንገሰብጠው አንችልም። ይህ ሀቅ በእግዚአብሄር ለሚያምነውም ሆነ ለማያምነው አንባቢ ግልጽ እንዲሆን ይገባል። መሰለም ለሆነ ኢትዮጵያውያንም ይህ የቅድመ-አባቶቻቸው መንፈሳዊና ዐለማዊ ገድል እጅግ የሚያኮራቸው የጀርባ ታሪካቸው ነው። ሊቀካህናቱና ንጉሠነገሥቱ መልከጸዲቅና ልክ እንደ አባቱ

ሊቀካህናት እና ንጉሠነገሥት የነበረው ኢትዮጵም የመስሊም ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንም ቅድመአባቶች ነበሩና። ኢስላም ከመወለዱ ከ2600 ዓመት አስቀድሞ የሁላችንም የኢትዮጵያውያን፣ የመስሊሞቹም የክርስተያኖቹም አባቶች፣ በአንድ እግዚአብሄር ያምኑ ነበር። ኢስላም በዐለም ላይ እስኪጠነክር ድረስ ለነቢዩ መሀመድ ቤተሰቦች ጥገኝነት የሰጡት እና በተዘዋዋሪ እስልምና እንዲስፋፋ ያደረጉት ክርስቲያኖቹ ንጉሥ አርማህ እና ልጁም የቀድሞ አባቶቻችን ነበሩ። በእነዚህ ክርስትያን አባቶቻቸው መስሊሞቹ ኢትዮጵያውያንም ሊታበዩ ይገባል። ሁሉም ኢትዮጵያውያን ንጉሠነገሥታት እና ንግሥተነገሥት አማኞች ነበሩ። ከነሱ ውስጥ ቁጥራቸው እንደ ትንሽ የማይታየው ከአማኝነትም ዘልለው ሥልጣንን እና ይህን ዐለም ንቀው መንነዋል። አጼ ካሌብ እና ልጃቸው፣ ንጉሠነገሥት ራስ ዳሽ የተባሉት የአጼ ባዜን ልጅ፣ እና ከዛጉዌ ነገሥታትም ጥቂቱ መንግሥታቸውን ትተው ገዳም ገብተዋል። ከዛጉዌ ነገሥታት ላሊበላን ጨምሮ አራቱ እንዳውም ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ። የእኛ ዘመን ፖለቲከኞች ግን፣ ኢአማኒ እና በጣም ዐለማዊ ሆነው እጅግ ሥልጣን ከመውደዳቸው ብዛት ስልጣን ላይ መጭጭ ብለው ሥልጣናቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ይገላሉ፤ ይሞታሉም። የእኛ የአሁኖቹ ትንንሾቹ እና የጥንቱ ታላላቆቹ አባቶቻችን ልዩነት ይሄ ነው። ያም ሆኖ፣ እኛ በአስተሳሰባችን እና መንፈሳችን

ዐለማዊ-ምአራባዊ ነን ብንልም፣ ከዛ ሕብረተሰብ ውስጥ ስለወጣን በውስጠውስጣችን ወይም በስረ-ሕሊናችን (subconscious) ውስጥ ፍጹም ከመንፈሳዊነት አልቦ ነን ለማለት አንችልም። ዛሬ አውነተኛ መንፈሳዊ ራሳችንን ለመሆን ባንችልም እንኳን ታሪካዊ ምንነቱን መረዳቱ ራሱ የማንነት ቀውሳችንን ሊፈውሰን ይችላል።

በአርግጥም ማንነታችንን ጠንቅቀን ብናውቅ ኖሮ ዛሬ የገባንበት የማንነት ቀውስ ውስጥ አንገባም ነበር። ማንነታችን የዘር ማንዘሮቻችን አፍአዊ ወይም ውጫዊ ማንነት ብቻ አያደለም። ውስጣዊም ነው። ውስጣዊ ማለት ደግሞ መንፈሳዊ ማለት ነው። ዘር ማንዘሮቻችን ባብዘኛው በአንድ እግዚአብሄር የሚያምኑ ሰዎች ነበሩ። በእዚህ እምነታቸው ላይ ተመርኩዘው፣ ኖረውበትና ሠርተውበት ኢትዮጵያን ለኛ አስረክበዋል። እኛ እነሱን በቅጡ አላወቅናቸውም። ብናውቃቸው ኖሮ፣ የእነሱን ማንነት ያገናዘበና ግምት ውስጥ ያስገባ ለውጥ ለማምጣት በተጣጣርንና ለውጡም መሬቱ ላይ ባለው በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ስለሚሆን ውጤታማ በሆንን ነበር። እነሱን ስላላወቅናቸውና ልናውቅም ስላልፈቀድን፣ በራሳችን ፍላጎት ተመርተን መልካም ዓረ ሳናፈራ ቀረን። ለወደፊት የሚደረግ ለውጥ ሁሉ የቅድመ-ዘሮቻችንን ሀቀኛ ማንነት እና ታሪክ ያገናዘበ መሆን ይገባዋል።

ይች መጽሀፍ ለእዚህ ዐላማ አንድ አይነት ግንዛቤ እና አስተዋፅ
ታደርጋለች ብዬ አስባለሁ።

ስለዘራችን ስናወጋ፣ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን፣ የዛሬ 40
ዓመት የኖሩ የአንድ ኢትዮጵ የተባለ ሰው እና እንቁዮጳግየ
የተባለች የአንዲት ሴት ልጆች እንደሆንን መገንዘብ አለብን። ይህ
እውነት ባለማወቃችን ግን ጎሳችን (ጎሳ ማለት ቋንቋ ነው። ዘር
አያቅፍም፤) ላይ አተኩረን ኢትዮጵያውያን በመሆን ፈንታ ጎሰኛ
(ቋንቋ ላይ አትኳሪዎች) ሆነናል። ለጎሳ ‹‹ብሄር›› የተባለ፣ ጎሳ
በትክክል የማይገልጸውን ቃል ሰይመንለት ‹‹የብሄር ጥያቄ›
የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ በተማሪዎች ንቅናቄ እና በአብዮት ውስጣ
ከሩሲያ አስመጥተን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ እውነታ ጋር
ልናጣጥመውና ልናዋህደው አልቻልንም። በእዚህ ምክንያት
ባለፉት 40 ዓመታት የማንነት ቀውስ ውስጥ ተዘፍቀን መጀመሪያ
ብሄሬን (ጎሳዬን) ነኝ፣ ቀጥሎ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ እስከማለት
ደርሰናል። እውነቱ ግን መጀመርያ ኢትዮጵያዊ መሆን በተገባን
ነበር። ምክንያቱም ሁላችንም ኢትዮጵ ከተባለ ሰው ደምና ስጋ
ተፈጥረን፣ ኢትዮጵያ በተባለች፣ እሱ በስሙ ባስጠራት እና
በመሰረታት፣ እሰካሁንም በአለች ሀገር-ምድር ውስጥ ስለተገኘን።
ሰው መጀመሪያ ከወላጆች በአካል (በስጋና ደም) ይወለዳል።
ከወላጆቹ ጋር ከአደገ ቋንቋ እና ባህላቸውን ይማራል። ቋንቋና

ባህልን ለመማር በአንድ ሀገር ከሁለት ወላጆች መጀመሪያ ሰው
ሆኖ ይገኛል። ስለዚህ ቀዳሚው ሰው እና የበቀለበት አፈር ነው።
ቋንቋ እና ባህል ሁለተኛ ወይም ተከታይ ነው። ወላጆችህ እነማን
ናቸው ተብሎ ሲጠየቅ፣ በዘር ያስገኙህ እነማን ናቸው መባሉ
ነው። እኛንም በዘር ያስገኘን ኢትዮጵ ነው። የተገኘንበትም ቦታ
ኢትዮጵያ ነው። ስለዚህ፣ በመጀመሪያ ኢትዮጵያውያን ነን።
ቀጥሎ ጎሳችንን (አሁን ብሄር የምንለውን) ነን። ኢትዮጵያውያንን
እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያንን ሁሉ የሚያገኛኘን በዘረ-ምንጫችን
ኢትዮጵ ከተባለ ሰው አብራክ መፍለቃችን ነው። ይህ ግልጽ
ካልሆነልን ውዥንብርና የማንነት ቀውስ ውስጥ እንገባለን። ያ
እንዳይሆን፣ የተለያዩ ቋንቋዎች ብንናገርም (ኢትዮጵያ ውስጥ
እስከ 82 የሚደርሱ ቋንቋዎች ይነገራሉ ይባላል)፣ ሁላችንም በዘር
ከሁሉ አስቀድሞ ኢትዮጵያውያን እንደሆንን መገንዘብ አለብን።
ኖሚያዛምደንም አንድ ዘር መሆናችን ነው። ለስጋ ዝምድና ወሳኙ
ዘር እንጂ ቋንቋ ወይም ባህል አይደለምና። ሰው ቋንቋ እና ባህል
ሊለውጥ ወይም ሊረሳ ይችላል። ዘሩን ሊለውጥ ወይም ሊረሳ ግን
አይችልም። አካሉና ገፅታው፣ የውስጥም ህዋሳቱ እና ንጥረ-ነገሩ
ይመሰክራሉና።

በመፅሀፉ ዝርዝር የተመለከቱት ዓመታት በኢትዮጵያ
ቀናት አቆጣጠር ነው። የኢትዮጵያ ቀናት ቀመር ከአውሮጳውያኑ

በስምንት ዓመታት ገደማ ይቀንሳል። ለምሳሌም አሁን ያለነው በአውሮጳ አቆጣጠር 2017 ላይ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ገና 2009 ነው።

የዋቢ መፅሃፍት ዝርዝሩን በተመለከተ፣ ታሪክ ከጻፉ ኢትዮጵያውያንና (መሪራስ አማን በላይን ጨምሮ) የውጭ ምሁራን፣ 66 መጻህፍትን ካካተተው ከንጉሥ ጀምስ መፅሃፍ ቅዱስ፣ ከኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ውስጡ 81 መጻህፍት ከአሉት መጽሃፍ ቅዱስ፣ እንዲሁም ውስጡ 76 መጻህፍት ከአሉበት ከ ‹‹ካቶሊክ መፅሃፍ ቅዱስ››፣ ድርሳናት ጠቅሼያለሁ። መፅሀፍ ቅዱስ ለሶስት ዐላማ ሊውል ይችላል። ዐንደኛው ለ ስነመለኮት እውቀት፣ ሁለተኛው ለ ታሪክ፣ ሶስተኛው ደግሞ ለስነጽሁፍ። ለእዚህ መጽሀፍ የተጠቀምኩት የታሪኩን ክፍል ነው። መጽሀፍ ቅዱስ የእስራኤልን ህዝብ ታሪክ ፍንትው አድርጎ ያንጸባርቃል። አልፎ አልፎም ስለ ኢትዮጵያ ይናገራል። በእዚህ ምክንያት ስለ አይሁዳውያን እና ኢትዮጵያውያን ታሪክ የሚከትብ ሰው መጽሀፍ ቅዱስን መመርመር ግድ ይላል። መጽሀፍ ቅዱስ እንደ ታሪካዊ ሰነድነቱ ባለፈው 3500 ዓመታት የተረካቸው ቁጥራቸው የማይናቅ ክስተቶች በቁፋሮ (አርኪዎሎጂ ጥናት) እውነተኛነታቸው ተረጋግጧል። ለምሳሌ የዳዊት ከተማ የተባለው እና ሌሎችም በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ተወግቶላቸው የነበሩ

ቦታዎች ዛሬ በቁፋሮ እየወጡ የመጽሀፍ ቅዱስን ታሪካዊ ሰነድነት እያረጋገጡ ነው። ስለእዚህ፣ የመጽሀፍ ቅዱስን ታሪካዊ ሰነድነት አልተቀበልም የሚል ሰው፣ የመጽሀፍ ቅዱስን ምንነት ያልተገነዘበ ሰው ነው ማለት ነው። የመጽሀፍ ቅዱስን የታሪክ ሰነድነት አንደ ምሁር ስለተቀበለ ሃይማኖታዊ ነው ወይም ሳይንቲስት አይደለም ማለት አይደለም። በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰው በኋላ በሳይንስ ሲመረመሩ እውነት ሆነው የተረጋገጡ ብዙ ነገሮች አሉ። ይህም ከግንዛቤያችን ውስጥ መግባት አለበት።

ስለቅዱስ ዳዊትና ቤተሰቡ እና ስለ ኢትዮጵያውያን ሴት አያት ቅድመአያቶቹ በ አይሁዳውያኑ መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ መዘርዘር ያለበትን ያህል አልተዘረዘረም። የአይሁዳውያን ጸሀፍት ሰራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ የሚለውን በመፈጸማቸው ስለራሳቸው ብቻ አጉልተው ሲጽፉ ኢትዮጵያ-ነክ የሆኑትን ምዕራፎች ወይ አድበስብሰዋቸዋል ወይም እስከነ አካቴው ዘልለዋቸዋል። ዕድለኛ ሆነን የኛ ቀደምት አባቶቻችን ግን በእኛው ያሻር በተባው ጥንታዊ መጽሀፍ ውስጥ ስለ ቤተ-መሴ፣ ስለ ቤተ-ዳዊትና ስለ ሁሉም ከእስራኤል ጋር ስለተዛመደው ታሪካችን መዝግበዋል። መሪራስ አማን በላይ ያሻር ን በግዕዝ አግኝተው አሳጥረው በአማርኛ ስለ አተረጓጎሙ እና እውነተኛ ታሪካችን እዛ ውስጥ ስለተገኘ እኔም ከሳቸው መጻህፍት በብዛት እጠቅሳለሁ።

የመሪራስ አማን ድርሳናት ተውጣጥተው ወደ አማርኛ የተተረጎሙትን ክፍ ብዬ እንደጠቀስኩት፣ ከጥንታዊዉ የቤተክህነት፣ እስከዛሬም የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያ ከምትገለገልበት ከግዕዝ ቋንቋ ነው። የመሪራስ አማን በላይ ግኝ የተለያዩ ድርሳናት መድበል ሲሆን፣ በዓለም ዙርያ ተፈልጎ ጠፍቶ እኛ ዘንድ የተገኘውን ጃንሸዎን ወይም ጣንሸዎን ይጨምራል፡ እሱም *መፅሃፈ ሰብኤ* በሚል ርዕስ በሚታወቀው ድርሳን ውስጥ ተካቶአል። በጣንሸዎ ከተገኙት መጻህፍት ውስጥ *ያሻር* የሚባል አለበት። ጃሻር ወይም ያሻር፣ በእብራይስጥ *ሰፈር ሀ ያሸር*፣ በግዕዝና በአማርኛ ‹‹የአሳር›› ወይም የፍዳ የሚል ትርጉም ሲኖራቸው በርካታ ገፆቻቸው የሰው ዘር ከእግዚብሔር ትእዛዝት በማፈንገጡ እግዚአብሄር መቆጣቱንም የሚያትቱ ናቸው።። በ*ጃንሸዎ* ውስጥ እየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን የሚገልጽ መረጃ ስለነበር፣አዬዎቹን ቀበተው ያነገሡ የግብጽ ፓትርያርኮች፣ እየሱስ ሲሆን ቆዳችን ወደነጣው ወደ ግብጾች ሀገር እንጂ እንዱት ወደ ጥቁሮቹ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ያመራል፣ ብለው በቅናትና በምቀኝነት ተገፋፍተው እነዚህን ብርቅዬ መፃህፍትን እና ባለቤቶቻቸውን ያሳድዱ ነበር። በዚህም ምክንያት ጻህፍቱ ሥራዎቻቸውን ደብቀው ወደ ግብጽ እና ኑብያን (ሱዳን) መኮብለል ግድ ሆኖባቸዋል። የመሪራስ ብራናዎች ባለአደራዎች ብራናዎቹን ለወደፊቱ ለምሁራኖች ሁሉ በሚገልጹበት ወቅት

አትምና ጊዜ ያላቸው ምሁራን ብዙ ሊጽፉ ይችላሉ። እኔ ባገኘኋት በትንሽዋ መረጃ ላይ ተመስርቼ በትንሽዋ አቅሜ የቻልኩትን አድርጌአለሁ። የኢትዮጵያ ታሪክ ገና መጀመሩ እንጂ መፈፀሙ አያደለም። ስለዚህ ገና ብዙ ያስጽፋል። አቅም እና ጊዜ ያለው የታሪክ ተማራማሪ በእዚህ ረገድ ገና ብዙ ይፈጽማል።

የሚገርመውና ለማመንም የሚያዳግተው ክክርስቲያን ተብዬዎቹ በኢትዮጵ የግብጽ ፓትርያርኮች ውስጥ አንዳንድ ክርስቲያን መሰል ሙስሊሞች መኖራቸው ነው። ክርስትያን ነን አያሉ፣ ከቤተክርስቲያን ይልቅ መስጊዶችን እያስገነቡ፣ የኢትዮጵያን ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልሳንን ግዕዝን ለማጥፋት አረብኛን ያስፋፉ ነበር። አረቦቹ ሙስሊም ሆነው እና ሙስሊም መሆናቸውን ይፋ አውጥተው መስጊዶች አስገንበተው ቢሆን ኖሮ ሥልነም በነበር። ምክንያቱም ሀይማኖታቸውን ማስፋፋት ግዴታቸው ስለሆነ። ዳሩ ግን ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስቲያን ነን አያሉ መስጊድ መሥራታቸው ቅጥፈት ነበር። ለጥንቶቹ መጻህፍት መሰወር አንደኛው ምክንያት የግብጾቹ አረብ ጳጳሳት ሲሆኑ፣ ሌላው ደግሞ መጻህፍቱን ለማጥፋት የቀዳማዊ ምኒሊክ መከራ ነው። እሱ ለምን እንደዚያ እንዳደረገ ይህ መፅሃፍ በተጣይ ምእራፎቹ ያብራራልናል። የጃንሸዎ እና የያሻር ድርሳናት ከመፅሃፍ ቅዱስ ቀደምት ስለመሆናቸው የሚመሰክሩላቸው፤

እነሱን ያነበቡአቸው ሙሴ፣ እያሱ እና ነብዩ ሳሙኤል ናቸው። ይህንንም በቦታው አሳያለሁ።

ቀደም ሲል በነቢያ ተገኝተዋል የተባሉት ድርሳናት የጥንቶቹ ወሪጅናሌዎቹ አልነበሩም። በብራና ላይ በቱም ፅሁፍ ሰፍረው የተላለፉልን ሥራዎች ናቸው። በዚያን ዘመን ማተሚያ ቤቶች አልነበሩም። ጸሀፍቱ ለራሳቸው መጠቀሚያ ወይም ለሽያጭ ከሌሎች ድርሳናት ይገለብጡ ነበር። የዛሬ 350 ዐመታት ገደማ ዓፄ አድያም ሰገድ እያሱ የተባለ ንጉሠነገሥት እንደነበረን የታሪክነገሥቱ ብራናዎች ያወሳሉ። ከዚያ ጊዜ በኋላ ስለኢትዮጵያ ነገሥታት ወይም ድርጊቶች አንዳች መልእክት አልዘከሩም። በዚህ መሰረትም፣ ምንም እንኩዋን ትረካዎቹ ጥንታዊ ጉዳይዎችን ቢያጠነጥኑም፣ ታሪክነገሥቱ የተደመደመበትን ዘመን በግምት 350 ዓመታት እናደርገዋለን።

አንዳንድ የሀገራቸውን ታሪክ ገናናነት ለመቀበል የማይፈልጉ ግለሰቦች ወይም ምሁር-ተብዬዎች የኢትዮጵያ ታሪክ እጅግ አስደናቂ ሆኖ ሲያገኙት፣ አፈታሪክ ነው፣ ብለው ሊበትኑት ይሻሉ። በአፈ-ታሪክና በጽሁፈ-ታሪክ መሀል ያለውን ልየነት እንኳን ለመገንዘብ ይሳናቸዋል። ስለ አፈታሪክና ጽሁፈ-ታሪክ ትንሽ ለመናገር ፍቃዴ ነው። እነዚህን ሁለት የታሪክ አይነቶች የሚያዛምዳቸው አንድና አንድ ነገር አለ። ታሪክ

ይባላል። ሁለቱም ታሪክ ናቸው። በጅምላዊ አባባል ልዩነታቸው አንዱ የቃል፣ ሁለተኛው የጽሁፍ መሆኑ ነው። ጥንት በጽሁፍ ሰፍሮ የነበረው የኢትዮጵያ ታሪክ፣ በተለምዶ ዮዲት ጉዲት የምትባለዋ ፈላሻዋ አስቱር እኤአ በ878 ዐመተ ምሕረት አካባቢ የአክሱምን መንግሥት ከአፈረሰችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አጼ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ (እኤአ 1299) ማለትም ለ421 ዐመታት ያህል ደብዛው ጠፍቶ በቃል ወይም በአፈታሪክ ብቻ ይነገር ነበር። ታላቁን ንጉሠነገሥት አምደጽዮንን ይህ ነገር አሰግቶት፣ እንደ ክቡር ተክለጻድቅ መኩሪያ ትረካ፣ በድፍን ኢትዮጵያ የነበሩትን የኢትዮጵያን ታሪክ በቃል የሚያውቁትን ሊቃውንት አሰባስቦ አፈታሪኩን በመጽሃፍ አጽፎ፣ ጠፍቶ የነበረው ታሪካችን እነሆ፣ ብሎ ለኢትዮጵያ ህዝብ ታሪኩን እና ክብሩን መልሶለታል። ተክለጻዲቅ መኩሪያ እንደሚሉት የጥንቱ መጻህፍት የጠፉት በዮዲት ተቃጥለው ነበር። ዮዲት የኢትዮጵያን ታሪክ አቃጥላለች የሚባለውን እኔ እጠራጠረዋለሁ። የጥርጣሬዬ ምክንያት ወደ ፊት ግልጽ ይሆናል። ለማንኛውም፣ ዮዲትም ታቃጥለው ወይም ሌሎች ጠላቶች ያጥፉት፣ ለጊዜው የክቡር አቶ ተክለጻዲቅ መኩሪያን አባባል እንቀበል እና አጼ አምደጽዮን እንደገና የኢትዮጵያን አፈታሪክ እንዴት አንደ አጻፈው እናስተውል፦

‹‹ስለዚህ ከዮዲት ወዲህ እስከ አጼ አምደጽዮን ድረስ ታሪክ የሚጠቀሰውና የሚተረከው ከአዋቂዎች ቃል በቃል በወረደው ብቻ ነበር። ይህ ብልህ ንጉሥ እዙፋን ከወጣ ወዲህ ይህ ቃል በቃል የሚነገረው ታሪክ በቶሎ ክብራና ላይ ሰፍሮ ለልጅ ልጅ እንዲተላለፍ ካልሆነ ወደ ፊት ሊጠፋ እንደሚችል ተገነዘበ ማለት ነው። ...ስለዚህ ያለፈ ታሪክ የሚያውቁትን ሊቃውንቱን ሰብስቦ ታሪክ እንዲጻፍ አዘዘ ይባላል።›› (ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐጼ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐጼ ልብነ ድንግል*፣ ገጽ 40)

የተክለጻድቅ መኩሪያ ትረካ እንደሚለን ስለዛ ዘመን የሚያወጋው አሁን በመጽሀፍ ማህደር ውስጥ የተቆለፈው ለ 421 ዐመታት በቃል ሲነገር የነበረው ታሪካችን መሆኑ ነው። ይህ የሚያረጋግጠው፣ ታሪክ በቃልም ቢሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መሆኑን ነው። ስለዚህ አፈታሪክን አቅልለው በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የሚሰለቁ ሰዎች እጅግ የተሳሳቱ አላዋቂዎች ናቸው። አፈታሪክ የታሪክ አንዱ ገፅታው ነውና።

መሪራስ አማን በላይ ከኑብያ ያገኙአቸውን ድርሳናት አንተ ዐይተሃቸዋል ወይ፣ ተብዬ ከዚህ በፊት በአንድ ‹‹ጋዜጠኛ›› ተጠይቄ ነበር። ይህን መጽሃፍ በእንገሊዝኛ ከማሳተሜ አስቀድሞና *የ ኦሮሞና የ አማራ እውነተኛው የዘር ምንጭ*፣

የተባለው የታሪክ መጽሀፌ ለገበያ ከመዋሉ በፊት ከቁርጥራጭ ወረቀ መሉ ሰነድ ዐላየሁም ነበር። ስለዚህ ‹‹ዐላየሁም፤›› ስል አውነቱን ተናገርኩ። ሰነዶቹን ያኔ የዐላየሁት ማየት ስለማያስፈልገኝ ነበር። ከአግኚው ጋር ለስምንት ዐመታት ተወዳጅተን እንነጋገር ስለነበርና እሳቸው በሰነዶቹ ላይ ተመስርተው የከተቡአቸውን ሁሉ መጻህፍት ስለመረመርኩ፣ በተጨማሪም ሰውዬው በፍጹም የማይዋሽ ሀቀኛ ስለነበሩ፣ ሰነዶቹን ማግኘታቸውን ከቶውንም ተጠራጥሬ አላውቅም። ዐያተሃል ወይ የሚለው ጥያቄ ከተነሳ በኋላ ግን መሪራስ አማን በላይ ራሳቸው ፈቅደው ለጽሁፌ የሚጠቅሙኝን አንዳንድ የብራና ግልባጮችን ዐሳዩኝ። ስለ ብራናዎቹ መኖር ቀድሞውኑ ጥርጣሬ ሰላልነበረኝ እነሱን ማየቱ በእምነቱ ላይ የጨመረው ምንም አዲስ ነገር አልነበረም። ‹‹ሳያዩ የሚያምኑ በጹአን ናቸው›› ብሎ እየሱስ ክርስቶስ በቶማስ አማካኝነት የተናገረው በእኔ ላይ ተፈጽሞ ነበር። የሚገርመው ነገር፣ ፈረንጆች ሳያዩ እንደ ዐየ ሰው ሆነው የሚጽፉልንን ታሪካችንን ወይም በመንገድ ሲያልፉ ያዩትን እኛ ኢትዮጵያውያን ስንቀበል፣ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የሚከትቡትን እውነት ግን እንጠራጠራለን። ለምሳሌ The Sign and The Seal (እኤአ በ1992 ያሳተመው) የተባለውን መጽሀፍ የጻረሰው ፈረንጅ፣ እንግሊዛዊው ተመራማሪ Grahm Hancock (ግራሃም ሃንኮክ)፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ የሚባለውን ታቦተ-

ጽዮንን በዐይኑ በብረቱ አላየም። ሆኖም፣ በተዘዋዋሪ መረጃዎች ላይ ተመስርቼ ታቦቱ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን አረጋገጫለሁ፤ ብሎ አንድ ባለ 600 ገጽች ጠበደል መጽሀፍ ጽፎ እንደ ጉድ ችበችበው። እኛ ብቻ ሳንሆን ዐለም በሞላ አምኖት መጽሀፉ ከታተመ በኋላ ታቦቱን አሰሳ ምድሪ ቱሪስት ወደ ኢትዮጵያ ይጎርፍ ጀመር። ሌላም ፈረንጅ በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ገዳማቱን እና አድባራቱን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን ቅዱሳን ስፍራዎች ሁሉ አዳርሶ እየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር፤ ብሎ በፊት እየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለ ሶስት ዐመታት ኖሮ ነበር የሚለውን አፈታሪክ እውነተኛነት በሲኒማ አስደግፎ አረጋገጠ።

የዛሬ 6 ዓመት ደግሞ Jim Rankin (ጂም ራንኪን) የተባለ አንድ አሜሪካዊ ምሁር እና ወንጌላዊ የኢትዮጵያን የብስና ባሕር መርምሮና በርብሮ፣ እየሱስ ክርስቶስ በልጅነቱ ወደ ምድረ ኢትዮጵያ መምጣቱን በተዘዋዋሪ መረጃዎች ተገንዝቦ እና አረጋግጦ *Jesus In Ethiopia* (እየሱስ በኢትዮጵያ) የሚል መጽሀፍ ደርሷል። መጽሀፉም በዐለም ዙሪያ ተቀባይነትን አግኝቷል። መሪራስ አማን በላይ ግን ከዚህ ፈረንጅ መረጃዎች በተሻለ ‹‹ዜና ማርሄር›› በተሰኘ፣ እየሱስን በልጅነቱ ከግብጽ ጀምሮ በሚያውቀውና ኢትዮጵያ ውስጥም ለሦስት ዓመታት አብሮት

በኖረው ማርሔር በተባለ ኢትዮጵያዊ መጽሀፍ ላይ ተመርኩዘው እየሱስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ የሚል መፅሐፍ አቅርበው ነበር። እኔም በዛ ላይ ተንተርሼ ስለ እዚሁ አስደናቂ ጉዳይ ከትቤ ነበር። ሆኖም እየሱስ እንዴት ኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖር ይችላል እያሉ፣ አግዚአብሄር ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ማክበሩን ለመረዳት ተስኗቸው ይህን እውነት ለመቀበል የተቸገሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ከእዚህም በላይ የሚያሳዝነው ነገር፣ መሪራስ አማን በላይ እጅች ውስጥ የጥንት ታሪክ መጻህፍት እንደ አሉ እኔ የህግ ጠበቆች ወንጀል መሠራቱን በሚያረጋግጡበት በተዘዋዋሪ ማስረጃ በ(Circumstancial evidence) አረጋግጫለሁ፤ ሰል አንዳንድ ግለሰቦች አልተቀበሉኝም ነበር። ቀድሞውንም ቢሆን፣ መሪራስ አማን በላይ፣ ዋቢ መጻህፍት ሳይኖሯቸው እነዛን ሁሉ አስደናቂ መጽሀፎች ከልባቸው አንቅተው ሊጽፉ አንደማይችሉ ለኔ ግልጽ ነበር። ምክንያቱም መረጃ የሌለው የሰው ልጅ አእምሮ ያን ሁሉ እፁብ ድንቅ የምድርና የሰማይ ነገር ሊከትብ ስለማይችል። የሆነ ሆኖ የመሪራስ ባለአደራዎች ለወደፊቱ ግኝቶቹን በቤተመዘክር ወይም በዩኒቨርሲቲ ቤተመጻህፍት እንደሚያኖሩት እምነቱ ነው። የሚቹ የመሪራስ አማን በላይ የመጨረሻ ምኞት ይህ ነበርና።

የመልከጸዲቅና አብርሃሐም ግንኙነት እና ማንነት፣ መጽሀፈ ያሻር እና ዣንሸዋ

በአይሁድና በኢትዮጵያውያን ህዝቦች መካከል ያለዉ ግንኙነት የተመሰረተው የአይሁዶች አባት አብርሃም፡ የኢትዮጵያውን ዘረ-ግንድ የሆነው የኢትዮጵ አባት መልከጸዲቅ የሳሌም ንጉሥ፣ የዛሬ 4000 ዓመታት የተወዳጁ ጊዜ ነው። ያም ወዳጅነታቸው እያበበ ሄዶ በአብርሃምና በመልከጸዲቅ ትውልዶች ወደ ጋብቻ ዝምድና ተመነደገ።

አይሁዳውያን ሰዎችን ወይም ባልንጀሮቹን አግኝቹ ‹‹ኢየሩሳሌም›› የተሰኘው ስም ምን ማለት እንደሆነና ከተማዋንስ ማን እንደሰየማት ስጠይቃቸው ምንም እንደማያውቁ ይነግሩኛል። መልሱን ለመስማትም ይጓጓሉ። በዐለም ላይ ከተከሰቱት የረጅም

ዘመን ወዳጅነት ምናልባት እጅግ ረጅሙ እና ጥንታዊው ሰለሆነውና ዘመን ሳይሽረው እስከዛሬ ስለዘለቀው የአይሁዶችና የኢትዮጵያውያን ግንኙነት በዚህ መፅሐፍ አወጋለሁ።

በመግቢያዬ እንደጠቀምኩት መረጃዎቼ ከሚያጣቅሱት ውስጥ እነ *መፅሐፈ ዣንሸዋ* (ከመጽሃፍ ቅዱስ በፊት መኖሩን ነቢዩ ሙሴ የመሰከረለት *ዣንሸዋ* የእግዚያብሔር ታላቁ ሰራዊት ወርነት ድርሳን)፤ *መፅሐፈ ያሻር* (ከመጽሀፍ ቅዱስ በፊት መኖሩን እያሱና ነቢዩ ሳሙኤል ያረጋገጡለት ጥንታዊ መጽሀፍ) እና *ታሪክ ነገሥት ዘኢትዮጵያ* ከሚሰኙት ዘመናት ያቋረጡ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሰነዶችና ሌሎችም ታሪካዊ መፃህፍት ነው። ነቢዩ ሙሴ፣ *ዣንሸዋን* ማንበቡን በኦሪት ዘሀልቆ 21፣ ቁጥር 14 ይገልጻል። የአይሁዳውያን ታሪክ *ዣንሸዋ* ውስጥ መመዝገቡንም ይጠቅሳል። ይህን መልእክት ግልፅ ለማድረግ ከነብዩ ሙሴ ቀጥሎ የእሰራኤልን ህዝብ የመራው እያሱ እና ነቢዩ ሳሙኤል የታሪካቸውን እውነተኛነት ለማረጋገጥ *መፅሐፈ ያሻርን* ለእማኝነት ወይም ለማጣቀሻ እንዳነሱት ሁሉ እርሱም የሥራውን ሃቀኝነት ለማስረጃት (ማስረጃ ለማቅረብ) እኛ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ያነበትነውን ቅርሳችንን በማስረጃነት ጠቅሷል። ለዚህ ጽሁፍ እንደተጨማሪ መረጃና ምስክርነት እያሱ በመጽሀፍ ቅዱስ ስለ *ያሻር* እንዲህ ይላል፦ ‹‹ህዝቦቹ በጠላታቸው ላይ ድልን

እስኪቀናጁ ፀሃይ ሳትጠልቅ ቀጥ ብላለች። ጨረቃም ባለችበት ጸንታለች። ታዲያ ይህ በ*መጽሃፈ ያሻር* አልሰፈረምን?›› (እያሱ 10.13)። ይህ ተአምራታዊ ክስተት በ*መፅሃፈ ያሻር* በዝርዝር ስለተቀመጠ፣ እያሱ እውነት ተናግሮአል። ከንጉሥ ሳኦል ሞት በኋላ ስለደረሰው አሳዛኝ ሁኔታ ሲገልፅ፣ ነቢዩ ሳሙኤልም *መፅሃፈ ያሻርን* አጣቅሶ፡- ‹‹እናም በሳኦልና በልጁ በዮናታን ሞት ዳዊት አዘነ፣ የይሁዳ ልጆች ስለ ቀስትና ደጋን አጠቃቀም እንዲማሩ ፈቀደላቸው፤›› የሚል ዕሁፍ በ*መፅሃፈ ያሻር* ሰፍሯል (*መፅሃፈ* ሳሙኤል ካልዕ 1,17) በማለት ያትታል።

መፅሀፈ ያሻር እና *ጃንሸዋ* በመልከጸዲቅና የኢትዮጵያውያን ቅድመ-አባት በሆነው በኢትዮጵ በኩል ከኖህና ከኩሽ ለኢትዮጵያውያን የተላለፉ ናቸው። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ጸሀፍት የነገሥታቶቻውን እና የሃገራቸውን ታሪክ ውስጡ እየጨመሩ አስረዘሙት። እንዲሁም አስፋፉት። አይሁዳውያን በታሪክ አጋጣሚ ስለቀረቧቸው እና ስለተዛመዷቸው እግረመንገዳቸውንም የአይሁዳውያንንም ታሪክ እየከተቡ አሰፈሩበት። ኢትዮጵያውያን አበው ያደረጉት እስራኤላውያን ነብያትና ካህናት ሙሴ በከተባቸው በአሪት ዘፍጥረትና ሌሎቹም መጻህፍት ላይ የየራሳቸውን መጻህፍት ጨምረው የዛሬውን መጽሀፍ ቅዱስ እንደ አዳበሩት ማለት ነው። በአፅንኦት ለመግለፅ

ያህል፣ መጽሃፈ ያሻርና ጎርንሽዋ በመጀመሪያ የተደረሱት በአዳምና ሄዋን ቋንቋ በሰባ ነው ብዬ አስባለሁ። የሰባ ቋንቋ ፊደላት፣ መዝገበቃላት እና መጽሃፍም በመሪራስ አማን በላይ ተገኝተው በኛ ዘንድ አሉ። በኋላ በአብራይስጥና በግዕዝ ተገልብጠው የተጠናቀሩ ቢሆኑም፣ መፅሃፈ ያሻርና ጎርንሽዋ ኢትዮጵያዊ ስለመሆናቸው አፋችንን ሞልተን መናገር እንችላለን።

አንዳንድ ተጠራጣሪ ግለሰቦች የሰባ ቋንቋ ስመኖሩ ምን ማስረጃ አለ ስለሚሉ፣ ከእዚህ ቀደም ከታተሙት የሰባ ፊደላት፣ የሰባ እና የግዕዝ መዝገበቃላት በተጨማሪ የሰባ ቋንቋ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ከዚህ በታች ያለው የብራና መጽሀፍ ፎቶግራፍ ለአማኝነት ቀርቧል። በመጽሀፉ የቀኝ ገጽ ላይ የላቲን የሚመስሉ ፊደሎች ይታያሉ። እነዚህ የላቲን ፊደላት መሳይዎቹ ከጥንቱ የሰባ ፊደላት ወደ ላቲን የተወሰዱ ናቸው እንጂ የተገላቢጦሽ አያደለም። ሰባ የመጀመሪያው የሰው ልጅ ቋንቋ እና ፊደላት ነውና።

ቅዱስ ላሊበላ ከመወለዱ ከ1000 ዓመታት በፊት ንግሥት ዮዲት ማርካ ነፍሱን ያተረፈችው ልዑል (ወደ ኑብያ ከተሰደደ በኋላ እዛው ንጉሥ የሆነው) አክሱማይ ሲራክ የሱባን ቋንቋ አቀላጥፎ ይችል እንደነበር ተጽፏል። ከኢትዮጵ ጀምሮ እስከ ንግሥት ዮዲት (ጉዲት፣ እሳቶ እያሉ የሚያቃልሏት) ድረስ የተከሰተውን የኢትዮጵያን የ1000 ዓመታት ታሪክ በ*ሻንሸዎ* እና በ*ያሻር* ላይ አግኝቶ ወደ ግብጽና ኑብያ ወስዶ ያቀየልን ትልቁ ባለታሪክ የኢትዮጵያ ባለውለታ መሆኑ የማይዘነጋ ነው። ቅዱስ ላሊበላም የሱባን ቋንቋ ጠንቅቆ ያውቅ እንደነበር ይነገራል። ከወንድሙ ቅናትና ቁጣ ሸሽቶ በኢየሩሳሌም በስደት ኖሮ በግብጽ በኩል አማርና ደልታ በተባለው የአማሮች መንደር ሲያልፍ ወይም ወደ መርዌ የኢትጵያ ከተማ ጎራ ባለ ጊዜ አክሱማይ ሲራክ ቀደም ብሎ እዛ የተዋቸውን በሱባ እና በግዕዝ የተከተቡትን *ያሻርን* እና *ሻንሸዎን* እንደአገኘና ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶ እንደ አራባቸው ተመዘግቧል።

መዕሃፈ ያሻር እንደሚለው፤ የሙሴ ልጆች በግማሽ ጎን ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ የነብዩ በልዓም የልጅ ልጅና የአቤድ እናት የሆነችው ሩት፣ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ሃብሌ (አብሌ) የሚሏት፣ እስራኤላውያን ግን አዶሊያ (አዩል) ብለው የሚጠሯት

የንጉሥ ዳዊት እናት ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በዚህ ምክንያት፣ የሙሴና የንጉሥ ዳዊት ቤተሰቦች ስለ ቅዱስ ዳዊትና የሙሴ ቤተሰቦች ከማንም ይበልጥ ታሪካቸውን በኋላ *መጽሃፍ ቅዱስ* ከተባለው መጽሃፍ ጎን ለጎን በመጽሃፈ *ያሻር* እና በ*መጽሃፈ ሰባኤ* ውስጥ በዝርዝር አስፍረዋል።

ከሙሴ እና ኢትዮጵውያን ልጆቹ ከንጉሥ ዳዊት እና ኢትዮጵያውያን እናቱ፣ አያቱና ቅድመአያቱ ታሪኮች በተጨማሪ *ሻንሸዎ* ስለ ስነፍጥረት እና የኛን ዓለም ጨምሮ እግዚአብሄር 100 ዐለማትን እንደ ፈጠረ በዝርዝር ያወሳል። ሙሴ ራሱ ኦሪት ዘፍጥረት ብሎ የጻፈውን መጽሀፍ የመሰረተው በዚሁ በኢትዮጵያዊው አማቹ በዮቶርአብ ዘንድ አግኝቶ በአነበበው በ*ሻንሸዎ* ላይ ነው። ስለ መቶው ዐለማት ሙሴ ቢያነብም፣ ሰለዚችው ስለ አንዲቱ ዐለም መፈጠር ብቻ አተኩሮአል። ርግጠኛ ምክንያቱን የሚያውቀው ሙሴ ብቻ ቢሆንም፣ ስለ መቶ ዐለማት ቢናገር፣ ምን ይቀባዥራል ብለው፣ ምናልባት ሰበብ እየፈለጉ በሃጊዜው በድንጋይ ሊወግሩት የሚያሰፈስፉትን አመጸኞቹን የእስራኤል ህዝብ ፈርቶ ሊሆን ይችላል።

መዕሃፈ ያሻርን በተመለከተ፣ በምእራቡ ዓለም ሶስት የተሞከረበሩ አስመሳይ ቅጂዎች አሉ። እነዚህን ቅጂዎች አጥብቆ ለመረመረ ሰው መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡት

የመጀመሪያዎቹ 7 መጻህፍት እንደሆኑ ይገነዘባል። እነዚህ ሀሳዊ መጻህፍት፣ ነብዩ ሳሙኤል በመፅሃፈ ያሻር እንዳነበበ የሚያወሳውን በሳኦል ሞት ምክንያት የአደረበትን የንጉሥ ዳዊትን ሃዘን አይጠቅስም። ይህ ብቻውን እነዚህን የውሸት ክታቦች ውድቅ ያደርጋቸዋል። እውነተኛው የእኛ መጽሃፈ ያሻር ቅጂ ግን ከብዙው በጥቂቱ የዮቶርአብን ቤተሰብ፣ የሙሴን ከዮቶርአብ ጋር ኑሮ የኢትዮጵያውያን ቤተሰቡንና በቤተልሄም የልጆቹን ህይወት፣ ኢትዮጵውያኑ የሙሴ ልጆች ወሪጅናሌውን ታቦት በአደራ ጠባቂነት የተጫወቱትን ሚና፣ የሱንና የሚስቱን ወንድም የአባብሄርን (መጽሀፍ ቅዱስ ሆባብ የሚለውን) ግንኙነት፣ የሙሴ ልጆች ትውልዶች ወደ ኢትዮጵያ መሰደዳቸውን፣ የበልአምን ታሪክ፣ የእያሱን፣ የዳዊትን፣ የዳዊትን እናት አዶልያን (አዴልም ትባላለች)፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነችውን የዳዊትን የሴት አያት የሩትን፣ የሳሙኤልንና የዲቦራን ገድል ከኢትዮጵያውያን እይታ አንባር ይዘክራል።

እስከዛሬ የተከተቡት የአይሁዳውያን ታሪክ የተመሰረቱት በሙሴ አምስቱ መጻህፍት፣ በጠቅላላው ቶራህ ተብሎ በሚታወቀው የብሉይ መጻህፍት፣ በአዲስ ኪዳን ድርሳናት፣ እንዲሁም ምስራቃዊ እና ምእራባዊ ዐለማዊ ባለታሪኮች በክተቡት ላይ ነው። የሚያሳዝነው ኢትዮጵያዊ ምንጮቹ ከአይሁዳውያን እና

ከኢትዮጵውያን ጭምር ተሰውረው መቆየታቸው ነው። በዚህ ምክንያት የአይሁዳውያን ታሪክ ተብለው የሚቀርቡት ፅሁፎች ያልተሙዋሉ ናቸው። ይህ የኔ ሥራ በመጠኑም ቢሆን የጎደለውን ያሟላዋል ብዬ አስባለሁ።

የአይሁዳውያንን ህዝብ ያፈራው አብርሃም ይስሃቅን፣ ይስሃት ያቆብን፣ ያአቆብ አሰራ ሁለት ወንዶች ልጆች ወለዶ፣ አነሱ ተባዝተው አሰራ ሁለት ነገዶች እንደሆኑ መፅሃፍ ቅዱስ ይመሰክራል። እንዲሁም የሳሌም ንጉሥ መልከጸዲቅ ኢየሩሳሌም ላይ ኢትዮጵ በመባል የሚታወቀውን የኢትዮጵያውያን አባት የሆነውን ኢትኤልን አፈራ። ይህ ክስተት ከፍተኛ ታሪካዊ ውጤት ስላስከተለ የመልከጸዲቅን የህይወት ታሪክና ከአብርሃም ጋር ያለውን ግንኙነት ባጭሩ መጥቀስ አስፈላጊ ነው።

በእርግጠኝነት መልከጸዲቅ ማን ነበር? አንዳንድ የአውሮፓና አሜሪካ ወንጌላውያን መልከጸዲቅ የተባለውን ትልቅ ሰው ያለ አጋ አባትና እናት እንደተፈጠረ፣ መንስኤና ፍፃሜ እንደሌለው አድርገው (የመሲሁን ባህርያት በማላበስ) ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር ያምታቱታል። ስለሆነም ሰብአዊ የዘር ሃረጉን መግለጽ ግድ ይላል።

መልከጸዲቅ በመጀመሪያ የተጠቀሰው በኦሪት ዘፍጥረት አብርሀም ሄዶ ዐስራት ሲሰጠውና በቅዱስ ዳዊት አፍ ሲነገር ነው። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ መልከጸዲቅን የእግዚብሔር ዘላለማዊ ሊቀካህን ከሆነው ከመሲሁ ጋር በማነፃፀር እንዲህ ይላል፦ ‹‹እንደ መልከፀዲቅ ስርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ እግዚያብሔር ምሎአል፤ እርሱ ቃሉን አይለውጥም።›› (መዝሙረ ዳዊት፣110:4)

ከላይ የቀረበው በእግዚያብሔር የተሰጠ መሀላ ለ ንጉሥ ዳዊት አልነበረም። ምክንያቱም ዳዊት የዘላለማዊ ካህን ቀርቶ የጊዜያዊም ከቶ አልነበረምና፤ ወደፊትም አይሆንምና። እንዲሁም ሞቶ አልፏልና።

በ *ሣንሸዋ* እና *ያሻር* መሰረት፣ የሳሌሙ ንጉሥ መልከጸዲቅ የኖህ ቀጥተኛ ተወላጅ ነው። ኖህም ካምን ወለደ፤ ካም ኩሽን፤ ኩሽ ሳባን፤ ሳባ ካህኑን ኑባን፤ ኑባ ጋናን፤ ጋና ኢታንን፤ ኢታን የባቢሎንን ግንብ ያቆመውንና እስኪፈርስ ድረስ የባቢሎን ንጉሥ የነበረውን ናምሩድን ወለደ። (አማን በላይ፣ *መፅሃፈ ሰብዓ ዘበአማን ካልእ*፣ ገፅ 31)

በመፅሃፍ ቅዱስ ግን ኩሽ የናምሩድ አባት ሆኖ ናምሩድ የኖህ የልጅ፣ ልጅ፣ ልጅ በመደረጉ የዝክረ ትውልዱ አወራረድ

ተዛብቷል። በኛ ታሪካዊ ምንጭ አቀራረብ በኖህና በናምሩድ መሃል ስድስት ትውልዶች አልፈዋል።

ናምሩድ፣ አዳማህን፣ አዳማህ ራፌልብን፣ ራፌልብ ቀንአን፣ ቀንአ ጌራን ወይም በክህነት ስሙ መልከጸዲቅ (ጻዲቅ ንጉሥ) ተብሎ የሚታወቀውን ትልቅ ሰው ወለደ። አባቱ ቀንአ ‹‹አብ መሊክ››፣ ማለትም ‹‹የነገሥታት አባት›› ተብሎ ይጠራ ነበር። እግዚአብሔር ለቀንአ እና ለአማቹ በራዕይ ተገልጾላቸው፣ ጌራ ‹‹መልከጸዲቅ›› ተብሎና የጠቢባን ጠቢብ ሆኖ፣ እግዚአብሔር በመልከጸዲቅ ስርዓት በምድር ላይ ሊቀካህናት እስከሚሆን ድረስ ዓለማዊ ንጉሥና የእግዚአብሔር ሊቀካህናት እንደሚሆን አብስሯቸዋል።(መዝሙር 110፡ 4)

አባቱ ንጉሥ ቀንአንም ልጁን ጌራን (መልከጸዲቅ)ን ይህንን በማገናዘብ ቀደሰውና አነሳው፣ የክህነትና ንጉሣዊ ኃይሉም እንዲጠነክር በተለየ አካኋን ባረከው። ከዚያ በኋላም ዘውድ ደፋለት፤ ሃብቱን አወረሰው፣ አሥራት ከፈለው። ልጁ መሆኑን እያወቀም ታላቅ የእግዚአብሄር ካህን እንደሚሆን ስለተረዳ ሰገደለት። በዚህም አካኋን መልከጸዲቅ በመጨረሻ፣ ከነዓንን በገዙ ሊሎች ነገሥታት ዘንድ በእጅጉ የተከበረ ታላቅ ካህንና ንጉሥ ለመሆን በቃ። በኋላም ለአንድ ካህን የሚገባውን አስራት

አቀረቡለት። የመልከጼዲቅን ቡራኬ ለመቀበል ሲል ካህን ያልነበረው አብርሃምም እንኳ እንዲሁ አደረገ።

መልከጼዲቅ ሳሌምን አገባ። መጠርያዋን ዘላለማዊ ሊያደርግላትም፣ ውጥንዋን አግኝቶ ገንብቶ ያሳያታትን ከተማ ‹‹ኢዮርሳሌም›› ብሎ ሰየማት። ‹‹ኢዮር›› የሚለው ቃል የተገኘው ውስጣቸው የተሰያዩ ዐለማት ካለባቸው ሰባቱ ሰማያት የመጀመሪያውና ሀመልማል የምትባለው የኛ ዐለም የምትገኝበት ሰማይ ነው። ሻንሸዋ እንደሚተርክልን፣ ይህ የመጀመሪያው ሰማይ ከኛ ዐለም በተጨማሪ ውስጡ 11 ዓለማት አሉበት። ምናዝል በሚል ስም የተሳለውን አውደ ከዋክብት ስእል፣ የአሁን ዘመን ሰዎች ምንም ለክክብ ቆጠራ ቢያውሉትም ስእሉ በኢዮር ውስጥ 12 ነፍሳት የአሉበት ዓለማት እንዳሉ ይጠቁማል። አየር የሚለውም ቃልም ከዚህ ይገኖማል። ‹‹ሳሌም›› ‹‹ሰላም›› ማለት ነው። በሰማይቱ ገነት አንዲት እየሩሳሌም አለች። ምድራዊቷ ኢየሩሳሌም የሰማይዊቱ ኢየሩሳሌም ጥላ ወይም ድኩም ቅጂ ናት። ሰማያዊትዋ ገነትም የምትገኘው በሰስተኛው ሰማይ ውስጥ ነው።

ሳሌም ለመልከጼዲቅና ለራስዋ፣ አራት ሴቶችና ሦስት ወንዶች ልጆች ወለደች። ወንዶቹ ኢትኤል፣ ሃሙኤል፣ መሊክ

ወይም አቡመሊክ ነበር። አቡመሊክ የተሰየመው በመልከጼዲቅ ‹‹ሰው መንግሥት›› ነበር።

ኢትኤል በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ኢትዮጵያ አምርቶ፣ ኢትዮጵያ ላይ ነግሦ፣ 10 ወንድ ልጆች ወልዶ፣ እነሱ ገባዙተው፣ በ4000 ዓመታት ውስጥ አሁን በስሙ ለሚጠሩት ወደ 100 ሚሊዮን ለሚጠጉት ኢትዮጵያውያን አባት ሆነ ማለት ነው። ሁለተኛው ልጁ፣ ሃሙኤል በፋርሳውያንና በባቢሎናውያን ዘመን ላይ ተቀምጦ፣ ታሪክ በአግራሞት የዘገበለትን ‹‹የሃሙራቢ ሥርዓተ ህግጋት›› (Hamurabi's Code of law) ደነገገ። ሦስተኛው ልጁ አቡመሊክ በሌባኖናውያንና ዛሬ ፍልስጥኤማውያን በሚባሉት ላይ ነገሠ።

ከጊዜ በኋላ የአብርሃም ልጆች አካባቢውን ተቆጣጥረው የዕላቱ ማረፊያ በማድረግ ደብረ ዕዮን ብለው በጠሩት ቅዱስ ስፍራ በተድሞው በራማ ተራራ፣ አንድ ቀን መልከጼዲቅ እና ልጆቹ መሰዋእት ሲያቀርቡ እግዚአብሔር በደምና በስጋ ፊንታ ወይንና ኅብስት እንዲያቀርቡ፣ ኢትኤልንም የዓባይ ወንዝ መነሻ ወደሆነው ቦታ ወደ ጣና ሀይቅ እንዲያመራ አዘዛቸው። እግዚአብሔር በመልከጼዲቅ በኩል ‹‹ከቦታው ስትደርስ ‹‹ዮጵ›› በሚባል ብጫ ወርቅ ትከብራለህ። ‹‹ኤል›› የሚለውን ቃል ከስምህ አውጥተህ፣ ‹‹ኢት›› የሚለውን ከፊለ-ስምህን አስቀርተህ መጠሪያህን ‹‹ኢት-

ዮጵ›› ታደርጋለህ›› አለው። በዚህም አኳኋን የምታርፍባት አገር በስምህ ‹‹ኢትዮጵያ›› ትባላለች። ‹‹ኢትዮጵያ›› (ለእግዚአብሔር የሚቀርብ) ‹‹ቢጫ ወርቅ ስጦታ ወይም በረከት›› ማለት ነው። ከዘመናት በኋላ፣ እግዚአብሔር መሲህ እና የሰላም ንጉሥ ሊሆን በምድር ላይ ሲወለድና የሰው ልጆችን ለማዳን በዚች ምድር ሲገኝ፣ ዘሮችህ ያን ብርቅዬና ውድ፣ ቢጫ የኢትዮጵያ ወርቅ፣ ከርቤ እና እጣን ይዘው የመሲሁን መወለድ የምታበስር ኮከብ በሰማይ ሆና እየመራቻቸው እሱ ወደ ተወለደበት ስፍራ ታደርሳቸዋለች።›› አላቸው። (አማን በላይ ዝኒከማሁ ገጽ 49-51)

በእግዚአብሔርና በመልከጸዲቅ እንዲያ የተመከረው ኢትኤል ወላጆቹን፣ ወንድሞቹን እና ኢየሩሳሌምን ተሰናብቶ፣ ከባለቤቱ ጋር በ49 ካህናት ታጅቦ፣ ኖህ ከመርከቡ አውርዶአቸው የኖህ ሚስት እማቴ ሀይካል በጣም ለምትወደው ልጇ ለኩሽ ሰጥታው ሲወርድ ሲዋረድ ወደ መልከጸዲቅ ከደረሱት መጻህፍት ውስጥ ብርቅዬ የሆኑትን ተሸክሞ፣ የዛሬ 4000 ዐመት አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ አመራ። ከተደላደለም በኋላ ልክ እንደ አባቱ እንደ መልከጸዲቅ ንጉሥና ካህን ሆኖ፣ <<ዮጵ>> በተባለው ልዩ የኢትዮጵያ ወርቅ ስለከበረ ‹‹ኢትዮጵ›› ተባለ። ከዚያ ዘመን አንስቶም አገሪቱ በእሱ ስም ‹‹ኢትዮጵያ›› ትባል ጀመር። ኢትዮጵና ልጆቹ ከፍተኛውን እና ወደር የማይገኝለትን የኢትዮጵያ

ሰላሳኒ በመላው አፍሪካ በማዳረሳቸው፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ ማለትም የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን እስከያዙበት ዘመን ደረስ፣ መላው አፍሪካ ‹‹ኢትዮጵያ›› ይባል ነበር። ይህንን የሚያረጋግጡ የድሮ ዘመን ካርታዎች በእዚህ መጽሀፍ ውስጥ እንደ ማስረጃ ቀርበዋል። በኢትዮጵያ ስም የተጠራው አህጉሩ ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ አትላንቲክ እና የህንድ ውቅያኖስ የሚባሉት ውቅያኖሶች በጥንት ዘመን የኢትዮጵያ ውቅያኖሶች ይባሉ ነበር። እነዘህንም ከእዛው ከአፍሪካ ካርታ ላይ መመልከት ይቻላል። ምንም እንኳን ግዛታችን ሚሙታ ዛሬ ብታንስም መላው አፍሪካ አሁንም የምትጠራው በኛው በጥንት ገናኖቹ በአፋሮች ወገኖቻችን ስም ስለሆነ ኩራት ይሰማናል። ትልቁ አህጉር እስያም በእኛው ጎሳ ንጉሠነገሥት በአጼ እስያኤል ስም ስለሚዘከር በእዚህም እንታበያለን። የኢትዮጵያን ታሪክና ገናናነት ወደ ተረታተረት ለመቀየር ለሚፈልጉ ጸረ ኢትዮጵያ ግለሰቦች እነዚህ ባውሮፓውያን አገር አሳሽ ባህረኞች እጆች ውስጥ የተገኙት የጥንት ካርታዎች የማይበግሩትና የማይነቀንቁት ማስረጃ ሆነውባቸዋል። የጥንቱ ካርታዎች ከእዚህ በታች ይቀርባሉ።

ይህ ካርታ መላው አፍሪካ ኢትዮጵያ ይባል እንደነበረ ይመሰክራል፡ : ከአሁኗ ኢትዮጵያ በስተግራ ጀምሮ እስከ ደቡብ አፍሪካ ያለው ላእላይ አፍሪካ (UPPER AFRICA) ሲባል ከምእራብ አፍሪካ እስከ ኪቲ ባህር (ሚዲትራኒያን ሲ.) ድረስ ያለው የሰሜኑ ክፍል ደግሞ (LOWER AFRICA) ታህታይ አፍሪካ ይባል እንደ ነበር እነሆ ፍንትው ብሎ ይታያል። ከእዚህ በታች የተቀመጡት ካርታዎች ደግሞ ከአፍሪካ የግራ ብጠት ጀምሮ ቁልቁል የአለው ውቅያኖስ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ እንደሚባል በእስፓንሽ እና እንግሊዝኛ ቋንቋ በግልጽ ያረጋግጣሉ።

ÆTHIOPIA
INFERIOR
EXTERIOR


OCEANUS
PARS
ASIÆ
ARABIA
OCCIDEN
OCEANUS ÆTHIOPICUS SIVE AUSTRALIS



ቀደም ሲል እንዳነሳሁት፣ ስለ የሳሌም (ኢየሩሳሌም) ንጉሥ መልከጸዲቅ ስናወሳ የእሱን ማንነት አስመልክቶ ውዥንብር አለ። መልከጸዲቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኦሪት ዘፍጥረት (11:18-21)፣ በቅዱስ ዳዊት መዝሙር (109-110.4) እና የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ እብራውያን (ምእራፍ7) ተጠቅሶአል።

በኦሪት ዘፍጥረት (14፣ 18-21) ስለ አብርሃም እና መልከጸዲቅ እንዲህ ይላል፦

"አብርሃም ኮሎዶጎሞርንና ከእሱ ጋር የነበሩትን ነገሥታት ወግቶ ከተመለሰም በሁዋላ የሶዶም

ንጉሥ፣ የንጉሥ ሸለቆ በሆነው የሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ። የሳሌም ንጉሥ መልከጸዲቅም

እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ። እርሱም የልኡል እግዚአብሔር ካህን ነበረ። ባረከውም፤

(አብርሃምን)-- አብርሃም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልኡል እግዚአብሀር የተባረክ ነው። ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልኡል እግዚአብሔርም የተባረክ ነው፣ አለውም። አብርሃምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው።"

በዳዊት መዝሙር ደግሞ (109–110፣ 4) እግዚአብሔር አብ፣ በዳዊት አፍ ውስጥ ስለ እየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ካህንነት ምሎአል።

“እንደ መልከጸዲቅ ሥርዐት አንተ የዘላለም ካህን ነህ፣ ብሎ እግዚአብሔር ማለ፣ አይፀፀትም።” ...

ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ (ኢብራይስጥ 7) በመጀመሪያ ስለ መልከጸዲቅ፣ ቀጥሎም መልከጸዲቅ

ምሳሌው ስለ ሆነው ስለ እየሱስ ክርቶስ ይናገራል። እንዲህ ሲል፦ ‹‹የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነው ይህ መልከጸዲቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አስራትን አካፈለው። የስሙም ትርጉሞሜ በመጀመሪያ የፅድቅ ንጉሥ ነው። ሁዋላ ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው።›› ስለ እየሱስ ክርስቶስ ማንነት ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ አያይዞ ሲናገር፣ ‹‹አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት፣ ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።” ይላል።

ስለ እየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር “አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም” ያለውን ቆንጽሎ በማውጣት

አየሉ መጽሐፍ ቅዱስን እናውቃለን የሚሉ ሰዎች ይህን አባባል ለኢየሩሳሌም ንጉሥ ለመልከጸዲቅ በመስጠት “መልከጸዲቅ አባትና እናት ስሌለውና ዘመኑ ጥንት፣ ትውልዱ ቁጥር፣ ህይወቱም ፍጻሜ ስለሌለው ከእናትና አባት የተወለደ አጥንትና ሰ.ነ የነበረው ሰው አይደለም። እሱ ራሱም ልጆች ሊወልድ አይችልም፤” ይላሉ። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ “አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት፣ ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል፤” የአለው ስለ እየሱስ ክርስቶስ አንጂ ስለ ሳሌም ንጉሥ እነዳልሆነ አይገነዘቡም። የእየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ንጉሥ መልከጸዲቅ የተባለው ትልቅ ሰው ግን የዛሬ 4000 ዐመት በክህነት እና ንጉሥነት ኖሮ ሞቶአል። በመሞቱም ህያውቱም፣ መንግሥቱም ክህነቱም አልፈዋል። ሞቶአል የምለውም ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ነበር፣ ስለሚል ነው። የት ነው ይህን የሚለው? በዛው በእብራውያን ምእራፍ 7 ቁጥር 4 ላይ እንዲህ ይላል፦

‹‹የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፈው የሚሻለውን አስራት የሰጠው ይህ ሰው (ይህ ሰው የሚለውን በአፅንኦት ፅንየው፤) እንዴት ትልቅ እንደነበረ አስክ ተመልከቱ።›› በእርግጥም ሰው ስለነበር ሞቶአል። መንግሥትና ክህነቱም አልፈዋል። እሱ ምሳሌ

የሆነለት የእየሱስ ክርቶስ መንግሥት፣ ህይወት እና ክህነት ግን ዘላለማዊ ናቸው። እሱ የማይሞት ዘላለማዊ ነውና። አባታችንን፣ ማለትም የኢትዮጵን አባት መልከጸዲቅን፣ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ይህ ሰው ትልቅ እንደነበረ እስቲ ተመልከቱ፣›› ባለው ደስ እያለኝ በእሱ አባባል እስማማለሁ። አዎን በአባታችን ትልቅነት ሁላችንም የኢትዮጵ ልጆች ኢትዮጵያውያን ልንደሰት እና ልንኮራ ይገባል።

ቅዱስ ጳውሎስ፣ አባታችንን መልከጸዲቅን ትልቅ ሰው ካለባቸው ምክንያቶች ዋነኛው የእየሱስ ክርቶስ ስርዐተ-ክህነት አነስተኛው የዕብራዊው የሌዊ ስርዐተ-ክህነት ሳይሆን የአባታችን የኢትዮጵ አባት፣ ስለዚህም የኛ አባት የሆነው የትልቁ የመልከጸዲቅ ስርዐተ-ክህነት መሆኑ ነው። እሱ አባታችን ስለሆነ ከእብራውያኑ ከነ ሙሴና ከነ ቅዱስ ጳውሎስ የበለጠ ስለ እሱ ማንነት መረጃ አለን። በመጀመሪያ ነገር፣ ከቅዱስ ጳውሎስ አስቀድሞ ስለ መልከጸዲቅ በጥቂቱም ቢሆን የጻፈው ሙሴ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ሙሴ በጻፈው ላይ ተመርኩዞ ከተበ። ሙሴ ራሱ መረጃውን ያገኘው ከኛው ከኢትዮጵያውያን ነው። እንዴት ቢባል፣ እንደ መልከጸዲቅ ካህን ከነበረው ከመልከጸዲቅ ዝርያ፣ ከኢትዮጵያዊው አማቱ ከየቶርአብ ጋር 40 ዐመት ሙሉ በኢትዮጵያ ሲኖር እኛ የአባታችንን የመልከጸዲቅን ትውልድ ታሪክ በዝርዝር የዘገብንበትን መጽሃፈ ዣንሸዎን አግኙቶ ስላነበበ ነው።

አላይ እንደ ጠቀስኩት ሙሴ አስቀድሞ የኛን መጽሐፍ ማንበቡን ራሱ አምኖአል፣ መስክሯልም። ይህንንም የመሰከረው ቀደም ሲል እንደ ጠቀምኩት፣ በመጽሐፈ ሆልቆ (21፣14) ነው። ይህን አውነት አንባቢው በቀና ልቦና ሊመረምረው ይችላል።

በዛው በእብራውያን 7 እና 8 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠ የዘላለም ሊቀ-ካህን አለን፣ የሚለውም ፈጣሪን እየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንጂ ሰው የሆነውን አባታችንን መልከጸዲቅን ሊሆን አይችልም። ለአብርሃም ህብስትና ወይንጠጅ ያበረከተለት (ከማንም አስቀድሞ ያቆረበው ማለት ነው፣) ሊቀ-ካህኑ አባታችን መልከጸዲቅ አንጂ እየሱስ ክርስቶስ ራሱ ስጋ ለብሶ፣ ገዝፎና ታይቶ አልነበረም። እየሱስ ክርስቶስ ከተድስት ማርያም ስጋ ነስቶ የዛሬ 2000 ዐመት ከመወለዱ በፊት ሰጋ ሆኖ ገዝፎ ለሰው ተከስቶ ነበር፣ ማለት የስህተት ስህተት ነው። ከሴት ሳይወለድ ስጋ ለመሆን ቢፈቅድ ኖሮ ለምን ከቅድስት ማሪያም ተወልዶ የሰውን ልጅ ከሃጥያቱ ለማዳን አቀደ?

በእርግጥ መልከጸዲቅ አባታችን ስጋ ለባሽ ሰው ነበር። ሰው ስለነበረ ነው ከእናትና አባት የተወለደውና ራሱም ልጆች የወለደው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በፊት በተጻፈው፣ ሙሴ እኛ ዘንድ ሰለ ባነበበው ዣንሸዎ በተባለው መጽሐፋችን ውስጥ የአባታችን ትውልድና ልጆች የዘር ሐረግ ተመዝግቦአል። በዚህ መጽሐፋችን

ውስጥም መልከጸዲቅ፣ ከናምሩድ፣ ማለትም የባቢሎንን ግንብ ከገነባው ታላቅ ንጉሥ ዘር ይጠቅሳል። እንዲህም ይላል፦ ‹‹ናምሩድ አዳማን ወለደ፣ አዳማ ራፌልብን፣ ራፌልብ ቄናን፣ ቄና ደግሞ ጌራን። ጌራ በክህነት ስሙ መልከጸዲቅ የተባለው ነው። ጌራ (መልከጸዲቅ) በበኩሉ እናታችንን ሳሌምን አግቦ ከእስዋ ዐራት ሴቶችና ሶስት ወንዶች ልጆች ወልዷል። የወንዶቹ ስሞች ኢትኤል (አባይን ተከትሎ ሄዶ ጣና ላይ ሰፍሮ በሁዋላ "ኢትዮጵ" የተባለው አባታችን) ሃሙኤል (ሃሙራቢ ተብሎ ወደ ባቢሎን ተጉዞ የሃሙራቢን ህጎች Hamurabi's Code of Lawን የሰጠው) እና አቡመሊክን (የፍልስጥኤማውያን ንጉሥ የሆነውን) ወልዶአል። ከእሱ አብራክ እኛን ኢትዮጵያውያንን ያስገኘን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። ታዲያ ይሄ ሁሉ ለምን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልሰፈረም? ነብዩ ሙሴ መጽሐፍ ቅዱስን ከመጻፉ ወይም ከማጻፉ በፊት ይህን ታሪካችንን ጠንቅቆ ያውቃል። አንበታልና። ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ለምን በአሪት ዘፍጥረት ውስጥ እንዳላካተተው ትክክለኛውን መልስ ሊሰጠን የሚችለው ነቢዩ ሙሴ ብቻ ነው። እሱ ስላልከተበው ግን የኛ እውነተኛ ታሪክ የለም ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት የእኛን ጉዳይ እኛው ከትበነዋል። ስለዚህ፣ እሱ ስላልከተበው ብዙ አይጨነቀንም። ይህ ለሁሉም ሰው ግልጽ ሊሆን ይገባል።

የመልከጸዲቅን ታሪካዊ ዳራ እንዲህ መጥኜ እንዳቀረብኩት ሁሉ የአብርሃምንም ለአንባቢ መግለፅ ተገቢ ይሆናል። አብርሃምን፣ እግዚአብሔር ‹‹አብርሃም›› ሲል ከመሰየሙ በፊት፣ የሚጠራው ‹‹አብራም›› ተብሎ ነበር። የተወለደውና እስከ ወጣትነቱ ዘመን የኖረው ዛሬ ኢራቅ በምትሰኘው አካባቢ፣ በሜሶፖታምያ ውስጥ ኡር በተባለች ስፍራ ነው። አባቱ ኢቦር ከኖህ ልጆች አንዱ የሆነው የሴም ዝርያ ነው። አባቱ ኡርን ከአነቢተሰቡ ሰቆ ራቅፋ ሃራን ወደ እምትባል ከተማ ሄዶ እየኖረ ጣኦቶችን እያነጸ በመሸጥ ይተዳደር ነበረ።

አብርሃም የአባቱን ጣኦቶች የመቅረፅና መሸጥ ተግባርን አልወደደም። በዚህም ምክንያት ከአባቱ ጋር ተጋጨ። አባቱም ጣኦቶቹን እንደማያመልክና የሚቀርፃቸው መተዳደሪያ ገንዘብ ለማግኘት መሆኑን በማስረዳት ሊያሳምነው ሞከረ። አብራሃም ግን የአባቱ ተግባር የሰማያት፣ የምድርና የሁሉም ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሄርን እንደሚያስከፋው አሰበ፣ እናም ምሽት ላይ አባቱ የሚሠራበትን ስፍራ ከጣኦቶቹ አቃጠላቸው። ወንድሙም ጣኦቶቹን ከእሳት ለማዳን ሲጣጣር ተቃጥሎ ሞተ። አብርሃም ሳራይ ከምትባለው፣ ቡኋላ እግዚአብሔር ሳራ ብሎ ከሰየማት ባለቤቱና ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋራ አገር ጥሎ ተሰደደ።

እግዚአብሄር በአብርሃም እምነት ጽናት ተደስቶ፣ ዘመዶችህን ተለይተህ እኔ ወደ እምመራህ የማርና ወተት ምድር ወደ ከንአን አቅና አለው። ይህንንም ምድር ከሱ አብራክ ወደ ፊት ለሚገኙት ልጆቹ እንደ እሚዳርጋቸው ቃል ገባለት። ምንም እንኩዋን አብርሃም እና ሳራ እድሜአቸው ገፍቶ አስዋም ያረጠች ብትሆንም፣ ይስሀቅ የሚባል ልጅ እንደሚወልዱና በይስሀቅ ዘር አማካኝነት ጊዜው ሲደርስ መሲሁ እግዚአብሄር (እየሱስ) በምድር ላይ ተወልዶ ዐለምን እንደሚያድን ቃል ገባላቸው። ከዚያ በኂላ ይስሀቅ ተወለደ። እግዚአብሄርም፣ አብርሃም ይታዘዘው እንደሆን ለማወቅ ፈልጎ አንድያ ልጁን እንዲሰዋለት አዘዘው። አብርሀም ልጁን ሲሰዋ ሲል እግዚአብሄር እውነተኛውን በግ (የእየሱስ ምሳሌ የሆነውን) በመልአክ ልኮ በይስሀቅ ፈንታ ይህን በግ ሰዋልኝ፣ ብሎ ይስሀቅን አተረፈው። የአብርሃምንም ታዛዥነት እግዚአብሄር ከጽድቅ ቆጠረለት። የሱ ዘሮችም ከባህር ዳር አሸዋና ከሰማይ ከዋክብት እንደሚበዙ እንደገና አረጋገጠለት።

የአብራውያን አባት አብርሃምና የሚሊዎኖች ኢትዮጵያውያን አባት የሳሌም ንጉሥ የመልክጸዲቅ ግንኙነት እንዴት እንደ ተጀመረ ጥቂት መግለጽ መልካም ነው። ቀደም ሲል እንደጻፍኩት አብርሃም ለእግዚአብሔር ሊቀ ካህንና ለሳሌም ንጉሥ መልክጸዲቅ ምርቃቱን ለማግኘት አስራት ከሚያስገቡለት ሰዎች አንዱ ነበር።

ሙሴ በጻፈው በቶራ (ብሉይ ኪዳን) ውስጥ የሎጥን መማረክና የአብርሃምን ዘመቻ እንደሚከተለው ይተርካል፦

‹‹የሶዶምም ንጉሥ፣ የጎሞራም ንጉሥ፣ የአዳማም ንጉሥ፣ የሰቦይም ንጉሥ፣ ዞዖር የተባለች የቤላ ንጉሥም ወጡ፣ እነዚህ ሁሉ በሲዳር ሸለቆ በእነርሱ ላይ በሰልፍ ወጡ። የኢሳምን ንጉስ ከልዶሎምርን፣ የአህዛብን ንጉስ ቲድአልን፣ የሰናኦርን ንጉሥ አምራፌልን፣ የኤላሳርን ንጉሥ አርዮክን ለመውጋት፣ አምስቱን ነገሥታት በእነዚህ በአራቱ ላይ ወጡ።›› (ኦሪት ዘፍጥረት 14፡ 8-9)

የሶዶምና ገሞራ ነገሥታትና ተባባሪዎቻቸው ድል ተመቱ። የአብርሃም ወንድም ልጅ ሎጥ ተማርኮ ከሰዶም ተወስዶ ነበር። አብርሃም ይህን ሰምቶ በምሽት ወቅት ከ318 አገልጋዮቹ ጋር በመዝመት ሎጥንና ቤተሰቡን ነፃ አወጣቸው። መልክጸዲቅም ይህን ሲሰማ ሊቀበለው መጣ። የሣሌም ንጉሥ መልክጸዲቅም እንጀራና የወይን ጠጅን አወጣ። እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር። ባረከውም። ሰማይና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው። ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልኡል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም። አብርሃምም ከሁሉ አስራትን ሰጠው። (ኦሪት ዘፍጥረት 14፡18-20)

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ሙሴ ከትቦ አስፍሮታል የተባለው ድርሳን ነገሥታቱ ለጦርነት የተሰለፉበትን ምክንያት በትክክል አያሳውቅም። በእኛ መረጃዎች የጦርነቱ መንስኤዎች አብርሃምና መልከጸዲቅ ናቸው። መረጃውም ሙሴ ከመወለዱ ቢያንስ 650 ዐመታት ቀደም ብሎ የተፃፈ ነበር። ስለሆነም ሙሴ የድርሰቱ ታሪክ የዐይን ምስክር አይደለም። ከዚያም በላይ ቶራን የመጻፍ ተልእኮው የአይሁድ ህዝቦችን ታሪክ እና ከእግዚአብሄር ጋራ ያላቸውን ግንኙነት እና በምን ህግጋት ለእርሱ እንደሚገዙና እንዴትም ማምለክ እንዳለባቸው በአጭሩ ለማሳወቅ እንጂ እርሱ ራሱ የዐይን ምስክር ስለነበረባቸው ወቅቶች እንኳ ሲያወሳ ዝርዝር ውስጥ አይጠልቅም ነበር። እናም የጦርነቱን እውነተኛ መንስኤ በኢትዮጵያዊው አማቱ በዮቶርአብ ዘንድ በተገኙት በ ሣንሸዋ እና በ ያሻር ውስጥ ቢያነብና ዝርዝሩን ችላ ቢለው አያስገርምም። የኛ መረጃ ግን በቀጥታ የወረደው የእዚህ ሁሉ ክስተት እማኝ ከሆነው ከአባታችን ከኢትዮጵ አባት ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከመልከጸዲቅ ነው። እንደ እሱ ትረካ፣ የጦርነቱ መንስኤ እሱ ነው። ይህም እንደሚከተለው ነው።

በአንድ የመኸር ዘመን መባቻ ላይ ምርቃቱን ለመቀበል አብርሃም ለመልከጸዲቅ ከወይን፣ ከስንዴና ከሌሎች ምርቶቹ አንድ አስረኛውን አበረከተለት። በተጨማሪም ከቀደምት አባቶቹ

የወረሰውን እንቁአርያ (እንክብል ክቡር ድንጋይ) ሰጠው። እንቁአርያው ከአዳምና ከሄዋን በቀጥታ የተላለፈ ነው ይባላል። በዚያች ቅፅበት የእግዚአብሔር መንፈስ መልከጸዲቅ ላይ ወረደ። መልከጸዲቅም ቅዱሱን ህብስትና የወይንጠጅ ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ ቁጥራቸው 1200 የሚደርሰው ካህናቱ በተገኙበት ስለ አብርሃም መፃኢ ዘር፤ ዓለምን ስለሚያድነው መሲህ፣ ትንቢት ተናገረ። የዓለም ቤዛ ከአብርሃም አብራክ መገኘቱን ቀድሞ አበሰረ፣ ፣ በዚህም ምክንያት በአብርሀም አብራክ ውስጥ ተሰውሮ ለነበረው መድህነዓለም በአብርሃም ፊት ሰገደ።

ለወትሮው ነገሥታት በሙሉ የሚሰግዱለት የሳሌሙ ንጉሥ መልከጸዲቅ ንጉሥ ላልሆነው ለተራ ሰው ለአብርሃም መስገዱን ሌሎቹ ነገሥታት ሲሰሙ ድርጊቱ ውርደት ሆነባቸው። ክፉኛም ተቆጡ። ስለሆነም ንጉሥ ከልዶጎመር ለመልከጸዲ ለማናውቀውና እንደ አንተ ካህን ወይም ንጉሠነገሥት ላልሆነ አብራዊ አንተ ሰግደሃልና ላለፉት ጊዜያት ያስገባሁልህን መብዓዎችና ገፀበረከቶች በሙሉ መልስልኝ፤ አለበለዚያ መጥቼ አወጋሃለሁ፤ አለው። (አማን በላይ፣ ዝንቱ ከማሁ ገፅ 45-49)

መልከጸዲቅ ግን እግዚአብሄር እንደሚጠብቀው በመተማመን አልፈራውም። ጭራሹንም ረገመው። ንጉሥ ከልዶጎመርም፣ የአህዛብን ንጉሥ ቲድአልን፣ የሰናኦርን ንጉሥ እምራፌልን፣

የእላሳርን ንጉሥ አርዮክን በመልከጸዲቅ ላይ አስተባብሮ ዘመተበት። የሶዶም፣ የጎሞራ፣ የአዳማ፣ የሰቦይም እና የቤላ ነገሥታት ለመልከጸዲቅ ወገኑ። በዚህም ጦርነት የመልከጸዲቅ ጠላቶች አሸነፉና አብርሃም ነፃ እስከሚያወጣቸው ድረስ ሎጥና ቤተሰቡ በምርኮኛነት ተጋዙ። እንግዲህ አብርሃም ድል የመታው እነዚህን በመልከጸዲቅ ላይ የዘመቱትን ነገሥታት ነው ማለት ነው። ከዣንሸዋ ውስጥ ተውጣጥቶ *መጽሀፈ ሱባዔ ዘበአማን* ካልእ በሚለው በተጻፈው ድርሳን ውስጥ ስለ ሁለቱ የነገሥታት ቡድኖች ውጊያ የሚያወሳው ይህንን ነው።

የመልከጸዲቅ ልጅ ኢትኤል ጣና ላይ ሰፍሮ ኢትዮጵ እንደተባለ፣ ልጆቹ ጠቢባን ነገሥታት ስለመሆናቸው

ኢትኤል ወደ ኢትዮጵያ ከመጓዙ አስቀድሞ አብርሃም ያበረከተለትን፣ ጥንት የአዳምና የሄዋን ንብረት የነበረውን እንቁአርያ ‹‹የእንቁ እንክብል›› መልከጸዲቅ ለልጁ ለኢትኤል አበረከተለት። እንዲህም አለው ‹‹ይኽን የእንቁ እንክብል ውሰድ፤ ሂደህም በአባይ ወንዝ መነሻ ኑሮህን መስርት። እንክብሉ በረሃብና በመከራ ወቅት ይጠቀራል፤ በጥጋብና በመልካም ወቅቶች ደግሞ ያበራል። ኢትዮጵያውያን የሚሆኑ ትውልዶችህ ይህን እንቁ ተንከባክበው እንዲጠብቁ አዘዛቸው። የሰላሙ ንጉሥ መወለዱንም ለዘሮችህ አንድ ብሩህ ኮከብ ከሰማይ ያመለክታቸዋል፤ እንቁው ኮከቡን በመሰለ ብርሃን ይሞላል፤ ጨረሮቹም የሰላሙ ንጉሥ

የእላሳርን ንጉሥ አርዮክን በመልከጸዲቅ ላይ አስተባብሮ ዘመተበት። የሰዶም፣ የጎሞራ፣ የአዳማ፣ የሰቦይም እና የቤላ ነገሥታት ለመልከጸዲቅ ወገኑ። በዚህም ጦርነት የመልከጸዲቅ ጠላቶች አሸነፉና አብርሃም ነፃ እስከሚያወጣቸው ድረስ ሎጥና ቤተሰቡ በምርኮኛነት ተጋዙ። እንግዲህ አብርሃም ድል የመታው እነዚህን በመልከጸዲቅ ላይ የዘመቱትን ነገሥታት ነው ማለት ነው። ከዎንሸዎ ውስጥ ተውጣጥቶ *መጽሀፈ ሱባዔ ዘበአማን ላልኣ* በሚለው በተጻፈው ድርሳን ውስጥ ስለ ሁለቱ የነገሥታት ቡድኖች ውጊያ የሚያወሳው ይህንን ነው።

የመልከጸዲቅ ልጅ ኢትኤል ጣና ላይ ሰፍሮ ኢትዮጵ እንደተባለ፣ ልጆቹ ጠቢባን ነገሥታት ስለመሆናቸው

ኢትኤል ወደ ኢትዮጵያ ከመጓዙ አስቀድሞ አብርሃም ያበረከተለትን፣ ጥንት የአዳምና የሄዋን ንብረት የነበረውን አንቱአርያ ‹‹የእንቁ እንክብል›› መልከጸዲቅ ለልጁ ለኢትኤል አበረከተለት። እንዲህም አለው ‹‹ይኸን የእንቁ እንክብል ውሰድ፤ ሂደህም በአባይ ወንዝ መነሻ ኑሮህን መስርት። እንክብሉ በረሃብና በመከራ ወቅት ይጠቁራል፤ በጥጋብና በመልካም ወቅቶች ደግሞ ያበራል። ኢትዮጵያውያን የሚሆኑ ትውልዶችህ ይህን እንቁ ተንከባክበው እንዲጠብቁ እዘዛቸው። የሰላሙ ንጉሥ መወለዱንም ለዘሮችህ አንድ ብሩህ ኮከብ ከሰማይ ያመለክታቸዋል፤ እንቁው ኮከቡን በመሰለ ብርሃን ይሞላል፤ ጨረሮቹም የሰላሙ ንጉሥ

(መሲሁ) ወደሚወለድበት አቅጣጫ ይፈነጥቃሉ። በሰማይ ላይ ያለውን ኮከብና እንቁውን ያስተያዩ። አንድ ሆነውም ያዩአቸዋል። መሲሁ የተወለደበት ስፍራ ሲደርሱ ኮከቡ ንቅናቄውን ያቆማል። ነገሥታቱ ልጆችህም በዚያ ለመሲሁ ‹‹አንተ የዘላለም አምላክ ነህ፤›› ብለው ይሰገዱለት። ልዩ የሆነውን የኢትዮጵያ ‹ዮጵ›› የተባለውን ቢጫ ወርቅ፣ እንዲሁም እጣንና ከርቤ ለሰላሙ ንጉሥ ገጸበረከት ያቅርቡለት።›› (አማን በላይ፣ ዝንቱ ከማሁ፣ ገጽ 49-51)

በዚህ ምክንያት፣ ከፍ ብዬ እንዳመለከትኩት፣ መልከጸዲቅ ልጁን ኢትኤልን እንደ ንጉሥና ካህን መርቆ ተልእኮውን ይፈጽም ዘንድ ወደ አባይ መነሻ ወደ ጣና ደሴት ከሚስቱ ከሲና (በኋላ እንቁዮጵግዮን የተባለችው እናታችን) እና ከ49 ካህናት ጋራ ሸኘው። ከካህናቱ በተጨማሪ፣ ኢትኤል አያሌ ጥንታዊ መጻህፍትን ይዞ ነበር። ከኢየሩሳሌም ተነስቶ ለ400 ቀናት ተጉዞ የዛሬ 4000 ዐመት አካባቢ ኢትኤል ከአባይ መነሻ ጋ ደርሶ አዲሱን የእግዚአብሄርን ተልእኮ ሕይወት ጀመረ።

ኢትኤል ጣና ደሴት ሲደርስ ‹‹ኢትኤል›› (የእግዚአብሄር ስጦታ ማለት ነው፣) የተባለውን ስሙን ‹‹ኢትዮጵ›› (ቢጫ ወርቅ ስጦታ ለእግዚአብሄር) አለው። ሚስቱም ሲና ስምዋን ቀይራ ‹‹እንቁ-ዮጵ-ግዮን›› (እንቁዮጳግዮን) አለችው። ኢትዮጵ በአዲሲቱ ሀገር ላይ ሰፍሮ ከተደላደለ በሁዋላ ጥንት ‹‹ኩሽ›› ትባል

የነበረውን ሀገሪቱን በስሙ ‹‹ኢትዮጵያ›› አስባላት። እነሆ አስከዛሬም ኢትዮጵያ ትባላለች። ከኢትዮጵያም አልፎ ተርፎ፣ አላይ እንደተረጋገጠው፣ የኢትዮጵያን ስልጣኔ ወደ ተረፈው የአፍሪካ ክፍል ልጆቹ አሰራጭተው፣ መላውን አፍሪካ በስሙ ኢትዮጵያ አሰኝተው። በአፍሪካም ምስራቅና ምእራብ ያሉትን ውቅያኖሶች ‹‹የኢትዮጵያ ውቅያኖሶች›› አስባላቸው። ከዛ በኋላ ኢትዮጵ ከሚስቱ ከእንቁዮጳግዮን 10 ወንዶች እና ሶስት ሴቶች ወለደ። ስማቸውም እንደሚከተለው ነው፡- የወንዶቹ ስሞች፡- አቲባ፣ ቢኦር፣ ተምና፣ ኡቤር፣ አሻን፣ አክዚብ፣ በሪሳ፣ ቴስቢ፣ ቾላ እና አዜብ ይባላሉ። ሴቶቹ፣ ሚልካ፣ ሱቫባ (ሱባ)፣ እና ሎዛ ነበሩ። እነዛ 10 ወንዶች ተባዝተው በ4000 ዐመታት ውስጥ የተለያዩ ጎሳዎች (የተለያዩ ቋንቋዎች) ተናጋሪዎች ሆነው የሁላችንም ኢትዮጵያውያን ቅድመ-አባቶች ለመሆን በቁ። አስፍቶ ለመናገር፣ የእነሱ ደም በእኛ የደም ስር ውስጥ እየተዘወዋወረ ዛሬ ተውልደ-ኢትዮጵያውያን የሆንነውን ሁሉ አዛመደን። ሁላችንንም አፋሮችን፣ ሃዲያዎችን፣ ኦሮሞዎችን፣ አማሮችን፣ ጉራጌዎችን፣ ተጋሩዎችን፣ አኙዋኮችን፣ ሶማሌዎችን፣ ኩናማዎችን፣ ኤርትራውያኖችን (ፖለቲካውን ትተን ስለደም ስናወሳ) ሳይቀር ሌሎችንም ሁሉ፣ በደም የአንድ ኢትዮጵ ልጆች ኢትዮጵያውያን አደረገን።

የእየሱስ ክርስቶስ አምሳል ከሆነው ከትልቁ የእግዚአብሔር ካህን ከመልከጸዲቅ ዘር በኢትዮጵያ የተወለዱት ሁሉ ነገሥታት ዲበ-ሰብኣ ሆነዋል። ልክ እንደ አባታቸው የሳሌም ንጉሥ እንደ መልከጸዲቅ ንግሥናን እና ክህነትን (ፖለቲካን እና ቅስናን) አጣምረው ይዘው ህዝቦቻቸውን በፍትህ እና ርትህ ያስተዳድሩ ነበር። በኢትየጵያና በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ የነገሡት ሁሉ የኢትዮጵ ዝርያዎች በጣም ትልልቅ ነበሩ። ከእነዚህ ታላላቅ ሰዎች መሀል የኦሮሞ እና የአማራ ግንደዘር የሆነው ነቢዩና ፈላስፋው ደሽት (ደሴትም ይባላል) ይገኝበታል። ይህ ሰው በግምት የዛሬ 3600 ዐመት ካህን፣ ነቢይ እና ጠቢብ ሆኖ ከጣና ደሴቶች በአንደኛው ይኖር ነበር። በእዚህም ምክንያት በጣና ሀይቅ የተከበቡትን መሬቶች በስሙ ደሴት (ደሽት) አሰኝቶ፣ የደሽት ከተማ የምትባል መኖርያም በዛው በጎጃም ቆርቁሮ ወይም አስቆርቁሮ ነበር። በዛው በጎጃም የቀሩት የሱ የቀጥታ ዝርያዎች እስከዛሬ ድረስ ‹‹ዘረ-ደሽት›› እና ‹‹እነማይ›› ይባላሉ።

ይህ ነቢይ በግዮን መነሻ አጠገብ ተቀምጦ በተመስጦ ሲጸልይ መሲሁ እየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ 1600 ዐመታት በፊት ቅድስት ማርያም ህጻኑን መሲህ እየሱስ ክርስቶስን ታቅፋ፣ የኢትዮጵን ልጆች ወደፊት ወደ ቤተልሄም የሚመራው ኮከብ ማርያም እና እየሱስ ላይ ረብቦ በራዕይ ያያል። ወዲያውኑም

የክብሩን፣ የህጻኑን እና የእናቱን ምስል በወርቅ ሰሌዳ ላይ ነድፎ ይሆ ለልጆቹ ያስተላልፋል። መሲሁ፣ እናቱ እና ኮከቡ እንደዚያ እንደሚመስሉ አብስሮአቸው ሰሌዳውን በእንክብካቤ እንዲጠብቁ ያዛቸዋል። እሱ ይህን በማድረጉ እና አውራው አባታቸው ኢትዮጵም በተልእኮ ከኢየሩሳሌም ተነስቶ ጣና ላይ መስፈሩ፣ ነቢዩ ሲወለድ ልጆቹ ስጦታ ይዘው ወደ እስራኤል እንዲጓዙ መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ የደሽት ልጆች የአባታቸውን ተአዛዝ በዋዛ ፈዛዛ ዐሳዩትም ነበር። እነሱም ስለኮከቢቱ መከሰት፣ ስለመሲሁ መወለድ፣ እሱን ለማምለክ እና ለእሱ ስጦታ ለማበርከት ወደ እስራኤል መጓዝ እንዳለባቸው ለልጆቻቸው ያሳስቡና ይመክሩ ነበር።

የኢትዮጵ ልጆች በኮከቧ ተመርተው፣ የኢትዮጵያን ስጦታዎች ጭነው፣ ወደ እስራኤል ሄደው ለመሲሁ እንደሚሰግዱለት እግዚአብሔር የተነበየው እና የአዘዘው ቃሉም ዋጋ በትትክል በተግባር ውሏል። ‹‹ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች›› (መዝሙረ ዳዊት፣ 67:31) የሚለው የትዱስ ዳዊት ትንቢትም ኢትዮጵያውያን ሰብአሰገል ወደ ቤተልሄም ተጉዘው እጃቸውን ዘርግተው ገፀበረክቱን ለህጻኑ እሰሱስ ባበረከቱለት ሰዐት ተፈጽሞአል። ትንቢቱ ከተፈጸመም አንሠ 2000 ዐመታት ተቆጥረዋል። ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌሉ

በቤተልሄም ለህጻኑ ለእየሱስ ገፀ-በረከቶች እንዳቀረቡ የሚጠቅሳቸው ሰብዐሰገል ጠቢባን (ማቴ. 2፡ 1-12) የአባቶቻችን የመልከጸዲቅ እና የኢትኤል (ኢትዮጵ) ተወላጆች ከኢትዮጵያ ሀገሮች የተነሱ 12 ነገሥታት ናቸውና። ጠቢባኑ ነገሥታት ከ12 የኢትዮጵያ ነገሥታት በቀር ከቶውንም የሌሎች አገሮች ሊሆኑ አይችሉም። እንደ ኢትዮጵያ ሀይማኖቱና ታሪክ ከእስራኤል ጋራ የተሳሰረ እና በእግዚአብሄር ነብያት ትንቢት የተነገረለት ሌላ ሕዝብና አገር የሉምና። እነዚህ 12 ነገሥታትም ቁጥራቸው በትክክል 12 መሆኑ፣ በኋላ የተከሰቱት የእየሱስ ደቀመዛሙርትም ቁጥር 12 ትነቱ፣ የሁለቱ ሕብራዊ ግንኙነት በእዚህ መፅሐፍ ጸሀፊ አመለካከት አንድ ዐይነት መለኮታዊ ምስጢር አለው።

ስመ-መንግሥቱ ሶማቤላ የተባለው አጼ ባዜን (ባዝን) የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት በነበረበት ጊዜ አንድ የሰው እራስ፣ እጅና እግር የሚመስል ቅርጽ ያለው ኮከብ በኢትዮጵያ ግዛት ሀገሮች ላይ ታየ። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ግዛት ሀገሮች ላይ 12 ነገሥታት የነበሩት የኢትዮጵ ተወላጆችም ኮከቡን አስተውለው፣ መሲሁ መወለዱን አውቀው ፈነጠዙ። ለ2000 ዐመታት የጠበቁት የኮከቡን በሰማይ ላይ ፍንትው ማለት አብርሃም ለመልከጼዴቅ ባበረከተው ክቡር የእንቱ እንክብል አማካኝነት አመሳክረውና

አገናዝበው ተረዱ። የኮከቡ ቅርጽም እንቁአርያው (የአዳምና ሄዋን ንፀረት ነበር የተባለው፣ መልከጸዲቅ ከአብርሃም ተቀብሎ ለልጁ ለኢትኤል የሰጠው የእንቱ እንክብል) ውስጥ ተንጸባርቆ ቁርጥ ፊሱን መሰለ። ይህም ተአምራዊ ክስተት የሰላሙን ንጉሥ የመሲሁን መወለድ ያለጥርጣሬ አረጋገጠላቸው። ስለዚህም የኮከቡ አግረ-ጨረሮች ወደ እሚፈነጥቁበት አቅጣጫ እየቃኙ ኮከቡን ተከትለው ወደ ቤተልሄም ደረሱ። ኮከቡ በአንድ በረት ላይ ቆሞ ሲሰግድ ዐይተው ለህጻኑ እየሱስ ሰገዱለት። የከበሩ ደንጊያዎች እና ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር አንድታቀርብ የተተነበየውን ‹‹ዮጵ›› የተባለውን ቢጫ ወርቅ፣ እጣንና ከርቤ፣ ጌጦችና አልባሳት ጨምረው ለእናቱ ለማርያም አበረከቱ። ለቅዱስ ዮሴፍም ገዳ ሰጠ። የ12ቱ ነገሥታት ስሞችም የሚከተሉት ናቸው፡-

ጎላው አማራ፣ በጎጃም ደሽት ኩተማ እየኖረ፣ ጎንጂን እና ጉንዳጉንዲትን ያስተዳድር የነበረው አጎጃ ጃቦን በቅድመ-አባቶቹ በእነ መልከጸዲቅ እና ኢትዮጵ የታዘዘውን የግዮንን ብጫ ወርቅ (ዮጵ፣ እንቁ-ዮጵ-ግዮን)፣ይዞ፣ በእሱ መሪነት ወንድሞቹን የጣና ጻጋን እና የዙሪያውን ሶስት ንጉሦች፣ ማለትም ዛሬ ስማቸው ከሁና ጋር ተያይዞ የሚጠራውን ንጉሥ አቦል፣ ንጉሥ ቶናን እና ንጉሥ በረካን አስከትሎ፣ ከመርዌ ኩተማ (የዛሬው ሱዳን) እና አረብያ የኢትዮጵያ ግዛት የተነሳው ንጉሥ መሊክ አቡሰላም፣

የደርዲና፣ የሰገል እና የማጂ ንጉሥ መጋል (በአፋር መርከብ ተሳፍሮ በኦሮሞና አማራ ሰራዊት ስፔንን እና ፖርቲጋልን ቅኝ የገዛ) ፤

የአውላጥ (የዛሬው ኦጋዴን) እና የሶማሊያ ንጉሥ መቃዲሺ (የዛሬው መቃዲሾ በስሙ የሚጠራው)፣ የአካባቢውን እጣንና ከርቤ ይዞ፤

የአዳል ንጉሥ አውር፣ ከአፋር (ከአፌር) ንጉሥ ከ ሙርኖ ጋር ሆነው ከወርቅ ሀመልማል የተሠራ መጎናጸፊያ፣ እጀ-ጠባብ፣ አልባብ፣ የሰንደል እንጨት፣ እጣን፣ ከርቤ፣ የተከበረውን የኦፌር (የአፋር) ወርቅ እና ሉል ይዘው፤

በገነቱ እየተቀመጠ (የዛሬው የጁና ዋይዝ ከተማ ሆኖ) የአዜባውያን (የአዘቦ) ንጉሥ የነበረው አጋቦን፤

የነባው ንጉሥ ሀጃቦን እና በሳባ ከተማ፣ በሃማሴን ይቀመጥ የነበረው አርስጣ ናቸው። (አማን በላይ፣ ዝንቱ ከማሁ ፣ ገጽ 324-325.)

ኢትዮጵያኑ ነገሥታት አባቶቻችን የኢትዮጵ ተወላጆች፣ በብዙ የጦር ሰራዊት ታጅበው ኢየሩሳሌም ከተማ በገቡ ጊዜ፣ ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌሉ እንደሚነግረን፣ የሮማውያን አሻንጉሊት

ሆኖ ኢየሩሳሌምን በንጉሥነት ያስተዳድር የነበረው ሄሮድ እና የኢየሩሳሌም ኗሪዎች በጣም ደነገጡ። ተሸበሩም። የተሸበሩትም ወረራ ስለመሰላቸው ነበር። ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን ከሮማውያን ጋር በድንበር እየተጋጩ በየጊዜው ሮማውያኖችን አያተጡ ቅጣት ይቀጧቸው ስለነበር ነው። እንዲሁም፣ እያንዳንዱ ንጉሥ እሱን እና ለእየሱስ በግመሎች የጫነውን ሥጦታዎች የሚጠብቁለት ከ3000 ያላነሱ ወታሮች በስሩ ነበሩና። የ12ቱም ንጉሦች ወታደሮች ቢደመሩ ወደ 36000 ስለደረሱ ይህም የኢየሩሳሌምን ባለሥልጣኖችና ኗሪዎች ሊያስደነግጣቸው ችሏል። ሁሉም የተረጋጉት ኢትዮጵያውያኑ ለሰላም እንደመጡ ባወቁ ጊዜ ብቻ ነበር። ከጣልያኖች (ከሮማውያን) ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሮማውያንን ደጋግመው በጦርነት ድባት የመቱት በአድዋ ብቻ ሳይሆን፣ ከአድዋ ጦርነት 2000 ዐመታት አስቀድሞ በግብጽና በኑብያም ነበር። አውግስጦስ ቄሳር ሲያቀብጠው የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ጥሶ ድባቅ ተመትቶአል። ሮማውያን የኑብያን እና የግብጽ ግዛታችንን ወርረው ሲትዋ ንግሥተነገሥታችን እቴጌ ጌርሳሞትም ሰባብራ አድቅቃቸዋለች።

"አጼ ፅንፈአርእድ ታናሽ እህቱን አስራ ሰባተኛይቱ የህንደኬ ንግሥት (ንግሥተ-ህንደኬ) ብሎ አንግሦ ከ200000 (ሁለት መቶ

ሺ) ባለሰረገላ ጦር ከ 400 ፈረሰኞች ጦር ጋር ወደ መርዌ ላካት። መርዌም የድንጉላና የ ኑብያ፣ የኩብያ ዋና ከተማ ናት።

‹‹ንግሥተ ህንደኬ ገርሳሞት ወደ መርዌ ስትሄድ ህንደኬን፣ ጣኬምስን፣ ጳጥሮስን፣ ሜግዶልን፣ ደልታን (እየሱስና ማርያም ጥገኝነት ያገኙበት የግብጽ የኢትዮጵያ ግዛት)፣ ኤልፋንታይን፣ አስዋንን፣ እና ሴዋንንም የአውግስጦስ ጭፍሮች ወረው ይዘውት ነበርና ከአውግስጦስ ሠራዊት ጋር ተዋግታ ነጻ አወጣቻቸው። በአሞን (ጣኦት) ማምለኪያ ደጃፍ ሰቁሳር ተሠርቶ የነበረውን ሃውልትም አፈራረሰች።›› (አማን በላይ፣ *መጽሀፈ አብርሂት*፣ ገጽ 89) ሆኖም በዛን ጊዜም እስራኤልን በቅኝ ገዢነት ይዘው የነበሩት እነዛው ሮማውያን ስለነበሩ የኢትዮጵያ ቤተ-እስራኤሎችና አማአዝያን በፈለጉት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በቤተመቅደስ እንዲሰግዱ ሲባል ከሮማውያን ጋር እርቅ ተደረገና ታህታይ ግብጽ ለሮም ተሰቶለት ላእላይ ግብጽ ለኢትዮጵያ እንዲሆን ተደረገ። በእዚህ ዐይነት የሮምና የኢትዮጵያ ዜጎች አንደኛቸው ወደ ሌላኛቸው ሀገር እንደ ልባቸው በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ተፈቀደላቸው።

ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ጠቢባን የኢትዮጵያ ነገሥታት፣ ከኢየሩሳሌም ተነስቶ ለዚህ ተልእኮ ከ2000 ዐመታት አስቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በጣና ደሴት የሰፈረውን የቅድመ-

አባታቸውን የኢትዮጵን ትንቢትና ትእዛዝ ለመፈጸም ወደ ቤተልሄም ተጉዘው ለህፃኑ መሲህ ለእየሱስ ክርስቶስ ሰግደው ገጸበረከት አቅርበዋል። ይህን ሁሉ በማድረጋቸው፣ ነቢዩ ቅዱስ ሳሙኤል፣ መሲሁ ከመወለዱ ከ1000 ዐመታት አስቀድሞ ኢትዮጵያ ለመሲሁ ስጦታ ይዛ እጆችዋን ወደ እሱ እንደምትዘረጋ የተናገረውና ሌሎቹም ይህንን አስመልክቶ የሳባ (የዛሬው ትግራይና ኤርትራ አካባቢ) የተርሴስ (የአፋር) እና የአረብያ (የያኔው ኢትዮጵያ ግዛቶች) ነገሥታት የሆኑት ሁሉ የኢትዮጵያን ወርቅና እጣን አበርክተው እንደሚሰግዱለት የተነበየው ትንቢት ቃል በቃል ተፈጽሞአል። በእዚህ እና፣ እየሱስ ክርስቶስ እመሀላቸው ተወልዶ ወገኖቹ እስራኤላውያን ይህን ትልቅ የምስራች ሳያውቁ፣ አባቶቻችን ጠቢባኑ ነገሥታት ይህን ክስተትና ብስራት ለ2000 ዐመታት በናፍቆት ጠብቀው፣ መወለዱን አውቀው፣ ከዐለም ህዝቦች ሁሉ ቀድመው ሄደው ስለሰገዱለት እኛ የመልክጸዲቅ እና የኢትዮጵ ልጆች ኢትዮጵያውያን ሁሉ እጅግ ልንኮራ ይገባል።

ኮከቡ (በኮኮብ የተመሰለው ለቅድስት ማርያም እየሱስን እንደምትወልድ ያበሰራት ሊቀመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ራሱ ነበር።) በኢትዮጵያ ግዛት ላይ ለነገሥታቱ የታያቸው እየሱስ ከመወለዱ ከሁለት ዐመታት አስቀድሞ ነበር። ምክንቱም

እያንዳንዳቸው ብዙ ሰራዊቶች፣ ወርቅና እጣን፣ ሌሎችም ስጦታዎች የተጫኑ ግመሎች ይዘው፣ የሚነሱት ከሩቅ በመሆኑ መንገዱ አድካሚ እና ረጅም ስለነበር ነው። የጉዞአቸውን እቅድ የመራው እግዚአብሄር ራሱ ነው። የጉዞአቸውን ጊዜ ነዳፊውና ተቆጣጣሪው ራሱ እግዚአብሄር መሆኑን ማስረጃው ለሁለት ዐመታት ተጉዘው ልክ መሲሁ የተወለደ እለት ቤተልሄም መድረሳቸው ነው።

ንጉሥ ሄሮድስ፣ አዲስ ለተወለደው እየሱስ፣ 12 ታላላቅ ያውም ጠቢባን የኢትዮጵያ ነገሥታት ሊሰግዱለት እንደመጡ ሲያይ ለመንግሥቱ ቀንቶ ሊገለው እንደ አሰላ ጠበቢባኑ ነገሥታት በህልማቸው ከእግዚአብሄር ተነግሮአቸው፣ ቅዱስ ዮሴፍን እና እናቱን ቅድስት ማርያምን፣ እንዲሁም ህጻኑንን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ወይም ወደ ግብጽ እንዲሸሹ መከሯቸው። ዣንሽዋ የተባለው የኛ ጥንታዊ መጽሀፍ እንደሚነግረን፣ ሄሮድስ በራሱ ስልጣን እየሱስን ሊገል ቢመኝም አለቃውን አውግስተስ ቄሳርን ሳያስፈቅድ ርምጃ መውሰድ ፈርቶ ራሱ ሰፊና የረጅም ጊዜ ዝግጅት አድርጎ፣ ወደ ሮም ሄዶ ቄሳሩን አሳምኖ ተመልሶ እስከሚመጣ ሁለት ዐመት ፈጀበት። ከዛ በፊት ግን ከቄሳሩ በደብዳቤ ሲላላክ ቆይቶ ስለነበር ራስህ ና እና ጉዳዩን አስረዳኝ ስለ አለውም ጭምር ነበር ወደ ሮም ለመሄድ የተገደደው። ህጻኑ

የሁለት ዐመት ዕድሜ ሳለ ሄሮድስ ሊገለው እየገሰገሰ መሆኑን ቅዱስ ገብርኤል ለቅዱስ ዮሴፍ ገልጦለት ህጻኑን እና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ እንዲሸሽ መከረው።

የእየሱስ ክርስቶስ በግብጽ፣ መርዌ እና ኢትዮጵያ ቆይታ

እየሱስን እና ማርያምን ይዞ ወደ ግብጽ እንዲሸሽ ቅዱስ ገብርኤል ቅዱስ ዮሴፍን እንደመከረ በመጽሀፍ ቅዱስ ቢሰፍርም ቅዱስ ዮሴፍ፣ ቅድስት ማርያም እና እየሱስ ክርስቶስ በግብጽ የት እንደኖሩና ምን ያደርጉ እንደነበር አልተገለጸም። ነገር ግን በእኛ ጥንታዊ መረጃ መሰረት፣ ሁሉቱ ቅዱሳን እና ህጻኑ የኖሩት በግብጽ የኢትዮጵያ ግዛት፣ በአማርና ደልታ መንደር ነበር። ጥንት፣ መላዋ ግብጽ የኢትዮጵያ ግዛት ነበረች። በርካታ ፈርኦኖች ወንዶች እና በህንደኬ ማእረግ የነገሡ 17 ሴት ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በኋላ የኢትዮጵያ ልዑላን ቤተሰቦች ተጣልተው ተከፋፍለው ወደ ካይሮ አካባቢ የነበረውን ደቡብ ግብጽን የፋርስ (ፐርስያ) ሰዎች ያዙት። ወደ አስዋን አካባቢ እና አማርና ደልታ የተባለው

የሰሜን ግብጽ ብቻ ለኢትዮጵያ ቀረላት። ከዛም ትልቁ እስክንድር ተነስቶ ያንን ፋርሳውያን ከኛ ወስደውት የነበረውን የግብጽ ክፍል ነጠቃቸው። ግሪኮችን ታሪክ ጥሎአቸው የግሪኮች ኃያልነት በአውሬዎቹ በሮማውያን በተተካ ጊዜ ሮማውያኑ በተራቸው ታህታይ ግብጽን ወሰዱባቸው።

እንግዲህ እየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ወቅት ግብጽ በሁለት መንግሥታት ትገዛ ነበር ማለት ነው። አንደኛው ታህታይ ግብጽ (ካይሮ እና አሌክሳንድሪያ ያሉበት) በሮማውያን እጅ፣ ሁለተኛው ላእላይ ግብጽ፣ ለኑብያ እና ኢትዮጵያ የሚቀርበው ክፍል የኢትዮጵያ ግዛት ነበር። ቅዱሳን ዮሴፍ፣ ማርያም እና ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ከሮማን አገዛዝ ሸሽተው ጥገኝነት ያገኙት ከኢትዮጵያ ግዛት ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ወደ ሮማው ግብጽ ቢኮበልሉ ኖሮ ይያዙ ስለነበር።

በዛን ዘመን፣ የኢትዮጵያውን ክፍል ግብጽ አስተዳዳሪ ኢትዮጵያዊው (የጎጃም ሰው) የኢትዮጵ የቀጥታ ተወላጅ ንጉሥ አማናቱ ተትናይ ነበር። አማናቱ ተትናይ በጎጃም የደሸት ከተማ ንጉሥ የነበረው የአጎጃ ጃቦን ልጅ ነበር። ታላቅ ወንድሙ ደግሞ የጎላ ንጉሥ የነበረው ሀጃቦን ነበር። የንጉሥ አማናቱ ተትናይ አባት አጎጃ ጃቦን እና ታላቅ ወንድሙ ሀጃቦን ለእየሱስ ክርስቶስ ገጸበረክት ይዘው ወደ ቤተልሄም ከተጓዙት 12 ነገሥታት ሁሉቱ

ነበሩ። ቅዱሳኑ ዮሴፍ፣ ማርያም እና እየሱስ ክርስቶስ የኖሩት በንጉሥ አማናቱ ተትናይ ጥበቃ አማርና ደልታ በተባለው የኢትዮጵያውያን መንደር ነበር። አማርና ደልታ የተቆረቆረችው፣ አጼ አክሱማይ በሀጻንነቱ ግብጽ ላይ ራሚሱ (ራምዘዝ) በሚል ማእረግ በእናቱ በንግሥት ሳዶንያ (ሱዳንን በስሟ ያስጠራችው) ሞግዚትነት ነግሦ ሳለ እሱን እና መንግሥቱን ለመጠበቅ ወደ ግብጽ በዘመቱ አማሮች ነበር። ዘመኑም እየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ850 ዐመታት በፊት ነበር። ይህ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረው አማርና ደልታ (ደልቶን አማርን እንደማለት) የሞቀ የደመቀ የኢትዮጵያውያን መንደር ስለነበር ቅድስት ማርያም፣ ቅዱስ ዮሴፍ እና ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ የስደት ዘመናቸውን ያለስጋት ያሳለፉት እዛ ነው ማለት ነው። ንጉሥ አማናቱ ተትናይ፣ እየሱስ ክርስቶስ ልጅ ሆኖ ብዙ ተዐምራትን ይፈጽምና ከእሱም የበሁር ልጅ ከሲማር (በኋላ እየሱስ ማርሄር ብሎ ከሰየመው ጋር) እንዴት ወዳጆች እንደነበሩ፣ ቅዱስ ዮሴፍ እንዴት እናትና ልጁን ይዞ ወደ እስራኤል እንደተመለሰ፣ በኋላም እየሱስ የ22 ዕድሜ ወጣት ሳለ እንዴት ኑብያ ድረስ መጥቶ እንደ ጠየቃቸውና ከዛም ከልጁ ከማርሄር፣ እና ከታላቅ ወንድም ልጅ ከ ዲማስ ጋራ ሆኖ በእነሱ አገልጋይነት እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደኖረ ትዝታውን ጽፎአል።

እየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተማረውን የመሠረተና የፈጸመውን ተአምራቶች ሁሉ የእየሱስ ወዳጅና አጃቢ የነበረው ልጁ ማርሄር በየጊዜው ይጽፍለት ስለነበር፣ ዜና ማርሄር በተባለው መጽሀፍ የእየሱስ ክርስቶስን በኢትየጵያ ቆይታ ዘርዝሮታል። ማርሄር እንደ ዘገበው፣ እየሱስ ክርስቶስ የኢትዮጵያን መሬት እንደረገጠ ወደ ጣና፣ ጎጃም ሄዶ፣ ወደ ደሴዮቹ ተሻግሮ፣ እዛ ለነበሩት ቤተ እስራኤሎች ለ2000 ዐመታት የሚጠበቁት መሲሃቸው እሱ መሆኑን ገልጾ፣ ተዐምራት እየሠራ ሲያስተምራቸው፣ ገሚሶቹ ወደውት ሲቀበሉት፣ ገሚሶቹ ደግሞ ስህተታችንን እና ኃጢአታችንን አጋለጠብን በማለት ተቃውመውት ነበር። ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ለሁለት ዐመታት በግልጽ ነበር የሚንቀሳቀሰው። ሌዋውያን ካህናት ተተናኩለው ሊያሳስሩት ስለፈለጉት የመጨረሻውን ዐንድ ዐመት እየተሰወረ ነበር ተልእኮውን የፈጸመው። በጠቅላላው ለሦስት ዐመታት ቆይቶ ኢትዮጵያን ለቆ ሲሄድ ቅዱስ ማርሔርን እና የአጉን ልጅ ቅዱስ ዲማስን በኢትዮጵያ ላይ በጳጳስነት ሾማቸው። ቅዱስ ዲማስ ለብዙ ዐመታት የሀዋርያት ሥራውን ሲፈጽም ኖሮ፣ በቀናተኞች ሊዋውያን በሀሰት ተከስሶ፣ በእሳት ተቃጥሎ፣ ከመጀመሪያዎቹ ሰማእት ክርስቲያኖች አንዱ ለመሆን በቅቷል።

እየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማስተማር በመጣበት ወቅት፣ በፊት በአማርና ደልታ የኖረው ንጉሥ አማናዝ ተተናይ መናገሻውን መርዌ ላይ አድርጎ ስለነበር፣ እየሱስ የእሱ እንግዳ ሆኖ በእልፍኙ ውስጥ አንድ ሳምንት አሳልፎ ነበር። እየሱስ የነብያን ሀዘቦች እያስተማረና እየፈወሰ ለአንድ ሳምንት ቆይቶ ከንጉሡ ልጅ ከማርሄር እና ከወንድሙ ልጅ ከዲማስ ጋራ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አቋርጦ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ እሱ አንድ ሳምንት ያሳለፈበትን እልፍኝ ንጉሡ አማናዝ ቤተክርስትያን አደረገው። ስለመሲሁ መወለድ እና ማዳን በነብያቱ የተነገሩትን ትንቢቶች እየጠቀሱ የሚያስተምሩ አይሁዳውያን መምህራንን ቀጥሮ ምእመናንን እየሰበሰበ ስፍራውን ወደ ክርስትያን ቤተመቅደስነት ለወጠው። እንደዚህ በማድረጉም፣ እየሱስ ክርስቶስ በሕይወቱ እያለ እኛ ኢትዮጵያውያን በዐለም የመጀመርያውን ቤተክርስትያን አቋቁምንለት ማለት ነው። ይህ እጅግ የሚያኮራን ትልቅ ቁምነገር ነው።

እየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሦስት ዐመታት ኖሮ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ከተሰቀለ በኋላ ደቀመዛሙርቱ እነ ቅዱሳን በርጠሎሜዎስና ማቴዎስ በእዚሁ ቤተክርስትያን ውስጥ እየሰበኩ እና እየዘመሩ ሰንብተው ለንጉሥ አማናዝ ተተናይና ቤተሰቡ ስጋ ወደሙ ሰጥተው አቁርበዋቸዋል። የዐለሙ ፈጣሪ እየሱስ ክርስቶስ

እስራኤል ለነበሩት ወገኖቹ ራሱን ሳይገልጥ ለእኛ ኢትዮጵያውያን በጠቅላላው፣ ለኢትዮጵያውያን ቤተእስራኤሎች በተለይ በመግለጡ ሀላፊነም እንኮራለን። ከእዚህ በተጨማሪ፣ በ25 ዐመቱ ወደ እስራኤል ተመልሶ በ30 ዐመቱ ማስተማር ጀምሮ፣ ልክ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሦስት ዐመታት እንዳስተማረውና ተዐምራትን እንደሠራው በእስራኤልም ለሦስት ዐመታት ያንኑ ስለአደረገ እና ያንኑ ያህል ጊዜ ለእኛም ስለመደበልን እኛንም ከወገኖቹ እኩል አክብሮናል። ተሰቅሎ ከመሞቱ በፊት ኢትዮጵያውያን ሰብአሰገል የአሳዩትን አምልኮና ክብር፣ እንዲሁም ስለ አማናዝ ተተናይ፣ ስለ ማርሄርና ዲማስ፣ በተጨማሪም ስለቤተእስራኤልና የሶስት ዐመት የኢትዮጵያ ቆይታው ለደቀመዛሙርቱ አጫውቶአቸው ስድስቱ ወደ ኢትየጵያ መጥተዋል። በመጀመሪያ የመጣው ቅዱስ በርጠሎሜዎስ ሲሆን፣ ቀጥሎ ማቴዋስ፣ ማርቆስ፣ እንድርያስ፣ ናትናኤል እና ቶማስ ናቸው። እየሱስ ኢትዮጵያ ለሦስት ዐመታት በቆየበት ወቅት እሱ ራሱ እያስተማረና ተዐምራት እየሠራ መሲሁ መሆኑን ኢትዮጵያውያኑን አሳምኖ ስለነበር ደቀመዛሙርቱ ለማሳመን ብዙ ሳይደክሙ ጥቂት ቃለ-ስብከት ብቻ አድርገው ህዝቡን እያጠመቁ ስጋ ወደሙ ሊሰጡ ችለው ነበር። እንደዚህ ኢትዮጵያን ስለአከበራትና ስለ አስበላት የኢትዮጵያ እና የእስራኤል አምላክ ይክበር፣ ይመስገን።

ነብዩ ሙሴ እና ኢትዮጵያዊው አማቹ ሊቀካህናት ዮቶርአብ

በመልከጸዲቅ ዘርና በአብርሃም ቤተሰብ ትውልድ መሃል የመጀመሪያው የጋብቻ ግንኙነት የተጀመረው የኢትዮጵ ሁለት ሴት ልጆች የአብርሃምና የሎጥን ወንድ ልጆች አግብተው ዘር ባፈሩ ጊዜ ነበር። ሁለቱ የኢትዮጵ ሴት ልጆች ሱቫባ (ሱባ) እና ሎዛ ናቸው። ሱቫባ ወይም ሱባ አብርሀም ከቀጡራ የወለደውን ምድያምን አግብታ የምድያማውያን እናት ሆነች። ሎዛ የአብርሀምን የወንድም ልጅ የሆነውን የሎጥን ልጅ አግብታ አስራ ሁለት ጊዜ መንታ መንታ ወልዳ የአሞናውያን እናት ሆነች። ሚልከ የተባለችው ሶስተኛዋ ልጁ ግን በድንግልና ኖራ ነቢይት ሆና እድሜዋን አሳልፋለች። (አማን በላይ፤ ዝንቱ ከማሁ ገጽ 56-57)

ቀጣዩ ጠንካራና መሰረታዊ የኢትዮጵያውያን እና የአይሁድ ህዝቦች ትስስር የተከሰተው፤ የአይሁድ ህዝቦች በባርነት ቀንበር በሚማቅቁበት ዘመን አንድ ግብሚዊ አለቃ አይሁዳዊ ባርያን ሲያንገላታ የተመለከተው ሙሴ ጨካኙን ግብጻዊ ገድሎት ከምድረ ግብፅ ሲሰደድ ነው። በእኛ መረጃ መሰረት፤ ሙሴ ህይወቱን ለማትረፍ ከግብፅ ካመለጠ በኋላ በመጀመሪያ ወደ ቂራ (ጎንደር) ሸሸ፤ ለ20 ዐመታት ያህል እዛ ሰንብቶ፤ ከዛ ምድያም (የኛ መረጃ እንደሚለው መደነ በተባለ የኢትዮጵያ ግዛት) ደርሶ አንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ አረፍ አለ። እዚያ እረኞች በደል ሲፈፅሙ አይቶ አስቆማቸው። ያንንም ሁኔታ ሙሴ ራሱ የጻፈው ቶራ እንዲህ ሲል ያብራራዋል፦

‹‹ሙሴ ከፊርኦን ፊት አምልጦ ምድያም ደረሰና አንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። ሰባት ሴት ልጆች ያሉት አንድ የምድያም ካህን ነበር። ሴቶቹ ልጆች ውሃ ሊቀዱ መጡ፤ ለአባቶቻቸው ከብቶች ሊያደርሱ፤ እንስራዎቻቸውን ሞሉ። ያኔም እረኞች መጥተውባቸው አባረሯቸው፤ ነገርግን ሙሴ ደርሶላቸው ከብቶቻቸውን አጠጡ። ወደ አባታቸው ራጉኤል በመጡ ጊዜ፦

‹‹ለምን ዛሬ ፈጥናችሁ መጣችሁ?›› አላቸው።

እነርሱም፡- ‹‹አንድ የግብፅ ሰው ከእረኞች አዳነን፣ ውሃ ሞላልን፣ ከብቶቹንም አጠጣልን›› አሉት።

‹‹የት ነው ያለው? ለምንስ ትታችሁት መጣችሁ? እህል እንዲቀምስ ጥሩት፤›› ሲል አዘዛቸው።

ሙሴም ከዚያ ሰው ጋር ሊቀመጥ ወደደ። ያም ሰው ልጁን ሲፓራን፣ ለሙሴ ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። ወንድ ልጅም ወለደች። የሌላ ምድር መጻተኛ ነኝ ሲል ስሙን ጌርሳም ብሎ ጠራው። (ኦሪት ዘጸአት 2፣ 16-22)

እንደ እኛ መረጃ፣ ሙሴ ወገኑን ከግብፅ ባርነት ነፃ ሊያወጣ ከመጓዙ በፊት ሲፓራ፣ አልዓዛር የሚባል ሌላ ወንድ ልጅና አራት ሴት ልጆች ወልዳለታለች። ቶራ የተባለው የአይሁዳውያን መጽሀፍ ስለ አራቱ ሴት ልጆች አይጠቅስም። ሲፓራ የሙሴን ሁለት ወንድ ልጆች፣ አብርሃም ለእግዚአብሔር በገባው ቃልኪዳን መሰረት ገረዘቻቸው። በዚያም መንስኤ ኢትዮጵያውያን ወንድ ልጆቻቸውን መግረዝ ጀመሩ ይባላል። እስከዛሬም ድረስ ይገርዛሉ። እኔም የእዚህ መጽሀፍ ደራሲ እንደ ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ወንዶች፣ ገና የ40 ቀናት ህፃን ሳለሁ ተገርዣለሁ።

ራጉኤል (ዮቶር ወይም ዮቶር-አብ) በእርግጠኛነት ማነው? በምድያም (የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ አንድ ክፍለ ግዛት) ኢትዮጵያዊ

የእግዚያብሔር ሊቀ ካህን ሙሴ በእግዚአብሄር ተራዳኢነት እስራኤላውያንን ከግብጽ የባርነት ቀንበር አርነት ካወጣ ከሦስት ዓመታት በኋላ በኢትዮጵያ ላይ ነግሦ የነበረ የነገሥታት ዘር ነው። የእግዚያብሔር ሊቀካህን የሳሌም ንጉሥ የመልከጸዲቅ ቀጥተኛ ዘርያ ነው። እንዳውም እንደ ቀደምት አባቶቹ፣ መልከጸዲቅና ኢትዮጵ እርሱም የአዳምና የሔዋን፣ የሔኖክና የኖህ ፈጣሪ፣ የእግዚአብሔር ሊቀካህንና ንጉሥ በመሆኑ ከታላቁ የጥፋት ውሀ በኋላ ሄኖክና ኖህ ፅፈው ለኩሽ ያስተላለፏቸውን ድርሳናት ወራሽ ነው። ካህን የነበረው ኩሽ ደግሞ ድርሳናቱን ክህነት ላላቸው ለልጅ ልጆቹ እያስተላለፈ፣ እስከ መልከጸዲቅ ደርሶ፣ መልከጸዲቅም ዛሬ ዑሚሊዮን ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አባት ለሆነው ለኢትዮጵ አወረሰው። በዚህም ምክንያት፣ ኢትዮጵያውያን የትም ስፍራ የማያገኙ ብርቅና ጥንታዊ ድርሳናት ባለቤት ለመሆን በቅተናል። ከእነዚህም ድርሳናት መካከል ስለ ዓለም አፈጣጠር፣ ስለአዳምና ሔዋን አወዳደቅ፣ ስለ ‹‹ኖህ ውሀ ጥፋት››፣ በዘር አስካል መዛባት ምክንያት አስቀያሚና ግዙፍ (ክህዋ የወረዱ ወይም ሰብአዊ ገፅታ የሌላቸው ግን ስል አእምሮ የነበራቸው) በሙሴ ብእር ግን ‹‹የእግዚያብሔር ልጆች›› ተብዬዎች፣ ከምድራዊ ቆነጃጅት ሴቶች ስለመጋባታቸው የሚዘክሩ መፅሃፈ ሔኖክ እና ሌሎች ቅዱሳት መጻህፍት ይገኙባቸዋል።

በግርንሽዎ በተካተተው በስነፍጥረት ድርሳን፣ እግዚያብሔር ሰባት ሰማያትን (ነብዩ ህዝቅኤል እንደሚለው፤ ሰባት ሰማያት ተከፍተውለት ራዕይ አይቷል። ቅዱስ ጳውሎስም እስከ ሦስተኛው ሰማይ በመንፈስ ይሁን በአካል ሳይለይ መወሰዱን ይናገራል) ፈጥሮ 100 ዐለማትን አኖረ። ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት፣ ምድር በመጀመርያው ሰማይ በኢዮር ከሚገኙት 12 ዐለማት አንዷ ብቻ ናት። ሆኖም ይቺ የኛ ምድር ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረባት ስለሆነች፣ የዐለማት ሁሉ ቁንጮ ነች። በሌሎቹ ሰማየ ሰማያት ሌሎች አእምሮአቸው ብሩህ ፍጥረታት ነበሩ። ግን በእግዚያብሔር አምሳል አልተፈጠሩምና ምን ያህል ጠቢባን ቢሆኑ በክብር ከሰው እኩል አልተቆጠሩም። የዐለሙ ሁሉ ፈጣሪ እየሱስ ክርስቶስ ሰውን ሊያድን የተወለደውና የሞተው፣ ከሙታንም ተነስቶ የአረገው፣ በራእየ ዮሀንስ ትንቢት መሰረት ወደ ፊትም ዳግመኛ መጥቶ ለ 1000 ዐመታት አሚነግሠው በእዚችው በኛ ምድር ላይ ስለሆነ፣ ከሌሎቹ ዐለማት ይልቅ እስዋ ልዩ የክብር ቦታ ይዛለች።

የታላቁ ኢትዮጵያዊው ንጉሠ-ነገሥት የታንዛን ልጅ ዮቶርአብ፣ በአሞናውያን፣ በሞአባውያን፣ በአሞራውያን እና በፈርዛውያን ዘንድ ታላቅ ክብር ነበረው። ለኃያሉ መልከጸዲቅ ያደርጉ እንደነበር ሁሉ ሌሎች ነገሥታት አስራት ያቀርቡለት፣

ግዙን ይቀስሙ፣ ምርቃቱንም ይቀበሉ ነበር። ሙሴ ለ40 ዓመታት የዮቶርአብን የመስዋዕት በጎች ከመጠበቅ ሌላ ተግባር ማከናወኑን ቶራ አይገልጽም። ነገርግን ሙሴ ለእግዚአብሔር መሰዋእት የሚሆኑትን ጠቦቶች እየጠበቀ፣ ጎን ለጎን የዮቶር ይቀመዘሙርና የክህነት ሞያ ረዳቱ እንደነበርም መረጃችን ይጠቁማል። በመቅደሱ ዋና ባለሟል ሆኖ ከማገልገሉም በተጨማሪ ኦሪት ዘፍጥረት የተባለው ድርሳኑ እንደሚለው በዮቶርአብ እጅ የሚገኙ የነበሩትን፣ ስለ አዳምና ሔዋን አወዳደቅ፣ ስለ ሔኖክ መንፈሳዊ ተሞክሮዎች፣ የኖህ ውሀ ጥፋትን ለሳስከሰቱት ግዙፍ ፍጡራን (ነፊሊም፣ ሩሃውያን) ማንበቡ አያጠረጠርም። ሆኖም፣ ቀደም ሲል እንዳመለከትኩት፣ እርሱ በቻ በሚያውቃቸው ምክንያቶች ስለዚች ዓለም መፈጠር ብቻ አውስቶ፣ የሌሎቹን 99 ዓለማት ህልውና ችላ ማለትን መርጧል።

እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ ወገኖቹን ከባርነት ነፃ እንዲያወጣ በላከው ጊዜ ልጆቹንና ሚስቱን ያቆየው አማቱ ዮቶርአብ ዘንድ ነበር። በድል አድራጊነት ሲመለስም፣ ዮቶርአብ ሙሴንና የያዕቆብ ልጆችን በደስታ ተቀብሏል። ታላቅ ድግስ አዘጋጅቶም የህብረት መስዋዕትና ጸሎት ለከሃሊው እግዚአብሄር አድርሰዋል።

ሙሴ ብቻውን ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝቡን በፍርድ ቤት ተሰይሞ መዳኘቱን ለራሱም ሆነ ለህዝቡ እንደሚከብድ ዮቶርአብ በአንድ ወቅት ተገንዝቦለታል። ስለሆነም አስተዋዩ አማቱ ጥቃቅን ጉዳዮችን የሚከታተሉና የሚዳኙ ሽማግሌዎችን እንዲሾምና እሱ ትላልቁ ጉዳይ ላይ ብቻ እየፈረደ ሌላውን የእግዚአብሄርን ተግባር እንዲፈጽም መክሮታል። በራሱ በሙሴ ቃላት፡- ‹‹ዮቶርም እግዚአብሔር ለእስራኤል ስላደረገው ቸርነት ሁሉ፤ ከግብፃውያንም እጅ ስላዳናቸው ደስ አለው። ዮቶርም ከግብፃውያንና ከፈርዖን እጅ ሕዝቡን ያዳነ እግዚያብሔር ይባረክ። ትዕቢት ባደረጉባቸው ነገር እግዚያብሔር ከአማልእክት ሁሉ እንዲበልጥ አሁን አወቅሁ። እነሱ ታብየው ጉራ ካደረጉባቸው በላይ እሱ ውሎአልና›› አለ።

‹‹የሙሴ አማት ዮቶርም የሚቃጠል መስዋእትን እና ሌላ መስዋእትን ለእግዚአብሔር ወሰደ። በእግዚአብሔርም ፊት ከሙሴ አማት ጋር እንጀራ ሲበሉ፤ አሮን የእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ መጡ።››

‹‹እንዲህም ሆነ፤ በነጋታው ሙሴ በህዝቡ ሊፈርድ ተቀመጠ። ህዝቡም በሙሴ ፊት ‹‹ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ ቆመው ነበር። የሙሴም አማት በህዝቡ ያደረገውን ሁሉ ባየ ጊዜ ‹ይህ በህዝቡ የምታደርገው ምንድነው? ህዝቡ ሁሉ ከጠዋት ጀምሮ እስከማታ

ድረስ ‹‹በዙርያህ ቆመው ሳሉ፤ አንተ ብቻህን ስለምን ተቀምጠሃል?›› አለው። (ኦሪት ዘ ጸአት 9-14)

‹‹ሙሴ በህዝቡ መሃል ብቻውን እንደሚፈርድ ገለፀለት። ዮቶርም እንዲህ አለው፡- ‹‹አንተ የምታደርገው ይህ ነገር ትክክል አይደለም። ይህ ነገር ይከብድሃልና አንተ፤ ‹‹ከአንተም ጋር ያለው ህዝብ ትደክማላችሁ። አንተ ብቻህን ልታደርገው አትችልም። ‹‹አሁንም እመክርሃለሁና ቃሌን ስማ። እግዚያብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል። አንተ ‹‹በእግዚአብሔር ፊት ለህዝቡ ሁን። ነገራቸውንም ወደ እግዚያብሔር አድርስ። ስርዓቱንም፤ ‹‹ህጉንም አስተምራቸው። የሚሄዱበት መንገድ፤ የሚያደርጉትንም ስራ አሳያቸው። አንተም ‹‹ከሕዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን፤ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ሰዎች ምረጥ። ከእነርሱም የሺህ ‹‹አለቆችን፤ የአሰርንም አለቆችን ሹምላቸው። በህዝቡ ላይ ሁልጊዜ ይፍረዱ፤ አሠራውን ‹‹ነገር ሁሉ ወደ አንተ ያምጡት። ታናሹንም ነገር ሁሉ እነርሱ ይፍረዱ፤ እነርሱም ከአንተ ‹‹ጋር ሸክሙን ይሸከማሉ፤ አንተም ይቀልልሃል። ይህንንም ብታደርግ፤ እግዚአብሔር ‹‹እንዲሁ ቢያዝዝህ፤ መቆም ይቻልሃል። ደግሞም ይህ ህዝብ ሁሉ በሰላም ወደስፍራው ይደርሳል።›› ሙሴም የአማቱን ቃል ሰማ። ያለውንም ሁሉ አደረገ። (ኦሪት ዘ ጸአት 18፡ 17-24)

ከላይ እንደተመለከተው፣ ዮቶርአብ ስለ ሕዝባዊ አስተዳደርና ፍርድ አሰጣጥ ሙሴን አስተምሮታል። ከዚህም በላይ፣ በክህነት ሞያው ላይ እንዲያተኩር፣ አስተማሪና አስታራቂም ሆኖ በህዝቡና በእግዚአብሔር መሃል እያማለደ ሰላም ያወርድ ዘንድ ኮትኩቶታል።

ዮቶርአብ ይሄን ሁሉ እንዴት ማወቅ ቻለ፣ የሚል ይኖራል። ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት፣ የዮቶርአብ ዘረ-ግንድ ከሳሌም ንጉሥ መልከጸዲቅና ከኢትዮጵያውያን አባት ከኢትዮጵ፣ ህዝብን እና መንግሥታትን በህግ፣ በፍትህ እና ስርዓት ካስተዳደሩ ነገሥታትና ሊቀካህናት የወረደ ነው። እላይ እንዳልኩት፣ እስራኤላውያን ከባርነት ነጻ ከወጡ ከሦስት ዐመታት በኋላ ዮቶርአብ ድፍን ኢትዮጵያን ያስተዳደረ ንጉሠ ነገሥት ሆኗል።

በዘሩ ዐይሁዳዊ፣ በዜግነቱ ሮማዊ የነበረው ዝነኛው የድሮ ዘመን ባለታሪክ ፍሌቪዩስ ዮሴፈስ በእስራኤላውያን ጥንታዊ ታሪክ መድበሉ ሁለት ምዕራፎች (ምዕ.3 እና 4 ገጽ 69) ስለ ዮቶርአብ እንዲሁም ሙሴ ዮቶርአብን አክብሮ ጠቃሚ ምክሩን በልቡ ማሳደሩን ዘግቧል።

ዮቶርአብ፣ አባቢሄር የሚባል፣ እሥራኤላውያን ‹‹ሆባብ›› ብለው የሚጠሩት ወንድ ልጅ ነበረው። በቅዱሳት መፃህፍት

አጠራርና በአስተዳደር የተካነ ነበር። አባቢሄር፣ ከይሁዳ ጎሳ የተወለደችውን የአሚናዳብን ልጅ፣ ሩት አሚንን አግብቷል። ዮቶርአብ ሲሞት የክህነትና ንግሥና ተግባሩን ተረክቧል። ዐንደኛው ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት የሆነውን ኢትዮጲስን ከነገደ ይሁዳ ከሆነችው ከሩት አሚን አፍርቷል። ኢትዮጲስም በኢትዮጵ ዙፋን ላይ ከ3500 ዐመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀመጠ የአይሁዳዊ ደም ያለበት ንጉሠነገሥት ሆኖአል።

ሙሴ ዳኞች መርጦ፣ የሚሰቱ ወንድም አባቢሔር በአስተዳርና በዳኝነት ተግባራት እስራኤሎችን እንዲያስለጥናቸው አድርጓል። አባቢሔርም ሥርዓተ ሕግ ቀርፆላቸው፣ አዲስ የተመለመሉት ዳኞች እንዴት እንደሚተገብሩት አሳይቶአቸዋል። በዚህም ብቻ ሳይወሰን የእግዚአብሔር ትእዛዛት እና ከኖህና ከመልከጸዲቅ ሲወርዱ ሲወራረዱ የመጡ ቅዱሳት መፃህፍት መምህር በመሆን የእስራኤልን ሰዎች እያገለገለ ሙሴን እፎይታና ደስታ አላብሶታል።

ከቅድስት አገር ለመድረስ መንገዶቹንና የሲና ምድረበዳን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ እግዚአብሔር የሚለግሳቸውን ሁሉ እንደሚያካፍሉት ቃል ገብቶለት አብረዋቸው እንዲጓዙ ሙሴ አባቢሔርን በአንድ ወቅት ጠየቀው።

‹‹ሙሴም የሚስቱን ወንድም፣ የምድያማዊውን የራጉኤልን ልጅ (ሆባብን) ‹‹እግዚያብሔር ለእናንተ እሰጠዋለሁ ወዳለው ስፍራ እንሄዳለን፤ እግዚአብሔር ስለ ‹‹እስራኤል መልካምን ነገር ተናግሯልና፣ አንተ ከእኛ ጋር ና፤ መልካም እናደርግልሃለን›› አለው። እርሱም ‹‹አልሄድም ነገርግን ወደ አገሬና ዘመዶቼ እሄዳለሁ›› አለው።

እርሱም ‹‹እባክህ በምድረበዳ የምንሰፍርበትን አንተ ታውቃለህና እንደ ዐይኖቻችንም ትሆንልናለህና አትተወን፤ ከምናገኘው መልካም ነገር ሁሉ እኛ ለአንተ እናደርጋለን›› አለው። (ዘ ኅልቁ 10፡29-32)

ከነበሩበት ራቅ ባለ ቦታ ይኖር የነበረውን አባቱን ዮቶርን ሄዶ ለማየት ማቀዱን (አባብሔር) ሲገልፅለት ሙሴ ደግሞ አብሮት እንዲቆይና በበርሃ የተበተኑትን እስራኤላውያን ማስተማሩን እንዲገፋበት አጥብቆ ለመነው። አባብሄርም እግዚአብሔር በራእይ ተገልጦለት በነገረው መሰረት በእድሜ የገፋው አባቱን ዮቶርአብን እንደ ንጉሥና ካህን ሊተካው ማሰቡን በማስረዳት እንዲሄድ ይፈቅድለት ዘንድ ሙሴ እግር ስር ወደቀ። እንዲህም አለው፡-

‹‹ለእግዚያብሔር መታዘዝ አለብን። በቅድሚያ አባቴን ማየት፣ ከዚያም ዘመዶቼ ዘንድ ወደ ኢትዮጵያ ሄጄ ንጉሠ ነገሥት ከሆንኩ በኋላ የእግዚያብሔር ፈቃዱ ከሆነልኝ ሁለታችንም በአንድ እግዚአብሔር እናምናለንና ላይህ እመለሳለሁ።››

ሙሴ ሁኔታውን ተረድቶለት የተመኘውን እንዲፈፅም ፈቀደለት። ወዳጅነታቸውን ለማስታወስም ቀይ ባህርን የከፈለበትን በትር እና በእሳት ይጋይ በነበረ ጥሻ እግዚያብሔር ተገልጾለት የያእቆብን ልጆች ነፃ እንዲያወጣ በነገረው ቦታ በ(ኮሬብ) ተራራ ዋሻ ውስጥ ያኖረውን፣ አስርቱ ትእዛዛት የሰፈሩበትን ፅላተ ምስል አንድ ግልባጭ ሙሴ ለአባብሔር ሰጠው። መርቆትና መክሮት የእያሱን ያህል ይወደው ስለነበር አዝኖ አሰናበተው። (አማን በላይ፣ *መጽሀፈ ሰባኤ ዘበአማን ካልዕ*፣ገጽ 89-90)

ዮቶርአብ ለ22 ዓመታት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ አለፈ። ልጁ አባ ብሔር ስመ መንግሥቱ ‹‹ኢትዮጵ-መልከ ሰብያና›› ተብሎ አልጋውን ወረሰ። የይሁዳ ነገድ ተወላጅ የአሚናዳብን ሴት ልጅ ሩት አሚንን አግብቶ እርሷም በኢትዮጵያ ግዛት እንዳውም በዓለም ዙርያ ቀዳማይቱ አይሁዳዊት ንግሥት ለመሆን በቃች።

አባ ብሔርም አስርቱ ትእዛዛት የሰፈሩበትን ፅላት ምስል እና በትረ ሙሴውን (ሙሴ ቀይ ባህርን የከፈለበትንና ሌሎች ተአምራት ያደረገበትን) በትር በኮራብ ተራራ ዋሻ ግርጌ በድንኳን ውስጥ አኖረ። ከዚያም በዚያው ቅዱስ ስፍራ ለጽላቱ ማረፊያ ቤቱል የሚባል መቅደስ አሳንጾና 70 ሌዋውያንን እንዲንከባከቡትና እንዲያገለግሉ ሾመ። ስፍራውንም ከሩት አሚን ባፈራት ሴት ልጁ ስም ቱስቢያ አለው። ቱስቢያ ያላትም ቱስቢያን ለመዘከር ነው። ቱስቢያም ከኢትዮጵ 10 ወንዶች ልጆች አንዱ ነበር። ነቢዩ ኤልያስም ቱስቢያዊው የተባለው ከእዚህ ቅዱስ ስፍራ የተነሳ ነው። ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነው ይላሉ። ሩት አሚን ለአባብሔር ወንድ ልጅም ወልዳለት ‹‹ኢትዮጲስ›› ብሎ ጠራው። ኢትዮጲስም በለጋ እድሜው የጥበበኛነትና መንፈሳዊነት ባህሪ አንፀባረቀ።

አባብሄር ዘውድ ጭኖ የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት ከሆነ ከዐስር ዓመታት በኋላ በአባቱ በዮቶርአብ ስር የነበሩ የአሞን፣ የኤሊምና የግብፅ መኳንንትና ልኡላን ሊጎበኙት መጡ። አስማተኞችና ጠንቋዮች አስከትለዋል። እርሱም ቱስቢያ በሚባለው ቦታ ቤቱል መቅደስ ውስጥ በአክብሮት ያስቀመጣቸውን ጽላት፣ በትረ-ሙሴና ሌሎች ንዋየቅዱሳትን በኩራት አሳያቸው። ጎብኚዎቹም፣ ንዋየቅዱሳቱ ከእግዚያብሔር ቅዱሳት ንብረቶች ይልቅ የኛ የአምልኮ እቃዎች ይበልጣሉ፤ ሲሉ ጉራቸውን ነፉ። ከዚያም

ከለፈው ተርፈው አስማተኞቹና ጠንቋዮቹ ከድፍረታቸው ብዛት መቀጣጫ ያደርጋቸውን መቅደሱ ውስጥ ከጎደሉ እግዚአብሄር የጻላት ቁሳቁሶቹ ጎን አኖሩ። ያም ድርጊት የእግዚያብሔርን ቁጣ አመረደ። እግዚአብሄርም እርኩስ ቁሳቁሶቹን ሰባበራቸው። አማልታውያንና ግብጻውያን ይገሉት ዘንድ አባብሄርንም ለነሱ አሳልፎ ሰጠው።

ሌዋውያኑም የጽላቱን ግልባጭ፣ የሙሴን በትር እና ሌሎቹን ንዋየ-ቅዱሳት ይዘው፣ ከሆራብ ተራራ፣ ከቱስቢያ በጥድፊያ ከ3000 ሰዎች ጋራ ሆነው የአባብሔርንና የሩት አሚንን ልጅ ኢትዮጲስን ለማንገሥ ወደ ኢትዮጵያ ገሰገሱ። ከዛም፣ ኢትዮጲስን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አድርገው አነገሡት።

ከጊዜ በኋላ ኢትዮጲስ፣ ለሌዋውያን ካህናትና ተከትለውት ለመጡት እስራኤላውያን መሬትና ስልጣን ሰጥቶአቸዋል። ኢትዮጲስም ግብጽ ወርዶ አስዋንን እና ኤለፋንታይንን ቆርቁሮ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ አካቶአል። ቤተመቅደሶች አንጾና ኢትዮጲስ ራሱ እንደ ቀደምት አባቶቹ የንጉሠነገሥትነትንና ሊቀ ካህናትነትን ማእረግ አጣምሮ ይዞ ህዝቡን በፍትህ መራ። በሊቀካህንነቱም ለሙሴ ከእግዚአብሄር የተሰጠውን 10ቱን ትእዛዛት ከቅድመ-አባቶቹ ከእነ መልከጻዲቅ፣ ኢትዮጵ እና

የዮቶርአብ ጥንታዊ አስተምህሮና ስርአት ጋራ እያገናኘና እያስማማ አስተማረ፡፡

ኢትዮጲስ ከሰባት ሚስቶቹ ሃምሳ ልጆች አፍርቷል፡፡ እነሱም አሥራ ሦስቱ ንጉሦችና ንግሥቶች ሆነዋል፡፡ አንጋፋው ልጁ ኤልካኖ አባቱ ሲሞት አልጋውን ወርሶ የኢትዮጵያ፣ የአረቢያ፣ የኑቢያ፣ የግብፅና ሰሜን አፍሪቃ ንጉሠነገሥት ሆኗል፡፡ ኤልካኖ አስርቱ ትእዛዛትን በማክበር እንደ መልከጸዲቅ እንደ ቅድመ-አባቶቹ እሱም በክህነት አገልግሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ሳባ የተባለውን ከተማ ቆርቁሯል፡፡ በእዚህ ከታማም ውስጥ አያሌ ነገሥታት እያንዳንዳቸው ለ10 ዐመታት ነግሠዋል፡፡ አዝሚና የተባለችው እናትዋ ‹‹ኢትያኤል›› ስትል የሰየመቻት የንግሥተ-ሳባ አያት አጋቦና በዚሁ ከተማ ለ16 ዐመታት ነግሦበት ነበር፡፡ ኢትያኤልም፣ (ንግሥተ-ሳባም ማለት ነው) ይህንኑ ከተማ፣ ኢትዮጵያን፣ ግብጽን እና አረብያን ደርባ፣ ልጅዋ ምኒልክ ሰለሞን ዳዊት እስከሚተካት ድረስ ለ51 ዐመታት ገዝታለች፡፡

ይህ የሳባ ከተማን፣ ከነገሡበት ሁሉ ነገሥታት እና ንግሥተ-ነገሥታት ኢትያኤል በመላው ዐለም የሳባ ንግሥት ተብላ ገንናበታለች፡፡ ከዘመናት በኋላ ይቺ የሳባ ከተማ በመሬት ነውጥ ተሰባብራ ሰምጣ ጠፍታለች፡፡ ከሳባ ከተማ ተነስተው ቀይ ባህርን አቋርጠው የመንን ቅኝ የገዙ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ

የቀረችውን ከተማቸውን ለማስታወስ ሳባ የተባለች ሌላ ከተማ በየመን ቆርቁረው ነበር፡፡ የመን በነበረችው የሳባ ከተማ የኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የመናውያንም ሳባውያን ተብለው ነበር፡፡ ይህን ምክንያት በማድረግ አንዳንድ የተሳሳቱ ምሁራን ንግሥተ-ሳባ (ኢትያኤል) የየመኑ ሳባ ንግሥት እንጂ የኢትዮጵያ ንግሥት አልነበረችም ይላሉ፡፡ ስለዚህም የዐረብ ንግሥት ሊያደርጓት ይፍጨረጨራሉ፡፡ ይህ ግን ትልቅ ቅጥፈት ነው፡፡ በመጀመሪያ ነገር፣ ዐረቦች (የመኖች) በታሪክ የተመዘገበች ራሳቸው የሾሟት ንግሥት የለችም፡፡ የኛ ተቃራኒ ሆነው አረቦች ሴትን ስለሚንቁና በሴት ልጅ ከወንድ እኩልነት ስለማያምኑ፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ሴትን ከወንድ ሳናሳንስ ከጥንት ጀምሮ አንግሠናል፡፡ ከንግሥት ሳባ በፊት ሰባት መቶ ዐመታት አስቀድመን (የዛሬ 3700 ዐመት ማለት ነው) ሴትን አንግሠን ነበር፡፡ ከአጼ አክሱማይ (የዛሬ 2850 ዐመት) ጀምሮ ወንዶቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሴቶች ዘመዶቻቸውን ሕንደኬ በሚል ማእረግ በአረቢያ፣ በኑብያ፣ በግብጽ እና ሊብያ ላይ ለአያሌ ምዕተዐመታት 17 ሴቶች ነግሠዋል፡፡ የስማቸው ዝርዝር በእጃችን ይገኛል፡፡ ንግሥተ-ሳባም ቢልቂስ የተባለችውን ትውልደ ኢትዮጵያ ዘመዷን በየመን አንግሣ ነበር፡፡ በእዚህ ምክንያት አንዳንድ ታሪክ አናውቃለን የሚሉ፣ ወይም የሀገራችውን ክብር የሚያጣጥሉ ሰዎች ሁለቱን ሴቶች አምታተው ወይም ሆነ ብለው ቢልቅስን

በአረቦች የተሸመች ዘረ-አረብ አድርገው፣ ቢልቂስ ማለት ሳባ ነች ይላሉ። የስህተት ስህተት ነው። ሀቁ ግን የቢልቂስ ሹዋሚዋና አለቃዋ ንግሥተነገሥቷ ኢትያኤል ንግሥተ-ሳባ ነበረች።

ልእለ-ሰብዕ የሆነው አጼ እስያኤልና ንግሥተ-ሳባ

የዚህ መዕሐፍ ደራሲ እንደሚያምነው የኤልካኖ ወንድ ልጅ አሴ (አጼም ይባላል)፣ ስመ-ክህነቱ እስያኤል የተባለው፣ በምድር ላይ ከኖሩ ንጉሠነገሥታት ሁሉ የላቀው ነበር። በሰው ልጆች ፊንጠዝያ ላእለ-ሰብ (superman) ወይም ዲቦ-ሰብእ ተብሎ ሊታሰብ የሚችል እሱ ብቻ ነው። የተወለደው የዛሬ 3480 ዓመታት ገደማ ነው። እሴ እንደ ነገሥታት አባቶቹ ነቢይና ካህን ከመሆኑም በላይ፣ የመድብለ ዘር ወይም መሀንዲሰ-ዘር ‹‹ጀኔቲክ ኢንጂነር›› ፣ የእፅዋት ተመራማሪና የማእድናት አዋቂ ነበር። ደፋርና በጣም ብርቱ ነበር። በወጣትነቱ ተፈጥሮን ለማጥናትና ለመመርመር ያለፍርሀት ብቻውን ከዱር ኖሯል። ጉልበቱ ኃይለኛ በመሆኑ ከሰው ልጆች ትግል የሚገጥመው አጥቶ፣ እንደሚባክለው ቁጥራቸው 150 ከሚደርስ አንበሶች ጋራ አንድ ባንድ ተፋልሞ ገድሎ የሰውና የዱር አውሬዎች ንጉሥ ነኝ፣ ሲል

አውጆ ነበር። ዛሬ የምትውለበለበውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓልማ ፈልስፎ ሁሉም ንጉሦችና ንጉሠነገሥታት በፈረሶቻቸው በሰረገላዎቻቸውና በቤተመንግሥታቸው ላይ እንዲያውለበልቡ ያዘዘው እሱ ነው። አያሌ የእንቆቅልሽ መጻህፍትንም ደርሶ ነበር። ሁሉም ልዑላን በጉራ የመግዛት እድል እንዲያገኙ የንጉሥን የስልጣን ዘመን በአስር ዓመታት ብቻ ገድቦ ራሱ የደነገገውን ህግ በራሱም ላይ አውሎ ለ10 ዐመታት የሳባ ክተማ ንጉሥ ሆኖ ወቅቱ ሲደርስ ለቆ ቆይቶ የአስተዳደር ብልሽት ሲያይ እንደ ገና ተመልሶ ዙፋን ላይ ወጥቶአል። ለብዙ ዘመናት በንጉሠ-ነገሥትነት እና በካህንነት ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን የውጭ ሀገራት አስተዳድሮ በሽምግልናው ሰዐት ኢትያኤል የተባለችው ኮረዳዋ ንግሥተ-ሳባ እሱን በቂም በቀል ገድላው ነበር ዙፋኑን የወረሰችው፡ ፡ አጼ አስያኤል ተብሎም የሚታወቀው ይህ ዲበ-ኩሉ ሰው፣ ስነመንግሥትን፣ የፍትሐብሔር ህጋትንና የቤተመንግሥትን ሥነምግባር መመሪያ ዕፎ ሁሉም ይሰሙት ዘንድ በኢትዮጵያ ሀገራት ሁሉ አውጇል።

በተጨማሪ፣ ወጣት እንደሆኑ ለመቆየት የሚያስችሉ እድሜ ማራዘሚያ ሚስጥራትን አግኝቷል። በመድብለ ዘር ባለሞያነቱ (genetic engineer) ሥራዬ ብሎ ፈረሶችንና አህዮችን በማዳቀል ለመጀመሪ ጊዜ በቅሎን ያስገኘው እሱ ነውም

ተብሎአል። አያሌ ጥራጥሬዎችንና አበቦችን በማዳቀል አዳዲስ አዐሞት አበርክቷል። ከዚህም በተጨማሪ ጥንታዊውን ዓለም በግዛቱ ካጠቃለለ በኋላ ህዝቦቹ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ እንዲያባለቱ በማድረጉ ዛሬ የኢትዮጵያ ጎሳዎች በተለያዩ የቆዳ ቀለማት ደምቀው ውብ የጥበብ ውጤት መስለዋል። በዚህም ምክንያት፣ አንዲት ኢትዮጵያዊት እናት ከአንድ አባት የምትወልዳቸው ፍሬዎች በቆዳ ቀለማቸውና በጸጉራቸው ቀለም በለያዩ አይገርምም። እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ባለብዙ ቀለማት አበቦች ፊክተን የምንታይበት እውነታ ይኸው ነው።

እሴ በትውልዱ ዮቶርአብ ቅምአያቱ ነበር። ዮቶርአብ አባብሄርን ሲወልድ፣ አባብሄር ኢትዮጲስን፣ ኢትዮጲስ ኤልካኖን፣ ኤልካኖ በተራው እሴን ይወልዳል። የኢትዮጲስ ሚስት ሩት አማን፣ ማለትም የእሴ አያት አይሁዳዊት ነበረች።

አጼ፣ በተለያዩ ድንጋዮች ይዘት ላይ ተመራምሮ ስለ ድንጋይዎች ባህሪና ተግባር መጽሀፍ ጽፎአል። በእርሱ አስተሳሰብ ድንጋዮች ህመምን የመፈወስና ህዋሳትን የማደስ ኃይል አላቸው። ሰለዚህ በዙርያው የተለያዩ ድንጋዮች ያኖር ነበር። ንጹህ ውሃ መጠጣትም እድሜ ያረዝማል በማለት የሚጠጣው ውሀ በተራሮች ላይ ከበቀሉ ከልዩ ዛፎች ስር ከሚፈልቅ ምንጭ ነበር።

እስያንና መካከለኛውን ምስራቅ ካስገበረ በሁዋላ ኢየሩሳሌም በታላቁ የዘር ግንዱ በሳሌም ንጉሥ በመልከጸዲቅ መገንባቷ ምናልባት ትዝ ብሎት ይሆናል እስዋንም ሊያጠቃልል ወደዚያው ሲያመራ እግዚአብሔር በእሳት ሰረገላ ዐየር ላይ ተክሰቶ አስቱሞት ኢየሩሳሌም ለሰላሙ ንጉሥ (ለመሲሁ) የተጠበቀች ስፍራ መሆኗን አሳሰበው። አጼም (እሴም)፣ ድንገት ለተከሰተለት ሕያው እግዚአብሔር፣ ለሰላሙ ንጉሥ የተለያዩ ገጸበረከቶችን አቅርቦለት ሊሰግድለት እንደሚፈልግ ገልጾለት የት እንደሚያገኘው ጠየቀው። እሱ እንዲህ የአለው ቅድመ-አባቱ ኢትዮጵ ገዳ ሰጥቻችሁ ለመሲሁ ስገዱለት ብሎ ለተወላጆቹ የመከረውን በማስታወስ ነበር። እግዚአብሄርም በአነጋገሩ ተደስቶ፣ መሲሁ የሚመጣው በአንተ ዘመን አይደለም፤ ሆኖም ለመሲሁ መልካም ለማድረግ ስለተመኘህ፣ አባቶችህ ኖሮአቸው የማያውቀውን ረጅም ዕድሜ ከተጎናጸፍከው ጥበብ ጋራ እዳርግሃለሁ፤ አለው። በዚህ ምክንያት፣ እድሜ ጠግቦ (ገድሉ እንደሚያወሳው፣ እንደ እነ አዳም እና ማቶሳላ ከ 480 ዐመት በላይ ኖሮአል። በመጨረሻ ግን ንጉሠነገሥትነትና መኖር ታክቶት እንዲሞት ጸልዮ ሞቱን በሚጠባበቅበት ጊዜ ነበር ኢትያኤል ንግሥተ-ሳባ የገደለችው።

እግዚአብሄርም እሱን (አጼን) በዛው በጋዛ ባገኘው በዚሁ ወቅት ‹‹እሴ›› የተባለውን ስሙን ወደ እስያኤል ለውጦለት

በመሲሁ ፋንታ ነብዩ ሳሙኤልን እንዲገናኝ መከረው። ስለሆነም እሴ (አጼ) ሳሙኤልን ጋዛ ውስጥ አገኘው። ሁለቱ ወዳጆች ሆነውም ለአጭር ጊዜ አብረው ከረሙ። በመሰንበቻው ማክተሚያ ለወዳጅነታቸው መታሰቢያ እንዲሆንላቸው አብረው በቆዩበት ቦታ ላይ አንድ ድንጋይ አኖሩ። ከዚያም እግዚአብሔር እስያኤል ብሎ የሰየመው አጼ ወደ እስያ ዘምቶ ዘመኑ ያፈራቸውን መሣርያዎች ዘምዘው አንድ ሚሊዎን የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ኃይል አሠራሩን የራሱ በማድረግ አካባቢውን በስመ-ክህነቱ ‹‹እስያ›› አለው። ለተለያዩ ክፍለ ግዛቶችም ንጉሦች ሾመ፤ እርሱ ንጉሠ ነገሥት መሆኑንም ለህዝቡ አወጀ። እስያኤል በግዛቱ ያካለለው ሰፋፊ እስከ ዛሬ እስያ ይባላል። አህጉራቸው በምድር ላይ ከነበሩ ንጉሠነገሥታት ሁሉ በሚልቀው በኢትዮጵያዊው ንጉሠነገሥት ስም መጠራቱን እስያውያን አንዳችም ፍንጭ አለመጨበጣቸው ያሳዝናል። አጼም፣ ደሞም እሴም ስለሚባል፣ የቅዱስ ዳዊትም አባት ‹‹እሴ›› ተብሎ የተሰየመው ይህን ትልቅ ንጉሠነገሥት ለማስታውስ ይመስላል። ምክንያቱም፣ ሰማይ የምትባለዋ የእሴ እናት የቅዱስ ዳዊት አያት፣ እንደ ቅዱስ ዳዊት እናት እንደ አዬል እና እንደ ቅድመአያቱ እንደ ሩት፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነበረችና። ኃያሉን የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት እሴን (አጼን) ለማስታወስ ልዩዋን የዳዊትን አባት ምናልባት እሴ ብላዋለች። ስለንጉሥ

ዳዊት የእናት ዘር ግንድ ሳወሳ ወደፊት በዚሁ መጽሀፍ ዝርዝሩን እገልጻለሁ፡፡

ቁጥራቸው 150 ከሚደርሱ አንበሳዎች ጋራ ተፋልሞ በጉልበቱ የገደለውና ጥንታዊውን ዓለም ድል የመታው ንጉሠ ነገሥት አጼ (እሴ) ዲበኩሉው ሰው፣ እናቷ ኢትያኤል ብላ በሰየመቻት ከጊዜ በኋላም ቅድመ አያቷ ይገዛው በነበረና በወረሰችው ግዛቷ ስያሜ (ንግሥተ-ሳባ) ተብላ በዛን ጊዜ ዕድሜዋ ከ17 ዐመት በማይበልጠው ልጃገረድ እጅ ተገደለ፡፡ ድርጊቱ የተፈፀመው እንደሚከተለው ነው፡፡

ታሪኩ የሚጀምረው አዝሚና በምትባለው በኢትያኤል (በሁዋላ ንግሥተ-ሳባ) እናት ነው፡፡ እሴ (አጼ) 475 ዓመት ገደማ ሲሞላው በምድር ላይ መኖር ተሰላቸና እግዚአብሔር እንዲወስደው ጸለየ፡፡ እናም መንፈሳዊ ሽብሸባ የሚያሳዩና ዝማሬ የሚያወርዱ እውቅ ባለሙያዎች በዙርያው አሰባሰበ፡፡ እዚህ ላይ አንባቢው አጼ እስያኤል ያን ያህል ዘመን እንዴት ኖረ ብሎ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ግን እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ የሰጣቸው አዳም፣ ማቱሳላ እና ሌሎች ሰዎች ከዛም በላይ እንደኖሩ አውግቶናል፡፡ የቅዱስ ላሊበላ ወዳጅ የነበሩት አቡነ ገብረመንፈስቅዱስም ከ400 ዐመታት በላይ እንደኖሩ ይነገራል፡፡

ለማንኛውም በታሪክ ነገሥት ኢትዮጵያ ውስጥ ታላቁ ንጉሠነገሥት አጼ እስያኤል 480 ዓመታት እንደኖረ ተዘግቧል፡፡

በእድሜ ለገፋው ንጉሠነገሥት መዘምራን ከነበሩት እውቅ ቆነጃጅት ኮረዶች መሃል የኢትያኤል ንግሥተ-ሳባ እናት አዝሚና እንዲ ስትሆን ድንግል ነበረች፡፡ አብሯት ከሚዘምር አንድ ጃንደረባ ጋር በፍቅር ተጠመደች፡፡ ሲሳሳሙና በብልቶቻቸው ሲተሻሹ ዘር ተቀብላ ጸነሰች፡፡ አዝሚና ሴት ልጅ ወልዳ ኢትያኤል አለቻት፡፡ ትርጉሙም በሱባ ቋንቋ ‹‹የእግዚያብሔር ስጦታ›› ማለት ሲሆን እንዲያ በማለት የሰየመቻት፣ ኢትኤል ይባል የነበረውን ኢትዮጵን መዘከሯ ይሆናል፡፡ በቤተመንግሥቱ እንዲያ የመሰለ ክብር-ነክ እና አስነዋሪ ተግባር መፈጸሙን እሴ ሲሰማ፣ በቁጣ ነዶ ያለርህራሄ ወድያውኑ አዝሚና ጃንደረባው እና ህጻንዋ ኢትያኤል በሞት እንዲቀጡ አዘዘ፡፡ ደግነቱ ፈጻሚዎቹ የራሷ የአዝሚና ነገዶች የአዘቦ ተወላጆች ሆኑ፡፡ ያልታደለች ሌላ ህጻን ሰርቀው በ ኢትያኤል ፈንታ ተክተው፣ ኢትያኤልን የሣባ ንጉሥ ለነበረው ቅድም-አያትዋ ለአጋቦና አስረከብዋት፡፡ እናትዋ አዝሚና እና ጃንደረባው አባትዋ ግን ተገደሉ፡፡ ኢትያኤልን፣ አያትዋ ማንነትዋን ደብቆ አሳደጋት፡፡

ኢትያኤል እያደገች ስትሄድ ቁርጥ እናቷን ከመምሰሏም በላይ በእናቷ ሞያ የተካነች ሆነች፡፡ ስለዚህ፣ እሴ ማንነትዋን

ሳያውቅ ከሱ ዘማሪዎች አንዱ ሆነች። የሱ ዘማሪ ከመሆኗ በተጨማሪ በእርጅና ዘመኑ የግሉ ተንከባካቢ ሞግዚት ለመሆን በቃች። ሽማግሌው ንጉሥ ግን እስከ መጨረሻው ድረስ አገልጋዩ ኢትያኤል መሆኗን አላወቀም። እርሷ ግን ልትበቀለው አመቺ ጊዜ ትጠብቅ ነበር። እናም ጊዜው ሲመቻችላት ደክሞት አሸልቦት አግኝታው ገደለችው። ገድላውም የእናትና አባትዋን ደም ተበቀለችው። የነገሥታት ዝርያነቷን መሰረት በማድረግ የአልጋው ወራሽ ሆነች። ይህን ድርጊቷን የኢትዮጵያ ህዘብ አውግዞ የርስበርስ ግጭት ተከሰተ። የሆነ ሆኖ በመጨረሻ ላይ ድንግልናዋን ጠብቃ ያለ ባል እንድትነግሥ ተፈቅዶላት በ17 ዐመት ዕድሜዋ የንሥተነገሥታትነት ዘውድ ደፋች። በአፍሪቃ አረቢያና እስያ እስያኤል ያጠቃለለውን ግዛቱን ሁሉ ወረሰች።

ይሁን እንጂ በእግዚብሔር ተቀብቶ የነገሠውን ታላቅ አረጋዊ ሰው በመግደሏ ክፉኛ ተጸጸተች። እግዚአብሔር ይቅር ይላት ዘንድ እሴ መካነመቃብር ላይ ለአንድ ሳምንት እምባዋን አፈሰሰች። እግዚአብሔርም በራዕይ ተገልጾላት እሴ ለረጅም ዘመን መኖሩ አሰልችቶት ለመሞት ይፀልይ እንደነበር ነግሯት፣ ወላጆችዋንም መግደሉን አስታውሶአት፣ ምህረቱን አወረደላት። እርሷም ለሞቱ ሰበብ ብቻ እንደሆነች አመለከታት። እርሱ ግን ወላጆቿን ከመግደል በላይ፣ ለእርሷም አልተመለሰም ነበርና።

በተጨማሪም እግዚአብሔር እርሷን በህይወት ያቆየበት የራሱ አትድም ነበረው። ያም እቅዱ እርሷን ከንጉሥ ዳዊት ልጅ፣ ከሰሎሞ ከንጉሥ ሰለሞን ጋር ማገናኘት ነበር። ከጊዜ በኋላም ከንጉሥ ሰለሞን ጋር ተገናኝታና ምኒልክ የሚባል ወንድ ልጅ አፍርታለች። ልጅዋም ጎረምሳ ሳለ ታቦተጽዮንን በ40,000 አስራኤላውያን አሳጅቦ ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶ የሰለሞንን ሰርወመንግሥት መሰረተ።

ንግሥተ-ሳባ እና ንጉሥ ሰለሞን

መፅሃፍ ቅዱስ ስለ ኢትያኤል ንግሥተ-ሳባ እንዲህ ይላል፦

‹‹የሣባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በጥልቅ ጥያቄዎች ትፈትነው ዘንድ መጣች። በግመሎችም ላይ ሽቱና እጅግ ብዙ ወርቅ፣ የከበረም እንቁ አስጭና ከታላቅ ጓዝ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ገባች። ወደ ሰለሞንም በመጣች ጊዜ በልቧ ያለውን ሁሉ አጫወተችው። ሰለሞንም የጠየቀችውን ሁሉ ፈታላት።

ለፈታላት ያልቻለውና ከንጉሡ የተሰወረ ነገር አልነበረም።

‹‹የሣባም ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ሁሉ ሠርቶትም የነበረውን ቤት፣ የማእዱንም መብል፣ የብላቴኖቹንም አቀማመጥ፣ የሎሌዎቹንም አሠራር፣ አለባበሳቸውንም፣ ጠጅ አሳላፊዎቹንም፣ በእግዚያብሔርም ቤት የሚያደርገውን መስዋእትነት ባየች ጊዜ ነፍስ አልቀረላትም።››

ንጉሡንም አለችው፦ ‹ስለነገርህና ስለ ጥበብህ፣ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና ሁሉ እውነት ነው። እኔም መጥቼ በዐይኔ አስካይህ ድረስ የነገሩኝን አላመንኩም ነበር። ጥበብህና ሥራህ ከሰማሁት ዝና ይበጣል።

‹‹‹በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ፣ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና እነዚህ ባሪያዎችህ ምሥጉኖች ናቸው። አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን። እግዚአብሄር እስራኤልን ለዘላለም ወዶታልና ስለዚህ ፀድቅና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጎ አስነሳህ፤ ከዚያ ወዲህ አልመጣም ነበር።›››

‹‹ለንጉሡም ሙቶ ሃያ መክሊት ወርቅ፤ እጅግም ብዙ ሽቱ፤ የከበረም እንቁ ሰጠችው። ‹‹የሳባ ንግሥት ለንጉሱ ለሰለሞን እንደሰጠችው ያለ የሽቱ ብዛት ከዚያ ወዲያ አልመጣም ነበር።... ንጉሥ ሰለሞንም በገዛ እጁ ከሰጣት ሌላ የወደደችውን ሁሉ ከእርሱም የለመነችውንም ሁሉ ለሳባ ንግሥት ሰጣት። እርሷም ተመልሳ ከባሪያዎቿ ጋር ወደ ምድርዋ ሄደች።›› (መጽሀፈ ነገሥት ቀዳማዊ፣ 10፡ 1-13)

እየሱስ ክርስቶስም እንደ እስራኤል መሲህ አንቀበልህም ባሉት ወገኖቹ በእስራኤላውያ ምክንያት እንዲህ ሲል ይመሰክርላታል፡-

‹‹የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለች፣ እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ።››(የሉቃስ ወንጌል 11፡10)

አንዳንድ የሀገራቸውን ክብር ዝቅ የሚያደርጉ ምሁር-ተብዬዎች፣ ኢትያኤል ንግሥተ-ሳባ ወንድ ፍለጋ ወደ ንጉሥ ሰለሞን ዘንድ እንደተጓዘች ይናገራሉ። ይሄ እስዋን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም መስደብ ነው። ንግሥተ-ሳባ ብዙ ስጦታ ይዛ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደችበት ዋነኛው ምክንያት የመልከጸዲቅ እና የኢትዮጵ ተወላጆችና ኢትዮጵ ይመጣል ብለው ለአንድ ሺህ አመታት የጠበቁትን ‹‹የሰላሙን ንጉሥ›› የእስራኤልን መሲህ ተሸቀዳድማ አግኝታ፣ የጋዳው የመጀመርያ ሰፌ ሆና ለመባረክ

ነበር። ሰለሞን ጠቢብ ነው ሲባል ስለ እሱ ዝናም በጣም በመሰማቷ እና የጥበብ አፍቃሪም በመሆኗ የእሱን ጥበበኝነት ለማጣራትም በዘዴ እና በእንቆቅልሽ ከፈተነችው በኋላ እሱ የእስራኤል መሲህ እንዳልሆነና እራሱም መሲሁን ገና እንደሚጠብቀው ተረዳች።

ንግሠተ-ሳባ ወደ እርሱ የሄደችው ሁለት ሴቶችን አስከትላ ነበር። አንደኛዋ የግል ዘመድዋ የሆነች ሳሆይ የተባለች የአገው፣ የራያና ቆቦ ንግሥት ስትሆን፣ ሁለተኛዋ ቢልቂስ የተባለችው አላይ ስሟ የተጠቀሰው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሴት ነበረች። ቢልቂስ፣ አዜብ ከምትባል (ንግሥተ-ሳባ አይደለችም) ኢትዮጵያዊት እና በወቅቱ የየመን (በዛን ጊዜ የመን ናግራን ነበር የምትባል) ንጉሥ ከነበር ሰው በየመን የተወለደች ልእልት ነበረች። በሆነ ምክንያት ባልዋን ገድላ ከየመን ሸሽታ፣ የንግሥት ኢትያኤል ንግሥተ-ሳባ ጥገኛ ሆና በኢትዮጵያ ትኖር ነበር።

ሦስቱ ሴቶች ኢየሩሳሌም ከደረሱ በኋላ ንጉሥ ሰሞን ንግሥተ-ሳባን በማእረግዋ ልክ ሚስቱ፣ ሁለቱን ሴቶችም እንደ ደረጃቸው እቁባቶቹ አደረጋቸው። ከዚህም የተነሳ፣ ከንግሥተ-ሳባ፣ ምኒልክ፣ ከራያና ቆቦ እና አገው፣ ንግሥት ሳሆይ ዜጋዉ የተባሉ ልጆች ወለደ። ምኒልክ በ18 ዐመቱ በነገሠ ጊዜ፣ እናቱ ዜጋዉ

ያለችውን ወንድሙን ‹‹ዛጉዬ›› ሲል ሰይሞ እንደ እናቱ የራያና ቆቦ እና የአገው ንጉሥ አድርጎ አነገሠው።

ኢትያኤል እና ሳሆይ ወደ አገራቸው ሲመለሱ፣ ቢልቂስ ኢትዮጵያ ውስጥ ጉዳይ ስላልነበራት እዛው ኢየሩሳሌም ቀረች። በሁዋላ ግን የየመኑ ንጉሥ የቢልቂስ አባት ስለሞተ፣ ኢትያኤል ቢልቂስን ከኢየሩሳሌም አስወስዳ በአጋዚያን ጦርሰራዊት ኃይል የበታችዋና የየመን እንደራሴዋ አድርጋ በየመን ላይ አነገሠቻት። በዚህ ምክንያት፣ ዘመናት ካለፉ በሁዋላ አረቦች ቢልቂስን ከኢትያኤል ንግሠተ-ሳባ ጋራ በማምታታት ቢልቂስ ኢትያኤል ንግሠተ-ሳባ ናት እያሉ ያወሩ ጀመር። አሁንም ድረስ ያወራሉ። ይባስ ብለው አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ‹‹የታሪክ ምሁራን›› ይህን ስህተት እየሠሩ የሁለቱን ሴቶች ማንነት ያደበላልቃሉ። እስከነ አካቴውም ንግሥተ-ሳባ የየመን እንጂ የኢትዮጵያ ንግሥት አልነበረችም ይላሉ። ንግሥተ-ሳባ የኢትዮጵያ ንግሥት ሆና፣ ከንጉሥ ሰለሞን ምኒልክ የሚባል ልጅ ካልወለደች ልጅዋ ቀዳማዊ ምኒልክ እንዴት ኢትዮጵያ ውስጥ የሰለሞንን ስርወመንግሥት ሊመሰርት ቻለ? አባቱ ሰለሞን፣ እናቱ ኢትያኤል ካልሆነች፣ አባቱና እናቱ ማን ናቸው? ለ3000 ዐመታት በኢትዮጵያ የሰለሞን ስርወመንግሥት ተወካይ ነን ብለው የነገሡት 225 ንጉሠ ነገሥታትስ እንዴት ኢትዮጵያ ውስጥ ሊነግሡ ቻሉ? ቤተ

እስራኤሎች እና አጋዚያንስ እንዴት ኢትዮጵያ ውስጥ ሊገኙ ቻሉ? ቀዳማዊ ምኒልክስ ታቦተ-ጽዮንን እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ሊያመጣ ቻለ? ታቦቱን እሱ አላመጣም ቢባልም እንኳን በየአንዳንዱ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ውስጥስ በሌላው የዐለም አብያተክርስትያናት ውስጥ የሌሉ እስራኤላዊ ጽላቶች ሊኖሩ እንደምን ቻሉ? የመን ውስጥስ ለምን ይህ ሁሉ ነገርና ሰለሞናዊ ስርወመንግሥት አልተከሰቱም? እነዚህ ኢትያኤል ንግሥተ-ሳባን ወይ ለአረብ ሊድርዋት አለዚያም እስከነአካቴው ሀልውናዋን ሊክዱት የሚፈልጉት ኢትዮጵያውያን ‹‹የታሪክ ምሁራን›› ለእነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ የላቸውም። ከአላቸው መልሱን ሊሰጡ ይገባል። እኛ ግን፣ ሌላኛው ማስረጃ ሁሉ ቢቀር፣ የዘሯን ሀረግ በታሪክ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ውስጥ ተጽፎ አግኝተነዋል። ከፍ ሲል ከላይ ከኢትዮጵ፣ ዝቅ ሲል ከአያቷ የሳባ ንጉሥ ከአጋቦና እንደወረደች ዘረ-ፋራዋን አግኝተነዋል። እሱንም ማንም ሊበጥሰው በማይችለው የዘር ሀረግዋ ከዚህ በታች እናረጋግጣለን።

ቀጥሎ የተዘረዘሩት የኢትዮጵ ሥርወ-መንግሥትን ለአንድ ሺ ዓመት የወከሉ ነገሥታት እና ንግሥታት ናቸው። በመጨረሻው ላይ የኢትያኤል ንግሥተ-ሳባ ስም ይገኛል።

የንጉሡ/ንግሥትዋ/ ስም	ዘመነ-ንግሥና /በዓመት/
ኢትዮጵ	98
አቲባ	49
አዜብ	32
ሞሪ-ሰቢ	77
ልብና	44
መሊክ-መለክ	24
ጋዝያ	48
አድያም	83
ታንዛን	88

ዮቶር-አብ /የሙሴ አማት/	22
አባ-በሐር (የሱ ልጅ)	10
ኢትዮጵስ	10
ኤልካኖ	25
አጲ/አሴ/	10
ታምሪያ	10
ሸምያ	10
አክናሁስ	10
ኩሳዮጲ	10
ቦኑ-ሰንካ	10
አሚን	10
አሪፊሪ	10

ዮጲዮሪ	10
አሞር	10
ብሌና (ንግሥት)	10
ዘግዱር	10
ሄርሂተር	10
አንጋቦ	10
አጋቦስ	130
ኩርፋን	55
ሰርፌ	82
አክላ	80
ጽርስቅላ (ንግሥት)	40
አቅጃቦ	50

አጋቦና (የንግሥተሳባ አያት)	16
ኢትያኤል(ማክዳ፣ንግሥተ ሳባ)	51

ስለ ኢትያኤል ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊነት እና እውንነት አላይ ከሰፈረው የዘር ሀረግዋ በላይ ምን ማስረጃ ይገኛል? ያህንንስ እውነት በምን ውሸት መደምሰስ ይቻላል? የኢትያኤል አባትዋ በነገሥታቱ ሀረግ ውስጥ ያልተጠቀሰው ንጉሥ ካለመሆኑም በላይ በዝቅተኛ ደረጃ ያለ ጃንደረባ በመሆኑ ነበር። ስለዚህ፣ እሷ ስትወለድ የሳባ ንጉሥ የነበረው የአያቷ የአጋቦና ስም ብቻ ተዘግቧል። ይህም ሁኔታ፣ ስለ ልዕልት እናትዋ አዘሚና እና ስሙ ስለ አልታወቀው ጃንደረባ አባቷ፣ እንዲሁም ስለ አወላለዷ የተተረከው ሁሉ እውነት መሆኑን ያረጋግጣል። አባትዋ ትልቅ ሰው ቢሆን ኖሮ ስሙን እናውቀው ነበር። ከዚህ ሁሉ በላይ፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት ቤተሰብ ባትሆን ኖሮ በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ በምንም ተዐምር አትነግሥም ነበር። ስለዚህ ንግሥተ ነገሥታት ኢትያኤል ሳባ በእርግጥ ኢትዮጵያዊ ነበረች።

ስለ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ታሪክ የሚያወሳው መጽሃፍ ክብረ-ነገሥት የሰለሞንና የሳባን አልጋ መጋራት የሚገልጽበት የራሱ መንገድ አለው። እኔ በዝርዝር አልገባበትም።

ባጭሩ ሰለሞን ኢትያኤልን ለማግኘት ጥበቡን ተግባራዊ አድርጎበታል። አጼ እስያኤልን ንግሥተ-ሳባ ገድላ በነገሠች ጊዜ እድሜ ልኳን በድንግልናዋ ጸንታ እንደምትቆይ ለኢትዮጵያዉያን ቃል ገብታ ስለነበር ድንግልናዋን ለመግሰስ ሰለሞን ዘደ ፈጠረ። ለስንበት ግብጣዋ አብሳዮቹ ቅመምና ጨው የበዛበት ምግብ እንዲያዘጋጁ ያዛል። ኢትያኤል ወደ መኝታቤትዋ ከመግባቷ በፊት ያለእርሱ ፈቃድ አንዳችም ነገር እንዳታደርግ ቃል ያስገባትና ቃሏን ብታፈርስ አብሯት ለመተኛት እንድትስማማ ይዋዋላትና ትስማማለች። የበላችው ምግብ ቅመም የበዛበት ስለነበር እኩለ ለሊት ላይ ከባድ ጥማት ይቀሰቅሳታል። ሰለሞን ሆን ብሎ ከአልጋዋ አጠገብ ቀዝቃዛ ውሃ አኑሯል። ትጎነጫለች። ሰለሞን እጅ ከፍንጅ ይዟት ፍትወቱን ያረካና ተውኔቱ በምኒሊክ መፀነስ ይቋጫል። ይልቅየው ይዜ ተረት ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ኢትያኤል በሰለሞን አድናቆት ነፍስዋ ስለወጣ ያለምንም ጣጣ ፍቃዱን የማትፈጽምበት ምክንያት አልነበረም።

ኢትያኤል፣ ስለ ውልደቷ፣ እንዴት ከሞት እንደተረፈች፣ ለእናትዋ ብቸኛ ስለመሆንዋ እና እንዴት ዘውድ ለመጫን እንደበቃች ለሰለሞን አውግታዋለች። ኢትዮጵያውያን ያነሳሷትም፣ አንድ ወንድ እሷን አግብቶ፣ እሷን በማግባቱ ተኩራርቶ በፊላጭ ቆራጭነት እንዳይጨቁኗቸው ማንነም ሳታገባ በድንግልናዋ ፀንታ

ለመኖር ቃል መግባትዋንም ገልጻለት ነበር። እሱ ግን ለዚህ ደንታ ሳያሰጠው አግብቶአታል። ያደረገውን ሁሉ ከአደረገ በኋላ፣ የእሱ እናት ቤርሳቤህ ኩሻዊ ጥቁር ስለነበረች፣ የአባቱ እናት ኢትዮጵያዊትዋ ሃብሌም (አዬል) እንዲሁ አፍሪካዊ በመሆንዋ፣ ፊቱን እንደ ኢትያኤል ጥቁር አድርጎ ሁኔታዋን ከበግ ለምድ ቡተበጀ በጥቁር ድንኳን እና በራሱ መጋረጃ አስመስሎ ህያው ቅኔ ተቀኝቶላታል። እንዲህ ሲል፦

‹‹እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ እኔ ጥቁር ነኝ፤ እንደ ቄዳር ድንኳኖች እንደ ሰለሞንም መጋረጃዎች ፀሀይ መልኬን አነሰሎታልና ጥቁር ስለሆንኩ አትናቁኝ።›› (መኃልዬ መኃልይ ዘ ሰለሞን 1፡5)

ከዚያም ስለድንግልናዋ ሲያጣቅስ ወገኖቿ በአደራ ያስረከቧትን የወይን ተክል እንዳስነጠቀች አስመስሎ እንዲህ ይላል፦

‹‹የእናቴ ልጆች ተጣሉኝ፤ የወይን ቦታዎችንም ጠባቂ አደረጉኝ። ነገርግን የእኔን ወይን የወይን ቦታ አልጠበቅሁም።›› (መኃልዬ መኃልይ ዘሰለሞን 2)

ጠቢቡ ንጉሥ ኢየሩሳሌም ውስጥ ለንግሥት ሳባ መሬት ሰዮታል። እርሷም ማረፊያዋ እንዲሆናት በማሰብ ግምበኞች

ቀጥሮ ቤተ መንግሥት እንዲያሳንፅላት 120 የወርቅ መክሊቶች አበርክታለታለች። ቤተመንግስቱም ተገንብቶ አልቆ ለአያሌ ዓመታት የኢትዮጵያውያን እንግዶች ማረፊያ ሆኗል። ስፍራው በዝግባ፣ዋርካና የወይራ ዛፎች የተሸፈነ ነበር። የንግሥ-ሳባ ቅድመ-አባት የኢየሩሳሌም መስራች መልከጸዲቅ እና ልጆቹ ከ1000 ዐመታት አስቀድሞ በዚሁ ቦታ የሚቃጠል መስዋዕት እያደረጉ እግዚአብሄርን ያመልኩ ነበር። የሚያስደምመው ነገር እየሱስ ተሰቅሎ የሰው ልጆች መድህን ይሆን ዘንድ መስዋዕት የሆነው እዚሁ ነበር። ቀሬና ይባላል። እላዩ ላይ ዛሬ በርካታ አብያተክርስቲያናት ተገንብተውባታል።

ሳባ ከሰለሞን ጋር የከረመችው ለሦስት ወራት ሲሆን፣ የፀነሰችለት ወንድ ልጅ በእድሜ ከፍ ሲል፣ ከብዙ አጃቢዎች ጋር እንደምትልክለት ቃል ገብታለት ተሰናበተችው።

ሳባ በርሃ አቋርጣ ወደ ኢትዮጵያ በምትመለስበት ሰዐት፣ ሰለሞን ሕልም ዐለመ። ፀሃይ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ቦግ እልም ስትልና ኢትያኤልን የብርሃን አምድ በየደረሰችበት ሲከተላት፣ ባረፈችበት ስፍራ ሁሉ የብርሀን ድንኳን ሆኖ ሲያጸድልላትና ሲያደምቅላት ተመለከተ። ሕልሙንም ሲተረጉመው የመንግሥቱ ዝናና ክብር ከሱ ተነጥሎ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ሽሽ ተገነዘበ። የእስራኤል አለኝታና ክብር የነበረችውም ታቦተ-ጽዮን ከእስራኤል

አዮ አፈተልካ እንዳመለጠችው ተረዳ። በመጓልይ መጓልይ ዖርሳኑም እንዲህ ሲል አንጎራጎረ፦

‹‹መዓዛዋም እንደ ከርቤና እንደ እጣን የሆነችው፣ ይህች ከምድረበዳ እንደ ጢስ ምሰሶ የወጣችው ማናት? እነሆ፣ የሰሎሞን አልጋ ናት፣ ከእስራኤል ኃያላን ስድሳ ኃያላን በዙሪያው ናቸው። በሌሊት ከሚወድቀው ፍርሃት የተነሳ፣ ሰው ሁሉ ሰይፉ በወገቡ አለ።››

‹‹ኃያላን›› በማለት የሚጠቅሳቸው፣ ልጁ ምኒልክ በሁዋላ አድጎ አባቱ ዘንድ ከርሞ ከእየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ዕላቱን ይዞ ሲመለስ የሚያጅቡትን 40,000 ነገደ እስራኤላውያን ወታደሮች፣ ካህናትና ዘማርያን ናቸው። ‹‹የሰሎሞን አልጋ›› የሚለውም ፍቺ ከኢትያኤል የተወለደው ልጁ የስርወ-መንግሥት ዙፋኑን በኢትዮጵያ እንደሚመሰርት ይተነብያል።

የኢትያኤልና የንጉሥ ሰለሞን ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ

ሳባ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰች ከአንድ ወር በኋላ ምኒልክን ወለደች። እርሱም በእርግጥ የሰሎሞንን ስርወ-መንግሥት በኢትዮጵያ መሰረተ። የሆነውም እንደሚከተለው ነው።

ምኒልክ 14 ዓመት ሲሞላው አባቱን ሊጠይቅ ወደ እስራኤል ሄደ። ቁርጥ እርሱኑ ይመስል ነበርና አባቱ ተደስቶ የሃብቱን ሩብ ሸለመው። ምኒልክ እናቱ ባሳነፀችው ቤተመንግሥት (በዚያን ጊዜ ግንባታው አልቆ ነበር) ለሦስት ዓመታት ቆይቶ የአይሁድን፣ ስነመንግሥት፣ ስነሀይማኖት፣ ስነምግባራት፣ ስነአምልኮ እና ልማዶች ተማረ። የልጁ የሚኒልክ እናት ኢትያኤል ዙፋን ላይ

አንደ አለች ቢያውቅም፣ ንጉሥ ሰሎሞን ሳዶቅ በተባለው ሊቀካህን አማካኝነት በአይሁድ ስርዐተ-ንግሥ ቅባቅዱስ አስቀብቶ በኢትዮጵያ ግዛቶች ሁሉ አነገሠው።

አባቱ ዘንድ ለ3 ዐመታት ቆይቶ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ ሊመለስ ሲል ንጉሥ ሰሎሞን ከሌዋውያን ቤተመንግሥት ባለሟሎች ወታደሮችና አገልጋዮች መሃል ምርጦቹን በአጃቢነት አሰለፈለት። የአጃቢዎቹ ቁጥር በድምሩ 40,000 ነበር። ከእነርሱም መሃል 12,000 ጥርት ያሉ ዐይሁዳውያን፣ 1,000 ወርቅና ብር አንጣሪዎች የሆኑ ኢያቡሳውያን እና 27,000 የእየሩሳሌምና የጋዛ ነዋሪዎች የነበሩ የዮቅጣን ነገዶች ነበሩ።

ክብረነገሥት እንደሚያወሳው፣ የምኒልክ ቆይታ በእየሩሳሌም ሲገባደድ፣ ወደ ኢትዮጵያ የተከተሉት ሌዋውያን፣ ንጉሥ ሰሎሞን ሳያውቅና ሳይፈቅድላቸው ዋናውን ፅላት እጃቸው አስገቡ። ድርጊታቸውን በደፈናው ለመግለፅ ያህል፣ ፅላቱን ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ማጓጓዝ የራሱ የእግዚያብሔር ፈቃድ ሆነ።

ለዚህም ምክንያቱ፣ እርሱነቱን ለመሆን ያበቃውን የእስራኤልን አምላክ ሰሎሞን ገሸሽ በማድረግ አያሌ ሚስቶችንና አቁባቶችን ከማናር አልፎ ተርፎ ለጣዖቶችና ባእድ አማልክት ጣያግደግና መስዋእት ማቅረብ መጀመሩ ነበር። ሰሎሞን ለፅላቱ

ማረፊያ ቀዳሚውን ቤተመቅደስ ሲያሳንፅ እንደ ቀደምት አባቶቹ፣ እርሱም ለአንድ አምላክ ብቻ ሊሰግድና ጽላቱ እሱ በሚያንጸው ቤተመቅደስ ውስጥ ሊኖር ከእግዚአብሔር ጋር በመዋዋሉና እግዚአብሄርም ይህ እንዲሆን በመፍቀዱ ነበር። ሆኖም የእስራኤልን አምላክ በመርሳቱና መሀላውን በማጠፉ፣ ፈጣሪው ከመቅደሱም ከእርሱም ራቀ። ፅላቱ ወደ ኢትዮጵያ እስከ መወሰዱ ድረስ፣ የት እንደሚገኝ፣ እንዴት እንደሚጠበቅ እና የት እንዳለ እንኩዋን ለማወቅ ደንታ አልነበረውም። ስለሆነም ያን በዐለም ላይ ከሉት እቃዎች ሁሉ ብርቅዬ እና የተቀደሰ የሆነውን ፅላት እግዚአብሔር ወደ ልጁ ምኒልክ ሊያስተላልፈውና ስርወ-መንግሥቱንም ከግዛቱ በእጅጉ በምትልቀው በኢትዮጵያ ሊተክል ፈቀደ።

ሰሎሞን የእስራኤልን አምላክ ዘንግቶ ለባእድ አማልእክት በመስገዱ ሌዋውያን ልባቸው በሃዘን ተሰብሮ ነበር። የቢንያም እና የአይሁድ ነገዶችም ከሌዋውያኖች ጎን ቆሙ። ስለሆነም እነዚህ ሶስት ነገዶች ግንባር ፈጥረው ሰሎሞንን ተቃወሙ፤ የፅላቱን ምስል ቤተመቅደስ አስገብተውም ዋናውን ወሰዱ። ከዚያም እንኳን ለእርሱ ለምኒልክም ሳይገልጹ፣ ከእየሩሳሌም እስኪርቁ በሚስጥር ያዙት። መጀመርያ ላይ ምኒልክ በአድራጎታቸው ቅር ተሰኘ። በኋላ ግን፣ በአባቱ የተቆጣው እግዚአብሔር ባይፈቅድ ኖሮ

እንዲያ ሊያደርጉ አለመቻላቸውን ተገንዝቦ ጽላቱን በደስታ ተቀብሎ ወደ አገሩ ወሰደው። በዚህም አኳኋን የታቦተ ፅዮን አምላክ፣ የአስርቱ ትእዛዛት ፀሃፊና የፅላቱ አስቀራጭ፣ እስራኤልን ለተቶ በኢትዮጵያውያን መሃል መኖሩን አመለከተ። በዚህም አኳኋን ኢትዮጵያ የገናናነቱ መገለጫና ዳግማዊ ቤቱ ሆነች።

ምኒልክና 40,000 አጃቢዎቹ ከአምስት ወራት ጉዞ በኋላ በዘሪያን ዘመን የኢትዮጵያ፣ ዛሬ የሱዳን ግዛት የሆነችው መርዌ ሲደርሱ ተቃውሞ ገጠማቸው። አዘቦዎች (የሳባ ነገዶች) ኩሻውያንና ሱቃውያን ውጊያ ገጠሙት። እናቱ ሳባ ይሄን ስትሰማ የራሷን ሰራዊት ከትታ አስታጥቃ ከእርሱ ተዋጊዎች ጋር በማቀናጀት ተቃዋሚዎቹን ደመሰሰችለት። ተጓጉቹም በድል አድራጊነት ሳባ ከተማ ገቡ። 40,000 እስራኤላውያኑም በኢትዮጵያ ግዛት በፈለጉበት ስፍራ እንዲኖሩ ንግሥተ-ሳባ አወጅችላቸው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ንግሥተ-ሳባ የ18 ዓመት ገደማ ጉብል ለሆነው ልጇ ዘውዷን አወረሰችው። እርሱም ከአባቱ ከንጉሥ ሰሎሞን ይልቅ ወደ አያቱ ንጉሥ ዳዊት አደላ። እናም በንጉሥ ሰሎሞን ፈንታ ‹‹የዳዊት ልጅ›› መባልን መረጠ። ከአባቱ ከሰለሞን ይበልጥ በአያቱ በዳዊት ትልቅነት የሚኮራ ይመስላል።

ምኒልክ ጦርነት በገጠሙት ነገዶች ተናደ ነበር። ስለሆነም በመልከጸዲቅ ሥርዓት የሚመራውን ኃይማኖታቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ ዙፋናዊ ስነምግባራቸውንና፣ ስርዓተ ንግሣቸውን ሳይቀር ተቃወመ። የአመጹም ዋና መግለጫ፣ በኢትዮጵ (ስሙን ኢትዮጵያ የወረሰችው የመልከጸዲቅ ልጅ) ስርዓተ-ንግሥ፣ ግዮን ወንዝ ወርዶና በኢትዮጵያዊ ካህን ተቀብቶ ዘውድ ለመጫን ያሳየው እምቢተኝነት ሆነ። እናም ከእስራኤል አብሮት በመጣው ሲቀ ካህን፣ በሳዶቅ ልጅ በ አዛርያስ እጅ እንደ እስራኤል ልማድ ተቀብቶ ነገሠ።

በቀጣይ እርምጃው አዳምና ሄዋን ይናገሩት የነበረውንና ይህ ደራሲ እንደመጀመርያው የሰው ዘር ልሳን የሚገምተውን ሱባ የሚሰኘውን አሳይ የመጽሀፉ ስእል የተቀመጠውን ቋንቋ አስወግዶ፣ ከጋዛ በመጡት በተለይም እያቡሳውያን በሚግባቡበት ግዕዝ ቋንቋ ተካ። ከኢትዮጵያውያን ጠላቶቹ ጋር ተዋድቀውለታልና ከጋዛ የመጡትን አጃቢዎቹን ‹‹አግአዚ›› (በግዕዝ ነፃ አውጪ) ብሎ ሰየማቸው። የኢትዮጵያን ስያሜም ወደ ‹‹ሃገረ-አግአዚ›› ሊለውጥ ሞከረ። ሱባን ወደ እብራይስጥ አለመተካቱ ግር ይላል። ከተዋደቁለት ጦረኞች አብዛኞቹ ግዕዝ ተናጋሪዎች በመሆናቸው ሳይሆን እንዳልቀረ እገምታለሁ።

ከዚያ በኋላም ጎረምሳው ንጉሠ ነገሥት ስር ነቀል ለውጡን ወይም አመጻውን ገፍቶበት፣ አጼ እስያኤል እና ሌሎቹም የኢትዮጵ ዝርያዎች በዘውዳቸው፣ በበትረ-መንግሥታቸውና በዙፋናቸው ላይ አስቀምጠውት፣ ለወደፊት የነብዩን (የእየሱስ ክርስቶስን) መወለድ የሚጠቁመውን ኮከብ አምሳያ አንስቶ ወርውሮ፣ በይሁዳ አንበሳ ምስል ቀየረ። ምኒልክ ያሸተነጠረው ያም ለኢትዮጵያውያን የመሲሁን መወለድ የሚያበስራቸው ኮከብ የዳዊት ኮከብ ተብሎ ይታወቃል። የዛሬ ዘመን አይሁዳውያን በዚህ ኮከብ እየኮሩ ብሄራዊ አርማቸው አድርገውታል። በእግዚአብሄር ገላጭነት ኮከቡን ያበጀችው ግን የትዱስ ዳዊት ቅድመአያት ኢትዮጵያዊቱ ሩት ናት። ስለዳዊት ኮከብ አመጣጥ በተገቢ ቦታው እገልፃለሁ።

የጎረምሳው ንጉሠነገሥት ተከታይ አርምጃም አሳዛኝ ነበር። የታሪክ ቅርሶችን በሙሉ አፈራረሰ፤ ከመልከጸዲቅና ኢትዮጵ የወረዱ ብርቅዬ ሱባዊ መፃህፍትን አወደመ። አንዳንዱንም ለቅሞ አፈነ፤ ቀደምት ነቢያትን ፊላስፎችንና ምሁራንን አሳደደ። በህይወት የተረፉት ጠቢባንና ካህናት ወደ ነብያና ግብፅ ተሰደዱ። በተለይም የ ታላቁ ነቢይና ጠቢብ የደሸት ልጆች ማጂዎች፣ (ማጂ የ ማራ፣ ማለትም የአማራ አባት እንደሆነ እዚህ ላይ ልብ ይሏል) በጥበባቸውና በአማካሪነት

ብቃታቸው በእጅጉ ይፈለጉ ስለነበር፣ በግብፅ፣ መጠጊያ አገኙ። ምናልባትም ‹‹ማጂ›› የሚለው መጠሪያቸው ‹‹ማጂክ›› ለሚለው ወይም ‹‹ትንግርት›› ለሚለው ቃል ምንጭ ሳይሆን አይቀርም።

ተቀባይነት ለማግኘት ሲሉ፣ ጥቂት የመልከጸዲቅ ካህናት የአይሁድ እምነት ተከታዮች ሆኑ። ‹‹ቤቱል›› በመባል የሚታወቀውን የመቅደስ ስም፣ ወደ ‹‹ቤተ እግዚያብሔር›› ለወጡ። በመልከጸዲቅ፣ ኢትዮጵና የቶርአብ አስተምህሮዎች ፈንታ ‹‹የሙሴን አስርቱ ትእዛዛት›› እንዲስፋፉ ደነገጉ። በመልከጸዲቅ ሥርዓት መሰረት፣ ወይንና ዳቦ የነበረውን የወደፊቱን የመሲሁን ሥጋ ወ ደሙ የሚጠቁመውን የመስዋእት ሥርዐት ለውጠ፣ በበጎችና ፍየሎች መስዋዕት ቀየረ።

በመጨረሻም ሌዋውያንንና እስራኤላውያንን የመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት አደረገ። የእናቱን ህዝብ ተቃውሞ ችላ በማለት እስራኤላውያኑን በኢትዮጵያ ግዛት እንዲያስተዳድሩ በንጉሥነት ሾማቸው። ያም ሁኔታ፣ በታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ በርካታ አይሁዳውያንን በባዕድ አገር ለንግሥና እና ለክህነት ያበቃ ዕድል ሆነ። ስፋትዋ ከኢትዮጵያ ሲነጻጸር፣ የበሬ ግምባር በምታክለዋ በትንሽዋ አገራቸው ይህ ዕድል አልነበራቸውምና።

ቀዳማዊ ምኒልክ በርካታ ቤተመቅደሶችን አሳንጸ የጽላት ምስሎች አኖረባቸው። ዋነኛውን ዕላት ግን ንግሥተ-ሳባ ባሰፈለፈለችው በሀዋላ ደብረ ማክዳ በተባለው ዋሻ ውስጥ በተለየ ክብር አስቀመጠው። ማክዳ፣ የክዳ (ክሃዲ) ማለት ሲሆን፣ ለምኒልክ ወግነው የወጓቸውን እስራኤላውያንን በማገሟና በማስጠጋቷ ህዝቧ ለሳባ ያወጣላት ስያሜ ነው።

በዚያም አካሁዋን ወጣቱ ንጉሠነገሥት በኢትዮጵ ሥርወመንግሥት ፈንታ የሰለሞንን ስርወመንግሥት በኢትዮጵያ ግዛት መሰረተ። ሁለት ጊዜ ቢቋረጥም ትውልዶቹ ከ2500 ዐመታት በላይ እንዲኖር አድርገውታል። የሰለሞን ስርወንግሥት የመጨረሻውና 225ኛው ባለዙፋን ‹‹ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ስዩመ እግዚአብሔር፣ ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ›› ነበሩ። እርሳቸውም በ1966 ዓመተ ምህረት መሉ በመሉ ከልጣናቸውን ተገለሉ። የሰለሞንን ስርወ-መንግሥት ለማንሰራራት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ የልጅ ልጆቻቸው ቢሞክሩም ኢትዮጵያ ውስጥ የሰለሞን ስርወመንግሥት በእርሳቸው ተደምድሞአል።

እነርሱንና ግዛታቸውን የሚጠበቅላቸው ሠራዊት አሰልፎላቸው ሚኒሊክ በኢትዮጵያ የሾማቸውን የአይሁዳውያን ነገሥታትና ካህናት ሥም ዝርዝር እንደሚከተለው አቀርባለሁ። በያንዳንዱ ግዛታዊ ክልል ቤተ እግዚአብሔር አሳንፆ፣ የጽላት

ምስል ውስጡ መግባቱን እየተከታተሉ የሚያረጋግጡ ሌዋውያን መድቦላቸው ነበር።

ኤልኖን የአሞን ልጅ የጋፋትና ጉሙዝ ሕዝብ የሚኖሩበት የቤተአንዳ ንጉሥ ሆነ። ግዛቱ ቋራን፣ ጎንደርንና በዛሬው ወሊጋ አካባቢ (እናሪያን) ያካትታል። ግዮን መነሻ በሆነው የጣና ሀይቅ ደሴቶች በአንደኛው ላይ ቤተ-ሳሕል የሚባል መቅደስ አሳንጾአል።

አዲል የይትርሀም ልጅ የአማራ ገዢ ሆኖ በዛሬው ዘመን የጁ፣ መርሐቤቴ እና አማራ ሳይንት በሚባሉ ቦታዎች ነግሷል። ‹‹ደብረ-ድባብ›› የተሰኘ መቅደስም አሳንጾበታል። ሌዋዊያን ግን የዳዊት ከተማን፣ ዕዮንን ለማስታወስ ‹‹ደብረ ዕዮን›› ብለውታል።

ሀላል የአሞን ልጅ ዛሬ ወገራ በሚባለው አገር በቤተ አሹር ነግሶ የጠለምት፣ ቤጃ፣ ቅማንትና በጌምድር አካባቢ የጎርጎራ ንጉሥ ነበር። በአባቱ መጠሪያ ‹‹ደብረ-አሞን›› የሚባል መቅደስ አሠርቷል። ለንዋየ ቅዱሳት ማኖሪያ ዋሻም አስፈልፍሏል።

አቤሜሌክ የኢዮአስ ልጅ ዛሬ ተክዜ በሚባለው አካባቢ የዋይዝንና የሳባን ህዝብ ገዝቷል። በቦታውም፣ እስራኤላውያን ስለወደዱት የ‹‹ደብረ አዜብ›› መቅደስን አስገንብቷል።

ለምኒልክ ግማሽ-ወንድም የሆነው ዜጋዬ የንግሥተ-ሳባ ዘመድ ከሆነችው ከንግሥት ሳሆይና ከንጉሥ ሰለሞን የተወለደ ሲሆን የተወሰነውም ንግሥተ-ሳባን አጅባ በሄደችበት ጊዜ ነበር። እርሱንም ወንድሙ ቀዳማዊ ምኒልክ ዛሬ ዋግና ላስታ በሚባሉት ስፍራዎች አንግሶታል። ስሙንም ምኒሊክ ራሱ ከዜጋዬ ወደ ዛግዌ ቀያሮታል። ይሄም ወሎ ላሊበላ ላይ፣ ከንግሥት ዮዲት የዘመን ማብቂያ በኋላ፣ የዛግዌ ዝርያ የነበረው የዮዲት ባል መራ ተክለሃይማኖት፣ የዛግዌ ስርወ-መንግሥት በሚባል አዲስ ስርወ-መንግሥት የሰለሞንን ስርወ-መንግሥት እንዲተካ ምክንያት ሆኖለታል። አልጋወራሾቹም የአይሁዳውያን ነገሥታቱ የንጉሥ ዳዊትና ንጉሥ ሰለሞን ትውልዶች መሆናቸውን በማጣቀስ ኢትዮጵያን ለ300 ዓመታት ያህል ለገዙበት ታሪክ መሰረት ሆኗል። ንግሥናው እስከ አጼ ላሊበላ ደርሶ፣ ከሱም ወደ ልጁ ወደ ያትባረክ ተላልፎ፣ ከእሱ ደግሞ በአብላጫው በአማራ የጦር ኃይል በተደገፈ፣ ስሙ ተስፋእየሱስ፣ ስመ-መንግሥቱ ያኩኖአምላክ በተባለ፣ በአባቱ የሰለሞን ዘር፣ በእናቱ ሀዊ ጊፍቲ መንዲያ የተባለች የኦሮሞ ልጅ ተነጥቆአል። ይህም የሆነው በ13ተኛው ምዕተ-ዐመት ነበር።

በዚህ በመጨረሻው፣ ሽዋ ላይ ተመስርቶ በነበረው የሰለሞን ስርወ-መንግሥት ውስጥ ኦሮሞዎች በጋብቻ ‹‹ሰርገው›› ገብተው

ኢትዮጵያን ለ700 ዐመታት ገዝተዋል። በዘመነ መሳፍንት፣ የሰለሞንን ዘር ለይስመላ ዙፋኑ ላይ ጎልተው ራሳቸው ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ከፊል ኢትዮጵያን የገዙትን ኦሮሞዎች ከትልቁ ራስ አሊ እስከ ትንሹ የነበሩት ኦሮሞዎች ሁሉ ተደምረው።

ምኒልክ ወደ ሾማቸው አይሁዳውያን ስንመለስ፣ ኤልያብ የናታን የልጅ ልጅ የሃዲያ ንጉሥ ነበር። በደብረ አዶናይ ላይ ኤልያብ ቤተመቅደስ አሠርቶ ‹‹ቤተ አዶናይ›› ብሎ ሰየመው። በጥቅጥቅ ደን የተሸፈነውን ለም መሬትም ዘሌዋውያን ካህናት አደለው።

ከጋላ ተከትለውት ለመጡ አጃቢዎቹ ምኒሊክ ነብዩ ናታንን (ኦሪዮን የተባለውን አገልጋዩን ንጉሥ ዳዊት ሚስቱን ካስረገዘ በኋላ ሓጥያቱን ለመሸፈን በጦር ሜዳ ባስገደለው ጊዜ የእግዚአብሄርን ፍርድ ይዞበት ወደ ዳዊት የመጣው ነቢይ ናታን) መሪያቸው አድርጎላቸው በደብረ ማይ አንድ መቅደስ ነቢዩ አንጾአል፤ በዳሞትና በበረንታም ከነ ሰዎቹ ሰፍሯል። የኦሮሞና አማራ አባት እና አያት የነበረው ኢትዮጵያዊው ታላቁ ነብይ ደሸት በተቀበረበት ስፍራ ጠበል ፈልቆ ህመማን ስለተፈወሱበት ‹‹ደብረ-ማይ›› የሚባል መቅደስ አሠርቷል። ያም ቦታ ከጊዜ በኋላ ጎንዳ ጎንዲት የሚል ስያሜ ይዟል።

ምኒሊክ ጉኒ የተባለውን የሌዊውን የናታንን ልጅ የጥቂት ሌዋውያን እና አግአዚያን መሪ አድርጎ ግብፅ ውስጥ ንግሥተ-ሳባ ወደመሰረተቻት ናፓታ የምትባል ከተማ ልኳል። ጉኒ እስራኤል ይኖር በነበረበት ወቅት ከወንድሙ ከአዛርያ ጋር በሰለሞን መቅደስ ለተካህን ሆኖ አገልግሏል። ጉኒ እውነተኛ የእግዚያብሄር ሰው ነበር። በናፓታ ከቋጥኝ የተፈለፈለ ቤተ መቅደስ አቁሟል። እዚም አያለ ወደ ኢትዮጵያ የሚፈልሱ እስራኤላውያንን እና ሌሎች ከኢየሩሳሌም የሚመላለሱ መንገደኞችን እየተቀበለ በደግነት አስተናግዷል።

ሌዋዊው አቂማስ የሊቀ ካህኑ (ዘርዓይያ) ልጅ፣ የዛሬዋ ኤርትራና የባህር ዳርቻዎቿ ነዋሪዎች መስፍንና ሊቀ ካህን ሆኗል። ደብረ ቤዛ ፅዮን የተሰኘና ከቋጥኝ የተፈለፈለ ቤተ መቅደስ አሠርቷል።

የቢንያም ነገድ የሆነው ፊቃሮስ በዓባይና በጣና ሐይቅ መሃል ይኖሩ የነበሩ እስራኤላውያን ወገኖቹና የትውልደ ኢትዮጵያውያን ገዢ ተደርጎ ዘውድ ጭኗል። ፀለምትን ዋና ከተማው አድርጓል። ንጉሥ ፊቃሮስ በደብረ አዶናይ ውብ ቤተመቅደስ አሠርቶ ሃምሳ ሌዋዊያንን አስገባበት። አገሩንም ቤተ-አሹር አለው። በጣም ለም የሆነ ግዛት በመሆኑ በርካታ እስራኤላውያን የእርሻ መሬት ከልለው መኖሪያቸው አደረጉት።

ነብዩ ናታን ከእነርሱ አንዱ ነበር። እላይ እንደ ጠቀስኩት፣ ንጉሥ ዳዊት፣ ቤርሺባ ከምትባል ኩሻዊት ሴት ጋር የፈፀመውን ዝሙት ለመሸፋፈን ንጉሥ ዳዊት ኦርዮን የተባለውን ባሏን ከገደለ በኋላ የእግዚያብሔርን ቃል ለንጉሡ ጆሮ ያደረሰው ይሔው ታላቁ ነብይ ናታን ነበር። ጊዜዋን ጠብቃ ቤርሺባ የንጉሥ ሰለሞን እናት ሆነች። የንፁህ ሰው ደም ስላፈሰሰ እግዚአብሔር ዳዊትን ክፉኛ ቀጣው። ኢትዮጵያ ውስጥ በኖረበት ዘመን ነብዩ ናታን የአምላክን ሕግጋትና ትንቢቶች እንዲሁም ወደ ኢትዮጵያ የፈለሱትን አይሁዳውያን ታሪክ ፅፏል። ያረፈውም በመቶ ሁለት ዓመቱ ነበር። ያገሩ ሰዎች በህልፈቱ አዝነው በደብረ ማይ ዋሻ ቀበሩት። መካነ መቃብሩ ላይ እስከዛሬም ብርሃን ይፈነጥቃል ይባላል።

የናፍታሊ ጎሳ ተወላጅ የሆነው ማታን የተርሴስ፣ አፋር፣ ኢሳና ቤተሃጌ ገዢ ሆኗል። አዳም ስም ያወጣላቸው ዘንድ እግዚአብሔር የተለያዩ እንስሳቶችን ወደ እሱ ያመጣለት ቅዱስ አጸድ (ደብረ ኪሩብ) ነው በሚባለው ቦታ የተንጣለለ ቤተመቅደስ አሳንፆአል። ሃምሳ ሁለት ሴዋውያንንም ለአገልግሎት አሰማርቶበታል። የቤተ-መቅደሱ ፍርስራሽ እስከ ዛሬ በሐረር ግዛት ይታያል ይባላል።

የይሳኮር ጎሳ ተወላጅ የሆኑት ሁለት ወንድማማቾች ንጉሥ አውሳና አዳሪዝ የማጂንና አካባቢውን ሕዝቦች ገዝተዋል። ንጉስ

አውሳ መቅደሱን በደብረ ዙባ አሠርቷል። ውስጡንም በገዘፈን ጥርስና በወርቅ ለብጦ ከላይ እንደተጠቀሱት አይሁዳውያን ነገሥታትና ካህናት እርሱም የፅላቱን ምስል በቤተመቅደሱ አኑሯል።

የንጉሥ ሰለሞን ልጅና የንጉሥ ዳዊት የልጅ ልጅ ቀዳማዊ ሚኒሊክ ለአባቱ ወገኖች ለእስራኤላውያን ብዙ በጎ ነገሮች ውሎላቸዋል። በመንግሥቱ ከፍተኛ ስልጣን እንዲቆናጠጡ በማድረግ መኖሪያና ቤተመቅደስ መሥሪያ ቦታ በመስጠት በአገራቸው ያሉ እስከሚመስላቸው ሁኔታዎችን አመቻችቶላቸዋል። በፊት እንዳልኩት፣ በጠባቢቷ እስራኤል ቢቆዩ ኖሮ ሁሉም ይህን እድል ከቶ ባላገኙ። ይሁንና ለአባቱ ወገኖች አዳልቶ የእናቱን ችላ ማለቱ ወይም ጭራሹኑ እስከማሳደድ መድረሱ፣ ህይወቱን አሳጥቶታል። ከባድ ዋጋም አስከፍሎታል።

ቀዳማዊ ምኒልክ የመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አድርጎ ከሾማቸው ጊዜ ጀምሮ አግአዚዎቹ በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ጠንካሮች ነበሩ። በአገሪቱ ውስጥ አመጽ አያስነሱ የጠሉትን ንጉሠነገሥት ከዙፋን የሚያወርዱ፣ የወደዱትን ወደ ዙፋን የሚያወጡ ኃይለኞች እንደነበሩ ታሪክ መዝግቦታል። ለምሳሌ የአክሱማይት አባት ዘግዱር በገዛ ልጁ እንዲገደል እና ገዳዩም ወደ ዙፋን እንዲወጣ አድርገዋል። አባቱን

የገደለውን ወንድሙን እና አባቱን እንዲገድል ያነሳሱትን አግአዚዎችን ለመበቀል አክሱማይት ግብጽ ውስጥ በነበሩ አማሮች ወታደሮቹ ድጋፍ ወንድሙ የግብጽ ፈርኦንነቱን እንዲለቅ አስደርጓል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ9ኛው ዓመተ-ዓለምም ወንድሙን ገድሎ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆኗል። በአንደኛው ክፍለ-ዘመን እቴ ህንደኬ ጃን በቅዱስ ማቲዎስ እጅ ተጠምቃ ክርስቲያን ሆና ነበር። አይሁድ አግአዚዎች በአክሱም ተሰሚዎች እና ኃይለኞች በመሆናቸው እሷን (ሕንደኬን)፤ ልጇን እና ባሏን ገድለው በእሳት አቃጥለዋል። ወንድሟን ኬቱብን አጼ ባሕር-ሰገድ በሚል ስመ-መንግሥት በዙፋኗ ላይ አስቀምጠው አሻንጉሊታቸው አድርገውታል። አግአዚዎቹ መጀመሪያ ተጋሩዎቹ እስከሚደመስሷቸውና ቀጥሎም ዮዲት የመጨረሻ ምት አሳርፋባቸው ፈጽማ አስከምታጠፋቸውና በ9ኛው ክፍለ-ዘመን ንግሥት ተብላ በዙፋናቸው ላይ እስከምትቀመጥ ድረስ ኣግኣዚዎቹ ያን ያሕል ኃይለኞች ነበሩ። ቋንቋቸው ግዕዝ በአል-ነጋሽ ዘመን በ7ኛው ክፍለ-ዘመን ከእስልምና ተጽዕኖ የተነሳ በአረብኛና በሶርያ ቋንቋ ሲተካ ተዳክመ። አግአዚያኑ ራሳቸውም እንዲሁ በአሌክሳንደሪያ እየተመረጡ በኢትዮጵያ በሚሾሙ የግብጽ ፓትርያሪኮች ክፉኛ ተጎዱ። አንዳንዶቹ ከግብጽ የሚመጡ

ፓትርያሪኮች አረቦች በመሆናቸው አይሁድን ስለሚጠሉ አግአዚዎችን "የክርስቶስ ገዳዮች" ናቸው ብለው እንዲፈርጇቸውና አንዲያሰቃዩአቸው የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች አነሳሱባቸው።

ንግሥት ዮዲት እና ለኢትዮጵያ የዋለችው ውለታ

ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ከወጡ የአይሁዳውያን ዝርያዎች መሀል በጉልበታ ንግሥተ-ነገሥታት ለመሆን የበቃችው ዮዲት ጌዲዎን (አስቴርም ትባላለች) ናት። ለመሆኑ የዮዲት ጌዲዎን የዘር ሀረግ ምንድነው? የሰለሞናዊው ስርወመንግሥት አባል ሳትሆንስ እንዴት የኢትዮጵያ ንግሥተ-ነገሥታት ለመሆን በቃች? በእሷው ዘመን የነበረው እና ከእሷ ሰይፍ ያመለጠው ታላቁ የታሪክ ጸሀፊያችን ልዑል አክሱማይት ሲራክ ታሪኳን በግእዝ ከትቦት ነበር። ዘመነኛዋ የዘገበው እውነተኛ ታሪካ ጠላቶቿ የግብጽ አረብ ፓትርያርኮች እና የነሱ የመንፈስ ባሪያ የሆኑ አንዳንድ የኛው ጸሀፍያን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ባላንጣዎች ካቶሊክ-ሮማውያን ስሟን ለማጉደፍ ከከተቡት

የተለየ ነው። *ታሪከነገሥት ዘ ኢትዮጵያ* በተባለው ጥንታዊ መጽሐፍ ውስጥ ልዑል አክሱማይ ሲራክ ጽፎት፣ መሪራስ አማን በላይ በአጭሩ ከግእዝ ወደ አማርኛ ከመለሱት ላይ ቀንጭቤና አቀነባብሬ የዮዲትን ትውልድ እና እውነተኛ ማንነት አቀርባለሁ።

እላይ ‹‹ንግሥት ዮዲት ለኢትዮጵያ የዋለችው ውለታ›› ብዬ ስለጻፍኩ አንባቢው ሊደነቅ ይችላል። ምክንያቱም፣ እሷ የምትታወቀው ኢትዮጵያን በእሳት በማጋየት ብቻ ነውና። በዚህም ምክንያት ‹‹እሳቶ›› ወይም ‹‹ዮዲት ጉዲት› እስከመባል ደርሳለች። ሀቁ ግን እንደተወራባት እሷ የኢትዮጵያ ጠላት አልነበረችም። እንዳውም በተወሰነ ደረጃ ድረስ የኢትዮጵያ ባለውለታ ናት። የዚህንም ማስረጃ ዝቅ ብለን እናያለን።

ዮዲትም የነገሥታቱ ዳዊትና ሰለሞን ዘር ነኝ ባይ ናት። የተነሳሁትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር ትንቢት አስነግሮልኝ ነው ብላለች። እንደ እሷ አተራረክ አባትዋ ጌዲዎን ከተከዜ መለስ የመረባ፣ የይፋግ፣ የበገላ፣ የበለሳ፣ የሰሜንና የጸለምት፣ የበጀዳ፣ የቤተአሹር፣ የደንቢያና የቋራ ንጉሥ ነበር። የተረጋገጠው የዘርዋ ሀረግ እንደሚከተለው ነው፡-

በሳንደር በአይሁድ አምባ እዝራ ዘርአያን፣ ዘርአያ ሀዲስን፣ ሀዲስ ኤልያስን፣ ኤልያስ ፊንሀስን፣ ፊንሀስ ዳዊትን፣ ዳዊት ሰለሞንን፣ ሰለሞን እያሱን፣ እያሱ ላዶቅን፣ ላዶቅ ዳንኤልን፣ ዳንኤል ኤልያብን፣ ኤልያብ ጌዲዎንን፣ ጌዲዎን ደግሞ ዮዲትን ይወልዳል። እነዚህ ሁሉ ለአክሱም ንጉሠነገሥት እየገበሩ ከፀሰምት እስከደምቢያ ባሉት ህዝቦች ላይ መሳፍንት፣ አንዳንዶቹም ንጉሦች ሆነው ገዝተዋል።

የእነዚህ ሁሉ ቅድመ-አባት የንጉሥ ዳዊት ዘር ነው የተባለ ፊንሀስ ነው። ወላጅ አባቱ ዮሴፍ ይባል ነበር። የፊንሀስ ቤተሰቦች በኑብያ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በኢትዮጵያዊ ዜግነት ይኖሩ ነበር። በእዚህ ምክንያት ፊንሀስ ወደ አክሱም መጥቶ ይኖር ነበር።

ፊንሀስ አክሱም በሚኖርበት ሰዐት ከእስልምና መነሳት በፊት በአክሱም ቤተመንግሥት ውስጥ ለ1600 ዐመታት ገንነውና ሰልጥነው የነበሩት ቤተ-እስራኤሎች፣ ከአሌክሳንድርያ መጥተው የኢትዮጵያ ፓትርያርኮች በሆኑት አረቦችና ጊዜ በሰጣቸው ሶሪያውያኖች ተጠቅተው ነበር። ወቅቱ አረባዊ ተጽእኖ የሰፈነበት በመሆኑ ግእዝ እና አጋዕዝያን በአረብኛ እና አረቦች መሳሳቆል ላይ ነበሩ። የአክሱምም መንግሥት በተዘዋዋሪ በአረቦቹ ፓትርያርክ ቁጥጥር ስር ገብቶ ነበር። በወገኖቹ በደል ፊንሀስ ተናዶ

አክሱምን ለቆ ወደ ዋግ ሄዶ፣ አይሁዳውያን ወገኖቹ እንዲያምጹ በጦር ስልት ሲያሰለጥናቸው የአክሱም ንጉሠነገሥት ሰምቶ ሊገድለው አሳደደው። እሱም የአማርያን ልጅ ሚስቱን ሰሎሚትን ከብዙ ሰራዊት ጋር ይዞ ያኔ ናግራን ይባል ወደ ነበረው ወደ የመን ኮበለለ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም በየመን የነበሩትን ክርስትያኖች ተዋግቶ በጦር ሰራዊቱ ኃይል ዳግማዊ ዳዊት ተብሎ ነገሠ። (የይሁዳው ንጉሥ የቅዱስ ዳውት ዘር ነኝ በማለት) እሱን ለመቅጣት አጼ ካሌብ ብዙ ሰራዊት በመርከብ አሳፍረው ወደ የመን መገስገሳቸውን ሲሰማ ሚስቱን ሰሎሚትን፣ ልጆቹን ዘርአያን እና አቢሱን በስውር ኢትዮጵያ ገብተው እንዲኖሩ አሸሻቸው። እነሱም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የቀን ጭለማ፣ የአይሁድ አምባ እተባለው ስፍራ ተደብቀው ኖሩ። እሱም በርትቶ ከአጼ ካሌብ ሰራዊት ጋራ ብዙ ከተዋጋ በኋላ ተደመሰሰ።

እንግዲህ ኢትዮጵያ ተሰውረው ይኖሩ የነበሩት ልጆቹ ዘርአያ እና አቢሱ ተባዝተው ነበር ጌዲዎን ከ300 ዐመታት በኋላ የዮዲት አባት ሊሆን የቻለው። የዮዲት አባት ጌዲዎን፣ እኔ የቤተአሹር እና የይሁዳ አምባ መሥፍን እና ንጉሥ፣ እንዲሁም የንጉሥ ዳዊት ዘር ስለሆንኩ አክሱም ከአለው ከኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት ዙፋኑን ነጥቄ ንጉሠነገሥት መሆን አለብኝ ብሎ በርካታ ታጣቂዎች ይዞ አክሱም ላይ ዘመተ። ህዝበናኝ

የተባለውም የአክሱም ንጉሠነገሥት በጦርነት ማርኮት በአደባባይ ሰቀለው። ቀጥሎም ዕሬሳው በእሳት ከሞቱት እና ከተማረኩት አይሁዳውያን ሰራዊቶቹ ጋራ ተቃጠለ። ሲኖዳ በተባለ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ለአክሱም ጳጳስነት የተሾመ አባ መቃርስ በተባለ አይሁዳውያንን በሚጠላ አረመኔ አረብ ትእዛዝ የጌዲዎንን እና ቤተ እስራኤል የሆኑትን የጌዲዎንን የጦር ሰራዊቶች እሬሳ እና ምርኮኞቹን ከነ ነፍሳቸው እቤት ውስጥ አፍነው በእሳት አቃጠሏቸው። ዮዲት በአባቷ እና የወገኖችዋ አሰቃቂ ግድያ ምክንያት በአክሱም ንጉሥ በህዝበናኝ ላይ ቂም እና ቁጣ አርግዛ ነበር። በእዚህ ላይ በህይወት የአሉትም የህዝቦችዋ በአረብ ፓትርያርኮች ተጽእኖ ‹‹ቀታሌ እግዚአብሄር›› (የእየሱስ ክርስቶስ ሰቃይዎችና ገዳዮች) እየተባሉ በሚደርስባቸው ስቃይና የግእዝ ቋንቋ በአረብኛ ቋንቋ መዳከም ያንገበግባት ነበር።

የዮዲት ሁኔታ እላይ እንዳው ሳለ፣ የእሷን የህይወት አቅጣጫ የሚያስቀይስ አንድ እውነታ ተከሰተ። እሱም እንደሚከተለው ነው። በእዚያ ጊዜ የቀዳማዊ ምኒልክ ወንድም የዛጉዌ ዝርያ የሆነ በዋግ እና ላስታ የነገሠ መራሪ (መሪ) የሚባል አንድ የአዜብ (የአዘቦ) ንጉሥ ነበረ። ለእሱም እጅግ የተዋበች እንቁዮጳግዮን የተባለች ልጅ ነበረችው። የወደፊቱን እንናገራለን የሚሉ ሰዎች ይቺ ልጅህ አንድ የንጉሥ ዘር ያልሆነ ተራ ሰው

ታገባና የቆየውን ያንተን መንግሥት ሰርአት የሚለውጥ ልጅ ትወልዳለች፤ ብለውት ስለነበር ከወንድ እንዳትገናኝ፣ እንዳታገባም አሩኖ ይዞ በቤት ውስጥ ደበቆ ያስቀምጣት ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን ንጉሥ መራሪ ወደ አክሱም ሄዶ ሳለ አንድ የሌዊ ወገን የሆነ ሰለሞን የሚባል መልከመልካም አናጺ ያይና ቁመናውን በማድነቅ እና ተከተለኝና አገልግለኝ ብሎ ይዞት ወደ ቤተመንግሥቱ ወስዶ ጋሻጃግሬው ያደርገዋል። እንቁዮጳግዮን በሰለሞን ውበት ተማርካ ካላገባሁት ሞቼ እገኛለሁ ትላለች። አባትዋ ትንቢቱ ትዝ ብሎት እሱን አታገቢም ብሎ ድርቅ ይላል። እሷም እያለቀሰች ስላስቸገረችው ሰለሞንን ሊገለው አስቦ፣ ሰለሞንንም እሷንም ስለሚወዳቸው እሱን የግንድ ቀፎ ውስጥ ከምግብ ጋራ ከትቶ በአትባራ (በኋላ በንጉሡ ትካዜ ምክንያት ተከዜ) በተባለው ወንዝ ውስጥ ጨመረው።

እንቁዮጳግዮንም ፍቅረኛዋን ስለ አጣችው ምናልባት አባትዋ ወደ አክሱም አባሮት እንደሆን ብላ፣ ተራ ሴት መስላ ወደ አክሱም ተጉላ በአክሱም ከተማ ውስጥ ስትፈልገው አንድ እሱን የሚመስል ሰው ዐየች። እሷም ‹‹ሰለሞን›› ብላ ጥምጥም ስትልበት እሱም ‹‹እኔ ሰለሞን አይደለሁም። የሰለሞን ወንድም ንጉሤ ነኝ፤ ሰለሞን ሳይሰናበተን እንደ ወጣ ከቀረ ዐመታት አልፏል፣ የት እንዳለ እንጃ፤›› አላት። እሷም ከእሱ ወላጆች ቤት ጥቂት

ከሰነበተች በኋላ ንጉሤን ይዛው ወደ ቤተመንግሥት ወሰዳ የሰለሞንን ወንድም ለማግባት እንደምትፈልግ ለአባቷ ነገረችው። አባቷ አሁንም ችግር ውስጥ መግባቱን ተገንዝቦ ንጉሡ አንችን ልዕልቲቱን የሚያገባ ከሆነ በጦርነት ተሳትፎ ጀግንነቱን ማረጋገጥ አለበት ብሎ አሳምኗት ወደ ጦር ሜዳ ልኮ አስገደለው።

እንቁዮጳግዮን በእዚህ አዝናና ተባሳጭታ ከቤተመንግሥት ወጥታ የሰለሞን እና የንጉሡ ወላጆች ጋር ሄዳ በአክሱም ስትኖር፣ አጼ ህዝበናኝ በአጋጣሚ ያያትና በግድ ወደ ቤተመንግሥቱ አስወስዶ ሊደፍራት ይሞክራል። እሷም ኃይለኛ ስለነበረች ንጉሡን አንቃ ገድላ ከቤተመንግሥት ሾልካ ወጣች። ከዛም የራስዋን ሰራዊት ትሰበስብ ጀመር። በእዚህ ጊዜ ነበር ዮዲት ለእርስዋ በውትድርና የገባችላት። ሁለቱም ሴቶች በደል የደረሰባቸው በመሆናቸውና የዮዲትን አባት ጌዲዎንን የሰቀለውን ህዝበናኝን እንቁዮጳግዮን አንቃ ስለገደለችው ዮዲት እመቤትዋን በጣም ወደደቻት። በሙሉ ልብዋ እና ኃይልዋ ልታገለግላትም ቆረጠች። ዮዲትን ተከትለው ብዙ ቤተ እስራኤላውያን ለእንቁዮጳግዮን አደሩላት። እንቁዮጳግዮንም ስምዋን ለውጣ ራስዋን ‹‹ትርዳ ጎበዝ›› ልባል አለች። ዮዲትን እና ሌሎቹን ሰራዊቷን ይዛ ዘመተች። ቤተመንግሥቱን አቃጥላ ከአባትዋ ጋራ ተዋጋች፤ አባቷንም ማረከች። አባትዋም ስለበደላት ይቅርታ ጠይቋት

ታረቁ። ቤተመንግሥቱንም እንደገና ገነባችለት። የዮዲትን ጉብዝና ዐይታም የጦርሰራዊቷ ዋና አዛዥ አደረገቻት። የዮዲትም ዝና በሀገሩ ተላመተ።

ዮዲት በጦር ጀብዱዋ እና በሠራዊቷ ብዛት እየገነነች ስትሄድ ወደ አክሱም ዘምታ የህዝበናኝን ልጅ አጼ ጊዳጃንን ገደለችው። የ10 ዐመት እድሜ የነበረውን ልጁን አንበሳ ውድምን ዘመዶቹ አሸሽተው ተጉለት፣ በሸዋ ውስጥ ደበቁት። ከዚያም እነዛን አባቷን እና ወገኖችዋን ገድለው ከኢትዮጵያ ባህል ውጪ አስከሬናቸውን በእሳት ያቃጠሉትን አረቦች ገድላና አቃጥላ ተበቀለቻቸው። ኢትዮጵያውያን በግእዝ የጻፉትን መጻሕፍት ለይታ አትርፋ እነሱ በሶርያውኛ እና በአረብኛ የከተቧቸውን ሁሉ ሰብስባ አቃጠለቻቸው። ከቤተክርስትያንም የአክሱም ጽዮንን እና ሌሎችንም በአረቦች ያልተበከሉትን መርጣ ከእነሱ ጋር የተያያዙትን አጋየቻቸው። ዘመዳቸው እዙፋን ላይ ሳለ አገር እንዳያውኩ በደብረ ዳሞ ዋሻ ውስጥ ይታሰሩ የነበሩት ልዑላን ዘንድ ሄዳ ከነሱ መሀል የንጉሣውያኑ የህዝበናኝ እና የግዳጃን የቅርብ ዘመዶች የሆኑትን ገድላ ሌሎቹን ተወቻቸው። በማስጠንቀቂያ ብቻ አለፈቻቸው። በሰባት ነገዶች ተከፍለው ከነበሩት ተጋሩዎች ውስጥ ዐራቱን አገራችሁን ክዳችሁ ከሶሪያውያን እና ከአረቦች ጋራ ተመሳጥራችሁ ቤተ-

እስራኤላውያንን ጎድታችኋል በማለት በፍርድ ገደለቻቸው። ከተጋሩ ውስጥ ሶስቱን ነገዶች ግን እናንተ ምንም ወንጀል አልተገኘባችሁም ብላ ተወቻቸው። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የአሉት ተጋሩዎች የእዛ በዮዲት ጥፋት ያልተገኘባቸው የሶስቱ ነገዶች ዝርያዎች ናቸው። ይህን አሁን እኛ የምናወሳውን የንግሥት ዮዲትን እውነተኛ ታሪክ በኋላ ጽፎ ያስተላለፈልንን ልዑል አክሱማይ ሲራክንም እንዲሁ በማስጠንቀቂያ አለፈችው። እሱም ተሰውሮ፣ መጽሀፈ-ሱባኤ እና ታሪክ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ የተባሉት ጥንታዊ መጻህፍት ተሸክሞ ኢትዮጵያውያን ወደ ነበሩበት ወደ ግብጽ ሸሸ። እዛም ሆኖ በተለያዩ ቋንቃች መጻህፍቱን አባዛቸው። ከግብጽ ደግሞ ወደ ኑብያ ተጉዞ ለጥቂት ጊዜ የጁባ ሰዎችን ወንጌልን እየሰበከ ወደ ክርስትና እምነት ሲያስገባ ቆየ። ከእዛ በኋላ የአክሱም ነገሥታት ዘር በመሆኑ በመርዌ ንጉሥ ተሹሞ የኖባ ንጉሥ ሆነ።

ዮዲት ያጠፋችውን ጥፋት እመቤትዋ ልእልት እንቁዮጳግዮን ስትሰማ ተቆጥታ መጣሁልሽ ጠብቂኝ ብላ ዛተችባት። ዮዲትም ለጥፋቴ ሁሉ ምክንያት ስለአለኝ እመቤት እኔ መጥቼ ላስረዳሽ አንቺ እኔን ልትወጊ አትምጪ፣ ብላ ላከችባት። እንቁዮጳግዮን ግን በሰማችው ሁሉ እጅግ ተናዳ ስለነበር ገስግሳ መጥታ ተዋጋቻትና ተሸነፈች። ዮዲት ግን፣ አሁንም

እመቤቴ ነሽ ብላ ለምን አረቦቹን እና ልዑላኑን እንደገደለችና ያቃጠለችውን ሁሉ ስለምን እንዳቃጠለች አስረድታ፣ ሌዋውያን ካህናቱንም ቢሆን ጥፋታቸውን አንድ በአንድ እየመረመረች በማስረጃ በአደባባይ እንጂ በፍርደ-ገምድልነት እንዳልገደለቻቸው እና እርምጃዋ ትክክል መሆኑን ሳሳመነቻት። ከአባቷና ከአይሁዳውያን ወገኖችዋ መገደልና በእሳት መቃጠል ቀጥሎ፣ ዮዲትን ያንገበገቧት ነገሮች፦

1ኛ. የኢትዮጵያ ሌዋውያን ካህናት ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከሶርያ፣ ሮምና አሌክሳንድርያ መልእተኞችና ጳጳሳት ጋር መመሳጠራቸው፤

2ኛ. ሌት ልትነግሥ አትችልም ማለታቸው፤

3ኛ. የንግሥት ሳባን፣ የሰለሞንን እና የቀዳማዊ ምኒልክን ታሪክ ሮማውያኖቹ እና አረቦቹ ክደው፣ ሰሎሞናዊ የሚባል ስርወ-መንግሥት የለም ብለው ለአክሱም ስልጣኔ እነሱ ብቻ አስተዋጽኦ ያደረጉ ለማስመሰል መጣራቸው፤

4ኛ. 1800 ዐመታት የዘለቀውን አጼ አክሱማይ ያነጸውን አንድ ሀውልት እኛ ሠራነው ለማለት እላዩ ላይ በአረብኛ ለመጻፍ መሞከራቸው፤

5ኛ. የጥንት የኢትዮጵያን መጻህፍት አጥፍተው በአረብኛ መተካታቸው፣ ግእዝን አዳክመው ሶርያውኛንና አረብኛን ማጎልበታቸው ነበሩ።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ዮዲት ኢትዮጵያን ለማዳን ከእግዚአብሄር ተጠርቻለሁ ብላ ታምን ነበር። ድርጊቶችዋን ሁሉ እንደመለኮታዊ ትእዛዝ ነበር የምታየው። እነዚህን ሀቆች የዛሬ ዘመን ኢትዮጵያውያን ከተረዳን ዘንድ፣ ከዚህ በፊት ጠላቶችዋ በዮዲት ላይ የአካሄዱትን የስም ማጥፊያ ዘመቻ እንደ ገና ልንመረምረው ይገባል። እውነተኛ ማንነትዋንም እንደ ገና መፈተሽ ግድ ይላል።

እላይ የሆነው ሁሉ ሲሆን እግንድ ሳጥን ውስጥ ተከቶ እተከዜ ወንዝ ውስጥ ተጥሎ የነበረው የእንቁዮጳግዮን ፍቅረኛ ሰለሞን ሳይሞት ግንዱ እየተንሳፈፈ ኑብያ ደርሶ፣ እግዚብሄር ትረፍ ብሎት፣ ሰው ከግንዱ ውስጥ አውጥቶት የመርዌ ንጉሥ ባለሟል ሆኖ ያገለግል ነበር። የእንቁዮጳግዮን አባት መራሪ አግኝቶት ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶት፣ የምትወጂው ተገኘ፣ ብሎ ለእሱ ድሮአት ከእሱ አንድ መራ ተክለሀይማኖት የተባለ ወንድ ልጅ ወልዳ ነበር። ከዮዲት ጋራ ግንኙነቷን ለማጥበቅ ብላ እንቁዮጳግዮን ከዮዲት በ10 ዐመት የሚያንሰውን መራን ለ20 ዐመቷ ልጃገረድ ለዮዲት ዳረችላት።

የሁለቱ ሴቶች የእናትና ልጅ ግንኙነት እና ወላጅነት ተጥሎ መራ ተክለሀይማኖት ለአቅመ-አዳም ሲደርስ ከዮዲት ጋራ አብሮ መኖር ጀመረ፤ እስዋ በነገሠችበት በአክሱም መዲና። ልጅዋን ለዮዲት ከዳረችላት በኋላ እንቁዮጳግዮን በአዘቦ ግዛቶች ላይ ነግሣ ከምትወደው ባሳ ከሰለሞን (ባህር-ሰፍም ይባላል ውሀ ላይ ተንሰፍ ስለተረፈ) ጋራ በጸጥታና ሰላም ኖረች እንጂ አክሱም ለኔ ይገባኛል ብላ ዮዲትን አላስቸገረቻትም። ‹‹አስቴር፣ እሳቶ፣ ዮዲት ጉዲት›› ተብላ የምትጠራው ቤተ-እስራኤላዊት፣ ልክ እንደ እነ አጼ ቴዎድሮስ በጉልበቷ ዘውድ ጭና የሰለሞን ስርወመንግሥትን ነቅላ፣ በቦታው ራስዋ ተተክታ ለ41 ዐመታት ለሰሞናዊዎቹ ይገዙት የነበሩትን በሞላ እንኳን ባይሆን የተወሰኑትን አካባቢዎች አንቀጥቅጣ ገዝታለች። የእዚህ አንዱ ምክንያት፣ የራስዋ ጀግንነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ ከቁርጠኛ ፈላሻዎቹ ጦረኞችዋ በተጨማሪ፣ ዕጣቸውን ከእሷ ጋር ያጣመሩ ከክርስትያኑም ከሙስሊሙም፣ ከአማራውም፣ ከኦሮሞውም፣ ከሌሎቹም ሁሉ ጎሳዎች የተውጣጡ ወታደሮች ስለነበሩአት ነው። ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ የሆነላቸው በርካታ ሰለሞናውያን እንኳን የእሷን ያህል ረጅም ጊዜ አልገዙም። ከጦር ኃይልዋ በተጨማሪ ህዝቡ ዝም ብሎ የተገዛላት፣ የንጉሥ ዘር አላት ብሎ ስለአሰበና በእሷም የደም ስር ውስጥ የንጉሥ ሰለሞን አባት የንጉሥ ዳዊት ደም ይፈስሳል ብሎ ስለ አመነ ነበር። እሷም በእዚህ ትረካ ታምን

ነበር። እንደዛም ሆኖ የኋላ ኋላ ቅዋሜው በዝቶባት፣ ባልዋም አክሱምን ለቆ ወደ ላስታ ተመልሶ ሳለ እሷ ለምና፣ አባብላ ወደ አክሱም መለሰችው። የማይሞት የለም እና እሷ ስትሞት (ተገድላ ነው ይባላል፤) ራሱ ወደ ቆረቆራት ወደ ቡግና ከተማ ተመልሶ የቅድመ-አባቶቹን የእነ ዛግዌን ስርወመንግስት በቅጡ መሰረተ።

የዮዲት ጠላቶች ስለ አሟሟትዋና ከመንገሥዋ በፊት ስለነበረው ህይወቷ የተለያዩ የስም ማጥፊያ የሃሰት ወሬዎች ነዝተዋል። ከሁሉም የሚያሳዝነው፣ በተቀደሰችው የጽዮን ከተማ በአክሱም ውስጥ በዛን ጊዜ ሽርሙጥና የነበረ ይመስል በሴት አዳሪነት ትኖር ነበር ብለው ማስወራታቸው ነው። እሷ ግን የአንድ መስፍን ወይም ንጉሥ ልጅ ነበረች እንጂ የእዚህ ዐይነት ዝቅ ያለ ህይወት አላሳለፈችም። ከዚህ ሁሉ በላይ ስሟን የሚያጎድፈው ኢትዮጵያን ከአረቦች ተጽእኖ አውጥታ መታደግዋ ሳይዘከርላት፣ እንደ አውዳሚ ብቻ መታየቷ ነው። ሆኖም እሷ በሮም መንግሥት መልእክተኞች እና በአረብ ጳጳሳት ሴራ ከመጽሐፍ ሊጠፉ የነበረውን ገናና የኢትዮጵ ታሪክ ካተረፈች በኋላ ያወደመችው አረቦች ኢትዮጵያን አርክሰው ሊያጠፏት ጫፍ ላይ ደርሰው የነበሩትን አረባዊ ርኩሰቶችን እንጂ የኢትዮጵያን ቅዱስ ነገሮች አይደለም። (አማን በላይ፣ *መጽሀፈ አብርሂት*፣ ገጾች 283-312)

የዮዲት ባል መራ ተክለሃይማኖት እና የዛጉዌ ስርወመንግሥት

ከዮዲት ፍጻሜ በኋላ ስለሆነው ሁኔታ እርስ በርሱ የሚቃረን መረጃ ነው ያለው። አንዳንዶች መንዝ ተደብቆ የነበረው የጊዳ-ጃን ልጅ አንበሳ-ውድም ወደ አክሱም ተመልሶ በመራ ተክለ-ሃይማኖት እስከተገለበጠበት ጊዜ ድረስ ለ20 ዓመት ገዛ ይላሉ። ሌሎች የአገውና የአክሱም ሕዝቦች የተነጠቀውን የአባቱን ዙፋን መልሶ እንዳይዝ ከለከሉት ይላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የአገው ልዑል የነበረው የንግሥት ዮዲት ባል መራ ተክለ-ሃይማኖት ዮዲት ስትሞት ነገሠ፤ ስመ-መንግሥቱንም የንጉሥ ሰለሞን እና የኤትያ-ኤል ንግሥተ-ሳባ ዘመድ የነበረችው የአዘቦ ንግሥት የሣሆይ ልጅ የሆነውን ቀዳማዊ ዛግዌን ለማስታወስ ‹‹ዳግማዊ መራራ-ዛግዌ ›› ብሎ ራሱን ሰየመ ይላሉ። እዚህ ላይ መታወስ

ያለበት፣ ኢትያኤል (ንግሥተ-ሳባ) እና ንግሥት ዛሆይ ንጉሥ ሰለሞንን ለማየት ኢየሩሳሌም በሄዱበት ወቅት ሁለቱም ንግሥቶች ከሰለሞን ፀንሰው መጥተው እንደ ቅደም ተከተላቸው ምኒልክ እና ዜጋዬ የተባሉ ወንዶች ልጆች መውለዳቸው ነው።

በፊት እንዳልኩት፣ የዳግማዊ ዛጉዌ (መራ ተክለ-ይማኖት) መቀመጫ ላስታ አጠገብ ቡግና ነበር። ከዳግማዊ ዛጉዌ ጀምሮ ያሉትን የዛጉዬ ሥርወ-መንግሥት አባላትን ዝቅ ብዬ እዘረዝራለሁ። መራ ተክለ-ሃማኖት ስመ-መንግሥቱን ዳግማዊ ዛጉዌ ብሎ የሰየመው ባቦሰጡኝ አልነበረም። ዛጉዌም የንጉሥ ሰለሞን ልጅ እና ለቀዳማዊ ምኒልክ ከፊል ወንድሙ በመሆኑ እሱና ተተኪዎቹ ባጠቃላይ ለንግሥና በተለይ ደግሞ ለሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዘውድ ይገባናል ለማለት ነበር። ቀዳማዊ ምኒልክና ወንድሙ ዜጋዬ በኖሩበት ዘመን በልጅ ልጆቻቸው ሁሉ የሚፀና አንድ ውል ተዋውለው ነበር። በወንድማማቾቹ በምኒልክ እና በዜጋዬ (ዛጉዌ) መካከል ውይይት ተካሄደና ምኒልክ ዜጋዬን "ዛግዌ" ብሎ ሰይሞ ዛግዌን የላስታ ንጉሥ አድርጎ ሊያነግሠው፣ የምኒልክ ተወላጆች ብቻ ንጉሠ-ነገሥት እና ንግሥተ-ነገሥታት እየሆኑ ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት በመወከል ዙፋን ላይ ሊቀመጡ ስምምነት ተደረገ። እናቱ ሳሆይ ልጅዋን "ዜጋዬ" የለችው በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ

አማርኛ ቋንቋ ቢያንስ 3000 ዐመት እንደሆነው ይህ ስም ያረጋግጣል። ለነገሩማ ምኒልክ (ምንይልክ) የሚለውስ ቃል አማርኛ አይደል? ኢትያኤል የቀዳማዊ ምኒልክ እናት ንግሥተ-ነገሥታት ስለነበረች ልጇ ምኒልክም ነጉሠ-ነገሥት እንዲሆን ተደረገ። የዛግዌ እናት ንግሥት ዛሆይ የንግሥት ሳባ ታዛዥ ስለነበረች ዛግዌ ንጉሥ እንጂ ንጉሠ-ነገሥት መሆን አይችልም ነበር። (ይህን ስምምነት እታች ትንሽ እዘረዝረዋለሁ።) በንጉሥ ሰለሞን ልጆች መካከል ይህ ስምምነት ቢኖርም የዮዲት ባል መራ ተክለሃይማኖትና ተወላጆቹ ከዮዲት ሞት በኋላ ሰለሞናዊው ዙፋን ባዶ ሆኖ ሲያገኙት ጊዜ ነበር እኛም የሰለሞን ዘር ነን ብለው ጉብ ያሉበት።

ነገሩ አስቂኝ ቢመስልም የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ጸሀፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ ገብረ-መስቀል ዛጉዌን እንደ ንጉሥ ዳዊትም ሆነ እንደ ሰለሞን ዘር አይቆጥሩትም ነበር። ልጥቀሳቸው፡- ‹‹ዮእስራኤል ንጉሥ ግዛት ከድልነአድ መዳፍ ተፈልቅቆ ወጥቶ እስራኤላውያን ላልሆኑ ሌሎች ሰዎች ተሰጥቷል።›› (ጸሀፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ፣ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ*፣ ገጽ 22) ጸሐፌ ትእዛዙ በግልጽ የነገሩን የድልነአድ ግዛት የእስራኤል ሲሆን የዛጉዬ ግዛት ግን የእስራኤል አይደለም ብለው ነው። ሀቁ ግን የሰለሞን ዘር በመሆናቸው

የቀዳማዊ ምኒሊክ ልጆች እና ግዛታቸው እስራኤላውያን ከሆኑ ዛጉዬም የሰለሞን ልጅ በመሆኑ ልጆቹና ግዛቶቹ እስራኤላውያን የማይሆኑበት ምክንያት አለመኖሩ ነው።

ቡግና፣ አዳፋ እና ሮሃ ተቀምጠው የገዙ የዛጉዬ ሥርወ-መንግሥት አባላት ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል።

ስም	ዘመነ-ንግሥና (ዓመት)
መራ ተክለ-ሃይማኖት	13
ጠጠወ-ደም	40
አኩቴት	20
በዕምነት	20
መይራራ	49 (አንዳንዶች 15 ዓመት ይላሉ)
ሐርቤይ	49 (አንዳንዶች 8 ዓመት ይላሉ)
አሴዳ	40
ሓርቤ	40

ላሊበላ	40
ነኣኩቶ ለኣብ	40
ይትባረክ	10

የዛጉዌ/ዛጉዬ/ ሥርወ-መንግሥት ኢትዮጵያን ለ343 ዓመታት ገዝቷል። መይራራ የገዛው 15 ዓመት ብቻ ከሆነና ሀርቤ ደግሞ ለ8 ዓመት ብቻ ከሆነ የነገሠው 286 ዓመት ብቻ ይሆናል። የዛግዌ ስርወ-መንገሥት መስራች መራ ተክለሃይማኖት ለወራሾቹ እያንዳንዳቸው ከ40 ዐመት በላይ እነዳይነግሡ ደንግጎ ስለነበር ከዛ ዘመን በላይ የነገሠ አልነበረም። የላሊበላ ልጅ ይትባረክ ለ10 ዐመታት ከገዛ በኋላ በአቡነ ተክለሃይማኖት ቀስቃሽነት፣ በብዙ አማሮችና በጥቂት ኦሮሞ ወታደሮች ጦርነት ታግዞ ይትባረክን ገልብጦ፣ ስመ መንግሥቱ ይኩኖአምላክ የተባለው ተስፋእየሱስ የሰለሞንን ስርወመንግሥት በፈረሰ በ385 ዐመቱ በሸዋ ላይ እንደገና ገነባው። ተስፋእየሱስ የኦሮሞዋ የሀዊ ጊፍቲ መንዲያ እና የሰለሞን ዝርያ የነበረው በሸዋ ተደብቆ ይኖር የነበረው የአንበሳውድም ተወላጅ ነው።

የዛጉዌ እና የምኒልክ ልጆች ግንኙነትና እስራኤል

ቀደም ሲል አላይ ጀምረነው ወደ ነበረው የቀዳማዊ ምኒልክ ታሪክ ስንመለስ፣ ለምኒልክ መጥፎ፣ ለጠላቶቹ ግን መልካም አጋጣሚ ሆነና ምኒሊክ ለሃያ አንድ ዓመታት ከገዛ በኋላ በ39 ዓመቱ ህይወቱ በአሳዛኝ ሁኔታ ተቀጭቷል። እርሱና ወታደሮቹ በረሃ አቋርጠው ከዘመቻ በመመለስ ላይ ሳሉ በውሀ ጥም ተቃጥለው፣ ተገለፍልፊው ወድቀው ባሉበት ሁኔታ፣ በዛሬዋ አፋር ምድር ይኖሩ የነበሩ የእናቱ ወገኖች አዘቦዎች አግኝተዋቸው እሱን ገድለውት ተበቀሉት። ንግሥት ሳባን ተክትላ ወደ እየሩሳሌም ተገዛ የነበረችው ንግሥት ሳሆይ ከንጉሥ ሰለሞን የወለደችው የምኒልክ (የምንይልክ) ወንድም ዜጋዬ (ዛጉዌ) የወንድሙን ገዳይዎች አሳዶ ገድሎ ደሙን አስመለሰለት።

ወዲያውኑም ቶማይ የሚባለውን የምኒልክን የበሁር ልጅ በአባቱ አልጋ ላይ አስቀመጠው። ከዚያም ከምኒልክ ጋር ቀድሞ የገባውን ውል ከልጁ፣ ከአዲሱ ንጉሠነገሥት ጋር አደሰ። ውሉም ብቸኛዎቹ ህጋዊ የሰለሞን ዘውድ ወራሾች ቶማይና ትውልዶቹ ሆነው መላ ኢትዮጵያን ለሁልጊዜ እንደሚገዙ የሚያረጋግጥ፣ ዜጋዬ እና (ዛጉዌ) ዝርያዎቹ በዚያ ውል መሰረት፣ ታዛገሮቹ እንዲሆኑ የሚያነግግ ነበር። ይሁንና የዛጉዌ ወገኖችም እንደንጉሣዊ ቤተሰብ ታይተው ከግብር እና ሌሎች ግዴጆች ነፃ መሆናቸውንም ያሰምርበታል። የምኒልክ ወራሾች ከወርቅ በተሠራ መንበረ-ዙፋን ላይ ሲቀመጡ የዜጋዬ ትውልዶችም ከብር የተበጀ ዙፋን እንደሚሆንላቸው ተስማሙ። የሰሎሞን ስርወ-መንግሥት አደጋ ላይ በሚወድቅ ጊዜም የዛጉዌ ወገኖች ጠላቶቹን ተዋግተው በስልጣን ሊያቆዩትም ተዋዋሉ።

ቶማይ የሰሜን አፍሪካን አገሮች እስከ ግብፅ ኑቢያንና አረቢያን ጨምሮ ለ13 ዐመታት ከገዛ በኋላ በተወለደ በ31 አመቱ አረፈ። ልጁ ዘግዱር በ12 አመቱ በሳባ ከተማ ዘውድ ጫነ።

በዚያን ወቅት እስራኤል ለሁለት ተከፍላ እስራኤልና ይሁዳ ተብላ፣ ዘንበሪ የተባለ ንጉሥ እስራኤልን፣ ንጉሥ አሳ ደግሞ ይሁዳን ይገዙ ነበር። ያኔም በኢትዮጵያ ግዛት በሱባ ክፍለሀገር ዘራ ወይም ዘሪ የተባለ ሰው ነግሦ ነበር። እርሱም ስለ ንጉስ

ሰለሞን ገናናነት ለንግሥት ሳባ የነገራትና ወደ እርሱም የመራት የኢትዮጵያዊ ንጉሥና ነጋዴ የንጉሥ ታምሪ ልጅ ነበር። ንጉሥ ዘሪ እስራኤል ለሁለት መከፈሏን ሲሰማ ክፉኛ ተበሳጨ። ስለሆነም አስተባብሮ እንደገና ሊያቋቁማት ወሰነ። 300 ሰረገላዎችና አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያዉያን ወታደሮች አሰልፎ ወደ ዘንበሪና እና አሳ ገሰገሰ። ዘንበሪ ፈርቶ ሸሸ። አሳ ግን ይረዳው ዘንድ ለያዕቆብ አምላክ ጸለየ። ጸሎቱንም ሰምቶለት በንጉሥ ዘሪና በሰራዊቱ ልብ እግዚአብሄር ፍርሃት አሳደረባቸውና ተሸነፉ። ንጉሥ ዘሪም ሕይወቱ አለፈች። ንጉሥ አሳ በርካታ ግዳይና ንብረት አገኘ። (ዜና መዋዕል11፡8-15)

አዜ ዘግዱር (ዝግዱር) ንጉሥ ዘሪን በጣም ይወደው ነበር። መሸነፉንና መሞቱን ሲሰማ ክፉኛ አዘነ። በተቃራኒው ደግሞ በሳባ ከተማ ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን በዘሪ ሽንፈትና ሞት ፈነጠዙ። ንጉሠነገሥቱ ተናደባቸው ሌዋውያኑን አሰረ፤ ጥቂት አይሁዳውያንንም ገደለ። በዚህ ምክንያት አይሁዶቹ ዶልተውበት በተወለደ በ41 ዐመቱ ገደሉት። በእሱም ምትክ የዮሴፍ ወገን ከሆነች ሚሪያም ከተባለች ሴት የወለደውን ተዋሲያ የተባለውን ልጁን አነገሡት።

የምኒልክ ግማሽ ወንድም፣ የዛግዌ ሰሎሞን ልጅ ባራኪ፣ የዓዜ ዘግዱርን ሞት ለመበቀል ዘግዱርን የገደሉትን አይሁዳውያን

በስቅላት ቀጣ። ከዚያም ገና በሰባት ዓመቱ በናፓታና አማርና ደልታ የዓባይ ወንዝ መፋሰሻ ይኖሩ በነበሩ አስፈሪ የአማራ ጦረኞች እየተጠበቀ ራሚሱ (ራምሰስ) በሚል ማእረግ የግብፅ ፈርኦን ለነበረው አክሱማይ ዘውድ አስጫነለት። ስሟን ለዛሬዋ ሱዳን ያወረሰችው ኢትዮጵያዊቷ የአክሱማይት እናት ንግሥት ሳዶንያ፣ ቀደም ሲል፣ ልጅዋ ራሱን ችሎ እስኪያስተዳድር ድረስ ሞግዚቱ ሆና፣ በአማራ ሰራዊት ታጅባ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት ለመሆን እስከሚጠራበት ዘመን ድረስ ግብፅ ውስጥ ስትንከባከበው ነበር።

ራሚሱ (ራምሰስ) አክሱማይት ከአዜ እስያኤል በኋላ ዙፋን ላይ ከወጡት ነገሥታት ሁሉ የላቀ ንጉሠነገሥት መሆኑን አስመስክሯል። የአክሱምን ከተማ መስርቶ የዛሬ 2800 ዐመታት አካባቢ እነዚያን ዝነኞቹን ሃውልቶች አቁሟል። ልዩ መቅደስ አሳንጾ ጽላተ ሙሴን በማኖር ሌዋውያንንና አይሁዳውያንን ለአገልግሎት ሾሟል። እንደ ቅደመ ዐያቱ ምኒልክ እና አባቱ ዘግዱር በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች ቤተመቅደሶች አስገንብቶ አስርቱ ትእዛዛት የሰፈሩባቸውን ጽላት ምስሎችን አስገብቷል።

ቅድመ አያቱ ምኒልክ የፈፀመውን ስህተት በመገንዘብ ከትምአያቱ ከንግሥተ-ሳባ ወገኖቹ ከኩሽ ነገዶች ጋር እርቀ ሰላም አውርዷል። አጼ እስያኤል ቀደም ሲል ዙፋኑ ላይ ያኖረውን

የመሲሁን የወደፊት ልደት አብሳሪ የነበረውን፣ ምኒልክ አውርዶ አሽቀንጥሮ የጣለውን የዳዊት ኮከብ አንስቶ፣ በራሱ በትረመንግሥት ላይ አሰፈረው። ይህም በትረመንግሥት፣ ያእቆብ በህልሙ የበኸር ልጁ ይሁዳ ጨብጦት ያየው ምሳሌ ነው። እንዲህም በማድረጉ አጼ አክሱማይ የጥንቱን ዓርማ ወደ ቦታው በክብር መልሷል።

በሰባዊ ቋንቋ የተፃፉትን ድርሳናትና ከሳሌሙ ንጉሥ ከመልከጸዴቅ ወርዶ በምኒሊክ ታፍኖ የነበረውን *መፅሃፈ ጃንሸዋ* ለንባብ አብቅቷል። በተጨማሪም 45 የፍትህና የፍልስፍና መጻህፍት ጥንቅርና ‹‹ህትመት›› እንዲዘጋጁ በማዘዝ ሰብዊ ስነ-ፅሁፍ ሥራዎች እንዲሰራጩ እና እንዲያብቡ አድርጓል። እርሱ ራሱ የመልከጸዲቅ፣ የኢትዮጵና የንጉሥ ዳዊትም ዝርያ መሆኑን አውስቶ ተቀብሏል። ስርወ-መንግሥቱም በእስራኤል የተመሰረተው የሰሎሞን ስርወ-መንግሥት ቅጥያ መሆኑን በይፋ አውጇል። በሌሎች አገሮች የተገለሉትን አይሁዳውያን በኢትዮጵያ ሀገሮች ውስጥ አስጠግቶአቸዋል። መሬት አድሏቸውም ኢትዮጵያ እትብታቸው የተቀበረበት ምድራቸው እስክትመስላቸው ድረስ ሁኔታዎችን አመቻችቶላቸዋል። ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ግዛቶች በተሰባሰቡ ጠቢባን አናጺዎች እጅ የአክሱምን ከተማ የገነባው በዚህ ጊዜ ነበር። ይህም ታላቅ ሥራው ከቡር ስሙን እስከ አሁን

ግናና አድርጎት ይኖራል። አክሱማይ ነገርን አመዛዝኖ ለመረዳት እና ለመፍረድ የቻለ ልባም ሰው ነበረ። የድሀን እምባም ያደርቅ ነበር። ፍርድ-አዋቂ እና ሀቀኛ ሆኖ በመካከለኛው ምስራቅ የነበሩ ሀገራትን በፍትህ በማስተዳደሩ ‹‹የነገሥታት አራስ፣ የዐለም አባት›› ለመባል በቅቶአል።

እላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች፣ አይሁዳውያን በኢትዮጵያ ግዛት ከኢትዮጵያውያን ጋር ተጋብተዋል። በአክሱማይና በትውልዶቹ ዘመነ መንግሥታት ህልቆመሳፍርት አይሁዳውያን በኢትዮጵያውያን መሃል እፎይታ አግኝተዋል። እንዲሁም በልፅገዋል።

አርዕድ-አሚን በሰሎሞን ዙፋን ተቀምጦ የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት በነበረበት ዘመን መላውን ዐለም ያናወጠ ርእደ-ምድር ደርሶ ነበር። እየሩሳሌምና አካባቢዋ ስፍራዎች እንዲሁም ሰማርያ ክፉኛ ተመቱ። ኢትዮጵያም የንግሥተ-ሳባን መዲና የሳባን ከተማ አጣች። የሳባ ከተማ የታለች ለሚሉ ሰዎች፣ የሳባ ከተማ በዚህ ከባድ የመሬት ነውጥ ፊራርሳ ከመሬት በታች ተቀብራለች። አንድ ቀን ተቆፍራ ከከርሰ ምድር ውስጥ እንደምትወጣ የዚህ ታሪክ ጸሃፊ ተስፋ ያደርጋል። ኢትዮጵያውያን ወደ የመን ተሻግረው የመንን ባቀኑበት ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረችውን የሳባን ከተማ ለማስታወስ ሳባ የምትባል ቦታ ቆርቁረው ነበር።

ታዲያ ይህን ማመላከን ያቃታቸው አንዳንድ ታሪክ እናውቃለን ባዮች ንግሥተ-ሳባ የየመን እንጂ የኢትዮጵያ ንግሥት አልነበረችም፤ ይላሉ። የስህተት ስህተት ነው። ንግሥተ-ሳባ የኢትዮጵያ ንግሥተነገሥታት መሆኗን የኦሮም እና የአማራ እውነተኛው የዘር ምንጭ በተሰኘው መጽሀፌ በዝርዝር አረጋግጫለሁ። ያንን መመልከት ነው።

እግዚአብሔር ለሙሴ የዐስርቱን ትዕዛዛት ጽላቶች የሰጠበትና ሙሴም ለ40 ቀናት ሲጸልይበት የነበረውም የሲና ተራራ በዚሁ ዐለም-አቀፍ የመሬት መንቀጥቀጥ ፈራርሷል። ሙሴ ለአባበሄር ሽልሞት የነበረውም ግልባጭ ጽላትና ቀይ ባህርን የከፈለበት በትር፣ በሳባ ከተማ በዋሻ ውስጥ ተቀምጠው ሲኖሩ በእዚሁ የመሬት ርዕደት ሰምጠዋል። አንዳንድ አሜሪካውያንና እንግሊዛውያን ወንጌላውያን፣ የሲና ተራራን ማግኘታቸውን ይገልፃሉ። መዛግብት እንደሚጠቁሙት የሲና ተራራ ከምድር በታች ወርዷል። በዚሁ አደጋ ሳቢያ በፍልስጥኤም ረሃብና በሽታ ሰፍኖ ብዙ ሰዎችን ጎድቶአል። በዚህን ጊዜ ኢትዮጵያዊው ንጉሠነገሥት አርእድ -አሚን እስራኤላውያን ወገኖቹን አስታወሰ። ለአይሁድ ንጉሥ ለአዚያ እና ለእስራኤል ንጉሥ ኢዮርባም በ500 በቅሎዎችና ፈረሶች እንዲሁም በ700

ግመሎች የተጫኑ ደረቅ በለስ፣ ወይን፣ ስንዴና ገብስ አስጭኖ ከሀዘን መግለጫ ደብዳቤ ጋር ወደ እስራኤል ላከላቸው።

25ኛው የአርእድ-አሚን ንግሥ-በዓል በሚከበርበት ወቅት የአሞስ ልጅ ነቢዩ ኢሳያስ በግብጽ በኩል ወደ ኢትዮጵያ በመንገዘ ላይ ሳለ ኒካው በተባለ ግብፃዊ ጦር መሪ ተይዞ ወደ ግብፅ ተጋዘ። አፄ አርእድ-አሚን 15000 ዘማቾች ልኮ ነቢዩ ኢሳያስን አስፈትቶና ነካውን በሰንሰለት አስሮ ከኢሳያስ ጋር ወደ አክሱም አስመጣው። ነቢዩ ኢሳያስ እየተነበየና እያስተማረ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሦስት ዓመታት ኖረ። ከሦስት ዓመታት ቆይታው በኋላም አፄ አርዕድ-አሚን ብዙ ምግብና ለስለሞን ቤተመቅደስ የሚሆን ወርቅ አስይዞ ወደ እስራኤል መለሰው። (አማን በላይ፣ ዝኪማሁ፣ ገፅ 291-993) እየሱስ ክርስቶስ በመርዌ አቋርጦ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ሲያቅድ በግብጽ ለእሱ፣ ለእናቱ ለማርያም እና ለዮሴፍ ጥገኝነት ሰጥቶአቸው የነበረው ኢትዮጵያዊው ወዳጁ ንጉሥ አማናቱ ተትናይ ለምን ወደ ኢትዮጵያ መሄድ እንዳለበት ጠየቀው። እየሱስም፣ ነቢዩ ኢሳያስ ለሦስት ዓመታት በኢትዮጵያ በእግሩ እየተዘዋወረ ያስተማረውና የሰበከው፣ እኔ አሁን ኢትዮጵያ ሄጄ በእግሬ እየተዘዋወርኩ የማስተምረውን እና የምፈውሰውን በተግባር ለመተንበይ ስለሆነ፣ ትንቢቱን ለማስፈጸም እኔም እንደ ነቢዩ ኢሳያስ የግድ ወደ ኢትዮጵያ መሄድ አለብኝ፤ ሲል

መልሶለት ነበር። እንደተናገረውም እየሱስ ክርስቶስ ክንዮሥ አማናቱ ተትናይ ልጅ ከማርሔር እና ከታላቅ ወንድሙ ልጅ ከዲማስ ጋር ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ተጉዞ፣ ለሦስት ዓመታት የሀዋርያ ተግባር አከናውኖ፣ ኢትዮጵያውያን በቀላሉ እና በቀጥታ በእሱ እንዲያምኑ አመቻችቶላቸዋል። እንዲሁም ከእስራኤል ሕዝቦች አስቀድሞ ራሱን ገልጾላቸው አክብሯቸዋል።

ራሔብ፣ ነብዩ በልአም፣ ሩት እና የዳዊት እናት አዶልያ

ወደ ሙሴ መጨረሻ የህይወት ዘመን ተመልሰን ስለልጆቹ ለማውሳት፣ ልጆቹ በመሆናቸው ዘሌዋውያን ካህናት የነበሩት ጌርሾም እና አልዓዛር እንዲሁም የሊቀ ካህኑ የዮቶርአብ ሴት ልጅ ሲፓራ ጥብቅ ትስስር ከነበራቸው ከቢንያም ነገዶች ጋር ተቀላቅለው ከእስራኤላውያን ጋር ለመኖር ኬብሮን ገቡ። የሙሴ ልጆችም ሌዋውያን ስለነበሩ መሬት አላገኙም። ኢትዮጲስ፣ ኮራብ ኮረብታ ግርጌ ባሳነጸው ስያሜ ሴት ልጁን ቴስቢያ ብሏት ስለነበር፣ እነርሱም መኖርያቸውን ቴስቢያ አሉት። ነብዩ ኤልያስ በኋላ ዘመን ከዚሁ ከቴስቢያ ነው የተነሳው። የኢትዮጵ ዘር፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እንደነበረ ይነገራል። ‹‹ቴስቢያ›› የተባለው ስም የተገኘው ከኢትዮጵ 10 ወንዶች ልጆች ከ‹‹ቴስቢያ›› ነው።

ስለዚህም ቴስቢያዊው ኤልያስ እና የተወለደበት ስፍራ ከኢትየጵና ከልጁ ከቴስቢያ ጋራ አንድ ዐይነት ዝምድና እንዳላቸው ይህ ስም ይጠቁማል።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ የሙሴ ልጆች ሰልሞን (ንጉሥ ሰሎሞን አይደለም፤) አግብታት ቤተልሔም አቅራቢያ ቀራንዮ በሚባል ስፍራ (በሁዋላ እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት) ከወለደችለት ከራሃብ (ራሔብ) ልጆች ጋር ተጋቡ። ራሃብ፣ ሰልሞንና ካሌብ ኢያሪኮ ከተማ ውስጥ ለስለላ በተሰማሩበት ጊዜ ሊያዙ ሲሉ የደበቀቻቸው ሴት መሆኗ ይታወሳል። ላደረገችላቸው ውለታም የእስራኤል ወራሪዎች በሚዘምቱባቸው ወቅት እንዳይተናኩሏቸው ሃምረዊ ቀለም ያለው ክር ለምልክት በእርሷና በቤተዘመዶቿ በሮችና መስኮቶች ላይ እንድንታንጠለጥል መከሯት። በተጨማሪም ዘመዶቿን ሰብስባ እሷ ቤት ውስጥ እንድትደበቅ ነገሯት። ይህን ምክራቸውን በመቀበሏም እሷ እና ዘመዶቿ ከዝርፊያና ግድያ ተርፈውል። እያሪኮ በድል ከተመታች በኋላም ሰልሞን ራሃብን አገባት። እነዚያን ክሮች እና ተምሳሌትነታቸውን በማሰብም በልጆቿና በልጅ ልጆቿ በቦኤዝ እና ኢዮቤድ አንገቶች ላይ ክር ማሰር ጀመረች።

ንጉሥ ዳዊት፣ የእሱ አባት እና ቅድመአያት፣ ማለትም ቦኤዝና አቤድ እንዳደረጉት እርሱም በመታሰቢያነት አንገቱ ላይ

ክር ያስር ነበር። የሙሴም ልጆች ያን ወግ ተከትለዋል። እናም ይህ ሃምራዊ ቀለም ያለው ክር አንገት ላይ ማሰር ለዳዊት ቤተሰብና ትውልዶቹ በተለይም ለሙሴ ወገኖች ውርስ ባህል ሆነ። ከ500 ዓመታት በኋላም የሙሴና የአብርሃም ቤተሰቦች ከቢንያምና ሌሎች እስራኤላያውን ጋር ከቤተልሔም ከጋዛ ተነስተው ምኒልክ ሰሎሞንን አጅበው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፣ ኢትዮጵያውያን በኋላ ማተብ ያሉትን ያንን ክር በአንገት የማሰር ባህል ወደ ኢትዮጵያውያን አሸጋገሩ። ቀስ በቀስም፣ ያ ማተብ ከእየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት የዳዊት ቤተሰብ መታወቂያ፣ በክርስትና ዘመን ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታዮች፣ በሚልዎን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መለያ ሆነ።

ከዚህ ከማተቡ ጋር አያይዤ ስለዳዊት ኮከብ ጥቂት ማውሳት ግድ ይለኛል። የዳዊት ኮከብ እንዴት በእስራኤል አገር እንደተገኘ በርካታ ሰዎች አያውቁም። ጥንታውያን ኢትዮጵያውን ግን ያውቃሉ። የዳዊትን ኮከብ የሠራችው ሩት ነበረች። ምንም እንኳ በእስራኤል ጎን ባለው ምድር በሞአብ ሩት ብትወለድም፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊት ነበረች። የኑብዩ በልዓም የልጅ ልጅ ነበረች። በልዓም ራሱ የኢትዮጵያዊነት ዝርያ ነበረው። አባቱ ዳግማዊ ቢኦር የሚባል የኢትዮጵ ዘር ነበር። አሱም በጎጃም ውስጥ ቀራሚድ የሚባል ልጅ ወልዶ፣ ቀራሚድም ሸምሸል የተባለችውን ነቢይ

ወልዶ ነበር። እሷም ደሸት የተባለ ነቢይ ወልዳ፣ ደሸትም የኦሮሞና አማራ አባትና አያት ለመሆን በቅቷል። የበልአምን የዘር ግንድ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

የሳሌሙ ንጉሥ መልከጸዲቅ ልጅ የኢትዮጵያውያን አባት ኢትዮጵ ቢኦርን ወለደ፤ ቢኦር አራምን፣ አራም ናዬን፣ ናዬ ሃዬን፣ ሃዬ ዳግማዊ ቢኦርን ሲወልድ ዳግማዊ ቢኦር በበኩሉ በልዓምን አፈራ። (አማን በላይ፣ *ሀገዘዊ ቀዳማዊ የኢትዮጵያውን መስተዋት ታሪክ* ገጽ 41)

ስለ መሲሁ ልደት በልዓም ተንብዮአል። ከዘር ግንዱ የሳሌም ንጉሥ መልከጸዲቅ በወረሰው ማእረገ-ክህነቱ በልዓም የመመረቅም፣ የመርገምም ስልጣን ነበረው። አህዛብ ጠላቶቿ እስራኤልን እንዲረግምላቸው ተማፅነውት ሳለ እግዚአብሔር እንዲመርቃቸው አዘዘው። (ዘሕልቆ፣22-24) እግዚአብሔር የመሲሁን ሞገስ በኮከብ ምስል ፈንጥቆለታል። ኮከብ ከያእቆብ (እስራኤል) እንደሚነሳም አመላክቶታል። ስለሆነም ለእስራኤል ጠላቶች እንዲህ ሲል ተነበየባቸው።

‹‹አየዋለሁ፤ አሁን ግን አይደለም። እመለከተዋለሁ፤ በቅርብ ግን አይደለም። ከያእቆብ ኮከብ ይወጣል፤ ክእስራኤል በትር ይነሳል። (ዘሐልቆ፣ 24፡17) ‹‹ከያእቆብ የሚወጣው ኮከብ ገገር

ይሆናል። (ዘ ሐልቆ፤ 24፡ 19) ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት፣ በልዓም ከመወለዱ ከ650 ዐመታት በፊት ከማንም ቀድሞ መልከጸዲቅ ኮከብ ተመልክቷል። ለልጁ ለኢትዮጵም ትውልዶቹ ኮከቡን ተከትለው፣ ራሱ መልከጸዲቅ እንዳደረገው እነርሱም ከእለታት አንድ ቀን በስርዓተ-አምልኮ ወቅት፣ ኮከቡ ለሚሰግድለት እንዲሰግዱለት መመሪያ ሰጥቶታል። ሆኖም የተመለከተው ፋና ወጊውን ኮከብ እንጂ ወደ ሰላሙንጉሥ የእስራኤልና የዓለም መሲህ የሚመራውን ሕያው ኮከብ አልነበረም።

የፍሊቪያስ ጆሴፈስ ድርሳን (ዝንቱ ክማሁ፣ምእራፍ 6) ይህን የመሲሁን ኮከብና ልደት ሳይጠቅስ፣ የበልዓምን ድርጊትና አጣብቂኝ ይዘረዝራል።

የኮከቡን፣ የመሲሁን ከእስራኤል መነሳት ሩት ተገንዝባለች። በዚያ ዘመን ሁሉም ኢትዮጵውያን ሴቶች ይመኙ እንደነበረው እርሷም የመሲሁ እናት ለመሆን ትጓጓ ነበር። ሩት ያገባችው አይሁዳዊ ነበር። ግን ሞቶባታል። ሆኖም ባሌ ሞተ ብላ ከባሏ እናት ከናዖሚ በፍጹም አልተለየችም። ሁለቱ ሴቶች እንደ እናትና ልጅ ሆነው ሳይነጣጠሉ ኖረው ነበር። ስሎሚም ከሰልሞንና ከረሃብ (ራኬብ) ለተወለደው ቦአዝ ዘመዱ ነበረች። በኋላም ቦአዝ ሩትን አግብቶ አዮቤድን ወለዷል። ኮከቡ ለበልዓም፣ እንዲሁም ለናዖሚና ለራሷ ለሩት በራዕይ

ተገልጸላቸዋልና እይታውን በልቦናቸው ቀርፀው እንዲያኖሩ፣ ሩት ምስሉን አሠርታ በልጇ አንገት አጥልቃለች።

በመረጃችን መሰረት ሩትና ናሆሚ አንድ ላይ ተኝተው ሳሉ፣ አንድ አይነት ራእይ አይተዋል። በቀጣይ *Promise Fulfilled,* (የተፈጸመው ቃልኪዳን) በሚል ርእስ በእንግሊዝኛ በማቀርበው የግጥም መጽሃፌ ራእያቸውን አንድ ገጸባህርይ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል።

ሩትና ናሆሚ

ባንድ አልጋ ተኝተው፣

የጋራ ህልም ዐዩ

ባንድ ተቀራኝተው።

የሰላሙን ንጉሥ፣

የመሲሁን ውልደት የኡቤድን ጭምር፣

ነበረ ሁለቱ ያዩት ተመሳሳይ

አንድ ህልም በጥምር።

እኒህ ሁለት ሴቶች፣

አብረው እንደተኙ፣

ከምስራቅ ተነስቶ ሲንገዘ ቤተልሄም፣

ስድስት ቀስቶች ያለው አንድ ኮከብ ቃኙ፣

ወደ ሩት ማሕጸን

እያነጣጠረ፣

ጨረሩ ሆን ብሎ

የሩትን ማሕጸን ይነካው ነበረ።

የሰው ቅርጽ ነበረው ታዲያ ያ ኮከቡ፣

እራስ፣ እጅና እግር፣ ለአይታ የሚያስፈራ፣

በድቅድቅ ጽልመት ውስጥ፣

ለመላው ዐለም የሚያበራ።

ለሩትና ናሆሚ

ልዩ ህልም ነበር ያልተለመደ፣

ስድስት ቀስት የያዘ፣

ለሩት አንድ ህጻን ስለተወለደ።

ይህን ዐንድ ዐይነት ህልም፣

ሩትና ናዖሚ አንድነት ስላዩ፣

እንዲፈታላቸው

ለእግዚአብሄር ጸለዩ።

እግዜር እንደዚህ ሲል

ፈታላቸው ህልሙን

ከሩትና ቦአዝ እንደሚወለድ ልጅ፣

ሲጠበቅ የኖረ፤ የሚያድን ዐለሙን።

ስድስቶች ቀስቶቹ የሚያመለክቱት፣

ስድስት ሰማይ ናቸው፣ እሱ ፈጠራቸው፣

እውነት ያስተምራል፤

ለመላው የሰው ዘር ይሆናል ቤዛቸው፣

ወደ ብሩህ ብርሀን ራሱ እየመራቸው።

ይህ ኮከብ የሩትን ጠቢባን ዘመዶች፣

ያኔ ሚሆኑትን በኢትዮጵያ ንጉሦች፣ ከኢትዮጵያ ቀስቀሶ፣

ህጻኑ ሲወለድ፣ እሱ ወዳለበት፣

እሱ እየመራቸው ይቆማል አድርሶ።

መሲህ የሚሆነው ይሄ ብርቅዬ ልጅ፣

ከሰማይ ይወርዳል። የስድስቶቹ ቀስት

ሲገለጥ ሚስጢሩ---

በስድስት ቀኖች ውስጥ፣

እሱ ይችን ምድር አቅዶ መፍጠሩ።

ስለዚህ አንቺ ሩት

በስድስት ቀስት እራስ ኮከብ እንድትሠሪ፣

በወርቅና በብር ካስጌስጥሻቸው ኋላ፣

በኦቤድ አንገት ላይ ለትውስታ እሰሪ።

ሩትም በኩሏ

የዛን የህልም ፍቺ እንዳው ሰምታ አልቀረች፣

ያንን ኮከብ ሠርታ፣

በልጇ አንገት ላይ ሲወለድ አሰረች።

እየቤድ እሴን ከሸማይ፣ ኢትዮጵያዊያን ‹‹ሰማይ›› ከሚሏት፣ (ምናልባትም ኢትዮጵያዊት የሆነች) ወለደ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ወደ ኋላ ተመልሰን፣ በእርጅና እድሜው ንግሥተ-ሳባ በገደለችው በታላቁ ኢትዮጵያዊ ንጉሠ ነገሥት እሴ ስም ልጇን መጥራቷ የኢትዮጵያዊ ደም ቢኖራት ነው። የኢዮቤድ ልጅ እሴ በእስራኤላውያን ዘንድ አዴል ወይም አዶሊያ፣ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሃብሌ (አብሌ) የምትባለውን ኢትዮጵያዊት አግብቷል። (አማን በላይ *መፅሃፈ ክቡር*፣ ገፅ 44-47)

በእኛ መረጃ መሰረት፣ የእሴ እናት የሞአብ ንጉሥ ልጅ ናት። ዓዶሊም የሚባለው አካባቢ የእሱ ግዛት ነበር። በሚጽፅ ከተማ ነዋሪ ነበር። እንደ ሩት፣ ዮቶርአብ (የሙሴ አማት) እና ሌሎች ትውልደ ኢትዮጵያውያን በዜግነቱ ሞአባዊ ቢሆንም ግን በደም ኢትዮጵያዊ ነበር። ሌሎቹ ኢትዮጵያውያንም በሞአባውያን

እና በምድያማውያን መሃል በመወለዳቸው፣ ሞአባውያንና ምድያማዊያን ተብለዋል።

መጀመርያ ላይ ዳዊት፣ ወንድሞቹና የቤተሰቡ አባላት፣ በአዶለም ዋሻ አስተማማኝ መሸሸጊያ አግኝተዋል።

‹‹ዳዊት ከዚያ ተነሳ፤ ወደ አዶለም ዋሻ ኮበለለ፤ ወንድሞቹና የአባቱ ዘመዶች ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ ወደ እዚያ ሄደው ተቀላቀሉት። (1 ሳሙኤል፣ 22) ዳዊትና ቤተሰቡ በዚያ መጠጊያ ያገኙበት ምክንያት፣ ቀደም ሲል እንደተመለከተው፣ ዓዶለም የዳዊት አያት፣ ማለትም የእናቱ አባት ግዛት በመሆኑ ነበር።

በፊት እንደ ተገለጸው፣ የዳዊት እናት አዴል መጠሪያ ስሟ ሃብሌ ነበር። ሆኖም አዴል እና አዶልያ በመባል የታወቀችበት ምክንያት ዳዊትና ቤተሰቡ ከንጉሥ ሳያል ሸሽተው የተደበቁባት ዓዶለም የዳዊት አያት መናገሻ ከተማ ስለሆች ነበር። ዳዊት የአዶለምን ዋሻ ሲለቅ፣ አያቱን የሞአብን ንጉሥ ወላጆቹን እዚያው እንዲያቆይለት ተማጸነው።

‹‹ዳዊትም ከዚያ ከሞአብ ምድር ወዳለችው ወደ ሚጽጳ ሄደ። የሞአብን ንጉሥ እግዚአብሔር የሚያደርግልኝን እስካውቅ ድረስ አባቴና እናቴ ከአንተ ጋር ይቀመጡ ዘንድ እለምንሃለሁ፤›› አለው፡ : *(መፅሃፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ*፣ 22፤ 3-4) የሞአብ ንጉሥ፣

ትውልደ ኢትዮጵያዊ የአዶልያ እና የራሱ የዳዊት አያት ባይሆን ኖሮ፣ ዳዊት እሱን አምኖ ወላጆቹን ከንጉሥ ሳያል ቁጣ እንዲሰውራቸው ከሱ ዘንድ በአደራ ባላስቀመጣቸው ነበር። ስለዚህ በእርግጠኝነት ትውልደ ኢትዮጵያዊው የአዴል አባት፣ የዳዊት አያት ነበር ማለት ነው። ያ ባይሆን ኖሮ፣ ንጉሡም ቢሆን የዳዊትን ቤተዘመዶች ባላስጠጋቸው ነበር። ንጉሥ ሳኦል በጦር ኃይል ሊቀጣው ነበርና። ዳዊትን ቤተሰቡ የእሱ የራሳቸው ደምና ስጋ በመሆናቸው ግን የመጣው ይምጣ ብሎ አስጠግቷቸዋል።

በእኛም ኢትዮጵያውያን፣ በእየሱስ ክርስቶስ እና በእናቱ በቅድስት ማርያም ደም ስሮች ውስጥ ኢትዮጵያዊ ደም በመዘዋወሩ፣ ከሁለቱም ጋር የስጋ ዝምድና አለን ማለት ነው። አዴል (ሃብሌ፣ አብሌ) ‹‹ቀይና መልከመልካም›› *(መፅሃፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣* 16፡12) የሆነውን ንጉሥ ዳዊትን ወለደች። እንደ መደበኞቹ እስራኤላውያን ቆዳው ነጭ ያልሆነው በውስጡ የኢትዮጵያ ደም ስለነበረው ነው። በደም ስሩ የሚንኳለለው የሴት ቅም አያቱ፣ ቅድም አያቱና እናቱ፣ ‹‹ጥቁር ደም›› ተክለዛላውን በሚገባ አጉልቶ ያንጸባርቅ ነበር። በዚህም ምክንያት ነው ልጁ ንጉሥ ስለሞን፣ በመኃልየ መኃልየው ውስጥ ስለራሱ ጥቁርነት ውበትና ምኒልክ የተሰኘ ጥቁር ልጅ ስለወለደችለት ስለ ንግሥተ-ሳባ ጥቁረት የሚዘምረው። የሰለሞን እናት፣ ቤርሼባም ኩሻዊት

መሆኗ መዘንጋት የለበትም። ያም ሆኖ ይህ የዳዊት እናት እና አያት የኢትዮጵያ ዝርያ ያለባቸው ጥቁሮች የመሆናቸው ክስተት ነጭ ላልሆኑ በዐለም ዙርያ ላሉ ክርስትያኖች ልዩ ትርጉም ወይም አንድምታ አለው። በእየሱስ ክርቶስ ደም ስር ውስጥ ‹‹ጥቁር ደም›› መፍሰሱ፣ እየሱስ ክርስቶስን ባለሰማያዊ ዐይኖችና ባለብጫ አስተኔ ጸጉር ነጭ ወይም አንግሎ-ሳክሶን አስመስለው ለሚስሉት ዘረኞች አፍ መዝጊያ ነው። ለኛ ለኢትዮጵያውያን ክርስትያኖች ደግሞ ልዩ ትርጉም አለው።

ኢዩቤድ ሲሞት ሩት ያበጀችውን ያንኑ ኮከብ አዴል (የኛይቱ ሀብሌ) ለዳዊትም አጠለቀችለት። የእስራኤልን መሲህ የሚመስለው ኮከብ፣ ከቶውንም የማይደበዝዘው ኮከብ ለበልዓም ተወላጅ ለኢትዮጵያዊው ነቢይ፣ ለኦሮሞ እና አማራ አባትና አያት፣ ለደሽት በዓባይ ወንዝ ዳርቻ በተመስጦ እየጸለየ ሳለ በውሃው ላይ የተንጸባረቀለት ኮከብ መሆኑ አያጠራጥርም። እላይ እንደተስተዋለው፣ ያንንም ኮከብ እና የመሲሁን እናት ምስል የወርቅ ሰሌዳ ላይ ቀርጾ ወደ ጠቢባን ነገሥታት፣ (ሰብአሰግል) ልጅቱ አስተላልፏል።

የቤተእስራኤል ስልጣን፣ ሌዋውያን እና ክርስትና በኢትዮጵያ

የአይሁዳዊያን ወደ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፍልሰት የተፈጸመው ሙሴ ራሱ በህይወት እያለ የዛሬ 3500 ዐመት አካባቢ ነው። እሱም የዮቶርአብ የልጅ ልጅ ኢትዮጲስ አንድ የጽላተ ሙሴን ግልባጭና ሙሴ የሸለመውን የቀይ ባህርን የከፈለበትን በትረ-ሙሴን ይዞ ከምድያም ተነስቶ፣ በኢትዮጵያ ላይ ሊነግሥ ስርዓተ-ንግሥናውን ለማስፈጸም ወደ ኢትዮጵያ በገባበት ዘመን ነበር።

ሁለተኛው ፍልሰት የተከሰተው ወጣቱ ቀዳማዊ ምኒልክ ዋናውን ጽላትና 40,000 (አርባ ሺህ) እስራኤላዊያንን ይዞ በመጣበት ጊዜ ነበር።

ሶስተኛው ደግሞ የዛሬ 2500 ዐመት ኤርሚያስ በእስራኤል ሊቀ-ነብያት በነበረበት ሰዐት የባቢሎን (የዛሬው ኢራቅ) ንጉሥ ናቡከደነጾር እስራኤልን ወርሮ፣ የሰለሞንን ቤተመቅደስ አፈራርሶ፣ መጻህፈቱን አቃጥሎና ህዝቡን በሰንሰለት አስሮ ወደ ባቢሎን ባጋዘበት ወቅት ነበር። የእነዛን የባቢሎናዊያን እና የግበረአበሮቻቸውን የካሌዳውያንን ወረራ የተረፉትን እስራኤላውያን አምላካቸው ወደ ግብጽ አትሂዱ ብሎ በፊት ቢያስጠነቅቃቸውም፣ ገሚሶች ወደ ግብጽ ሸሽተው በርሀብ ከማለቃቸው በተጨማሪ በግብጹ ፊርኦን ኦፍራህ ሲጨፈጨፉ ሌሎቹ ገሚሶች ወገኖቻቸውን ወደ አሉበት እና ወደ እምንከበርበት ወደ ኢትዮጵያ እናምራ ብለው ወደ ኢትዮጵያ አቀኑ። ከነሱ ውስጥም ‹‹የሰማይዋ ንግሥት›› ተብላ የምትታወቀውን የግብጻውያንን የሲት ዐምላክ ዐምልኮ ቢባሉ አሻፈረኝ ብለው ወደ ኢትዮጵያ የሄዱት የዳን እና የቢንያም ነገዶች፣ እንዲሁም ሌዋውያን ካህናት ተገኝተውባቸው ነበር።

እነዚህ ሁሉ ቤተ-እስራኤሎች በኢትዮጵያ ላይ ሰፍረው፣ ታፍረውና ተከብረው ለረጅም ዘመናት በሰለሞናዊው ንጉሠነገሥት መንግሥት ግዛት እና በቤተክህነት አስተዳደር ውስጥ ገብተው፣ ቀድመው ከነበሩት ወገኖቻቸው ጋር ተደባልቀው ቁልፍ ቦታ ይዘው ኖረዋል። ከስልጣናቸውም ብዛት፣ ንጉሥን ይሾሙና ይሽሩ

ነበር። ከዛም አልፈው ተርፈው ነገሥታት ላይ ሞት የመፍረድም ጉልበት ነበራቸው። ለምሳሌ፣ እቴ ሀንደኬ ጣን የተባለችው ንግሥተ-ነገሥታት በእየሱስ ክርስቶስ አምና፣ በቅዱስ ማቴዎስ እጅ ከነቤተሰብዋ እና ሰራዊቷ ተጠምቃ ፍፁም ክርስትያን ሆና ትኖር ነበር። ክርስትያን በሆነች በ13 ዐመትዋ ክርስትያንነቷን ያልወደዱላት ሌዋውያን ሊያጠፏት አሰፈሩ አጋዝያንን እና ፈላሻዎችን አስነስተውባት፣ ወንድሟን ከተብን አጼ ባህር-ሰገድ ንጉሠነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ብለው በላይዋ አነገሡባት። ከዛም እስዋን፣ ባልዋን እና ልጆቿን ገድለው አቃጠሏቸው። እነሱም ሰማዕትነትን ተቀበሉ። በምድረ ኢትዮጵያ የአግአዝያን እና ፈላስያን ስልጣናቸው ይህን ያህል ነበር።

የአግአዝያን እና ፈላሾች፣ በጠቅላላው የቤተእስራኤል በኢትዮጵያ ውስጥ የነበራቸው ስልጣን ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊም ነበር። የኢትዮጵያ ሌዋውያን ስልጣን እስራኤል ሀገር ከነበራቸው ስልጣን ይበልጣል ማለት ማጋነን አይደለም። ለምሳሌ በእስራኤል ሳሉ በራሳቸው ችሎታ ንጉሥ የማውጣት ወይም የማውረድ ሥልጣን አልነበራቸውም። ኢትዮጵያ ውስጥ በነገሥታት እጣ ፈንታ ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ ነበር። በእዚህ ምክንያት በልዑላን ቤተሰቦች ዘንድ ይታፈሩና ይፈሩ ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው የሶስት ዐመታት ቆይታው ምንም

ክርስትናን ኢትዮጵያ ውስጥ ያስገባው ራሱ የክርስትና ሀይማኖት መስራቹ እየሱስ ክርስቶስ ቢሆንም ኢትዮጵያን ሊለቅ አንድ ዐመት ሲቀረው እነዚሁ ሌዋውያን በቅናትና ለምን ጥፋታችንን አጋለጠው በማለት ተተናኩለውት ተይዞ እንዲታሰር ለንጉሡ ለአጼ ባዚን ልጅ ለራስዳሽ ከሰሱት። ንጉሡም ልዩ ጦር ሰራዊት ልኮ ሊያስይዘው ሞከረ። ስለእዚህ እየሱስ መስወር ጀመረ። ራስዳሽ የሌዋውያኑን ምኞት ሊያስፈጽም የተነሳው ወይም ያስመሰለው ሌዋውያኑን ፈርቶ ነው። በይፋ እንደዚያ ቢያደርግም፣ እየሱስን በሚስጥር ተገናኝቶ በእሱ አምኖአል የሚል ጽሁፍም አለ። ይህም እውነት ነው የሚያሰኘው ይህ ንጉሠነገሥት ሥልጣኑን ለእህቱ ለቶ ከጥቂት ዐመታት በኋላ መመነኑ ነው። የአንደኛዋ ሀንደኬ ጃንደረባ፣ ሀዋርያው ፊሊጶስ በጋዛ፣ ሰረገላው ውስጥ ተቀምጦ የነቢይ ኢሳያስን ትንቢት ሲያነብ አግኝቶት ያጠመቀው ኢትዮጵያዊም ክርስትናን ለኢትዮጵያ አስተዋውቆ ነበር። የእሱንም ፈለግ ተከትለው በመከታተል የእየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት በርጠለሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ እንድርያስ፣ ቶማስ፣ ናትናኤል ተራ በተራ እና ባንድነት ወንጌልን አስተምረው፣ አጥምቀው እና አቁርበው ነበር። ሆኖም በኢየሩሳሌም የነበሩት ሌዋውያን እየሱስን እንደገደሉት ሁሉ ኢትዮጵያም የነበሩት ሌዋውያን ቃሉን እና ደቀመዛሙርቱን ተቃወሟቸው። በኋላም ክግብጽ ጀምሮ የእየሱስ ክርስቶስ ‹‹አብሮ-አደግ›› የነበረው የንጉሥ አማናቱ ተትናይ ልጅ

ማርሔር፣ እና የአጎቱ ልጅ ዲማስ ከእየሱስ ክርስቶስ ጋራ ለሦስት ዐመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ቆይተው እሱ ኢትዮጵያን ከለቀቀ በኋላ በኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ አስተምረዋል። የሚያሳዝነው ነገር እነዛው ሌዋውያን ተቃወሟቸው። ቅዱስ ዲማስንም በመጨመረሻ በእሳት አንድደው አቃጠሉት። ምንም እንኳን የተለያዩ የኢትዮጵያ ጎሳዎችና ነገዶች በእየሱስ ክርስቶስ የቀድሞ ሥራና እና በደቀመዛሙርቱ ስብከት ክርስትናን የተቀበሉ ቢሆኑም እነዚያኑ ሌዋውያንን በመፍራት ክርስትና በይፋ በኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት መንግሥት ሳይታወጅ ከ333 ዐመታት በላይ ቆይቷል። ከዛ በኋላ ግን በንግሥት አብርሂት እና በመንትያዎቹ ልጆችዋ በአብርሀ እና አጽብሀ አማካኝነት ክርስትና በይፋ የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት መንግሥት ሃይማኖት ሆነ።

ክርስትና የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት መንግሥት የሆነው ግን አሁንም ሌዋውያኑን እና እነሱ የሚያነሳሱአቸውን አይሁዳውያንን በመስጋት በታላቅ ጥንቃቄ ነበር። የአብርሀና አጽብሃ እናት ንግሥት አብርሂት በጣም ትልቅ አማኝና መንፈሳዊ ክርስትያን ነበረች። በእዚህ ምክንያት መንትያ ልጆችዋን በክርስትና እምነት ኮትኩታ ነበር ያሳደገቻቸው። እነዚህ ተዋደውና ተፋቅረው በስምምነት በፈረቃ የነገሡት ወንድማማቾች ክርስትናን ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን እንደ ኑብያ ባሉት የኢትዮጵያ ሀገራት

ጭምር በይፋ አውጀው አስፋፍተዋል። 130 በላይ ቤተክርስትያናትንም አንጸዋል። ብዙ ዲያቆናትና ካህናት እንዲኖሩም አመቻችተዋል። ዳሩ ግን ይህን ሁሉ የተቀዳጁት እንዲሁ በቀላሉ አልነበረም። ሌዋውያኑን ካህናት ማሳመን ነበረባቸው።

በእዛን ጊዜ በዙፋኑ ላይ የነበረው አጼ አብርሀ ስለነበረ፣ በክርስትና እምነቱ እየጠለቀ ሲሄድ ክርስትና ኢትዮጵያ ውስጥ ስር እንዲሰድ ፈለገ። ስለዚህ በ332 ዓ.ም በአክሱምና ከአክሱም ውጪ በሉ መንደሮች ቀድሞ የኦሪት አብያተመቅደስ ከኦሪት ህግና ሥርዐት ወጥተው በአዲስ ኪዳን በቅዱስ ወንጌል ህግና ስርዐት እንዲቀየሩ አጼ አብርሀ አወጀ። የአክሱም የኦሪት ቤተመቅደስ አገልጋይዎች ሌዋውያን እና አይሁዳውያን መኳንንትም በግዳጅ ሳይሆን በውዴታ ወንጌልን እንዲቀበሉ ተጠየቁ። በዙዎቹ ይህን ተቃውመው ከነጭራሹ ንጉሡን ስለተሳደቡ ተቀጡ። የተረፉት ከአክሱም ሸሹ። አጼ አብርሀና ወንድሙ አጽበሃ ፍቃዳቸው እንዲፈጸም ሌላ አቅድ ለመንደፍ ተገደዱ።

አብርሃና አጽብሃ የነደፉት አዲስ አቅድ ችግሩን በሃይማኖታዊ ውይይት ንግግር መፍታት ነበር። ይህንንም ለመተግበር ያለፈው እክል በተከሰተ በዐመቱ ሁሉን አማኝ ያካተተ ስብሰባ በአክሱም ጠሩ። ጥሪውንም አክብረው አያሌ የአይሁድ እና

የክርስትና እምነቶች ተከታዮች ተሰበሰቡ። የብሉይንና የሀዲስን መጻህፍት በጋራ ይዘው በጥልቀት መርምረው፣ ስለ መሲሁ እየሱስ ክርስቶስ መወለድ፣ የሰውን ልጅ ማዳን፣ በፍቃደኝነት መሞትና ከሞት መነሳት የአሪት ነብያት ተንብየውት የተፈጸመውን ሁሉ ለመረዳት ቻሉ። ይህንንም በማድረጋቸው በፊት ፍንክች ያላ ቢላዋ ልጅ ብለው አስቸግረው የነበሩት ሌዋውያን እና ምእመኖቻቸው እየሱስ ክርስቶስ ይጠብቁት የነበረው መሲሀቸው መሆኑን አስተውለው፣ በእየሱስ ክርስቶስ አምነው፣ ከዚህ በፊት ንጥሣቸውን አብርሀን አውከውት ስለነበረው ይቅርታ ጠይቀው ታረቁት። ሆኖም አሁን ክርስትናን ቢቀበሉም ከጥንቱ አሪት ከወረሷቸው ስርአት ውስጥ ክርስትናን የማይቃወሙትን ህግጋት፣ ስርአቶች፣ አልባሳት እና ንዋየ ቅዱሳት ወደ አዲሱ እምነታቸው እንዲዘዋወርላቸው አመለከቱ። አብርሀና አጽብሀ እና በክርስትና እምነት ውስጥ የነበሩት ካህናትም በእዚህ አስታራቂ ሃሳብ ተስማሙ። በእዚህ ደራሲ ፍርድ፣ ይህ ታሪካዊ ስበሰባና ውጤቱ ለግጭት፣ ያውም ለከባዱ ሃይማኖታዊ ግጭት መፍትሄን ያገኘ በዐለም ላይ ድርም ሆነ በዛሬው ዘመን አርአያ የሚሆን እና እጅግ የሚያስደንቅ ነው። የአባቶቻችንንም አርቆ አሳቢነት የሚመሰክር ነው።

ከአሪት ሃይማኖት ወደ ክርስትና በገቡት ሌዋውያን እና ከንጉሡ ጋር በተሰለፉት የቀድሞ ክርስትያኖች መሀል በተደረሰው ስምምነት መሰረት የሚከተሉት እርምጆች ተወሰዱ።

1. አሪተ ሕግጋቱ እና ትአዛዞቱ ሳይሻሩ ወደ ክርስትና እንዲሸጋገሩ፣
2. በታቦተ ሕጉ ላይ እየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል፣ በአሪት ላይ ቃለወንጌል ተስማምተው እንዲዋሃዱ፣
3. የእግዚአብሔር ቃል ስጋ መሆን ከሰው ጋራ መዋሀዱን የሚያመለክት ሀቅ ስለሆነ በአዲሱ እምነት ውስጥ ይጸል እንጂ አይሻርም።
4. ከአሪት የተላለፉት አሮናዊ የክህነት አልባሳት እና ንዋየ ቅዱሳት በክርስትያን እምነት ውስጥም ተካተው እንዲቀጥሉ፣
5. በአሪት ሕግ የሚቀርበው ያልተሸለተ የበግና የፍየል መስዋእት እንዲቆምና በነሱ ፈንታ የፈሰሰው የእየሱስ ክርስቶስ ደም ታስቦ፣ እየሱስ ክርስቶስ ራሱ የአደሰን የስጋ ወደሙ ምትክ የሆኑት ህብስትና ወይን ጠጅ እንዲሰጡ።

አላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ስምምነት ተደርሶ እየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ333 ዓመተ ምህረት ወንድማማቾቹ አብርሀና አጽብሀ፣ እናታቸው ንግሥት አብርሂት (አሀየ፣ ሶፊያም ትባላለች)፣ ከ200 መንደሮችና ብዜራት የተገኙ ቤተእስራኤሎችና ሌሎችም

ኢትዮጵያውያንና ንጉሦቻቸው ባሉበት፣ አክሱም ለ1000 ዓመታት በኦሪት ሀይማኖት ክቶየች በኂላ ክርስትናን መንግሥታዊ እና ሀገራዊ አድርጋ ተቀበለች። ይህንንም በማድረጓ ክርስትናን የይፋ መንግሥታዊ ሃይማኖታችን ነው ብለው ካወጁት ሀገሮች ውስጥ በዐለም የመጀመሪያዋ ሆነች።

በእዚሁ በቤተእስራኤልና በሌሎቹ ክርስትያን ኢትዮጵያውያን የጋራ ስምምነት መሰረት፣ በበግና ፍየል ደም መስዋእት ሩንታ ህብስትና ወይን ለመስጠት የፈለጉ፣ ከሀገ ኦሪት ስርአት ወደ ህገ ወንጌል ስርአት ፈቅደው የተሸጋገሩ በድፍን ኢትዮጵያ 400 የቀድሞ አይሁዳዊ ቤተመቅደሶች ወደ ቤተክርስትያንነት ተቀየሩ። ከእነዚህ በተጨማሪ ወንድማማቾቹ አብርሀ እና አጽብሀ ራሳቸው 150 አብያተ ክርስትያናት ገንበተዋል።

ድሮ፣ ማለትም ከቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ጀምረው የኦሪት ቤተመቅስ የነበሩት፣ በኂላ ወደ አብያተክርስትያን ከተለወጡት የጥቂቶችን ስም እና መገኛ ቦታዎች ለመጥቀስ ያህል፦

1. አክሱም ጽዮን	ኩዳ ድሀሀን ደብረላህም
2. ደብረ ማኸዶ	ወርቅ አንባ
3. ቤተ ሣህል	ጣና ሐይቅ

4. ተድባበ ጽዮን	ተድባበ ማርያም፣ አማራ ሣይንት፣ ቤተመራ
5. ደብረ ድባብ	ምድረ ሹራ በረንታ
6. ቤተ ዳዊት	ዳውንት፣ ባሕረቀጋ
7. ደብረ አሞን	ጉደሬ፣ ቤተቀዳር፣ ቤተጊደር፣ ምድረ ቅማንት
8. ደብረ አዲል	የመልከጸዲቅ ገዳም፣ መራኝ
9. ቤተ መሐሪ	መርሃቤቴ፣ ምእራፈ መልከጸዲቅ
10. ደብረ ሐዊ/	መርጡለማርያም፣ ፈለገብርሃን
11. ክበረቅዱሳን ገዳመ ዋለ.	የዋለያዎች አገር ዋልድባ
12. ቤተ አሹር	በዐለምትና በወገራ ደብረአሹር ደብረ ማክዳ
13. ቤተ ጉድረት	ዞዝ አንባ፣ ደብረ ዞዝ አካሌ
14. ደብረ ዘቦ	አዘቦ፣ እራያ-አዘቦ፣ ዞበል
15. ቤተ ወርቀዘቦ	ዋግ፣ ቡግና፣ አምደወርቅ
16. ደብረ አዶናይ	ቤተ አዶኒ፣ ዳሞት፣ ራስዳሽ
17. ቤተ ኤራ	ምድረ አባይ፣ ቤተአፍራስ፣ ፈረስ ቤት፣ ትክልድንጋይ
18. ቤተ ሃጌ	በአዋሽ ሸለቆ፣ ሐረርጌ፣
19. ደብረ ማይ	ደብረመዊስ ፈለገብርሀን
20. ቤተ ለእዳት	ጎንዳጉንዲት ፈረዳ
21. ቤተጉና ጉኒት	ምድረ ዝዋይ

22. ደብረ ሹራ ምድረ ዳንጉል፣ ሻሁራ ረፊደ ማርያም
23. ደብረ ኪሩብ ሐረርጌ፣ ከደብረ ወገግ አሰቦት ጎን
24. ደብር መገር ሞጌ ገዳም
25. ቤተ ጎይል ጎይላ ሚካኤል፣ ላስታ
26. ደብረ ከርቤ ደብረ ከርቤ ካቢ
27. ደብረ ፀሀይ ሀና ማርያም አንጎት
28. ደብረ እንቁ ደብረ ወርቅ
29. ቤተ ማጂ በጋሞጎፋ ብርብር ማርያም

ከእዚህ በላይ ከተጠቀሱት የቀድሞ የኦሪት ቤተመቅደሶች ሆነው ኖረው የዛሬ 1695 ዓመት አካባቢ ወደ አብያተክርስትያን ከተለወጡት መሀል ቁጥራቸው ቀላል የማይባለው አሁንም ድረስ አሉ። በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ የታነጹቱ እንግዲህ እድሜአቸው 3000 ዓመታት ሆኖአል ማለት ነው! እነሱን በእድሜ የሚልቅ ኦሪታዊ ቤተመቅደስ በየትኛው የዐለም ክፍል ይገኛል? ቀድሞ በዘመነ ኦሪት እንስሳት ሲሰዋባቸው የነበሩበት እቃዎችና ደም የሚፈስባቸው የድንጋይ ገበታዎች ሳይቀሩ ቅሪታቸው በቤተመቅደሶቹ ቅጥር ግቢ ውስጥ አሁንም ይገኛሉ ይባላል።

ኢትዮጵያ ስርአተ ኦሪትንና ስርአተ ሀዲስን፣ ወይም ወንጌልን ከነታቦቱ በመቀበልዋ በዐለም ከአሉት ቤተክርስትያናት ሁሉ ልዩ ሆነች። እግዚአብሄር እየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር

ወርዶ ከቅድስት ማርያም ተወልዶ ከስጋ ስለተዋህደ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ተዋህዶ ተብሎ ተጠራ።

ኦርቶዶክስ የሚለው ስም የተቀጠለበት ኦርቶዶክስ ግብጾች በሀሰት ኢትዮጵያ የራስዋን ጳጳስ ልትሾም እንደማይገባት ባልተሳተፈችበት የኒቅያ ጉባዔ ተበይኖባታል ብለው አጭበርብረው በደካማ የኢትዮጵያ ንጉሥ የጦር ድጋፍ ፓትርያርክነቱን ከኢትዮጵያውያን ከነጠቁ በኋላ ነው። የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያናት ግን ከኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ልዩነቶች አላቸው። አንደኛ፣ ኢትዮጵያውያን ወደ ክርስትና እምነት የተሸጋገሩት ለ1000 ዐመታት አንዱን እግዚአብሄርን አውቀው በኦሪት አይሁዳውያን ሃይማኖት ውስጥ ከቆዩ በኋላ ነው። ከኦሪት በፊት ደግሞ የአባቶቻችንን የእነመልከጸዲቅን እና ኢትዮጵን ፈጣሪ ሲያመልኩ ነው የኖሩት። የእብራውያን አባት አብርሃም ራሱ ለሊቀካህናት አባታችን ለመልከጸዲቅ አስራት እንደሚያቀርብ መጽሃፍ ቅዱስ ራሱ ዘግቦታል። የኦሪትን ሃይማኖት መስራቹ ነብዩ ሙሴ ራሱ እግዚአብሔር እስከሚጠራው ድረስ የኖረውና ስለ ስነመለኮት የተማረው ከሊቀ ካህናት አማቱ ከዮቶርአብ እንደሆነ ከፍ ብሎ ተዘርዝሮ ነበር። ግብጻውያን፣ ግሪኮች፣ ሶሪያውያን፣ አርመኖች እና ሩስያውያን፣ እንዲሁም ሁሉም አውሮጳውያን እና

የዐለም ህዝቦች ግን በቀጥታ ከአህዛብ ጣኦት አማልክት እምነት ነው ወደ ክርስትና የተሸጋገሩት።

የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን አባላት እግዚአብሄር እና አብርሃም የተዋዋለበትን የብሉይ ኪዳን ለማስታወስ ወንድ ልጆቻቸውን ይገርዛሉ። ኦርቶዶክሶቹ ግን ይህን እንደኛ አስበው አይተገብሩትም። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ምእመናን ስለርኩስና ቅዱስ ምግቦች በኦሪት የታዘዘውን ህግ በማክበር ከብት ኦርደው ደሙን አፍሰው ይበላሉ እንጂ ታንቆ የተገደለ ወይም ደሙ ሳይፈስ የሞተን ባለ አራትም ሆነ በለ ሁለት እግሮች የስጋ ባለቤቶችን አይመገቡም። ኦርቶዶክሶች ግን ለእዚህ አይጨነቁም። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን አማኞች ዋናው ኦሪጅናሌው ጽላትና ታቦት አለን ብለው ስለሚያስቡ የዋናውን ጽላቶች ግልባጮች በታቦቶች ውስጥ አስቀምጠው በቤተክርስትያኖች ያኖሯቸዋል። ኦርቶዶክሶች ይህን አያደርጉም። የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ስርዐተ ኦሪትን ከነአልባሳቱና ንዋየቅዱሳቱ ከስርዐተ ሀዲስ ኪዳን ጋራ አዋህደውታል። ኦርቶዶክሶች ግን ይህን አላደረጉትም። አያደርጉትምም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን እና የኦርቶዶክሶቹ ቤተክርስትያን አንድ ዐይነቶች አይደሉም።

ፍሬሚናጦስ እና ኦዴሲስ የተባሉ ሁለት የግሪክ ወንድማማቾች ልጆች ክርስትናን ለኢትዮጵያውያን እንዳስተዋወቁ አብዛኞቹ ባለታሪኮች ይነግሩናል። ይህ ስህተት ነው። ሁለቱ ወንድማማቾች ልጆች ፍሬሚናጦስ እና ኦዴሲዩስ ካንዲት መርከብ ላይ ተማርከውና ለአክሱም ቤተመንግሥት ተሰጥተው የኢትዮጵያን ባሕል፣ የክርስትና ሃይማኖትንና የቤተመንግሥቱን ወግና ሥርዓት እየተማሩ በቤተ-መንግሥት አደጉ። ሰይፈ-አርእድ ተብሎ ይገዛ የነበረው አልአሜዳ እና በዘሬ ኦሮሞ እና አማራ የነበረችው ንግሥት አብርሃት ዘ ኢትዮጵያ የምትባለው ባለቤቱ ኦሃየ፣ እነዚህን ሁለት ልጆች ሊያሳድጉ ከመቀበላቸው በፊት ጀምሮ ጽኑ ክርስቲያኖች ነበሩ። ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው፣ ንግሥት አብርሃት ክርስትናን ለማስፋፋት እጅግ ከፍተኛ ጉጉት ነበራት። በሷ ጉጉት እና ሁለቱን ልጆቿን አብርሃና አጽብሃን በማትጋት ነበር እናትና ልጆች ክርስትና የመንግሥታቸው ሃይማኖት እንዲሆን በይፋ ያወጁት ብለን ነበር። ማደጎዎቹ ልጆች ፍሬምናጦስ እና ኦዴስዩስ ብልሆች መሆናቸውን የተገነዘበችው ንግሥት አብርሃት ፍሬምናጦስን የአብርሃና አጽብሃ አማካሪ አደረገችው። ክርስትና የኢትዮጵያ ሃይማኖት ሆኖ በይፋ እንዲታወጅ ታሰላስል በነበረበት ወቅት የአይሁድን ሃይማኖት ለ1300 አመታት ሲተገብሩ የኖሩት አይሁዶች የክርስትና ሃይማኖትን በመቃወም የኢትዮጵያን ህዝብ ቀስቅሰው አመጽ

ያስነሱ ይሆናል ሲል የአክሱም ሊቀ-ካህናት ስጋቱን ገልጾላት ነበር። በዚህ ምክንያት የግሪክ ቋንቋ የሚችሉትን ፍሬምናጦስንና አደሲዩስን ወደ ግብጽ አሌክሳንደሪያ ልካ ከፓትርያሪኩ ከአትናቲዎስ ጳጳስ እንዲሾምላት እንድትጠይቅ ሃሳብ አካፈላት እና ሁለቱ ወጣቶች ተላኩ። አትናቲዎስም በሃሳቡ ደስ ተሰኝቶ ፍሬምናጦስን "ሰላማ" በሚል ስም ጳጳስ አድርጎ ሾሞ ላከው። በኋላ ከሳቱ ብርሃን የተባሉት አቡነ ሰላማ ኢትዮጵያውያን ቀሳውስትንና ረዳት ጳጳሳትን ለመሾም ሥልጣን ተሰጥቷቸው መጡና ባሳደገቻቸው አገር ክርስትናን ለማስፋፋት ትልቅ መሳሪያ ሆኑ። ባጭሩ የፍሬምናጦስ ሚና ይህ ነበር። ፍሬምናጦስ እና አደሲዩስ በእድሜ 10 ዓመት እና ከዚያም በታች ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ክርስትናን ከኢትዮጵያውያን ተምረው መልሰው አስተምረዋል። አውነቱ ይህ ነው እንጂ የተገላቢጦሽ አይደለም። ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ትንንሽ ልጆች ስለነበሩ ክርስትናን ለመስበክ የሚያበቃ ቃለ-ወንጌል ያውቁ ነበር ማለት አያስኬድም። ከነሱ የሚበልጡ እና በእምነቱ የተካኑ ኢትዮጵያውያንን ወደ ክርስትና እምነት ሊለውጡ ቀርቶ ራሳቸውም ሃይማኖቱን በወጉ ማወቃቸው ያጠራጥራል። ፍሬምናጦስ የአሌክሳንደሪያን ኮፕቲክ ቤተ-ክርስቲያን ስለማይወክል ለሷ ይሠራ ነበር ማለትም አያስኬድም። የወከለውም ያገለገለውም ተንከባክባ ያሳደገችውን ኢትዮጵያን ነው። እንደ ኢትዮጵያዊነቱ ታማኝነቱም ለኢትዮጵያ

ቤተ-ክርስቲያን ነበር። ደሞም የኢትዮጵያ ሕዝብ የክርስትና ዘር ሲዘራበት ለም መሬት ሆኖ ዘሩን ባይቀበል ኖሮ ንግሥት አብርሃትም ሆነች አብርሃና አጽብሃ ወይም ፍሬምናጦስ ስር የሰደደ ክርስቲያናዊ ዘር ማብቀል ባልቻሉም ነበር።

ይህ ሁኔታ ኢትዮጵያ በይፋ ክርስቲያን እስከሆነችበት እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ድረስ የነበረው ነው። "በይፋ" ለሚለው ቃል አፅንኦት እሰጣለሁ፤ ምክንያቱም እላይ እንደተመለከትነው፣ ከዚያ በፊት በግለሰብ ደረጃ በሐዋርያው ፊሊጶስ ተሰብኮ የተጠመቀውን ጃንደርባውን ጨምሮ የሃይማኖቱ መሰበክ ከተጀመረበት ከአንደኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ እንደተሰበከላቸው የክርስትና እምነትን የተቀበሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት እና ንግሥታት አሉ።

ኢትዮጵያ አዲሱን ሃይማኖት በመንግሥት አዋጅ በይፋ በተቀበለች በአጭር ጊዜ ውስጥ በመንፈሳዊው መድረክ ላይ ሌላ ሽማያ እና ቅማያ ታየ። ከዚህ በፊት እንደተጠቆመው፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በራሷ ፓትርያሪክ ሳይሆን በግብፅ ኮፕቲክ ፓትርያሪክ ብቻ እንድትመራ እንደ ጎርጎራውያን አቆጣጠር በ325 ዓመተ ምሕረት በተካሄደው የኒቂያ ጉባኤ ተወስኗል፤ ሲል የግብፅ ሊቀ-ጳጳስ በሃሰት አወጀ። ኢትዮጵያውያን ካህናት እነሱ በሌሉበት በማንም የተወሰነን ማንኛውንም ውሳኔ

እንደማይቀበሉ ከመከሩ በሁዋላ የኢትዮጵያ ቀሳውስት እና ዲያቆናት በአክሱም ከተማ በውሳኔው ላይ ተቃውሞ አነሱ። ሆኖም በህመም ላይ የሚገኘው ጡረተኛው ንጉሠ-ነገሥት ዋዜባ፣ ቅመም የተባለች ሚስቱ እና ንኡስ-ሰላማ በተባለው በአስመሳዩ ግብፃዊ ጳጳሥ እጅ ተቀብዩ መንገሥ ይፈልግ የነበረው ልጁ አጼ ኤል-ስሚሪሴዮስ (በስሙ ፊት ‹‹ኤል›› የሚል ስም መኖሩ በእሱና በንጉሣውያን ቤተሰቦቹ ላይ የአረብ ተጽእኖ እንዳደረባቸው ይመሰክራል። ‹‹ኤል›› ወይም ‹‹አል›› የአረብ ቃል ስለሆነ፤) ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ይልቅ ለአረቦቹ ለግብፅ ጳጳሳት የበለጠ ክበሬታ ይሰጡ ነበር። በመሆኑም ለዚያ ጮሌ የግብፅ ጳጳስ ለንዐስ-ሰላማ አባሪ ተባባሪ ሆነው የራሳቸውን ቅዱሳን ጨፍጭፈው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን መንፈሳውያን ያልሆኑ ህገ-ወጥ የግብፅ ኮፕቲክ ፓትርያሪክ ተብየዎች እንዲመሯት ፈቀዱ።

በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን እ.ኃ.አ. ከ325 ዓመተ ምሕረት እስከ 1951 ዓ.ም ድረስ ለአንድ ሺ ስድስት መቶ ዓመታት በነቀዙ፣ መንፈሳዊነት በሌላቸው አልፎም አንዳንዴ ሙስሊም በሆኑና ከቤተክርስቲያን ይልቅ መስጊድ ማሠራት በሚቀናቸው አስመሳይ የግብጽ ፓትሪያርኮች ተመራች። ግዕዝን በማዳከም እና አረብኛን

በማስፋፋት እንዲሁም የጥንት መጻሕፍትን እያወደሙ የኢትዮጵያ ታሪክ የአረቦችን ፍላጎት እንዲያሟላ እያደረጉ እንደገና በመጻፍ ገናና ታሪካችንን አበላሹ። ራሷን በጦር ኃይሏ ያነገሠችው፣ ብዙም ደህና ነገር የማይነገርላት ዮዲት እውነትም እነዚህን ጳጳስ ተብዩ አፍቃሬ-አረቦች ባታስቆማቸው ኖሮ ግዕዝ ሙሉ በሙሉ ይጠፋ ነበር። እነዚያ የግብፅ “ጳጳሳት” እና “ፓትሪያሪኮች” የኢትዮጵያን ነገሥታት በሴራ እያጠመዱና እየተቆጣጠሩ፣ ለነሱ ታዛዥ ካልሆኑ በስተቀር አውግዘው ከስልጣን እንደሚያወርዷቸው እያስፈራሩና የፈሩ ነገሥታትን እየተጠቀሙ፣ የተማሩ ኢትዮጵያውያንን በተለይም ቅዱሳን ቀሳውስትን፣ ሊቃውንትን፣ ከያኒያንን፣ የታሪክ አዋቂዎችንና ፈላስፎችን አረዱ፣ ጨፈጨፉ፣ አካል አሰናከሉ። የኢትዮጵያን ክብረ-ዝና ከፍ የሚያደርጉ መጻሕፍትንም እየሰበሰቡ አቃጠሉ። ከተቃጠሉት መጻሕፍት ውስጥ “መጽሐፈ ሱባኤ” በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ተካትቶ የነበረው እየሱስ ክርስቶስ ማንነቱን ለራሱ ሕዝብ ለአይሁድ ከመግለጡ በፊት እድሜው ከሃያ ሁለት እስከ ሃያ አምስት በነበረበት ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሶስት ዓመታት እንደኖረና እንዳስተማረ የሚያትተው መጽሐፍ *ዜና ማርሄር* ይገኝበታል። ይህን መጽሐፍ ለማጥፋት እና መጽሐፉ የተገኘባቸውንም ምሁራን ለማስወገድ የግብፅ ፓትሪያርኮች ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ለዚህ የነበሩአቸው

ምክንያቶችም ብሩህ የቆዳ ቀለም የነበረው እየሱስ ክርስቶስ በግብፅ ውስጥ ኖሮ ይሆናል እንጂ እንደኔ የጥቁር አገር በሆነችው በኢትዮጵያ ይኖራል የሚሉ ንቀትና ቅናት ነበሩ። እነዚያ ደናቁርት የግብፅ ጳጳሳት ያላወቁት ወይም ለማመን ያልፈለጉት ነገር ኢትዮጵያውያን ፈርኦኖች አሰልጣኞቻቸውና ጌቶቻቸው እንደነበሩ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ በዓለም ገናና በነበረችበት በዚያ ወቅት ፈርያኖች እየሆኑ ግብፅን ካስተዳደሩ አሥራ ሰባት የኢትዮጵያ እንስት ነገሥታት ውስጥ ሁሉንም ባይሆንም አራቱን ብልሆች እና እጅግ የተዋበ ንግሥቶችን ግብያች የፍቅር አማልክት ናቸው እያሉ ያመልኳቸው እንደነበረ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አኩሪ ታሪካችን ለዘመናት ተሰውሮብን ሊኖር የቻለው አንዱም በነዚያ ፓትሪያርክ ተብዬዎች ምቀኞች ግብፃውያን ተንኮል ነው።

ወደ ባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር የእስራኤል ወረራ ስንመለስ፣ በግብጽ ፒያንኒሮ ተብሎ የሚታወቀው፣ እኛ ዘዋራ-ንብረት የምንለው የወቅቱ የኢትዮያ ንጉሠ ነገሥት፣ ግብጽ ውስጥ ፈርኦን ኦፍራህ በቤተእስራኤል ያደረሰውን ጭፍጨፋ በሰማ ጊዜ ምታ ነጋሪት፣ ክተት ሰራዊት፣ ብሎ ወደ ግብጽ ዘምቶ፣ የኦፍራህን ሰራዊት ደምስሶ እሱንም ገደለው። እንደዚህ በማድረግም ንጉሠነገሥት ዘዋራ-ንብረት የወገኖቹን የቤተ-እስራኤልን ደም ተበቀለላቸው። በሚቹ ፈርኦን ኦፍራህ ፈንታም

ሀንደኬ በሚል ማእረግ አንዲት ኢትዮጵያዊ ዘመዱን በመላው ግብጽ፣ በሊቢያና ኑብያ (የዛሬው ሱዳን) አንግሦ ቤተ-እስራኤልን እንድትጠብቅ ሾማት።

በባቢሎን ወረራ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱትን፣ ከነሱ 500 ዐመታት ቀድመው ከቀዳማዊ ምኒል ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የነበሩት ወገኖቻቸው መልካም አቀባበል አደረጉላቸው። የሚያሳዝነው ግን፣ በኋላ በመጡት መሃል እና ቀድመው በሰፈሩት መሀል ግጭት ስለተነሳ ቀደምቶቹ አዲስ መጤዎቹን "ፈላሻ" አሏቸው። ቀደምቶቹም ከነባሮቹ ኢትዮጵያውያን ጋር ተመሳስለው በመኖራቸውና ያማቸውን፣ ባህላቸውን እና ቋንቋቸውን በርዘው ኢትዮጵያዊ በማድረጋቸው፣ በአዲስ መጪዎቹ ተነቀፉ። ሲቀልዱባቸውም "አበሾች" አሏቸው። ‹‹አበሳ›› ከሚለው ቃል የወጣ ነው። እብራውያን ‹‹ሻ›› ማለት ስለማይችሉ ‹‹ሳ›› ነው የሚሉት። ስለዚህ ‹‹አበሳ›› በማለት ፈንታ ‹‹አበሻ›› አሉ። ይህም አበሳ ያለበት፣ የተካለሰ፣ የተበላሸ እና የተነካካ የሚል ሃሳብ ይጭራል። ቀደምቶቹ በበኩላቸው አዲስ መጤዎቹን "ፈላሾች" ሲሏቸው ወደ እኛ ሀገር (ወደ ኢትዮጵያ) ፈልሳችሁ የመጣችሁ ሀገር-አልባ ስደተኞች ማለታቸው ነበር። ነገሩን በደንብ ጠልቀን ስናየው ግን ‹‹አበሳ›› የሚለውን ቃል ጎላ-መጤዎቹን ፈላሾች ያሳስባቸው ‹‹ኢያቡሳውያን›› የሚለው ቃል

ነበር። ምኒልክ ቀዳማዊ 40000 እስራኤላውያን አስከትሎ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ፣ ከእነዚህ ውስጥ 28000ዎቹ ንጉሥ ሰሎሞንን በእጅ ሙያና በውትድርና ያገለግሉ የነበሩ ኢያቡሳውያን (አይሁዳውያን ያልሆኑ የዮቅጣን ነገዶች) ነበሩ። 12000ው ግን ‹‹ንጹህ›› አይሁዳውያን ነበሩ። እንግዲህ ‹‹ንጹሆቹን›› አይሁዳውያን በአግቦ ለመናገር ነበር ማለት ነው ‹አበሳውያን›› ናችሁ፣ ብለው የወረፏቸው። ‹‹ንጹህ›› የተባሉትም ቢሆኑ በ500 ዓመታት በኢትዮጵያ ቆይታቸው ከኢትዮጵያን ጋር በመደበላለቃቸው ለአዲስ መጤዎቹ አይሁዳውያን በአካል ገጥታም ሆነ በሃይማኖት እሳይ እንደተባለው ‹‹ንጹህ›› መስለው አልታዩዐቸውም። ዳሩ ግን፣ ሌዋውያኑ የይሁዳ ነገድ፣ የንጉሠነገሥታቱ የንጉሥ ዳዊት እና ሰለሞን ትውልዶች ከመሆናቸውም በላይ መለኮታዊ ስልጣን አለን ይሉ ስለነበር፣ እነሱን ለመዝለፍ አልተዳፈሯቸውም። የሆነ ሆኖ፣ በፊት የመጡት በኋለኞቹ ‹‹አበሻ›› መባላቸውን አልወደዱትም። አዲስ መጤዎቹም ፈላሻ (ስደተኛ) መባላቸው ደስ አላላቸውም። ወጣም ወረደ፣ ዐመታት ሲቆጠሩ፣ “ፈላሻ“ የተባለው ቃል፣ እራሳቸውን አግልለውና ተገልለው የሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን አይሁዶች ሁሉ መለያ ሆነ። በመጨሻ ላይ ደግሞ ሁሉም ‹‹ቤተ-እስራኤል›› በሚለው አንድ መጠሪያ ተጠቃለሉ። ዳሩ ስማቸው ‹‹ቤተእስራኤል›› ቢባልም፣ በ3000 ዓመታት የኢትዮጵያ

ቆይታቸው ኢትዮጵያ ላይ ተወልደው እትብታቸውም እዛው ተቀብሮ ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ጋር በመዋሃዳቸው፣ በመልካቸው፣ በደማቸው፣ በአስተሳሰባቸው፣ በቋንቋቸው፣ በአኗኗራቸው እና በባህላቸው ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሆነዋል። ኢትዮጵያዊ በመሆናቸውም ነው በእስራኤል ኑሯቸው በአንዳንድ ከምእራቡ ዐለም ወደ እስራኤል በጎረፉ አሽከናዚ በተሰኙ አክራሪዎች የዘር እና የቀለም መድልዎ የሚደረግባቸው።

የያዕቆብ ልጆች ወደ ባቢሎን ሲጋዙ፣ ትልቁ የሰለሞን ቤተመቅደስ፣ ቅዱሳት መጻሃፍትና አያሌ ብርቅዬ ንዋየ-ቅዱሳት በወራሪዎቹ በባቢሎኖውያን እና ካሌዳውያን እጅ ወደሙ። እስራኤል ራስዋ ጠፍ መሬት ሆነች። በእግዚአብሔር ትዕዛዝ፣ ነቢዩ ኤርሚያስ ጥቂቶቹን ጉድጓድ ውስጥ ቀብሮ አኖረ። በአብርሃም፣ በይስሃቅ እና በያዕቆብ አምላክ ምህረት፣ ከሰባ ዐመታት የባቢሎን ግዞታቸው በኋላ አይሁዳዊያን ወደ እስራኤል መመለስ ጀመሩ። የሰለሞንን መቅደስ እንደገና እንዲገነባ ዘሩባቤል ከዳሪዎስ ፍቃድ አገኘ። እዝራ የመቅደሱ ሊቀ ካህን ሆነ። ሆኖም ግንባታውን በዛን ዘመን እና አካባቢ ስልጣን የነበራቸው አፋሮች ጥያቄ ውስጥ ከተቱት። የአፋሮችን ገናናነት ቀጥሎ እንመለከታለን።

የአፋሮች ገናናነት በአፍሪካ እና እስራኤል

በድሮ ዘመን አፋሮች እጅግ ገናና ነበሩ። ኢዮብ በእግዚአብሄር ፍቃድ በሰይጣን ተፈትኖ 7 ወንዶች ልጆቹን አጥቶ ራሱም በደዌ ተመትቶ ሰው ሆኖ መፈጠሩን እስከመጥላት ደርሶ እንደነበር መጽሀፈ ኢዮብ ይዘክራል። ወዳጆቹና ሚስቱ እንዲህ ከሰው በታች ከምትሆን እግዚአብሄርን ረግመህ ሙት እያሉ ተዘባበቱበት። እሱ ግን ‹‹እግዚአብሄር ሰጠ፤ እግዚአብሄር ነሳ። የእግዚአብሄር ስም የተባረከ ይሁን፤›› አለ። ይህ ጽናቱም እግዚአብሄርን አኮራ። ሰይጣንን አሳፈረ። በዚህም ምክንያት፣ ኢዮብ በሰይጣን ፈተና ምክንያት ያጣውን ሁሉ እግዚአብሄር መለሰለት። ከሀመሙ ፈወሰው። እንደገና 7 ወንዶች እና 3 ሴቶች ልጆችም ሰጠው።

ኢዮብ በዘሩ አይሁዳዊ አልነበረም። የኢትዮጵያውያን አባት የመልከጸዲቅ ዘር ነበር። እምነቱና እውቀቱ መለኮቱ እንደዚያ የጸናውና የጠለቀው የትልቁ ሊቀካህናት የመልከጸዲቅ ዘር ስለነበር ነው። በሌላ አነጋገር እሱም እንደኛው ከመልከጸዲቅ ልጅ ከአባታችን ከኢትዮጵ ጋር ይዛመድ ነበር ማለት ነው። በዚህ ምክንያት ነበር ‹‹ኢትዮጵ›› የተባለው። ስመ ክህነቱን ‹‹ኢትዮጵ›› ብለው የሰየሙትም የእኛን አባት፣ የሱን ዘመድ ‹‹ኢትዮጵን›› ለማስታወስ ነበር። ከዘመን ብዛት ‹‹ኢትዮጵ›› የተባለው ቃል ‹‹ት››ን ጥሎ እና ‹‹ጵ››ን በ‹‹ብ›› ቀይሮ ተጠሪው ሰው ‹‹ኢዮብ›› ተሰኘ። ‹‹ኢትዮጵ›› በመባል ፈንታ እስከዛሬ ‹‹ኢዮብ›› ይባላል። የኢዮብም ትውልድ እንዲህ ነው፦ የአባታችን የኢትዮጵ አባት መልከጸዲቅ አበመሊክን ወለደ። አበመሊክ የፍልስጥኤምና የሊባኖስ ንጉሥ ነበር። አበሚሊክ ከመጅሩን ወለደ፤ ከመጅሩ ሳዶቅን፣ ሳዶቅ ደሞ ኢትዮብን (በኋላ ኢዮብ የተባለውን)። ኢትዮብ የክህነት ስሙ ስለነበር ካህንነቱን ያመለክታል። እሱም የእሱ ቅምአያት፣ የኢትዮጵያውያን አያት የነበረውን የመልከጸዲቅን አምላክ ያመልክ ነበር።

ኢዮብ እና በኋላ የወለዳቸው ሰባት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ልጆቹ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ያላቸውን ዝምድና በማገናዘብ ነበር ዘመዶቻቸውን እና የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ የፈለሱት።

በኢትዮጵያም ከወገኖቻቸው ጋር ተቀላቅለውና ተጋብተው፣ ዛሬ አፋር የተባሉትን ሰዎች ለመሆን በቅተዋል። አፋሮች ለኢትዮጵያ ሀገራቸው ልዩ ፍቅር ያላቸውና እስከዛሬም ድረስ ኢትዮጵያን ከድተውና ኢትዮጵያዊነታቸውን አሌ ብለው የማያውቁት በዚህ ምክንያት ነው። ደጃዝማች አሊ ሚራህ እንደ አሉት፣ ግመላቸው ሳትቀር የኢትዮጵያን ሰንደቅዐላማ የምታውቀው ለእዚህ ነው። እኛ ከትልቁ ሰው ከኢትዮጵ በቀጥታ የምንወለደው ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያን መካዳችን እና በእሷም መኩራት ሲገባን እሷን ማንቋሸሻችን ያሳዝናል።

አዘቦዎች በተባሉት ነገዶች አማካኝነት አፋሮች ከንግሥተ-ሳባ ጋር ዝምድና ስለነበራቸውና በኋላም የጻዲቁ ኢዮብ ልጆች ከነሱ በመዋሃዳቸው በንጉሥ ናቡከደነጾር ቤተመንግሥት እና በራስዋ በፍልስጥኤምም (በእስራኤል) ይከበሩና ይደመጡ ነበር። ኢዮብ ትውልዱ በቤተልሄም አካባቢ በመሆኑ ከአፋሮች የተዋሃዱት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ልጆቹ ከእስራኤል ጋር ፈጽመው አልተቆራረጡም ነበር። በዚህ ምክንያት፣ በዚያ አካባቢ አፋሮች ተጽእኖ ፈጣሪ ነበሩ። አፋር የሚለው ስማቸው የወጣው ከኦፊር ነው። ኦፊር ማለት ጥንት ኢትዮጵያ ላይ የሰፈረው፣ የቀድሞዎቹ አፋሮች አባት ስም ነው። በኋላም አገሩ አፋር በመባል ይታወቃል። የአፋርን ጥንታዊ ገናናነት ለማስታወስ

አፍሪካም፣ ዝቅ ብዬ እንደምዘረዝረው አፍሪካ የተባለችው በአፋሮች ነው።

አፋሮች ድንቅ መርከብ ገንቢዎች እና ‹‹የተርሲስ ነጋዴዎች›› ተብለው በታሪክ የተመዘገቡ ስመጥር ባህረኞች ነበሩ። በዐለም ዝነኛ የነበረው ወርቃቸውም ‹‹የኦፊር ወርቅ›› ተብሎ ይታወቅ ነበር። ከወርቅ በተጨማሪ ይነግዱት የነበረው ቶፓግዮን፣ ያስፐር እና ኢያስፒድ፣ በተሰኙ የከበሩ ደንጊያዎች፣ እንዲሁም የነበር ቆዳ፣ እጣን፣ ከርቤ፣ ሰንደል፣ ወፎች፣ ጦጣዎች እና ሌሎች እንስሳትም ነበር። ሁለተኛውም መዲናቸው ተርሲስ ትባል ነበር። ተርሲስ፣ ዛሬ አሰብ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የኢትዮጵያ ሁለተኛዋ ወደብም ነበረች።

እየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ20 ዐመታት በፊት በኦሮሞው ንጉሥ መጋል መሪነት፣ ኢትዮጵያውያን በአፋር መርከቦች ተጭነው ለአጭር ጊዜ ፖርቱጋልን እና ስፔንን ቅኝ ገዝተው ነበር። በኢትዮጵያ ያለችውን ተርሲስ ለማስታወስ ያህል የእስፔንን ባህርዳርቻ ተርሲስ ብለው ሰየሙት። እስከ ዛሬም ድረስ ተርሲስ ይባላል። በንጉሥ መጋል የተመራው የኢትዮጵያውያን ጦር ስፔንን በአንድ ወቅት ስለመያዙ አንድ ተጨማሪ ማስረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ እየፈሰሰ የኢሊባቡር ኦሮሞዎች ዘንድ ታዋቂ የሆነው ሶር የተባለው ወንዝ ነው። በእዚሁ ስያሜ የሚጠራው

የሶር ወንዝ በስፔን ውስጥ ተንጣሎ ይፈሳል። ርዝማኔው 49 ኪሎሜትር ነው። አኮርኛ (A Coruna) እና ሉጎ (Lugo) በተባሉት ክፍለሀገሮች ውስጥ ይወርዳል። ታዲያ ይህ የሶር ወንዝ ኢትዮጵያም ስፔንም ውስጥ እንዴት ሊገኝ ቻለ? መልሱ፣ ኢትዮጵያውያን እዛ ሄደው የሀገራቸውን ወንዝ ለመዘከር ስለሰየሙት መሆን አለበት፤ ነው። ጋሊሲያ Galicia ወይም ጋሊ-ሺያ የሚባሉት በሶር ዳርቻ የሚኖሩት ራስ-ገዝ ብሄረሰቦች ከሌሎቹ ስፔናውያን በባህልና አለባበስ የተለዩ እና የተገለሉ ናቸው። የጦር የእራስ ጡሩራቸው አናት ላይ የአለው ጎፈር አሮሞ ጦረኞች እራስ ላይ የሚቀመጠውን ጎፈር ያሳስባል። ጋሊ-ሺያ የሚለው ቃል ራሱን ብንመረምር ‹‹ጋሊ›› በኢትዮጵያ ነገዶች ውስጥ ጋሊ የሚባል ነገድ ተዘመዝግቦአል። ‹‹ጋላ›› የሚለው እና ‹‹ጋሊ›› የተሰኙትም ቃላትና ነገዶች ተወራራሽ ሆነው ጎን ለጎን ተገኝተዋል። Gali-cia የሚለው ቃል ውስጥ ‹‹cia›› ማለት ‹‹የ›› ነው። ሲተረጎም ‹‹የ-ጋሊ›› ወይም ‹‹የጋላ›› የተሰኘውን ቃል ያመላክታል። ፖርቱ-ጋል በሚለው ውስጥም ‹‹ጋል›› የሚለው ቃል ‹‹ጋላ›› የሚለውን ስለሚጠቁም፣ እናም ኢትዮጵያ እስፔንን ለአጭር ጊዜ ቅኝ መግዛትዋ በድሮ ታሪካችን ውስጥ ስለተመዘገበ፣ የእስፔን፣ የፖርቱጋል እና የኢትዮጵያ ጥንታዊ ግንኙነት በትጋት እና በጥልቀት መጠናት ይገባዋል። የዚህ ታሪክ የሚገኘው ስፔን ሄዶ የጋሊሺያን ሰዎች ማንነት በመመርመር ነው።

አፋሮች፣ በመርከብ ገንቢነታቸው እና በቱጃር ነጋዴነታቸው ስማቸው ስለተጠራ፣ ንጉሥ ሰለሞን ከደንበኞቻቸው ውስጥ አንዱ ነበር። እንዳውም ዝነኛውን ቤተመቅደሱን ያሳነጸው እነርሱ ባቀረቡለት አንዳንድ እቃዎች ነበር። የአይሁድ ሰዎች አፋሮችን “አፋርስ“ ወይም ‹‹አፋርሳችተስ›› በማለት ይጠሯቸው ነበር። መጽሃፍ ቅዱስ በመጽሃፈ ነገሥት ቀዳማዊ 22፡ እንዲህ ይላል፡- ‹‹ንጉሡ፣ ከሄራም (ሂራም፣ ብዙ መርከቦች የነበሩት የቤተመቅደሱ መሀንዲስ ነበር) መርከቦች በተጨማሪ የተርሲስ (የአፋር) መርከቦች ነበሩት። በሶስት ዓመት አንዴ የተርሴስ መርከቦች ወርቅ፣ ብር፣ የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች ይዘው ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጡ ነበር።›› አሉን፣ በአፋሮች ተሠርተው፣ በሰለሞን እጅ ስለገቡት መርከቦች መጽሃፉ ሲጠቅስ፤ ስለ አፋሮችም ያነሳል። ከሰለሞን ሞት በኋላም፣ በልጁ በኢዮሳፌጥ ዘመን ወርቅ እና ሌሎችንም ውድ ነገሮች ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ያጓጉዙ ነበር። ትልቁን መጽሐፍ ስመጥቀስ፡-

“ኢዮሳፌጥም ወደ ኦፊር (ኦፋር) ሄደው ወርቅ ያመጡ ዘንድ የተርሲስን መርከብ ሠራ፤ ነገር ግን መርከቦቹን በኤጽዮን ጋብር እንደ ቆሙ ተሰበሩ እንጂ ርቀው አልሄዱም። (መጽሃፈ ነገሥት ቀዳማዊ፤ 22፡48) በመላው አፍሪካ ውስጥ አፋሮች ቀልጣፋ ነጋዴዎች፣ ጥንት ኢትዮጵያ ተብሎ ይጠራ የነበረው

የጥቁሮች አህጉር ‹‹አፍሪካ›› ተብሎ በስማቸው መጠራት ጀመረ። ከ70 ዓመት በፊት በካሌዶናዊያን እና በባቢሎናዊያን ፈርሶ የነበረውን የሰለሞንን ቤተ መቅደስ እዝራ፣ ዘሩባቤል እና ከእነሱ በኋላ የመጡት የእስራኤል ሽማግሌዎች መልሰው በሚገነቡበት ወቅት እንኳን አፋሮች በአካባቢው ተጽእኖ ፈጣሪዎች እና ወሳኞች ነበሩ።

በእስራኤል ከአንደኛው ወንዝ ማዶ አፋሮች ጭፍሮቹ የነበሩ ተንትናይ የተባለ አገረ-ገዥ፣ ከሁለተኛው ወንዝ ማዶ አስተዳዳሪ የነበረው ስተርቡዝናይ የእስራኤል አለቆች ቤተመቅደሱን የሚያንጹት በንጉስ ዳሪዎስ ፍቃድ መሆኑኑን ለማረጋገጥ እንደመረመራቸው በመጽሀፍ እዝራ ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፦

> “በዚያን ዘመን በወንዝ ማዶ የነበረው ገዥ ተንትናይ ደግሞ ስተርቡዝናይ ተባባሪዎቻቸውም ወደ እነርሱ መጥተው፣ ይህን ቤት ትሠሩ ዘንድ፣ ይህንንም ቅጥር ታድሱ ዘንድ ያዘዛችሁ ማነው? ብለው ጠየቋቸው`` *(መጽሃፈ እዝራ* 5፡3)።

እዚህ ላይ ተባባሪዎቻቸውም የሚለው አፋሮችን ነው። እታች የሰፈረው ጥቅስ ይህን ያብራራዋል።

‹‹ይህም ነገር ወደ ዳርዮስ አስኪደርስ ድረስ መልሱን በደብዳቤ አስኪመጣ ድረስ አልከለከሏቸውም። በወንዙ ማዶ የነበረው ተንትናይ ደግሞ ስተርቡዝናይ ተባባሪዎቹም በወንዙ ማዶ የነበሩት **አፈርስካዊያን** ወደ ንጉሱ ወደ ዳሪዎስ የላኩት የደብዳቤው ግልባጭም ይህ ነበር። እንዲህም የሚል ደብዳቤ ላኩለት፦

‹ለንጉስ ዳሪዎስ፣ ሙሉ ሰላም ይሁን፣ ወደ ይሁዳ አገር ወደ ታላቁ አምላክ ቤት እንደሄድን ንጉሡ ይወቅ። እርሱ (የአምላክ ቤት) በትልቅ ድንጋይ ተሠራ። በቅጥሩም ውስጥ እንጨት ተደረገ፤ ያም ሥራ በትጋት ይሠራል፤ በእጃቸውም ይከናወናል፣ እነዚያንም ሽማግሌዎች ይህን ቤት ትሠሩ ዘንድ፤ ይህንንስ ቅጥር ታድሱ ዘንድ ያዘዛችሁ ማነውን? ብለን ጠየቅናቸው።›› *(መጽሃፈ እዝራ* 5፡6-9) ቤተ-መቅደሱ በዘሩባቤል ከታነጸ በኋላ ካሌዶናዊያንና ባቢሎናዊያን ከ70 ዓመታት በፊት አውድመውት ስለነበር ማስተማሪያ መጽሀፍት ተቸገሩ። ስለሆነም በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለነበረው ስመ-መንግሥቱ ደንቀዝ ለተባለው አጼ ሪምሀይ ያስፈለጓቸውን መጻህፍት እንዲያገኙ ይረዳቸው ዘንድ ደብዳቤ ፃፉለት። አጼ ሪምሀይ የአጼ አክሱማይት ዝርያ ነበር። አጼ ሪምሀይም ኢትዮጵያዊያን ሌዋዊያን ጸሀፍትንና ምሁራንን የሚከተሉትን መጻህፍት ከግዕዝ ወደ ዕብራይስጥ

ተርጉመው ወደ እስራኤላዊያን ወገኖቻቸው እንዲልኩ መደበላቸው።

1. *መጽሃፈ አዳም፣ ቅጽ አንድ /ስለ አዳም አኗኗር፣ ስለ ፍጥረት እና ከአዳም እስከ ኖህ ስላሉት የአዳም ልጆች/*
2. *መጽሃፈ አውደ ጸሃይ ጀን ሸዋ /በመጀመሪያው ሰማይ ውስጥ እግዚአብሔር ፈጥሮ ስለአኖራቸው 16 ዐለማት፣ 12ቱ ነፍሳት ያለባቸው/*
3. *መጽሃፈ ሔኖክ፣*
4. *መጽሃፈ ሱባኤ ዘደቂቀ እግዚአብሔር /ስለ እግዚአብሔር ልጆች ሚስጥር/*
5. *መጽሃፈ አበው፣ ወልደ እግዚአብሔር ዘና አበው /ስለ አዳም ትውልድ ዘር ግንድና የቀድሞ አባቶች ዜና/*
6. *መጽሃፈ ጥበብ ለአምላክ /የአምላክ ጥበብ ድርሳን/*
7. *መጽሃፈ ጥበብ ዘአዕባነ ጉልቆ /ስለድንጋዮች እና ማዕድናት፣ ክርሰ ምድር ጽሁፎች/*
8. *መጽሃፈ ኢዮብ*
9. *መዝሙረ ኢዮብ*
10. *መዝሙረ ኢዮብ ወጸሎት እዮብ*
11. *መጽሃፈ ካህን ዘእግዚአብሔር*

ከላይ የተዘረዘሩት መጻህፍት በጣም የሚከበሩ እና በኢትዮጵያዊያን ነገሥታት የሚጠበቁ ነበሩ። ሆኖም አፄ ረምሃይ ወደ እብራይስጥ አስተርጉሞ ለእስራኤል አሸጋገረ። በተጨማሪም የሚከተሉትን መጽሃፍት ወደ እብራይስጥ አስተርጉሞ ለእስራኤል አስረክቧል።

1. *ሙሴ ደርሷቸዋል የተባሉት የብሉይ ኪዳን 5 ድርሳናት /ቶራ/፣*
2. *መጽሃፈ ኩፋሌ (በሙሴ የተደረሰ ስለቀናት አቆጣጠር እና ስለክብረ በአላት የሚገልጽ፣ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ካሏት ፹፪ቱ መጻህፍት ውስጥ አንዱ)*
3. *መጽሃፈ ዣንሸዋ እና መጽሃፈ መሳፍንት፣*
4. *የሳሙኤልና ሩት ድርሳናት፣*
5. *መጽሃፈ ነገሥታትና መጽሃፈ ነቢያት*
6. *የኤልያስ ሠረገላና የናታን ትንቢቶች፣*
7. *መዝሙረ ዳዊት እና መጽሃፈ ሰለሞን፣*
8. *መጽሃፈ ሲራክ፣ የአልዓዛር ልጅ፣*

ከላይ ከተዘረዘሩት መሳህፍት ውስጥ የተወሰኑት ቀዳማዊ ምኒሊክ ሰለሞንን አጅበው በፈለሱት እስራኤላዊያን ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ነበሩ። አፄ ረምሃይ እነዚህን መጽሃፍት ብቻ ሳይሆን፣ ለሰለሞን ቤተመቅደስ ማስገንቢያ የሚውል ብዙ ወርቅና ገንዘብ

ልኳል። ለዚህም ወሮታውን ለመመለስ ነቢያቶቹ ዳንኤል፣ ህዝቅኤልና ሃጋይ ባቢሎን ውስጥ በግዞት ላይ ሳሉ የደረሷቸውን መፃህፍት፣ እዝራ ወደ ኢትዮጵያ ልኳል።

የነብዩ ኤርምያስ እና የኢትዮጵያዊው አቡመሊክ ወዳጅነት

ስለ ነቢዩ ኤርሚስ ሲወሳ፣ ህይወቱን ስለታደገለት አንድ ኢትዮጵያዊም ይዘከራል። የእግሊዝኛው መጽሃፍ ቅዱስ ቅጂ ኤቤድ-መሊክ በሚል ስያሜ ይጠቅሰዋል። እኛ ግን አቡ መሊክ እንለዋለን። እናቱ ላቀች የምትባል የአማራ ጎሳ አባል ስትሆን፣ አባቱ ደግሞ አልቦዳ የሚባል በደቡብ ኢትዮጵያ ከእናሪያ ጎሳ ነበር። ኤቤድ-መሊክ በዘጠኝ ወራት እድሜው ወላጅ አልባ ስለሆነ፣ የተለያዩ የኢትዮጵያን ነገሥታትና ንግሥታት እያገለገለ፣ እነሱም በቤተመንግሥት ሥርዓት አጠባበቅ፣ በውትድርና ጥበብ፣ እንዲሁም በመንግሥታዊ አስተዳደር ኮትኩተው አሳደጉት። ወደ እስራኤል ከመሄዱ በፊት በኢትዮጵያዊው በንጉሥ ማሳሄርታ ስር የሠላም ጥበቃ ሰራዊት ዋና አዛዥ ሆኗል። አስተዋይ የጦር

መሪና የተከበረ የዘውድ አማካሪ ነበር። ጸደቂያ የእስራኤል ንጉሥ በነበረበት ዘመን የእርሱ ንጉሠነገሥት መሳሄርታ በእስራኤልና በኢትዮጵያ መሃል ያለውን ዲፕሎማቲካዊ ግንኙነት እንዲያጠናክር ወደ እስራኤል ላከው። እዚያም አብራይስጥ ተምሮ የአይሁድን እምነት ተቀበለ። ያን አገር ከመውደዱ የተነሳ መላ ህይወቱን እዚያው አሳለፈ። ንጉሥ ጸደቂያ እጅግ አድርጎ ይወደው ስለነበር አማካሪው እና የክብር ዘቡ ዋና አዛዥ አድርጎታል።

በጸደቂያ ዘመነ መንግሥት ኤርሚያስ ያለምንም ፍርሃት የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍ ትልቅ ነቢይ ነበር። ነገር ግን ንጉሡ እና የእስራኤል ህዝብ መስማት ይፈልጉ የነበረው መልካም ዜናን እንጂ ከአምላካቸው አፈንግጠው ሌሎች አማልክት ቢሰግዱ ስለሚደርስባቸው ጠንቅ የሚያስጠነቅቃቸውን አልነበረም። እንዲያውም ስለባቢሎን ግዞት እየተነበየ እውነቱን ፍርጥ አድጎ እየነገራቸው ንስሃ ካልገቡ እና መንገዳቸውን ካላስተካከሉ ስለሚገጥማቸው ፈተና ያስጠነቅቃቸው ነበር። ስለሆነም ንጉሡ እና ህዝቡ አሲረው ሞቶላቸው እንዲገላገሉት ጉድጓድ ውስጥ ጨመሩት።

"ኤርሚያስንም ወሰዱት፤ በግዞት ቤቱም አደባባይ ወደ ነበረው ወደ ንጉሡ ልጅ ወደ መልክያ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት፤ ኤርሚያስንም በገመድ አወረዱት፤ በጉድጓዱ ውስጥ ጭቃ እንጂ

ውሃ አልነበረውም፤ ኤርሚያስም ጭቃው ውስጥ ገባ። (ትንቢተ ኤርሚያስ 38፡6)

ነቢዩ ኤርምያስ የእግዚአብሔርን መልእክት እንደወረደለት የሚናገር ንጹህ ሰው ነበርና በግፍ ጉድጓድ ውስጥ መጣሉን አቡ-መሊክ ሲሰማ በጣም አዘነ። ስለዚህም ከጉድጓድ ውስጥ ሊያስወጣው ጣረ። ምንም እንኳን የህዝቡን ቁጣ የሚያስነሳበት ቢሆንም፤ በነቢዩ ጉዳይ ጣልቃ ገባ። ለኤርምያስ ምህረት እንዲያደርግለት ንጉሡን አጥብቆ ተማጸነ። ንጉሡም ኤርሚያስ ከተወረወረበት ጉድጓድ እንዲወጣ ፈቀደ።

"በንጉሡም ቤት የነበረው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርሚያስን በጉድጓዱ ውስጥ እንዳኖሩት ሰማ። ንጉሡም በቢኒያም በር ተቀምጦ ነበር። አቤሜሌክም ከንጉሡ ቤት ወጥቶ ንጉሡን እንዲህ አለው፡- ‹ጌታዬ ንጉሥ ሆይ እነዚህ ሰዎች ነቢዩ ኤርሚያስን በጉድጓድ ውስጥ በመጣላቸው በእርሱ ላይ ክፉ አድርገዋል።

‹‹በከተማይቱም ውስጥ እንጀራ ስለሌለ በዛው በራብ ይሞታል።›› ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌክን ‹ከአንተ ጋር ሰላሳ ሰምንት ወታደሮች ከዚህ ወስደህ ሂድ፤ ነቢዩም ኤርሚያስ ሳይሞት

ከጉድጓድ አውጣው፤›› ብሎ አዘዘው።›› (ትንቢተ ኤርሚያስ፣ 38፡ 7-10)

ኤቤሜሌክም ገመድና ‹‹ጠባቂዎች አስከትሎ በግንባር ወደ ጉድጓዱ ሄዶ አወጣው።›› (*ንጉሤ አእምሮ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሰላም ጥበቃ ታሪክ* ገጽ 41-43)

በኋላም የኤርሚያስ ትንቢት እውን ሆነ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ ናቡከደነፆር የሰለሞንን ቤተመቅደስ በውስጡ የነበሩትን መጻህፍት ጨምሮ አቃጠለ። ከአይሁዶችም የተወሰኑትን ገድሎ የቀሩትንም በሰንሰለት አስሮ ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው። ኤርሚያስም የወገኖቹን እጣፈንታ ሊካፈልና ሊያስተምራቸው አብሯቸው ተጋዘ። እዚያም በግዞት አይሁዳውያን ለ70 ዓመታት ቆዩ። እሱም ያንኑ ያህል ዘመን እዛ በክህነትና በነቢይነት አገለገላቸው።

አቤሜሌክ ለኤርሚያስ ያደረገለትን እግዚአብሔር ወደደለት፤ በእርሱ በማመኑም ባረከው። እንዲያውም ተይዞ ወደ ባቢሎን እንዳይወሰድ እና እሱ እንደሚጠበቀው ከእስራኤላውያን ግዞት በፊት በኤርምያስ አንደበት ትንቢት ተናግሮለት ነበር።

‹‹የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ ለበጎነት ሳይሆን ለክፋት ቃሌን በዚህች ከተማ ላይ

አመጣለሁ። ከዚያም ቀን በፊት ይፈጸማል፤ በዚያም ቀን አድንሃለሁ ይላል። እግዚአብሔርን በምትፈራቸው ሰሞች እጅ አልሰጥህም፤ ፈጽሞ አድንሃለሁ፤ ነፍስህም እንደ ምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይፍ አትወድቅም፤ በእኔ ታምነሃልና ይላል እግዚአብሔር።›› (ትንቢተ ኤርሚያስ 39፡16-18)

የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን መጽሀፍ ቅዱስ አካል የሆነው *ተረፈ ኤርሚያስ* እንደሚዘግበልን ባሩክ የተባለው የኤርሚያስ ደቀመዝሙር በዛፈው ድርሳን እግዚአብሄር አቡመለክ ላይ ከባድ እንቅልፍ ጥሎበት ባቢሎን እስራኤልን ወርራ ስታግዝ እንዳያይ ሰውሮታል። በእንቅልፍ ላይ ሳለም፤ የእግዚአብሔር መላዕክት የተንጋለለ አካሉን ከበው እየጠበቁት የባቢሎናዊያን ጥፋት እና ግዞት ሳይታወቀው አቤሜሌክ ለ66 ዓመታት በእንቅልፍ እንደ አሳለፈ ይገልፃል። ከእንቅልፉ የነቃውም ኤርሚያስ፣ ዘሩባቤል እና እዝራ ወደ እየሩሳሌም ከመመለሳቸው ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ ነበር። አፈታሪክ እንደሚለውም ሄኖክና ኤልያስ እንዳልሞቱ ሁሉ እርሱም አልሞተም፤ እግዚአብሔር ወደ ብሄረ ሕያዋን ወስዶታል።

ከኢየሩስአሌም መፈራረስና ከህዝቡ መጓዝ አስቀድሞ፣ የሚመጣውን ስቃይና ሃዘን ኤቤሜሌክ እንዳይመለከት ይረዳው ዘንድ ኤርሚያስ እግዚአብሔርን ተማጸነ። እግዚአብሔርም

ኤቤሜሌክ እየሩሳሌም ዳርቻ ወደሚገኘው የአግሪፓ የወይን እርሻ ሄዶ መድሃኒት ያለውን የዕጸበለስ ዛፍ ቅጠል ቢበላ የአይሁድ ህዝቦችን ስቃይ ሳያይ በዛፍ ጥላ ስር ለ66 ዓመታት እንደሚያስተኛው ይነግረው ዘንድ ላክው። ኤርሚያስ ይህንን አደረገ አቡመሊክም ታዘዘው።

አቡመሊክም ከረጅም እንቅልፉ ሲነቃ፣ እየሩሳሌም በጣም ተለዋውጣ ሊለያት አልቻለም። ስለዚህ ሁኔታው ፍንጭ ይሰጠው ዘንድ እግዚአብሔርን ለመነ። እግዚአብሔርም በእየሩሳሌም ውስጥ ወደነበረው የኤርሚያስ ደቀመዝሙር ወደ ባሩክ እንዲሄድ መራው። በዚያን ጊዜ ባሩክ የሚኖረው በመቃብር ቤት ውስጥ ነበር። አቡመሊክም እንደተባለው አደረገ። ሁለቱ የጥንት ጓደኛሞች ሲገናኙ ስለአይሁድ ህዝብ ክፉ እድል እና የኢየሩሳሌም መውደም አስበው ተላቀሱ። አቤሜሌክም እየሩሳሌም መውደሟ ከ66 ዓመታት በፊት ቀጥፎ በእቃ ያስቀመጣትን የእጸበለሷን ቅጠል ለባለእንጀራው አሳየው። ልክ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንደተቀጠፈች ሁሉ፣ ፈላሽ ያዘለች ለጋ ቅጠል ነበረች።

ባሩክና አቤሜሌክ ለኤርምያስ ደብዳቤ ጽፈው እስራኤልን ከምታድነዋ ለጋ ቅጠል ጋር በአንዲት ንስር መንቆር አሲዘው ወደ ባቢሎን ላኩለት። በእግዚአብሔር የታዘዘው ያ ንስርም ደብዳቤውንና ቅጠሊቱን ከምስራች ዜና ጋር ለኤርሚያስ

አደረሰለት። እስራኤላውያንና ኤርምያስ ከባቢሎን ስደት ወደ እስራኤል ከተመለሱ በኋላ፣ አቤሜሌክ እና ባሩክ ከኤርምያስ ሳይለዩ ኖረዋል። ኤርሚያስ ስለ መሲሁ መወለድ ራዕይ ማየቱን በመናገሩ በድንጋይ ተወግሮ በአይሁዳውያን እስኪገደል ድረስ። (*ተረፈ ኤርሚያስ* ምዕ 8፡11) የትውልደ ኢትዮጵያዊው አቤመሊክ እና የነቢዩ ኤርምያስ ወዳጅነት፣ የእስራኤልን እና የኢትዮጵያን ጥብቅ ግንኙነት የሚያሳስበን ከጥልቅ ወዳጅነቶች መሀል አንዱ ነው።

መደምደሚያ

በእዚች መጽሀፍ የተካተቱትን ነጥቦች ሰብሰብ ለማድረግ፣ ከኢትዮጵ መስራች አባታችን እንጀምራለን። ኢትዮጵ ከኢየሩሳሌም ተነስቶ እንዴት ጣና ደሴት ላይ እንደሰፈረ፣ እዛም ሰፍሮ 10 ወንዶች ልጆች ወልዶ እነሱ ተራብተው እንዴት የኢትዮጵያውያን ጥንተ-አባቶች እንደሆኑ፣ ከንጉሳውያን ልጆቻቸው ውስጥም 12ቱ ከ2000 ዓመታት በኋላ ጠቢባን ነገሥታት ሆነው፣ ለ2000 ዓመታት ሲጠበቅ የነበረ የመሲሁን መወለድ የሚጠቁም ኮከብ በሰማይ ዐይተው፣ በኮከቡ ተመርተው ወደ ቤተልሄም ደርሰው ለህጻኑ መሲህ ገጸበረክት እንዴት እንዳቀረቡለት ቃኝተናል።

ስለ እየሱስ በመርዋ እና ኢትዮጵያ ቆይታ፣ ስድስቱ ደቀመዛሙርቱ በኢትዮጵያ የሐዋርያት ሥራ እንደሠሩ፣ ስለ

ንግሥተ-ሳባ ማንነት፣ ስለ አጼ እስያኤል ማንነት እና ከየወደራቷ የሳባ ንግሥት ኢትያኤል ጋር የነበረውን ምስጢራዊ አጋጣሚ፣ ስለ ንግሥተ-ሳባ እና የንጉሥ ሰለሞን አብሮነትና ምኒልክን ስለመውለድ አንብበናል። በተጨማሪም ቀዳማዊ ምኒልክ እንዴት የሰለሞንን ስርወመንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከለ፣ አጋዝያንን ከእስራኤል አምጥቶ እስራኤላውያንን ከኢትዮጵያውያን እንዴት እንደ አስበለጠ እና በእዚህ ጠንቅም እንደሞተም ተመልክተናል።

የቤተእስራኤሏ ተወላጅ ዮዲትን እና የላስታዋን ልዕልት የእንቁዮጳግዮንን አለቃና ምንዝርነት፣ የዮዲትን መንገሥና ፍርድ፣ ከእሷ ጎልፊት በኋላ የባሏን የመራ ተክለሃይማኖትን በቡግና ላስታ የዛግዌን ስርወመንግሥት መመስረትም ተገንዝበናል።

ወደጥንቱዋ እስራኤል ስንዝዝ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያዊው ነቢዩ በልዓም፣ ስለ ቅዱስ ዳዊት ቤተሰቦች፣ ስለእነ ራሃብ (ራኬብ)፣ ስለኢትዮጵያኖቹ ሴቶች ስለእነ ሩት፣ ስለ እነ ሰማይ እና ስለ ቅዱስ ዳዊት እናት ስለ አዶሊያ (አዴል፣ ሀ/አብሌ) ማንነት እና ግንኙነት ተረድተናል።

በእግዚአብሄር ቁጣ እና ቅጣት ህዝበ እስራኤል ወደ ባቢሎን ከመሰደዳቸው በፊት በነብዩ ኤርምያስ እና በኢትዮጵያዊው

የንጉሥ አማካሪ እና የእስራል ክቡርዘበኛ አባሻር አቡመሲክ (አቤመሲክ) መሀል ስለነበረው ጥብቅ ወዳጅነት፣ ስለአቡመሲክ የእስራኤልን ግዞት በእግዚአብሄር ቸርነት ዐለማየት፣ ከ70 የግዞት ዓመታት በኋላ ስለ እስራኤላውያን ወደ ሀገራቸው መመለስ፣ ስለ ኤርምያስ፣ አቡመሲክ እና ባሩክ አብሮ መኖር፣ እንዲሁም እዝራና ዘሩባቤል የፈረውን የሰለሞን ቤተመቅደስ እንደገና ሲገነቡ የባቢሎንን ንጉሥ የዳሪዎስን ፍቃድ ስለማግኘታቸው አፋሮች ስለጠየቋቸው እና አፋሮች በዛን ዘመን በእስራኤል ላይ ስልጣን እንደነበራቸው ተምረናል።

እንግዲህ ይህን መጽሀፍ ከመዘጋታችን በፊት በእስራኤልና በኢትዮጵያ ህዝቦች መሃል ያለው ግንኙነት በጣም የቆየ እና ልዩ የመሆኑን እውነታ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። እንደ ኢትዮጵያዊያን ለአይሁዳዊያን በቅርበት የተዛመደ ማንም ህዝብ የለም። በመሰረቱ ግንኙነታቸው በደም፣ በእምነት፣ በባህልና በታሪክ ነው። በመልከጸዲቅና በአብርሃም የተጀመረው ወዳጅነት በኢትዮጵ ሴቶች ልጆች እና እንዲሁም በአብርሀም እና በሎጥ ወንዶች ልጆች ጋብቻ ተያይዞ፣ ከዛም በሙሴ እና በኢትዮጵያዊው ካህን በየቶርአብ ልጅ በሲፖራ ጋብቻ ቀጥሎ፣ በኋላም በእነ ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ አቤድን እና እሴን በወለዱት በእነ ሩት እና እነ ሰማይ እንዲሁም በቅዱስ ዳዊት እናት በእነ አዶልያ (ሀብሌ፣

አብሌ) አልፎ እስከ ንግሥተ-ሳባ እና ንጉሥ ሰለሞን ጋብቻ ዘልቆ ነበር። ቀዳማዊ ምኒልክ 40,000 እስራኤላዊያንን፣ ሌዋዊያንን ጨምሮ፣ ወደ ኢትዮጵያ ሲያመጣ እና መሬት ሲሰጣቸው፣ በየደብሩ ላይ ቤተመቅደስ እያሰገነባ ካህናት ሲያደርጋቸው፣ አንዳንዶቹንም በንጉሥነት ሲሾማቸውና ለ3000 ዘመናት የቆየውን የሰለሞንን ስርወ-መንግሥት ሲመሰርት ግንኙነታቸው በታላቅ ደረጃ ታደሰ።

በመጽሀፉ ውስጥ በግልጽ እንደተቀመጠው፣ ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ ካመጣቸው 40000 ሰዎች መሃል በተለይ ለ12000 ው አይሁዳውያን ልዩ ዳረጎት አድሎ ንጉሦች እና ካህናት አድርጎ፣ አገር እና ሠራዊት እየሰጠ ስለአደላደላቸው በአክሱምና በሌሎቹም የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ንጉሠነገሥት እስከማንገሥና መሻር ደርሰው ነበር።

ስለ ቤተእስራኤል ስልጣን ለመጨረሻ ጊዜ ለመጥቀስ፣ ሥልጣናቸው በፖለቲካ ብቻ ላይሆን በክህነትም ስለነበር ሌዋውያን ካህናቱ በጣም ይታፈሩና ይፈሩም ነበር። በሌዋውያኑ አነሳሽነት በንጉሣውያን ቤተሰቦች ላይ ሳይቀር የሞት ቅጣት ይደርስ ነበር። ምንም እንኳን በግለሰብ ደረጃ ነገሥታቱ እና ንግሥታቱ ክርስቲያንነትን የተቀበሉት ከመጀመሪያው ቢሆንም፣ የአሪትን ሃይማኖት የሚከተሉትን ሌዋውያኑን በመፍራት

ክርስትና የኢትዮጵያ መንግሥት ሃይማኖት ሳይሆን ለ333 ዓመታት ዘግይቷል። ይህንን ችግር የተረዳችው ብልኋ ንግሥት አብርሂት እና መንታ ልጆችዋ አብርሀና አጽብሀ ጉዳዩን በከፍተኛ ዘዴና ጥንቃቄ ይዘው እና አካሂደው በመጨረሻ ላይ ክርስትናን የኢትዮጵያ የይፋ ወይም መንግሥታዊ ሃማይኖት ለማድረግ ችለዋል። ይህንንም በማድረግ ከዐለም መንግሥታት ሁሉ ግንባር ቀደም ሆነዋል።

ቀደም ሲል እንደተባለው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምረን ብንቆጥር፣ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ፣ ስዩመእግዚአብሔር፣ ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ 225ኛው ንጉሠነገሥት ሆነዋል። ሰለሞናዊው ስርወመንግሥት፣ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አብዮት ፈንድቶ በ1966 ዓመተ ምሕረት እንደ አከተመለት አላይ ተመልክተናል። በዚህ ምክንያት አጼ ኃይለሥላሴ የሰለሞን ስርወመንግሥት የመጨረሻው ንጉሠነገሥት እንደሆኑም ተረድተናል።

በዚህች አጭር ጽሁፍ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአብርሃም እና በመልከጸዲቅ መሃል የነበረውም ግንኙነትም ቀርቧል። አንባቢው ሊያስተውል እንደሚችለው፣ በአይሁዳዊያንና በኢትዮጵያዊያን ትስስር፣ ታሪክ፣ እምነትና ባህል አዲስና ከዚህ ቀደም ያልታወቀ ወይም ትኩረት ያልተሰጠውን መረጃ ደራሲው

ፈንጥቋል። ይህች አነስተኛ መጽሃፍ ስለአይሁዳዊያን እና ኢትዮጵያውያን ዝምድና፣ ታሪክ እና እምነት ብዙም ያልተነገረ፣ ተነግሮም ከነበረ ባዲስ አወጋግ የተቀነባበረ መረጃ ይዛ እንደቀረበች ጸሀፊው ያምናል። ሁለቱ ጥንታዊ ህዝቦች፣ እረጅምና ዘመን ያልሻረውን ትስስራቸውን፣ የጋራ ታሪካቸውን፣ አንድነታቸውን እና ባህላቸውን የማይናጋ መሰረት አድርገው ወዳጅነታቸውን ይበልጥ በማጠናከር በተቻላቸው አቅምና መንገድ ሁሉ፣ ከምንጊዜም በላይ እንደሚቀራረቡ እና እንደሚተባበሩ የመጽሀፉ ከታቢ ተስፋ ያደርጋል።

**********ተፈጸመ**********

አባሪዎች

የኢትዮጵያዊነት ምንነት መግለጫ

ለምን በኢትዮጵያዊነታችን መኩራት እንደሚገባን

ከፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጅግላ

ኢትዮጵያዊ መሆን እጅግ የሚያኮራ ነገር መሆኑን ባለመገንዘባችን እና "አትዮጵያ" የሚለውን ቃል ትክክለኛ ፍቺ ባለማወቃችን፣ አንዳንዶቻችን በኢትዮጵያዊነታችን አናፍራለን።

"ኢትዮጵያዊነት" ምን ማለት እንደሆነ ለማብራራት የቃሉን ትርጉም ምንጭ ማወቅ ግድ ይላል።

"ኢትዮጵያ" ማለት ቢጫ ወርቅ ስጦታ (ለእግዚአብሄር ማለት) ነው። ይህ ስም የተሰጠው ለኢትዮጵያ መስራችና የኢትዮጵያውያን አባት ለሆነው ለ ኢትዮጵ ነው። እንግዲህ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ወርዶ፣ ወርዶ ወደ እኛ የደረሰው ከሱ ስም ነው ማለት ነው። "ኢትዮጵያዊ" ማለት በግሪክ ቋንቋ የተቃጠለ ፊት ነው የተባለው ነጭ ውሸት ነው። በግሪክ መዝገበ ቃላት ውስጥ እንደዚህ የሚል ቃል የለም።

ኢትዮጵያውያንን ሁሉ አንድ የሚያደርጋቸው፣ ከፍ ሲል ኢትዮጵያን በስሙ ካስጠራው ከካህኑና ከንጉሠ-ነገሥቱ

ከኢትዮጵ፣ ዝቅ ሲል የሱ ዘር ከሆነው ከነቢዩና ከፈላስፋው ከደሸት መወለዳቸው ነው።

ኢትዮጵ የዛሬ 4000 ሺ ዐመት አካባቢ ዐስር ወንዶች ልጆች ወልዶ ነበር። ስማቸውም እንደሚከተለው ነው። አቲባ፣ ቢኦር፣ ተምና፣ አቱር፣ አሻን፣ አክሲብ፣ በሪሳ፣ ቱስቢ፣ ቶላ እና አዜብ ናቸው። ከእነዚህ ስሞች ውስጥ አሻን፣ በሪሳ፣ ቶላ እና አዜብ አሁንም ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ።

የኢትዮጵ ዘር፣ የነቢዩ ደሸት ልጆች ደግሞ መደባይ፣ መንዲ፣ ጂማ እና ማጂ ይባሉ ነበር። ማጂ ማራ (አማራ) ን እና ጅማን ወለደ። ሰዎቹ የተሰየሙት የዛሬ 3600 ዐመት ቢሆንም፣ እነዚህ ስሞች አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ።

የኢትዮጵ 10 እና የደሸት 4 ልጆች ተባዝተው ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የአሉትን ሰዎች በሞላ ሆነዋል። በኢትዮጵያና በመላው ዐለም ባሉት ትውልደ ኢትዮጵያውያን የደም ስሮች ውስጥ የኢትዮጵ እና የደሸት ደም ይዘዋወራል። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን በሞላ ምንጫቸው አንድ እና አንድ ነው። ስለዚህም ቋንቋቸው ቢለያይም ደምና ዘራቸው አንድ ነው። ቋንቋ ደግሞ የመግባቢያ መሳሪያ እንጂ ዘርን አመላካች ወይም የዘር ክፍል አይደለም። ቋንቋ ማለት ጎሳ ማለት ነው።

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ጎስአ(ጎሳ) ልብየ ሰናይ ይላል። ልቤ መልካም ተናገረ፣ ማለት ነው። አገሳ ወይም ከውስጥ አወጣ፣ የተሰኘውም ቃል ከዚህ የመነጨ ነው። ጎሳ ማለት አንድ ዐይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎችን የሚያመላክት ነው። ዘር ማለት አይደለም። ለምሳሌ አንድ አባትና እናት ወደ ፈረንሳይ ሃገር ሄደው ልጅ ቢወልዱና ፈረንሳይኛ ቢናገር፣ ከዛም ወደ አሜሪካን አገር ተጉዘው ሌላ ልጅ ወልደው እንግሊዝኛ ቢናገር፣ ልጆቻቸው ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች ስለተናገሩ ወንድማማችነታቸው አይፋቅም። ወላጆቹም አማርኛ፣ ኦሮምኛ

ወይም አፋርኛ በመናገራቸው ወላጅነታቸው አይደመሰስም። ደምና ዘራቸው አንድ ናውና። ስለዚህ ወሳኙ ቋንቋ ሳይሆን ደምና ዘር ነው። ስለዚህ ቋንቋ ወይም ጎሳ ወሳኝ አይደለም። መግባቢያ ነው እንጂ። ኢትዮጵያ ውስጥም ከ 80 በላይ ቋንቋዎች የሚናገሩ ጎሳዎች አሉ። ሆኖም እነዚህ ጎሳዎች በቋንቋ ቢለያዩም በደማቸው አንድ የኢትዮጵ ልጆች ናቸው። የሚያገናኛቸውም ኢትዮጵያን በስሙ ያስጠራው ኢትዮጵ አባታቸው ነው።

ከ 200 ዐመታት በፊት መላው አፍሪካ ኢትዮጵያ ይባል ነበር። የእዚህ ምክንያቱ የኢትዮጵ ተወላጆች በመላው አፍሪካ ተሰራጭተው፣ አፍሪካን አሰልጥነው ስለኖሩበት ነው። የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን በቅኝ መግዛት ከጀመሩ ወዲህ ግን ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ቀርቶ አህጉሩ አፍሪአካውያን በተባሉት አፋሮች አፍሪካ መባል ጀመረ። አሁንም ድረስ ስሙ ከእኛው ስለአልወጣ ቅር አንሰኝም።

አንድ ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደ ወይም ትውልደ-ኢትዮጵየዊ ሰው በሁለት ምክንያቶች ኢትዮጵያዊ ይሆናል። አንደኛ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በመወለዱ። ሁለተኛ፣ ትውልደ-ኢትዮጵያዊ በመሆኑ። ሁለቱንም የሚያገናኛቸው በደምና በዘራችው ከኢትዮጵ መውረዳቸው ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት በዐለም ልዩ የሆነ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ዮጵ የተባለ ቢጫና ብርቅዬ ወርቅነት ማለት ነው። ከዚህም በላይ፣ ለዐለሙ ፈጣሪ ለእግዚአብሄር ብቻ የሚቀርብ ልዩ ገጸበረከት ማለት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የህይወት ምንጭነት፣ የሰብእና መገኛ ስፍራ ማለት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የስነመለኮት ከፍታ፣ የስልጣኔ መጀመሪያ፣ የሰው ዘር አርአያ፣ የስነምግባር ልእልና ማለት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የሀርነት፣ የጀግንነት እና የፍትህዊነት ተምሳሌነት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የእኩልነትና የሰው ልጅ ክቡርነት አርማ ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የታማኝነት እና የተአማኒነት እንዲሁም የመለኮት ማህደርነት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የፅናትና የብርታት እና የትእግስትና የዘላቂነት ምልክት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የሀቀኝነትና የእውነተኛነት ምሳሌ ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የርህራሄና የቸርነት ናሙናነት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት ሰው አክባሪነት፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ ይሉኝተኝነት እና አዙሮ ተመልካችነት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት የጥበበኝነት ቁንጮ፣ የብልህነት እራስ ማለት ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የቅድስና እና የብጹዕነት ጫፍ ነው።

- ኢትዮጵያዊነት ማለት የወንድማማችነትና የእህትማማችነት፣ የመተዛዘን ማማነት ነው።

ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሞላ በሚከተሉት ምክንያቶች በኢትዮጵያዊነታቸው ሊኮሩ ይገባል። የኩራቶቹን ሁሉ ምክንያቶች ለመዘርዘር ጊዜ ስለሚፈጅ ጥቂቶቹ ብቻ ይቀርባሉ።

1. ኢትዮጵያ በሳይንስም ሆነ በመፅሃፍ ቅዱስ የሰው ዘር መገኛ በመሆኗ፣

2. ከ 4500 ዐመታት በፊት በንጉሥ ስብኃህ አማካኝነት የጋዜጣን እና የፖሊስን ሥራ ከዐለም ቀድማ ኢትዮጵያ በማቋቋሟ፣

3. በዐለም ላይ የሌለ ከኖህ ጀምሮ ስሞቻቸውና የነገሡበት አዝማናት የተመዘገበ ነገሥታት በመኖራቸው፣

4. አባችን ኢትዮጵ እና ሚስቱ እናታችን ሲና እንቁዮጵግዮን መሲሁ እየሱስ ሲወለድ ልጆቻቸው ወደ እስራኤል ተጉዘው ገዳ እንዲያበረክቱለት በእግዚአብሄር ትእዛዝ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው እና ጣና ጎጃም ላይ በተልእኮ በመስፈራቸው፣

5. የኢትዮጵና የእንቁዮጳግዮን ልጆች ታላላቅ ነገሥታት ሆነው በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምስራቅና እስያ በመንሰራፋታቸው፣ ስልጣኔአቸውን በማሰራጨታቸው እና መላውን አፍሪካ ኢትዮጵያ በማሰኘታቸው፣

6. አጼ እስያኤል እስያን አሰልጥኖ በስሙ አህጉሩን እስያ በ ማሰኘቱ፣ እጽዋትን እና እንስሳትን አዳቅሎ አዲስ ውጤት ያስገኘው በዐለም የመጀመሪያው "ጂኔቲክ ኢንጂኔር" በመሆኑ፣ ከ3000 ዐመታት በፊት ይኸው ትልቅ ሰው ምናልባት በዐለም የመጀመሪያ የሆነውን ሰንደቅ-አላማችንን በመፈልሰፉ፣

7. በንግሥተ ሳባ ትልቅነት--- ኢትያኤል የተባለችው የሳባ ንግሥት በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰች፣ የዐለመ-ፈጣሪ እየሱስ ክርስቶስ ስሟን ጠርቶ፣ የንጉሥ ሰለሞንን ጥበበኝነት ለመፈተን ኢየሩሳሌምን መጎብኝቷን የመሰከረላት ትልቅ ሰው በመሆኗ፣

8. በአፋሮች ትልቅነት--- አፍሪካ በአፋሮች አፍሪካ ስለተባለች። ከ 3000 ዘመናት በፊት አፋሮች ታላቅ መርከብ ገንቢዎችና መርከቦኞች እንዲሁም በመካከለኛው ምስራቅና በእስራኤል ስመጥር የኦፊር ወርቅ ነጋዴዎች ከመሆናቸውም በላይ ተጽእኖ አሳዳሪዎች በመሆናቸው፣

9. የኢትዮጵ ዝርያዎች 12 ጠበብት ነገሥታት ሆነው እስራኤሎች የሚጠብቁት መሲህ መወለዱን ሳያውቁ የእኛዎቹ ከሩቅ ሆነው የመሲሁን መወለድ ተረድተው፣ ከኢትዮጵያ ተነስተው በኮከብ እየተመሩ ቤተልሄም ደርሰው ለመሲሁ ለእየሱስ ክርስቶስ ገዳ በማቅረባቸው፣

10. በዐለም ላይ ከአሉት ነገሮች ሁሉ በጣም ውድ እና ብርቅ የሆነው የታቦቱ ማረፊያ እና መኖርያ አድርጎ እግዚአብሄር ከእስራኤል ይልቅ ኢትዮጵያን በመምረጡ፣

11. ኢትዮጵያ በዳዊት መዝሙርና በሌሎችም መጽሃፍ ቅዱስ ገጾች ውስጥ በእግዚአብሄር በመጠራትዋ፣

12. ከእግዚአብሄር በታች ኢትዮጵያውያን አይሁዳውያንን በእግራችው ስለማቆሚያቸው፣ ከነብዩ ከሙሴ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ አይሁዳውያንን ወደ ግዛትዋ እያስገባች ጥገኝነት፣ መሬት እና ንግሥና ሳይቀር እየሰጠች አስተናግዳለች። በሌላ ሃገራት ግን እስራኤላውያንን ያሳድድዋቸው፣ እንዲሁም ይገድሏቸው ነበር። በእኛ በጎ አድራጊነት እንኮራለን። ከዚህ በተጨማሪ፣ እስራኤላውያን በባርነት በባቢሎን 70 ዐመት ሲሰቃዩ ቆይተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ቤተመቅደሳቸውን ካደሱ በሁዋላ መጻህፍት አጡ። መጽሃፍ ቅዱስን እና ሌሎች ብርቅዩ መጻህፍትን ኢትዮጵያ ስለላከችላቸው እንታበያልን።

13. ትልቅ ለሚባለው ለሙሴ ጥገኝነት እና ሚስት ኢትዮጵያ ሰጥታ የፍትህን እና የሕግ አስተዳደርን እንዲሁም ነገረመለኮትን ስለለስተማረችው፣

14. ኢትዮጵያ በርካታ የሴት ነገሥታትን በኢትዮጵያ እና በግዛቶቿ ላይ ሾማ የሴቶችን መብት በማስከበር በዐለም ግንባር ቀደም በመሆኗ፣

15. ኢትዮጵያ ከጣና ሃይቅ ተነስታ ወደ ኑብያ እና ግብጽ ወርዳ፤ የግብጽን እና የኑብያን ስልጣኔ በመፍጠርዋ፣

ሕልቆመሳፍርት ወንዶች ፈርኦኖችን እና ህንድኬ በሚል ማእረግ 17 የሴት ነገሥታትን በግብጽ፣ በሊብያ እና ኑብያ ላይ በመሾሟ፣

16. አጼ አክሱማይ የዐለም አባት፣ የነገሥታት እራስ ተብሎ ከባቢሎን ሳይቀር በንጉሦች የተበደሉ ዜጎቹ ለአቤቱታ ወደ እሱ ሲመጡ እምባቸውን ስለአበሰላቸው፣

17. እየሱስ ክርስቶስ፣ ቅድስት ማርያም እና ቅዱስ ዮሴፍ በኢትዮጵያ ግዛት በግብጽ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ጥገኝነት አግኝተው በመኖራቸው፣

18. እየሱስ ራሱን ለዐይሁዳውያን ሳይገልጽ በ22 ዕድሜው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለኛ ቅድሚያ ሰጥቶ ራሱን ለኛ ገልጾ እስከ 25 ዕድሜው ድረስ ሲያስተምርና ሲፈውስ ሃገራችን ውስጥ በመኖሩ፣

19. እየሱስ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ሲል ግብጽ ሳለ ጥገኝነት የሰጠውን ንጉሥ አማናቱ ተትናይን እግረመንገዱን ጎብኝቶ ለአንድ ሳምንት እሱ እልፍኝ ውስጥ ሰንብቶ ነበር። እየሱስ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር እንደተሻገረ እልፍኙን ንጉሥ አማናቱ ተትናይ ቤተክርስትያን አደረገው። እየሱስ ክርስቶስ በህይወቱ እየኖለ እኛ በዐለም የመጀመሪየውን ቤተክርስቲያን በመመስረታችን፣

20. የንግሥት ሕንደኬ ጃን በጅሮንድ በቅዱስ ፊሊፖስ መጠመቁና እሱ ከአውሮፓውያን ቀድሞ ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባቱ፣

21. አውሮፓውያን ወደ ክርስትና የተሸጋገሩት ከ አረማዊነት ሲሆን ኢትዮጵያውያን ግን ከአሪት ሃይማኖት ነው። ይህ በመሆኑም የክርስትና እውቀታችንን ከአውሮፓውያን ለማጥለቅና ለማበልጸግ አስችሎናል። በእዚህም እንኮራለን።

22. እየሱስ ክርስቶስ፣ ኢትዮጵያውያን ውስጣቸው የኖርኩ ዘመዶቼ ናችው፣ በእኔ ያምናሉ፣ እናንተ እነሱን ለማሳመን ሳትደክሙ አጥምቃችሁ አቁርቡአቸው፣ ብሎ ደቀመዛሙርቱን በርጠለሚዎስን፣ ማቴዎስን፣ ቶማስን፣ ናትናኤልን፣ እንድርያስን እና ማርቆስን ወደ ኢትዮጵያ ልኳቸው፣ ከሃዋርያቱ ግማሾቹ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ስለአስተማሩ በእግዚአብሄር እንደተከበርን ስለሚሰማን፣

23. ኢትዮጵያውያን ክርስትያናት እና አይሁዳውያን ያለደም መፋሰስ ተስማምተው የአሪትን እና የክርስትናን አምልኮ ስርዐቶች የሚተውትን ትተው የተረፉትን ወደ ክርስትና በማሸጋገራቸው፣

24. ከኢትዮጵ እስከ አጼ እስያኤል ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታት ከእግዚአብሄር ጋራ በቀጥታ የሚነጋገሩ ሊቀካህናት መሆናቸውና በፈሪሃ እግዚአብሄር ህዝባቸውን በፍትህ እና ርትህ በማስተዳደራቸው እና ይህ ክስተት በዐለም ላይ የሌለ በመሆኑ፣

25. ነብዩ መሃመድ በችግር ላይ ሳለ ዘመዶቹን ወደ ኢትዮጵያ ልኮ ኢትዮጵያ ጥገኝነት ስለሰጠቻቸው፣ መሃመድ ራሱ ሙስሊም ከመሆኑ በፊት፣ ኢትዮጵያ በመካና በመዲና

ውስጥ የራስዋ ቤተክርስትያን ስለነበራት እና እሱ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ተጠቃሚና የሊቀካህናቱ ወዳጅ በመሆኑ፣ እንዲሁም በመጀመሪያ አላሁ አክበር ብሎ አዛን ያሰማው ድምጸ-መረዋው ኢትዮጵያዊው ቢላል ሃበሽ በመሆኑ፣ ነብዩም ካልነካችሁ ኢትዮጵያውያን ላይ ጂሃድ አታካሂዱ በማለቱ፣

26. በ ኢትዮጵያ ሙስሊሞችና ክርስትያኖች በሃይማኖት ልዩነቶች ካለመጋጨታቸውም በላይ ተፋቅረውና ተባብረው ቤተክርስትያኖች እና መስጊዶች አንዱ ለሌላው በመገንባታቸው፣ አብረው በመጸለያቸው እና ከተዋደዱ ያለበዙ ችግር መጋባት በመቻላቸው፣

27. ኢትዮጵያውያን በዐለም ላይ የሌሉ ብርቅዬ የሱባ እና የሳባ ፊደላትን ፈጥረው ስለአቆዩልን፣

28. እንደ አክሱም እና ላሊበላ ዐይነት ያልተለመዱ የስነህንፃ ውጤቶች መኖራቸው፣ ከኢትዮጵያ የተገኘው ቅዱስ ያሬድ ልዩ ማህሌትን በመድረሱ እና ከአውሮፓውያን 700 ዐመታት አስቀድሞ የዜማ ምልክቶችን በመፈልሰፉ፣ እንዲሁም የማንንም የማይመስል ቅዳሴ እና ስርዐተ ዐምልኮ ስለአለን፣

29. በቀለማችን እና በተክለሰውነታችን የተቅለመለምን አበቦች ከመሆናችንም በላይ የተለያዩ አልባሳት፣ ዳንኪራዎች እና ባህላዊ እሴቶች ስለአሉን፣

30. ከተለያዩ የምግብ አሠራር መያዎች በተጨማሪ ለዐለም ያበረከትናቸው እንደ ቡና እና ጤፍ የመሳሰሉ አዝእርት ስለአሉን፣

31. ኢትዮጵያ፣ ባለፉት 4000 ዐመታት ሮማውያንን፣ ግብጾችን፣ አረቦችን እና ሌሎችንም በጦርነቶች ድባቅ እየመታች ነጻነታችንን እና ክብራችንን በማስጠበቋ እና ለዐለም ጥቁር ህዝቦች ሁሉ የነጻነት እና የድል አድራጊነት ዐርማ በመሆንዋ እንኮራለን። አባቶቻችን በኮሪያ ዘምተው፣ በተሰማሩበት የጦር ሜዳ ሁሉ ድል-አድራጊዎች ከመሆናቸውም በላይ አንዳቸውም ባለመማረካቸውና ጠላት እሬሳቸውን እንኳን ለመያዝ ባለመቻሉ ደጋግመን እንኮራለን።

32. ቀጥሎም፣ እጅግ የሚያኮራን በእየሱስ ክርስቶስ የደም ስር ውስጥ የእኛ የኢትዮጵያውያን ደም መፍሰሱ ነው። እንዴት ቢሉ፣ እየሱስ ክርስቶስ የቅዱስ ዳዊት ዘር በመሆኑ እና የእሱም እናት አይሁዳውያን አዶልያ ወይም አዴል የሚሏት፣ እኛ ደግሞ ሀበሌ የምንላት ኢትዮጵያዊት በመሆኗ።

33. በመጨረሻም በቅድመ ወላጆቻችን ክህነታዊ ማእረግ እና ክብር እንኮራለን። እግዚአብሄር ሁለት ዐይነት የክህነት ማእረግ ሰጥቶአል። አንደኛው ዝቅተኛው እና ለዐይሁዳውያን ብቻ የሰጠው የአሮን ክህነት ሲሆን ሁለተኛው እጅግ ከፍተኛው ለኢትዮጵ አባት ለሳሌሙ ንጉሥ ለመልከጸዲቅ ያቀደው ነው። የአሮን ሹመት

ካህንነት ብቻ ሲሆን የመልከጸዲቅ ግን የንጉሥ ንጉሥነት እና የካህን ካህንነት ነው። መለኮታዊ እና ዐለማዊ ማእረግ ነው። ራዕየ ዮሃንስ እንደሚተነብይልን የዐለሙ ፈጣሪ እየሱስ ክርስቶስ ወደፊት በመልከጸዲቅ ስርዐት የካህን ካህን፣ የንጉሥ ንጉሥ ሆኖ በእየሩሳሌም ላይ የራሱን ምድራዊ መንግሥት መስርቶ ይነግሣል። በዛም ጊዜ አባታችን ሆይ መንግሥትህ ይምጣ፣ ብለን የጸለይነው ይፈጸማል። የእየሱስ ክርስቶስ ክህነትና ንግሥና በአባቶቻችን በመልክጸዲቅ፣ በኢትዮጵ እና በልጆቹ ስርአት ስለሆነ እጅግ እንኮራለን።

የሚያኮሩንን ሁሉ ነገሮች በእርግጥ ዘርዝረን አንጨርሳቸውም። ከብዙ በጥቂቱ ከላይ የሰፈሩት ናቸው። እነሱን መስፈንጠሪያ አድርገን፣ ደረታችንን ነፍተን በኢትዮጵያዊነታችን ታብየን፣ እርስ በርሳችን ተከባብረን፣ ተፋቅረን እና ተቃቅፈን በእኩልነት ወደፊት እመር! እንላለን። እንግዲህ ጥንታዊ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ትልቅ ከነበሩ እኛም የእነሱን አርአያ እና ፈለግ ተከትለን በመነሳሳት ወደፊት ትልቅ የማንሆንበት ምክንያት የለም።

בס"ד

יושב-ראש הכנסת
Speaker of the Knesset

Jerusalem, 2 August, 2015
17 Av 5775

Prof. Fikre Tolossa
Vallejo, California
USA

Dear Sir,

I thank you for your letter and your fascinating work entitled "The Hidden and Untold History of the Jewish People and Ethiopians".

I would like to express my appreciation of the efforts you pour into researching the past of the Jewish people in the Ethiopian context. The backdrop of the affinity between the Jewish and the Ethiopian people is, as you indicate, the story of the Queen of Sheba, whose meeting with King Solomon is mentioned in the Book of Kings. As you say, most of us know little of about the history of the Jewish people in Ethiopia. Your letter and your work reveal many surprising details with which the Israeli public is unfamiliar.

It is of course no coincidence that the State of Israel actively assisted the immigration and absorption of thousands of Ethiopian Jews and that our kinship has been long acknowledged as part of our tradition. Operation Solomon, the large-scale airlift of Ethiopian Jews to Israel, bore the name of King Solomon precisely due to his meeting with the Queen of Sheba.

I am certain that raising the awareness to your findings among scholars as well as the general public is an important step towards shedding light on the close ties between the two peoples that may naturally improve both the sentiment towards our Ethiopian brothers within the Israeli society and the attitude of Ethiopia towards Israel.

Please allow me to congratulate you on your accomplishments and wish you every success in your endeavors.

Sincerely,

M.K. Yuli Yoel Edelstein
Speaker of the Knesset

ዋቢ መጻህፍት በከፊል

አማን በላይ፡---

መጽሀፈ ብሩክ ዣንሸዋ ቀዳማዊ (2000)፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 2000

መጽሀፈ ሰባኤ ዘ በአማን ካልእ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1998.

መጽሀፈ አብርሂት፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 2000

ሀገሀዊ ቀዳማዊ የ ኢትዮጵያ መስታወት ታሪክ፣ አዲስ አበባ (በግል ህትመት) 1988

መጽሀፈ ክብር፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

2001.W., *The Throne of Adulis*, Oxford, Oxford University Press. 2013

Bowersock, G.,G.W., *The Throne of Adulis*, Oxford, Oxford University Press. 2013

Budge, E.A. Wallis, *The Kebra Nagast, The Glory of Kings*,

translated from the Ethiopic. London: Oxford University Press. 1932

ገብረሥላሴ ገብረመስቀል (ጸሀፌ ትእዛዝ) ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠነገሥት ዘ ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1959

Good News Bible, Catholic Edition. Grand Rapids, Michigan: Published by Zondervan.

Holy Bible, the. New King James Version. (1985). Nashville, Tennessee: The Gideons International, National Publishing Company. 1993

Houston, Drusila, D., *Wonderful Ethiopians of The Ancient Cusite Empire,* Oklahoma City, Oklahoma, The Universal Publishing Co.. 1926

Josephus, Flavious. *The Complete Works of Josephus.* Grand Rapids, Michigan: Kregel Publications. 1981

Marcus, Harold, G. *A History of Ethiopia,* Berkeley, California. University of California Press.1994

Means, Sterling, M., Ethiopia, The Missing Link in African History, Chicago, Illinois, Lushena Books, 1980

Metsehaf Kidus, Ethiopian Tewahdo Church Bible, Nairobi, Kenya: United Bible Societies, Africa Regional Centre. 1980

Negussie, A'emro. *Tintawi Ye Ethiopia Ye Selam Tibekka Tarik.* Addis Abeba: EMPDA Printing Press. 2000

Rankin, Jim, *Jesus In Ethiopia,* (2011) Maitland, Florida. Xulan Press. 2011

Sergewe Hable Selassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270,* Addis Abeba. Unted Printers. 1972

ታዬ ገብረማርያም (አለቃ)፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ ኡፕሳላ ዩኒቨርሲቲ፣ ስዊድን፣ 1987

Hancock, Graham, *The Sign and The Seal,* The Quest for The Lost Ark of The Covenat, London, UK, Heineman, 1992

The Kibre Negest, Oxford Universtiy Press. London. 1932

ተክለጻዲቅ መኩሪያ፤

የኢትዮጵያ ታሪክ ከ ዐጼ ይኩኖአምላክ እስከ ዐጼ ልብነድንግል፤ አዲስ አበባ ተስፋ ማተሚያ ቤት በግርማዊ ቀዳማዊ ዐጼ ኃይለሥላሴ በ 28 ኛው ዘመነ መንግሥት

የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐጼ ልብነድንግል እስከ ዐጼ ቴዎድሮስ፣ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ ኃ ሥ ማተሚያ ቤት 1965

ተረፈ ኤርምያስ፣ በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን መጽንፍ ቅዱስ (81 ዱ መጻህት) ውስጥ የተካተተ

ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ

‹‹ስውሩና ያልተነገረው የአይሁድ ህዝብና ኢትዮጵያዊያን ታሪክ›› በሚል ርዕስ ላጠናቀሩት ግሩም መጽሐፍ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ስላለፈው ዘመን የእስራኤል ህዝብ ታሪክ በኢትዮጵያዊ አይታ ላከናወኑት ጥናታዊ ስራ አድናቆቴን ልገልፅልዎ እወዳለሁ፡፡ በአይሁዳዊያንና ኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያለው ቅርበት እንደጠቆሙት ሥረ መሰረቱ በመፅሐፈ ነገስት የሚጠቀሰው የንግስት ሳባ ከንጉስ ሰለሞን ጋር መገናኘት ነው፡፡ እንዳሉትም አብዛኞቻችን ኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረው የአይሁድ ህዝብ ታሪክ የምናውቀው ጥቂት ነው፡፡ መጽሐፍዎ የእስራኤል ሰፊ ህዝብ ያልተገነዘባቸውን አያሌ ዝርዝር ቁምነገሮች የሚገልጥ ነው፡፡

ኤም.ኬ. ዮኤል ኤደልስቲን
የእስራኤል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ

ይህ ጽሁፍ ከዚህ ቀደም ከኢትዮጵያ ውጪ በየትኛውም ቋንቋ በእዚህ መልኩ ያልተወሳና ያልታተመ ከአይሁድ ህዝብና በአጠቃላይ ከዓለም ህብረተሰብ ተሰውሮ የቆየ ታሪክን አካቷል፡፡ ምንም እንኳ የአይሁዳውያንና ኢትዮጵያውያን ታሪኮች የተሳሰሩና ሁለቱ ህዝቦች እነዛኑ ታሪኮች በስፋት የሚጋሩ ቢሆንም፣ ይህን ክስተት አይሁዳውያን አያውቁም፣ ዘመናዊዎቹ ኢትዮጵያውያንም እንዲሁ፡፡

****

የጎረምሳው ንጉሠነገሥት ተከታይ እርምጃም አሳዛኝ ነበር፡፡ የታሪክ ቅርሶችን በሙሉ አፈራረሰ፣ ከመልከጸዲቅና ኢትዮጵ የወረዱ ብርቅዬ ሰባዊ መፃህፍትን አወደመ፡፡ አንዳንዱንም ለቅሞ አፈነ፣ ቀደምት ነቢያትን ፈሳስፎችንና ምሁራንን አሳደደ፡፡ በህይወት የተረፉት ጠቢባንና ካህናት ወደ ኑቢያና ግብፅ ተሰደዱ፡፡

****

አላይ ‹‹ንግሥት ዮዲት ለኢትዮጵያ የዋለችው ውለታ›› ብዬ ስለጻፍኩ አንባቢው ሊደነቅ ይችላል፡፡ ምክንያቱም፣ እሷ የምትታወቀው ኢትዮጵያን በእሳት በማጋየት ብቻ ነውና፡፡ በዚህም ምክንያት ‹‹እሳቶ›› ወይም ‹‹ዮዲት ጉዲት› እስከመባል ደርሳለች፡፡ ሀቁ ግን እንደተወራባት እሷ የኢትዮጵያ ጠላት አልነበረችም፡፡

ዋጋ $20 USD

Brought to you by: Ethiopian Bookstore
link: https:t.me/etbookstore